የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ
AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE PLAN AND DEVELPOPMENT BUREAU

2018

ቁጥር አብክመ/ፕልቢ/ 59 /18

ቀን 12/05/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ምክር ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ

ለክቡር የአብክመ ርዕሰ መስተዳደር

ባህር ዳር፣

ጉዳዩ፡- የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ስለመላክ፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ2018 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅተን ከዚህ ሸኝ ደብዳቤ ጋር 141 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ለዓለም ጥላሁን አግደው (ዶ/ር)
ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ//

- ለአብክመ ምክትል ርዕሰ መስተዳደር
- ለአብክመ ገጠር ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ
- ለአብክመ ከተማ ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ
- ለአብክመ ማኅበራዊ ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ
- ለአብክመ አስተዳደር ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ

ባህር ዳር፣

- ለቢሮ ኃላፊ
- ለፕላን ትግበራ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት

ፕላንና ልማት ቢሮ

ምርምር ፣ ፈጠራ ፣ ተጽዕኖ !
esearching, Innovating, Influencing"
ስልክ ☎058-320-82-77 | ፖስታ ✉ 1378 Bahir Dar | ፋክስ Fax 058-226-39-10 | ኢሜይል Email plandevelopment16@gmail.con
ድህረ ገጽ Website:- http://www.anrsbopd.gov.et:82/

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# የ2018 በጀት ግማሽ ዓመት የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ጥር /2018 ዓ.ም

ባህር ዳር፣

## ማውጫ ገፅ


1. አህጽሮት....4
2. መግቢያ....7
3. የክልሉ ርዕይ....8
4. የትኩረት መስኮች....8

**ክፍል አንድ፡** የክልሉ ጥቅል የኢኮኖሚ አፈጻጸም....9

1.1. የኢኮኖሚ ዕድገት አፈፃፀም (GDP)....9
1.2. የክልሉ ዋጋ ግሽበት /ንረት ሁኔታ....12
1.3. የኑሮ ውድነትን መቅረፍ....14
1.4. የስራ እድል ፈጠራ....17
1.5. የክልሉ የፊዚካል ፖሊሲ አፈፃፀም....18
1.5.1.የክልሉ መንግስት ገቢ አፈፃፀም....18
1.5.2.የወጭ ምርት /ኤክስፖርት/ አፈፃፀም....19

**ክፍል ሁለት፡** የዘርፎች ልማት አፈጻጸም....21

2.1. አምራች ኢንዱስትሪ....21
2.2. ዘመናዊ ግብርና....26
2.3. የማዕድን ሀብት....31
2.4. ቱሪዝም....33
2.5. ትምህርት....34
2.6. ጤና....42
2.7. ንግድና ገበያ ልማት....46
2.8. ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ....50
2.9. ኮንስትራክሽን....54
2.10. ማህበራዊ ፍትህ....55

**ክፍል ሦስት፡** የከተማና የገጠር ልማት....59

3.1. የከተማ ልማት....59
3.2. የአካባቢ ጥበቃ ልማት....64

**ክፍል አራት፡** የልማት አቅሞች....68

4.1. መሬት....68
4.2. የሰው ኃይል ልማት....73
4.3. ቴክኖሎጅ....77

**ክፍል አምስት፡** *መሠረተ ልማት* ........ 80
5.1. *የመንገድ ዘርፍ* ........ 80
***ክፍል ስድስት፡*** *ስርዓታትና ልማት* ........ 89
6.1. የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ ........ 89
6.2. የባህል እና እሴት ልማት ........ 99
***ክፍል ሰባት፡*** *የልማት ፋይናንስ* ........ 103
7.1. *መዋዕለ ንዋይ* ........ 103
7.2. የመንግስት ፋይናንስ ........ 106
**ክፍል ስምንት፡** የማስፈጸሚያ ስልት ........ 107
8.1. ልዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ........ 107
8.1.1. የክልል ፍላግሽፕ ፕሮጀክቶች ........ 107
8.1.2. የፌዴራል ፍላግሽፕ ፕሮጀክቶች ........ 117
8.2. ክትትልና ግምገማ ........ 133
*9.* ***ማጠቃለያ*** ........ 136

## 1. አህጽሮት

እንደ ክልል ብሎም እንደ ሀገር ሰላምን ማስፈን፣ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትንና ልማትን ማረጋገጥ እንዲሁም ድህነትን መቀነስ ቀዳሚ አጀንዳዎች በመሆናቸው ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ እነዚህ እየተመዘገቡ ያሉ ሁለንተናዊ የልማት ውጤቶች በመንግስትና በህዝብ የተቀናጀ ጥረት በመሆኑ ይህንን ጥረት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በየበጀት ዓመቱ ያሉ መልካም ውጤቶችን ይበልጥ ለማስፋፋትና መሰረት ለማስያዝ እንዲሁም እጥረቶችን በመቅረፍና ወደ ታለመለት ግብ በመድረስ የተያዘውን የእድገትና የብልጽግና ጉዞ ለማረጋገጥ ሰፋፊ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

የክልላችንን የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ጠቅለል አድርገን ስናየው ክልሉ በፀጥታ ችግር ውስጥ ቢሆንም የክልሉን ኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳደግ ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራዎችን በመስራት 4,269 ኢንቨስተሮችን በመሳብ ወደ ልማት እንዲገቡ ለማድረግ በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ አቅምና ፍላጎት ያላቸዉን 2,243 ባለሃብቶች ለመለየትና ለመመልመል ታቅዶ 2,947 አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች መለየትና መመልመል ተችሏል፡፡ 243.2 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ እና ለ217,632 ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ 2,210 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ ብር 182.77 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ እና ለ298,829 (›100%) (ወንድ 73,933 ሴት 41,439) ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ 1,867 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ተደርጓል፡፡

የክልሉ የዋጋ ግሽበት ሁኔታን ስንመለከት በመስከረም ወር 2017 ዓ.ም አጠቃላይ ግሽበት 21.7 በመቶ፣ ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች 24.2 በመቶ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች 18.5 የነበረ ሲሆን በታህሳስ ወር 2018 ዓ.ም ከፍተኛ ቅናሽ በማሳየት ወደ አንድ ዲጂት (Single Digit) ወርዶ አጠቃላይ ግሽበት 5.2 በመቶ፣ ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች 3.8 በመቶ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች 7.1 በመቶ በመሆን ተመዝግቧል፡፡

በአሁን ሰዓት በአምራች ኢንዱስትሪዉ ዘርፍ ያሉን 301 ከፍተኛ እና 1014 መካከለኛ በድምሩ 1,315 ሲሆኑ የኢንዱስትሪዎች ቁጥር ከክልሉ የመልማት አቅም ጋር ሲነጻፀር ዝቅተኛ ስለሆነ በክልሉ ኢኮኖሚ ውስጥ በአጭር ጊዜ መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ለማድረግ አዳጋች ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተጨማሪም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አጠቃላይ ምርታማነት ከነበረበት 59.22% ወደ 63 በመቶ ለማድረስ የ91 ከፍተኛ እና 270 መካከለኛ በድምሩ 361 ለመለካት ታቅዶ የ169

ከፍተኛ እና የ482 መካከለኛ በድምሩ 651 ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም መለካት የተቻለ ሲሆን የማምረት አቅማቸውን 62.42% ማድረስ ተችሏል፡፡

የዘመናዊ ግብርና ዘርፍ አፈጻፀም ሲታይ በ2017/18 የምርት ዘመን 5,398,393 ሄ/ር መሬት በማልማትና ምርቱንም በ10% በማሣደግ 187,540,749 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 5,533,592 (103%) ሄ/ር መሬት በዘር በመሸፈን እስከአሁን 138,011,468 ኩ/ል ምርት ማምርት ተችሏል፡፡ በዚህም በምግብ ሰብል 75,275,997 ኩ/ል፣ በኢንዲስትሪ ሰብል 51,347,089 ኩ/ል እና በኤክስፐርት ሰብል 11,388,382 ኩ/ል ምርት መሰብስብ ተችሏል፡፡ በዚህም የግብርና ስራ በቴክኖሎጂ እንዲታገዙ በተደረገው ጥረት 1,793 ትራክተሮችን በመጠቀም 1,037,598 (100%) ሄ/ር መሬት ማረስ የተቻለ ሲሆን 76 ኮምባይነር እና 119 ትሬሸር በመጠቀም ምርት የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2017/18 ምርት ዘመን በመኸር (በመደበኛና በኮሞዲቲ) ሠብልች 5,398,393 ሄ/ር መሬት በማልማት 187,540,749 ኩ/ል ምርት ለማምርት ታቅድ 5,533,592 (103%) ሄ/ር መሬት በዘር በመሸፈን እስከአሁን 138,011,468 ኩ/ል ምርት ማምርት ተችሏል፡፡ በዙህም በምግብ ሰብል 75,275,997 ኩ/ል፣ በኢንዲስትሪ ሰብል 51,347,089 ኩ/ል እና በኤክስፐርት ሰብል 11,388,382 ኩ/ል ምርት መሰብስብ ተችሏል፡፡ በዚህም የግብርና ስራ በቴክኖልጂ እንዲታገዝ በተደረገው ጥረት 1,793 ትራክተሮችን በመጠቀም 1,037,598 (100%) ሄ/ር መሬት ማረስ የተቻለ ሲሆን 76 ኮምባይነር እና 119 ትሬሸር በመጠቀም ምርት የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የእንስሳት ሀብት ልማት ለማሳደግ 1,703,786.15ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 1,635,002 (96%) ቶን ማምረት የተቻለ ሲሆን 380,904 ቶን ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 496,391 ቶን በማምረት ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

ትምህርት አስቻይ ሁኔታ ባላቸው 9,730 ትምህርት ቤቶች ምዝገባ ተጀምሮ በትምህርት ዘመኑ በሁሉም እርከኖች ለመመዝገብ ከታቀደው 7,445,545 ተማሪዎች መካከል እስከ ግማሽ ዓመቱ ድረስ መመዝገብ የተቻለው 4,344,269 (59.06%) (ወንድ 2,127,472፣ ሴት 2,216,797) ብቻ በመሆናቸው ወደ ትምህርት ያልገቡ ተማሪዎችን እንዲገቡ በማድረግ በኩል የሁሉንም ዜጋ ርብርብ የሚጠይቅ ተግባር ስለሆነ በትኩረት ሊመራ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል በፀጥታ ችግር ውስጥም ሆነን የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት ለማሳደግ እየተከናወነ ያለው ተግባር አበረታች ሲሆን ክልሉ ካለዉ እምቅ የቱሪዝም ሀብት አኳያ ከዚህ የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ሌላው ከመሰረተ ልማት ዘርፍ አንዱ መንገድ ሲሆን አጠቃላይ የክልሉ የመንገድ ሽፋን ለማሳደግ 698.77 ኪ.ሜ ለመገንባት ታቅዶ 502.35 (71.89%) ኪ/ሜ የጠጠርና የአስፓልት መንገድ ለመገንባት ተችሏል፡፡

ንግድና ገበያ ልማት አዲስ ንግድ ምዝገባ ማካሄድ 51,650 ታቅዶ 60,470(100%)፣አዲስ ንግድ ፈቃድ መስጠት 61,850 ታቅዶ 85,561(100%)፣ንግድ ፈቃድ እድሳት 352,052 ታቅዶ 247,194 (70%) በአጠቃላይ የኦን ላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት 301,391 ለመስጠት ታቅዶ 445,669 (100%) አገልግለት መስጠት ተችሏል፡፡

ስለሆነም ክልላችን ባለፉት በጀት ዓመታት በፀጥታ ችግር ውስጥ ሆኖ የሰላም ማረጋገጥ ስራን ዋነኛ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ የቆየ እንደመሆኑ መጠን በልማት ስራዎች ላይም ያከናወናቸው ተግባራት እና የተመዘገቡ ውጤቶች አበረታች ናቸው፡፡ በቀጣይ ወራት የሰላምና የልማት ስራውን አስተሳስሮ በመምራት የበጀት ዓመቱን የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት እቅድ ለማሳካት ርብርብ ማድረግ ከሁሉም የክልላችን አመራሮች፣ ባለሙያውና ህዝባችን የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡

# 2. መግቢያ

የክልሉን ሕዝብ ከድህነት ለማውጣትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን ለመተግበር የሚስችል የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን አቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በዚህ መሠረት በ2017 በጀት ዓመት የ25 ዓመት የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት ፍኖተ ካርታ፣ የ5 ዓመት የስትራቴጅክ እቅድ እና የ2018 በጀት ዓመት የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በምክር ቤት በማፀደቅ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመግባት ክልሉን ከግጭትና ከድህነት አዙሪት ለመዉጣት፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የሕብተረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም 2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያዉ 5 ዓመት የስትራቴጅክ እቅድ መነሻ ዓመት እንደመሆኑ መጠን ከአሁን በፊት ታቅደው በተለያዩ ምክንያቶች ያልተፈጸሙ ተግባራትን በማካተት ወጥ የሆነ ክልላዊ ማክሮ እቅድ በማዘጋጀት ወደስራ መግባት ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት የክልል ተቋማት የአሻጋሪና የዘላቂ ልማት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ አቅደው የተገበሯቸውን ተግባራት በሪፖርት አሳውቀዋል፡፡

ፕላንና ልማት ቢሮም በክልል ተቋማት የተላኩ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን መሠረት በማድረግ በግማሽ ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን የተጠቃለለ የአሻጋሪና የዘላቂ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በዘርፍ በመለየት የማዘጋጀት ስራ የሰራ ሲሆን ሪፖርቱ በውስጡ አጽርሆተ ጽሁፍ ፣ መግቢያ፣ የክልሉ ጥቅል የኢኮኖሚ እድገት፣ የዘርፎች ልማት አፈጻጸም፣ የመሠረተ-ልማት፣ የልማት አቅሞችና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በማካተት የግማሽ ዓመት ሪፖርቱን ለማዘጋጀት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 3. የክልሉ ርዕይ

በ2022 የአማራ ብሔራዊ ክልል በወሳኝ ዘርፎች ንቅናቄ ለኢኮኖሚ ልማት መመንጠቅ አስተማማኝ መሠረት የጣለ እና የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆኖ ማየት፡፡

## 4. የትኩረት መስኮች

- ዘመናዊ ግብርና
- አምራች ኢንዱስትሪ
- የማዕድን ልማት
- ዘመናዊ ቱሪዝም፡- የገጠር ልማት
- ክትመት
- የሕግ የበላይነት
- መንገድ፣ ኢነርጂ፣ ዘመናዊ ሎጂስቲክስ እና አይሲቲ
- ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን
- ትምህርት እና ሥልጠና
- ዘላቂ የልማት ፋይናንስ

# ክፍል አንድ፡ የክልሉ ጥቅል የኢኮኖሚ አፈጻጸም

## 1.1. የኢኮኖሚ ዕድገት አፈፃፀም (GDP)

የአማራ ክልል ጥቅል ምርት መጠን በ2013 በጀት ዓመት ብር 242.5 ቢሊየን የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት አመት ክልላዊ ጥቅል ምርቱ ብር 398.74 ቢሊዮን ደርሷል። በክልሉ በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው ጥቅል ክልላዊ ምርት ጭማሬ ከ2016 በጀት ዓመት ከተመዘገበው ብር 370.64 ቢሊዮን ጥቅል ክልላዊ ምርት ጋር ሲነፃፀር የ28.1 ቢሊየን ብር ብልጫ ያሳየ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

በዘርፍ ደረጃ ሲታይ ደግሞ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች ጥቅል ምርት መጠን በ2013 በጀት ዓመት ብር 172.2 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት አመት ብር 203.2 ቢሊዮን ደርሷል። በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው የግብርና ዘርፎች እሴት ጭማሪ ከ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 192.5 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 11 ቢሊየን ብልጫ አሳይቷል። የኢዱስትሪ ዘርፎች ምርት መጠን በ2013 በጀት ዓመት 48.5 ቢሊየን ብር የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት አመት የዘርፎች ጥቅል ምርት መጠን ብር 66.9 ቢሊዮን ደርሷል። በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው የኢዱስትሪ ዘርፎች እሴት ጭማሪ ከ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 60 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 6.9 ቢሊየን ብልጫ አሳይቷል። የአግልግሎት ዘርፎች በ2013 በጀት ዓመት ግመታ መሰረት 98.5 ቢሊየን ብር የነበረ ሲሆን በ2017 በጀት አመት ግመታ መሰረት የዘርፎች ጥቅል ምርት ብር 133.7 ቢሊዮን ደርሷል። በ2017 በጀት ዓመት የተመዘገበው የአገልግሎት ዘርፎች እሴት ጭማሪ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 123.62 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 10.08 ቢሊየን ብልጫ አሳይቷል።

በተመሳሳይ በ2017 በበጀት አመት የክልሉ ጥቅል ኢኮኖሚ በወቅቱ የገበያ ዋጋ (Nominal GDP) ግመታ መሰረት ብር 1,584.07 ቢሊየን የደረሰ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 1,329.25 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር የብር 254.81 ቢሊየን ብላጫ ያለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። በዚህ ስሌት መሰረት የክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2017 በጀት አመት የአሜሪካ የዶላር የመግዛት አቅም (purchasing power parity) መሰረት 2,889 የአሜሪካን ዶላር መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡


**ሠንጠረዥ1፦ የአማራ ክልል ጥቅል ምርት መጠን በቢሊየን ብር**

| የኢኮኖሚ ሴክተር | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና | 172.2 | 177.3 | 183.7 | 192.5 | 203.2 |
| ኢንዱስትሪ | 48.5 | 51.6 | 54.8 | 60 | 66.9 |
| አገልግሎት | 98.5 | 107 | 116 | 123.6 | 133.8 |
| ጥቅል ክልላዊ ምርት | 315.2 | 331.1 | 349.74 | 370.64 | 398.74 |

*ምንጭ፡ በአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ የክልል ኢኮኖሚ አካውንት ዳይሬክቶሬት*

በ2017 በጀት ዓመት የክልል ምርት ግመታ መሰረት የግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች የ5.5 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የ11.6 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፎች የ8.2 በመቶ እድገት ያስመዘገቡ ሲሆን ጥቅል ክልላዊ ዕድገቱም 7.6 በመቶ በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በ2017 በጀት አመት የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በ2016 በጀት አመት ከተመዘገበው የ6 በመቶ ዕድገት አንፃር ሲታይ 1.6 በመቶ ብልጫ ያለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።


**ግራፍ 1፦ የአማራ ክልል ኢኮኖሚ ዕድገት በመቶኛ**




*ምንጭ፡ በአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ የክልል ኢኮኖሚ አካውንት ዳይሬክቶሬት*

በ2017 በጀት አመት የዋና ዋና ኢኮኖሚ የዘርፎች እሴት ጭማሪ ከጥቅል ክልላዊ ምርት እድገት 7.6 በመቶ ያላቸው ድርሻ ሲታይ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች 51.0%፣ ኢንዱስትሪ ዘርፎች 16.8 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፎች 33.5 በመቶ መሆኑን ክልላዊ የጥቅል ምርት መረጃ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ (ከ2008-2017) በነበሩት 10 አመታት የክልሉ ኢኮኖሚ በድርሻ አማካይ ሲታይ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች የ54.9 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የ15.4 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፎች ደግሞ የ30.9 ድርሻ የነባራቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

**ግራፍ 2፦ የዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ከክልሉ ጥቅል ምርት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ**




*ምንጭ፡ በአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ የክልል ኢኮኖሚ አካውንት ዳይሬክቶሬት*

ክልሉ በርካታ በርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ተጻሮቶች ቢኖሩበትም የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት መሰረት ሰፊ፣ ዘርፈ ብዙ፣ ፈጣንን፣ ቀጣይነት ያለውና ስጋቶችን የመቋቋም አቅሙ እየተጠናከረ የመጣ መሆኑን የተከታታይ ዓምታት መረጃዎች አመላካቾች ናቸው። ለዚህ ፈጣን ዕድገት መገኘት በምክንያትነት ከሚጠቀሰው መካከል መንግስት እየተከተለ ያለው የማክክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ትግበራ፣ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራሞች በአግባቡ


በመተግበራቸው እና አመራሩ በቀውስ ውስጥም ሆኖ ኢኮኖሚውን ለመመራት ያሳየው ቁርጠኝነት በዋናነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች ናቸው።

## 1.2. የክልሉ ዋጋ ግሽበት /ንረት ሁኔታ

የ2017 በጀት አመት አጠቃላይ የክልሉ የዋጋ ግሽበት 15.43 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በ2016 በጀት አመት ከነበረው 31.89 በመቶ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሆነ ቅናሽ አሳይቷል። በዚሁ በጀት አመት የምግብ ዋጋ ግሽበት 15.48 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው የ34.44 በመቶ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ቅናሽ ያሳየ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። በተመሳሳይ ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የዋጋ ግሽበት 15.45 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በ2016 ዓመት ከነበረው የ28.71 በመቶ ጋር ሲነፃፀር ሲታይ የመቀንስ አዝማሚያ አሳይቷል (የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት 2017 ሪፖርት)፡፡

የክልሉ የወርሃዊ የዋጋ ግሽበት ሁኔታን ስንመለከት በታህሳስ ወር 2017 በጀት አመት አጠቃላይ ክልላዊ የግሽበት ምጣኔ 17.1 በመቶ፣ ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 17.9 በመቶ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ 16 በመቶ ሆኖ ተመዝግቦ የነበረ ሲሆን የግሽበት ምጣኔው በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ በታህሳስ ወር 2018 ዓ.ም ምጣኔው ወደ ነጠላ አሃዝ (Single Digit) ወርዷል። በዚህም መሰረት በታህሳስ ወር 2018 ዓ.ም አጠቃላይ ክልላዊ የዋጋ ግሽበት ምጣኔ 5.2 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን ዓይነት ሲታይ ደግሞ ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ 3.8 በመቶ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች የግሽበት ምጣኔ ደግሞ 7.1 በመቶ መሆኑን የኢትዮጵያ ስታትስቲካል አገልግሎት መረጃ አመላክቷል።

**ግራፍ 3፣** የአማራ ክልል ወርሃዊ የዋጋ ግሽበት ታህሳስ 2017 እስከ ታህሳስ 2018 ዓ/ም




ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ስታትስቲካል ሰርቪስ ስታትስቲካል መረጃ ታህሳስ 2018 ዓ/ም

በክልል ደረጃ በበጀት አመቱ የዋጋ ግሽበቱን ወደ ነጠላ አሃዝ ለማውረድ ታቅዶ እየተሰራ ያለው ስራ በአግባቡ የተሳካ ሲሆን በተለይም ምግብ ነክ የሆኑ ምርቶች የዋጋ ግሽበት ከባለፈው አመት እና መድረስ ከሚገባው ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ደረጃ የተሳካ እና ትርጉም ባለው ሁኔታ የቀንሰ መሆኑን ከመረጃው ማረጋገጥ ተችሏል።

### የዋጋ ንረት ምጣኔ (Inflation) መቀነስ በምክንያይትነት የሚወሰዱት

በባለፉት አመታት ተቀዛቅዞ የነበረው የግብርና ዘርፍ ዕድገት እየተሻሻለ መምጣቱ በዚህም መሰረት በ2013 በጀት አመት 2.2 በመቶ የነበረው የግብርና ጥቅል ምርት ዕድገት በ2017 በጀት አመት ወደ 5.5 በመቶ ማደጉ እና የዚህ ዕድገት ደግሞ ዋነኛ አስተዋጽኦ አድራጊ ከሰብል እና ከእንስሳት ንዑስ ዘርፍ መሆኑ በቀጥታ ችግሩን ለመቅረፍ እያስቻለ መሆኑ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርታማነት እያደገ መምጣትና ተኪ ምርቶች በብዛት እየተመረቱ መምጣቱ እና አምራችና ሸማቹን ለማገናኘት እየተሰራ ያለው ስራ ውጤት እያሳየ መምጣቱ ለመቀነሱ በምክንያትነት የሚጠቀስ ነው።

በተጨማሪም የግብይት ሰንሰለቱን የማሳለጥ ስራ መስራቱ፣ የአምራችን ሸማች ትስስርን ማጠናከር መቻሉ፤ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን በብቃት መምራት መቻሉ፣ መንግስት ለግብርና ምርት ግብዓት የሚሆነውን ማዳበሪያ እና ነዳጅ ላይ ከፍተኛ ድጎማ ማድረጉ፣ መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ መንግስት ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡና የአንዳንዶቹን ማሻሻያ ማድረጉ እንዲሁም የክልሉ ሰላም እየተሻሻለ መምጣቱና የሸቀጦችና የሰራተኞች እንቅስቃሴ ገደብ ለውጥ ማሳየቱ ምርት ከቦታ ወደ ቦታ እንዲዘዋወር ፈቃጅ መሆኑ ተጠቃሾች ናቸው።፡፡

## 1.3. የኑሮ ውድነትን መቅረፍ

### የዜጎችን ገቢ ማሳደግን

**ቋሚ የስራ ዕድል በስፋት መፍጠርን በተመለከተለግል ሴክተሩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሰፊ የስራ ዕድል ለዜጎች እንዲፈጠር ማድረግን በተመለከተ፣** በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ አቅምና ፍላጎት ያላቸዉን 2,243 ባለሃብቶች በመለየት ለመመልመል ታቅዶ 2,947 ወይም ከ100% በላይ አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች መለየት እና መመልመል ተችሏል በተጨማሪም በክልሉ ብር 243.2 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ217,632 ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 2,210 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ 182.77 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡና ወደ ስራ ሲገቡ ደግሞ ለ298,829 (ወንድ 162,265 ሴት 136,564) ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 1,867 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ማደረግ ተችሏል፡፡

**ቋሚ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ገቢ የሚያሳድግ ድጋፍ ማድረግን በተመለከተ፡** የፌደራል መንግስት በያዝነው በጀት ዓመት ለመንግስት ሰራተኛው የደሞዝ ማሻሻያ በማድረጉ በሰራተኛው ላይ ይስተዋል የነበረውን የኑሮ ውድነት በመቅረፍ አጋዥ ሚና ተወጥቷል፡፡

**የመኖሪያ ቤት ግንባታን በተመልከተ፡-** በ6 ወሩ የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች 46,471 ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ በሪልስቴት 215 ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኅበራት 15,351 ቤቶች፣ በግለሰቦች 10,448 ቤቶች፣ ለዝቅተኛ ነዋሪዎች 1,341 ቤቶች በድምሩ 27,355 (58.86%) መኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል፡፡

**የፍጆታ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ሸማቾች እንዲያገኙ ማድረግን በተመለከተ**

የአነስተኛ ባለይዞታ አርሶ አደሮችን የገበያ ተደራሽነት በማሳለጥ የዘመናዊ ግብርና ውጤቶችን በበቂ መጠን ለሸማቾች እንዲደርስ ለማድረግ 1,213,728 ኩ/ል ለማስተሳሰር ታቅዶ 3,272,366 ኩ/ል (269%) በማስተሳሰር አምራቹንና ሸማቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ገበያውን ለማረጋጋት የኑሮ ውድነቱን ለመግታት ለሸማች ህብረት ስራ ማህበራትና ለዩኔኖች 566 ሚሊዮን ብር የተዘዋዋሪ ብድር ለማቅረብ ታቅዶ 1,375,608,000 ብር (243%) በማቅረብ 2,054,168 ኩ/ል (113%) የሰብል ምርት፣ 648,462 ኩ/ል (71%) የኢንዱስትሪ ምርት፣ 10,914,327 ሊትር (91%) የኢንዱስትሪ ፈሳሽ ምርት በማቅረብ ተችሏል።

የኬላ ላይ ቀረጥን ጨምሮ የባለ ድርሻ ተዋንያን መበራከት በአቅራቢዎች ወጪ መብዛት ምክንያት ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ለማድረግ ህገወጥ ኬላዎችን ለማስነሳት እስከዚህ ሩብ ዓመት 64 ታቅዶ145 (226%) ማስነሳት ተችሏል፡፡ የገበያ ማዕከላትን በማስፋፋት የገበያ ማዕከላት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት እንዲቀርብባቸዉ 56 (467%)፣ ነባር የእሁድ ገበያን ማጠናከር 187 (88%)፣ አዲስ የእሁድ ገበያ ማቋቋም 17 (340%)፣ ሁለገብ የግብይት ማዕከላትን በአዲስ ማቋቋም 56(160%)፣ ነባር የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር 557 (159%) እና አንደኛ ደረጃ የኤክስፖርት ምርቶች ግብይት ማዕከላትን ማቋቋም 9 (180%) ማከናወን ተችሏል፡፡

## ማሕበራዊ ድጋፍ (Social assistance)

ለተጋላጭ የማሕበረሰብ ክፍሎች የአስቸኳይ ጊዜ እና ድህነትን ለመቋቋም ቀጥታ ድግፍ ማድረግን በተመለከተ፤- የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ለተለያዩ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና እንክብካቤ አገልገሎት የሚውል ሀብት ብር 56,691,348.00 ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዞ በጥሬ ብር 45,772,753፣ በዓይነት 103,181,322 በድምሩ 148,954,075 ብር መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም ከዕቅድ በላይ ነው፡፡ በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶች አማካይነት በተሰበሰበ ሃብት 94,975 የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 84,968 (89.46%) (ሴት 47,798) ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ 310,539 የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 359,355 (ሴት 201.028) ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ለድጋፍ የዋለው ብር 307,206,984 ሲሆን በጥሬ ገንዘብ ብር 187,411,366 እና በዓይነት ብር 119,795,618 የሚገመት ድጋፍ ተደርጓል። በጥምረቱ አባላት 109,250,350 ብር( በጥሬ

ገንዘብ 57,367,404 እና በዓይነት 51,882,946 የሚገመት ሃብት በገንዘብ ለማሰባሰብ ዕቅድ ተይዞ ብር 182,132,078 በጥሬ ገንዘብ ብር 84,230,887፣ በዓይነት ብር 97,901,191 መሰብሰብ ተችሏል፡

በልዩ ልዩ አማራጮች ለ26,372 አረጋዊያን ቋሚ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ለማመቻቸት በዕቅድ ተይዞ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን፣ የሲቪክ ተቋማትን፣ እና ሌሎች ማኅበረሰባዊ ተቋማትን በማስተባበር ለ27,453 (ሴት17,371) ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡133,285 (ሴት 77,037) አረጋዊያንን 43,625 (ሴት 24,893) አካል ጉዳተኞችን የነጻ ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለአረጋያን ገቢ ማስገኛ ማዕከላት ግንባታ የሚሆን 8,250,000 ብር የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ከተለያዩ አካላት ለማሰባሰብ ታቅዶ 7,969,200.00 ብር ወይም የዕቅዳችን 97% መሰብሰብ ተችሏል፡ በክረምት በጎ ፍቃድ 118,845 ለሚሆኑ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ጊዜያዊ የቁሳቁስ፣ የገንዘብና ሌሎች ድጋፎችን ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ 315,176 (ሴት 169,445) ተከናውኗል፡፡75,802 በአስከፊ ድህነት ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበራዊ ተሃድሶ ድጋፍ እንዲያገኙ ታቅዶ ለ17,356 (ሴት 9,678) የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፉን እንዲገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በገጠር ልማታዊ ሴፍትኔት** በክልሉ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በሚተገበርባቸው 87 የገጠር ወረዳዎች የድሃ ድሃ የሆኑትን እና ለተለያዩ አደጋዎች የበለጠ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ማዕከል ያደረገ የተጠቃሚዎች የልየታ ስራ ተሰርቶል፡፡ በዚህም መሠረት በ2018 የበጀት ዓመት በ87 የፕሮግራም ወረዳዎች ለመፈፀም እቅድ ተይዞ በሁሉም 87 (100%) ወረዳዎች ውስጥ 22,419 የፕሮግራም ተጠቃሚዎችን ወደ ፕሮግራሙ በማስገባት ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በ2018 የበጀት ዓመት በአዲስ የተካተቱ የፕሮግራም ተጠቃሚዎችን ጨምሮ 676,812 የቤተሰብ ኃላፊዎች እና 1,887,378 የፕሮግራም ደንበኞችን ይዞ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ የፕሮግራም ተጠቃሚዎች መካከልም 1,591,340 (84.4%) ለማህበረሰቡ ልማቱ ጉልበት በማበርከት ድጋፍ የሚያገኙ የማህ/ድጋፍ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ 293,038 (15.6%) የፕሮግረም ተጠቃሚዎች ደግሞ ለልማት ስራ ምንም ጉልበት ሳያበረክቱ በነፃ ድጋፍ የሚያገኙ ቋ/ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም ከጠቅላላ የፕሮግራም ተጠቃሚዎች ውስጥ 993,705 (53%) የሚሆኑት ሴት የፕሮግራም ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በ2017 የበጀት አመት ሳይከፈል የከረመ የምግብ እህል ድጋፍ እቅድ 3,070.6 ሜ/ቶ ሲሆን 3,070.6 ሜ/ቶ እህል ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በክልል ደረጃ ያለዉን ፖቴንሻል መሰረት በማድረግ 8,969 ሂ/ር መሬት የሰብል ማሳ በሰብል በመሸፈን 358,756

ኩ/ል እህል እቅድ ተይዞ በ89 ወረዳዎች ላይ 5,404 ሄ/ር የሰብል ማሳ በዘር ለመሸፈን ተችሏል፡፡ እስካሁን ከተዘራዉ ማሳ ዉስጥ 2,069 ኩ/ል መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የከተማ ሴፍትኔት እና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራዎች

**የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎች፡-** በክልላችንም በፕሮግራሙ በታቀፉ 18 ከተሞች ወደ ፕሮግራሙ የተቀላቀሉ አዲስ የመንግስት መቀናጀ በጀት ተጠቃሚዎችን ጨምሮ 159,173 ዜጎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማሳተፍ እና 36,672 ዜጎችን በቀጥታ ድጋፍ በጠቅላላው 195,845 ዜጎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ግብ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**የተጠቃሚዎች ወርሀዊ ክፍያ፡-** በከተሞች የሚገኙ የመስራት አቅም የሌላቸዉና ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ 36,672 ዜጎች (የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአዕምሮ ህሙማን እና ህጻናት) የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ36,672 ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ለእያንዳንዳቸው 525 ብር ወርሃዊ ክፍያ በመፈፀም ከሀምሌ 1/2017 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30/2018 ዓ.ም 115,516,800 ብር (100%) ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ላይ 50,953 የመስራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎችን (ሰሪ ኃይሎችን) በማሳተፍ 159,173 ተጠቃሚዎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ18ቱ ከተሞች ወንድ 12,574 ሴት 38,104 በድምሩ 50,678 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ ወንድ 65,818 ሴት 91,381 በድምሩ 157,199 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለተጠቃሚዎች በ6 ወሩ 597,867,945 ብር ወርሃዊ ክፍያ ለማስተላለፍ ታቅዶ 600,705,204 ብር ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን አፈፃፀሙም 99% ነው፡፡

**የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ሥራዎች፡-** በ6 ወሩ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩና በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ 51,125 የቤተሰብ ሃላፊዎች በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ በማድረግ በዘላቂነት ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 12,166 ሴት 38,361 ድምር 50,527 አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## 1.4. የስራ እድል ፈጠራ

በአጠቃላይ በገጠረ እና ከተማ በበጀት ዓመቱ በሶስቱም ዘርፎቭ 65,710 እስከ ታህሳስ ወር 26,284 ኢንተርፕራይዞች ለመመስረት ታቅዶ፣ 36,787 ኢንተርፕራይዞች ማቋቋም የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከአመቱ 55.98%፣ ከ6 ወሩ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር በሁሉም የስራ አማራጮች 1,096,074 (ቋሚ 876,859 ጊዜያዊ 219,215) እስከ ታህሳስ ወር 438,430 (ቋሚ 350,744 ጊዜያዊ 87,686) የሥራ

ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፡- ቋሚ ወንድ 215,694 ሴት 240,557 ድምር 456,251 ጊዜያዊ ወንድ 101,265 ሴት 67,875 ድምር 169,140 በአጠቃላይ ወንድ 316,959 ሴት 308,432 በድምሩ ለ625,391 የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም ከዓመቱ 57.06%፣ ከ6 ወሩ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በግማሽ ዓመቱ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ ወንድ 17,052 ሴት 86,929 ድምር 103,981 በቋሚነት የውጭ አገር የስራ ስምሪት ያገኙ ናቸው፡፡ ከሚፈጠረው የሥራ እድል ውስጥ 80% እና በላይ ዘላቂ (ቋሚ) የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ456,251 ወይም 72.95 በመቶ የሚሆኑት በቋሚነት የተቀጠሩ ናቸው።

## 1.5. የክልሉ የፊዚካል ፖሊሲ አፈፃፀም

### 1.5.1. የክልሉ መንግስት ገቢ አፈፃፀም

በ2018 በጀት አመት የገቢ አሰባሰብን በተመለከተ ከታክስ ገቢዎች ብር 82 ቢሊዮን፣ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ደግሞ ብር 2.87 ቢሊዮን በድምሩ ብር 84.87 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ በስድስት ወሩ ታክስ ከሆኑ ገቢዎች ብር 37.05 ቢሊዮን ወይም የዕቅዱን 45.18 በመቶ እንዲሁም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ብር 0.885 ቢሊዮን ወይም የዕቅዱን 30.8 በመቶ መሰብሰብ ተችሏል። በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ብር 37.935 ቢሊዮን በመሰብሰብ በአመቱ ለመሰብሰብ ከታቀደው 44.7 በመቶ የሚሆነውን ማሳካት ተችሏል።

**ሠንጠረዥ 2፦** የ2018 በጀት አመት የክልሉ መንግስት ገቢ አሰባሰብ

| ተ.ቁ | ዓይነት | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከመደበኛ ገቢ | በቢሊየን ብር | 84.872 | 37.935 | 44.7 |
| 1.1 | ከታክስ ገቢዎች | በቢሊየን ብር | 82 | 37.05 | 45.18 |
| 1.2 | ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች | በቢሊየን ብር | 2.872 | 0.885 | 30.8 |
| 2 | ከተማ አገልግሎት ገቢ | በቢሊየን ብር | 15.5 | 4.85 | 31.3 |
| 3 | ከድጎማ | በቢሊየን ብር | 70.8 | 42.92 | 60.62 |

**ምንጭ፦** የአብክመ ገንዘብ ቢሮ

**የ2018 በጀት አመት የክልሉ መንግስት ወጪ አፈጻጸም፦** በበጀት አመቱ ለመደበኛ ወጪ ብር 144.285 ቢሊዮን እንዲሁም ለካፒታል ወጪ ብር 48.095,09 ቢሊዮን በድምሩ ብር

192.38 ቢሊዮን በወጪነት የተደለደለ ሲሆን ከዚህ ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በግማሽ ዓመቱ ለመደበኛ ስራዎች ብር 53.81 ቢሊዮን እንዲሁም ለካፒታል ስራዎች ብር 6.37 ቢሊዮን በድምሩ ብር 60.18 ቢሊዮን ወጪ ተየተደረገ ሲሆን ጠቅላላ ወጪ ከተደረገው 89.42 በመቶው ለመደበኛ ተግባራት ወጪ የተደረገ ሲሆን 10.58 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ለካፒታል ፕሮጀክቶች ወጪ ተደርጓል።

***ሠንጠረዥ 3፡-*** የ2018 በጀት አመት የክልሉ መደበኛ እና ካፒታል ወጪ ዕቅድ አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ዓይነት | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | አጠቃላይ ወጪ | በቢሊየን ብር | 225 | 60.18 | 26.75 |
| 2.1 | መደበኛ | በቢሊየን ብር | 138.47 | 53.81 | 38.86 |
| 2.2 | ካፒታል | በቢሊየን ብር | 86.98 | 6.37 | 7.3 |

***ምንጭ፡-*** *የአብክመ ገንዘብ ቢሮ*

### 1.5.2. የወጭ ምርት /ኤክስፖርት/ አፈፃፀም

***የኤክስፖርት ምርት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በገቢ ማሳደግ፡-*** 3,022,369 ኩ/ል የቅባት፣ የጥራጥሬ እህል ምርትን እና ቡናን ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 1,877,797 (62%) መላክ ተችሏል። የቁም እንስሳትን በቁጥር 8,030 ወደ ውጪ ለመላክ ታቅዶ 13,920 (100%) የተላከ ሲሆን ከተላከው የቁም እንሰሳት 893,408 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 1,140,180 ዶላር (100%) ማግኘት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ከሰብል ምርትና ከቁም እንስሳት በድምሩ 281,599,537 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 183,022,610 ዶላር (65%) እንደሚገኝ ይገመታል፡፡

***የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ ለማድረግ፣*** የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ በተሰራው ስራ ሰሊጥ፣ አኩሪ አተር፣ በቆሎ እና የቢራ ገብስ 932,966 ኩ/ል ለማቅረብ ታቅዶ 1,295,742 (139%) ተኪ ምርት ለፋብሪካዎች በማስተሳሰር ይወጣ የነበረዉን የዉጭ ምንዛሬ ማዳን ተችሏል፡፡

***የአምራች ኢንዱስትሪዎች የወጭ ምርት /ኤክስፖርት/ ማሳደግ፤*** በነባር ኢንዱስትሪዎች በመካከለኛ 8 እና በከፍተኛ 18 በድምሩ 26 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 36,819 ቶን በመላክ 70 ሚሊ.ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ በመካከለኛ 12 እና

ከፍተኛ 23 በድምሩ 35 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 42,182.07 ቶን በመላክ 111.026 ሚሊ.ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በምርት መጠንና በገቢ መጠን ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ 4 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 3,748 ቶን ምርት በመላክ 14 ሚሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ በ6 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 4,014 ቶን ምርት በመላክ 8.64 ሚሊየን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡

**ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን የሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያድኑትን የውጭ ምንዛሬ እና የአገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ማሳደግ፤** 286 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ በ46 አይነት ተኪ ምርቶች 219,150 ቶን ምርት በማምረት 280 ሚሊዮን ዶላር ውጭ ምንዛሬን ለማስቀረት/መተካት ታቅዶ 409 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ በ69 አይነት ምርቶች 296,966.57 (100%) ቶን እንዲመረት በማድረግ 335.77 (100%) ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬን መተካት/ማስቀረት ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ 25,139.39 ኪ.ግ በግማሽ ዓመቱ 12,569.695 ኪግ የከበሩ የማዕድን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ በበጀት አመቱ 10,389,720 በግማሽ አመቱ 5,194,860 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 12,289.57 ኪግ በመላክ 9,439,325.13 የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል። በዚህም መሰረት ከምርት ከዓመቱ 49% ከግማሽ አመቱ 97.77% መፈፀም የተቻለ ሲሆን በምንዛሬ ግኝት ደግሞ ከዓመቱ 84.4% እና ከግማሽ አመቱ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል። በአጠቃላይ ከተገኘው የውጭ ምንዛሬ መካካል ድርሻ ሲታይ ወርቅ 71.89%፣ ጥሬ ኦፓል 19.08% እና የተዋበ ኦፓል 9.03 % ነው፡፡

**የውጭ ሀገር ቱሪስትና ገቢን ከማሳደግ አኳያ፡-** ወደ አማራ ክልል ከሚመጡ ከውጪ ሀገር ቱሪስት ፍሰት የሚገኘውን ገቢ በግማሽ ዓመቱ 81,782,760 ብር ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ 108,793,638 ብር ማድረስ ከዕቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፦ በአራት ዘርፎች የተገኘ የወጭ ንግድ**

| ተ.ቁ | ዘርፍ | ወጭ ንግድ (ዶላር) | ወጭ ንግድ (ብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | ከግብርና | 183,022,610 | 27,819,436,720 |
| 2 | ከአምራች ኢንዱስትሪ | 119,666,000 | 18,189,232,000 |
| 3 | ከማዕድን | 9,439,325 | 1,434,777,400 |
| 4 | ከቱሪዝም | 715,748 | 108,793,638 |

| | | |
|---|---|---|
| ጠቅላላ ድምር | 312,843,683 | 47,552,239,758 |

*ምንጭ፦ የአብክመ አራቱ ዘርፎች የግማሽ አመት ሪፖርት*

# ክፍል ሁለት፡ *የዘርፎች ልማት አፈጻጸም*

## 2.1. አምራች ኢንዱስትሪ

የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች በሁሉም ዘርፍ ከመፈለጋቸው እና ረጅም የእሴት ሰንሰለትን መፍጠር የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ በውስን ሀብት ፊት የሚሰፋውን፣ የሚያድገውን እና የሚራቀቀውን እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ጤና (መድኃኒት)፣ መጓጓዣ፣ መገናኛ፣ ቴክኖሎጂ፣ ደህንነት እና ከፍ ሲልም ሉዓላዊነት በመሳሰሉት የሚገለጹ ፍላጎቶችን ማሟላት የሚቻለው በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ነው። በቴክኒካዊ ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪ የዚህ መሠረታዊ ሀብትን የማብዛት፣ የማሳደግ እና የማራቀቅ አቅም የዘርፉ የቋሚ ግብዓቶች ምርታማነት ከፍተኛ መሆን ነው። የሌሎች አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የኢንዱስትሪ እድገትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የሚወሰነው በአብዛኛው በአምራች አንዱስትሪ ልማት ስኬት ላይ ነው። ስለሆነም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሁለተኛዉ ሩብ ዓመት የተከናወኑ ተግባራትን ሪፖርት እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

**የክልሉን የቋሚ ግብዓቶችን ምርታማነት በመጨመር እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በማስጀመር እንዲሁም የመሰረተ ልማት አቅርቦት እና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በ2017 ከተደረሰበት 59.22 በመቶ በ2018 ወደ 63 በመቶ ማሳደግ፡-** ለ261 መካከለኛና ለ116 ከፍተኛ በድምሩ ለ377 ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ500 መካከለኛና ለ142 ከፍተኛ በድምሩ ለ642 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን የድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የአምራች ኢንዱሰትሪዎችን ምርታማነት በመጨመር የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ያለባቸውን የማምረቻ መሳሪያ ማዘመንና ማሟላት የሚያስፈልግ በመሆኑ 45 መካከለኛ እና 4 ከፍተኛ በድምሩ 49 አምራች ኢንዱስትሪዎችን የብድር ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ30 መካከለኛ እና ለ8 ከፍተኛ በድምሩ 38 (81%) አምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግር በመፍታት የሊዝ ብድር ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን 1,383.74 (100%) ሚሊዮን ብር ብድር ለመስጠት ተችሏል። በተመሳሳይ ምርት ላይ ያሉ 65 መካከለኛና 26 ከፍተኛ በድምሩ የ91 አምራች ኢንዱሰትሪዎችን የስራ ማስኬጃ ብድር ችግር ለመፍታት ታቅዶ የ66 መካከለኛ እና የ38

ከፍተኛ በድምሩ የ104 (100%) ኢንዱስትሪዎች የስራ ማስኬጃ የብድር ችግር ተፈቷል፡፡ ተጠቃሚነት በብር ሲታይ 6.525 ቢሊየን ብድር ለመስጠት ታቅዶ 18.056 (100%) ቢሊዮን የስራ ማስኬጃ ብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል እርስ በእርስ በተፈጠረ ትስስር ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ለ84 አምራች ኢንዱስትሪዎች 24,083 ቶን ግብዓት በማቅረብ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የግብዓት ችግር ለመፍታት ታቅዶ 87,484.97 (100%) ቶን በማቅረብ ለ123 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ችግርን መፍታት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለ2 መካከለኛ የቆዳ ኢንዱስትሪዎች 12,373 ካሬ ጫማ ለማቅረብ ታቅዶ ለ1 (50%) መካከለኛ ኢንዱስትሪ 262,312 (100%) ካሬ ጫማ ማቅረብ ተችሏል፡፡

ከትስስር ውጭ ማለትም ከግብዓት አቅራቢዎች፣ ከነጋዴዎች እና ከአምራቾች በሚገኝ ግብዓት ለ148 አምራች ኢንዱስትሪዎች 107,399 ቶን በማቅረብ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የግብዓት ችግር ለመፍታት ታቅዶ 240,283.7 (100%) ቶን በማቅረብ ለ241 መካከለኛና ለ79 ከፍተኛ በድምሩ ለ278 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ችግርን መፍታት የተቻለ ሲሆን ለ19 አምራች ኢንዱስትሪዎች በውጭ ገበያ የሚሸፈን 21,204 ቶን በማቅረብ የግብአት ችግርን መፍታት ታቅዶ ለ12 መካከለኛና ለ21 ከፍተኛ በድምሩ ለ33 (100%) ኢንዱስትሪዎች 196 ሚሊየን ዶላር የሚያወጣ 18,270.75 ቶን ግብዓት ማቅረብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንታዊ ድጋፍ በማድረግ መካከለኛ 295፣ ከፍተኛ 112 በድምሩ 407 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማጠናከር ታቅዶ መካከለኛ 396፣ ከፍተኛ 175 በድምሩ 571 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎችን እንዲጠናከሩ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የተዘጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማለትም ምርት ማምረት ጀምረውና ምርታቸውን ለገበያ ማቅረብ ችለው ነገር ግን ለ6 ወር እና ከዚያ በላይ ማምረት ያቆሙ ባጋጠማቸው ችግር ወይም በራሳቸው ምክንያት ሰራተኞቻቸውን የበተኑ/ያሰናበቱ፣ የስራ መስክ የቀየሩ ወይም ባለማምረታቸው ምክንያት የዘመኑን ግብር ያልከፈሉና ለሚመለከተው አካል ያሳወቁትን የተለያዩ ድጋፎች በማድረግ 25 መካከለኛ፣ 14 ከፍተኛ በድምሩ 39 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ምርት ለመመለስ ታቅዶ መካከለኛ 24፣ ከፍተኛ 11 በድምሩ 35 (92.1%) ወደ ምርት መመለስ ተችሏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለሃብቶች ፕሮጀክታቸውን ሲያቀርቡ በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ እና ክፍተታቸውን ለይቶ ድጋፍ ለማድረግ የፐርፎርማንስ ወይም ክዋኔ ኦዲት ይደረጋል፡፡ በዚህም መካከለኛ 201፣ ከፍተኛ 82 በድምሩ 283 ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ መካከለኛ

344፣ ከፍተኛ 131 በድምሩ 475 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች የአፈጻጸም ኦዲት የተደረጉ ሲሆን አምራች ኢንዱሰትሪዎች በየዓመቱ የፋይናንሻል ኦዲት እንዲያስደርጉ በመደገፍ ያሉበትን ነባራዊ እንቅስቃሴ በማወቅ ለቀጣይ የተሟላ ድጋፍ በማድረግ የማምረት አቅማቸውን በማሳደግ ከደረጃ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ለማስቻል ያግዛል፡፡ በመሆኑም መካከለኛ 208፣ ከፍተኛ 85 በድምሩ 293 ኢንዱስትሪዎች ፋይናንሻል ኦዲት እንዲያስደርጉ ለመደገፍ ታቅዶ መካከለኛ 273፣ ከፍተኛ 105 በድምሩ 378 (100%) አምራች ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ እንደ ክልል የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም አጠቃቀም ለማወቅ ካሉት ኢንዱሰትሪዎች ውስጥ 50%ቱን በመለካት በበጀት ዓመቱ 63% ማድረስ ግብ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሩብ ዓመት 270 መካከለኛና 91 ከፍተኛ በድምሩ 361 ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም አጠቃቀማቸውን ለመለካት ታቅዶ 482 መካከለኛና 169 ከፍተኛ በድምሩ የ651 ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም አጠቃቀማቸው የተለካ ሲሆን የማምረት አቅማቸውን 62.42% ማድረስ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ኢንዱስትሪዎች መለየትና ቀምሮ ለሌሎች በማስፋት ውጤታማነትን ከፍ እንዲል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም 5 ተሞክሮዎችን በመቀመርና 2 ተሞክሮዎችን ለ10 መካከለኛና ለ3 ከፍተኛ በድምሩ ለ13 ኢንዱስትሪዎች በማስፋት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 41 ተሞክሮዎችን በመቀመርና 26 ተሞክሮዎችን ለ61 መካከለኛና ለ37 ከፍተኛ በድምሩ ለ98 ኢንዱስትሪዎች በማስፋት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ከአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚገኘዉን የወጭ ምርት /ኤክስፖርት/ ገቢ ከነበረበት 156.8 ሚሊየን ዶላር ወደ 193.39 ሚሊየን ዶላር ማድረስ፡-** ለነባርና በአዲስ ምርታቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ እና ተጨማሪ አቅም በመፍጠር ምርታቸውን ወደ ውጭ እንዲልኩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የኤክስፖርት ገቢን የማሳደግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም በነባር ኢንዱስትሪዎች መካከለኛ 8፣ ከፍተኛ 18 በድምሩ 26 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 36,819 ቶን በመላክ 70 ሚሊ..ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ መካከለኛ 12፣ ከፍተኛ 23 በድምሩ 35 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 42,182.07 (100%) ቶን በመላክ 111.026 (100%) ሚሊ..ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 4 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 3,748 ቶን ምርት ልከው 14 ሚሊየን ዶላር እንዲያስገኙ ታቅዶ 6 የሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 4,014 ቶን ምርት ልከው 8.64 ሚሊየን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ በፕሮጀክት ቁጥር 100% በገቢ 62 % መፈጸም ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በግማሽ አመቱ በሁለቱም ዘርፍ ከወጭ ምርት 83.8 ሚሊ/ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 119.6 ሚሊ/ዶላር ማግኘት ተችሏል አፈጻጸሙ100% ነው፡፡

**ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን በሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚድን የውጭ ምንዛሬ መጠን ከ755.27 ሚሊየን ዶላር ወደ 770.09 ሚሊየን ዶላር ማድረስ፡-** በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ተገዝተው ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ የፍጆታም ሆነ ሌሎች ምርቶችን በሃገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም ገቢ ምርትን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና ድጋፍ በማድረግ ተኪ ምርትን እንዲያመርቱ እና የሃገር ውስጥ ምርትን የገበያ ድርሻውን ከፍ የማድረግ ስራ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት 286 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ በ46 አይነት ተኪ ምርቶች 219,150 ቶን ምርት በማምረት 280 ሚሊዮን ዶላር ውጭ ምንዛሬን ለማስቀረት/መተካት ታቅዶ 409 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ በ69 አይነት ምርቶች 296,966.57 (100%) ቶን እንዲመረት በማድረግ 335.77 (100%) ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬን መተካት/ማስቀረት ተችሏል፡፡

**በአምሥት ዓመቱ መጨረሻ ጥናታቸው ተጠናቆ በሁለተኛው አምሥት ዓመት የልማት ዕቅድ በስፋት ለሚጀመሩት የብረታ ብረት እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች ላይ መሥራት፤**10 የብረታ ብረት፤በማሽን፣ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 9 ከፍተኛ 1 በድምሩ 10 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር ተችሏል፡፡

**በክልሉ የአገር ዉስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙ ሆነ ከዉጭ የሚገቡ ማዕድናት ላይ እሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፡-** የአገር ውስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ማዕድናት ለግብርና እና ለኮንስትራክሽን ዘርፍ በግብዓትነት የሚጠቀሙ የኬሚካልና ኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ መካከለኛ 3፣ ከፍተኛ 3 በድምሩ 6 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ 13 መካከለኛ፣5 ከፍተኛ በድምሩ 18 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም የተቻለ ሲሆን መካከለኛ 5፣ከፍተኛ 2 በድምሩ 7 የአገር ውስጥ ማዕድናትን የሚጠቀሙም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ማዕድናት ለግብርና እና ለኮንስትራክሽን ዘርፍ በግብዓትነት የሚጠቀሙ ብረት ነክ ያልሆኑና ሌሎች ውጤቶች ማምረቻ ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 9 ከፍተኛ 1 በድምሩ 10 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር ተችሏል፡፡

**አምራች ኢንዱስትሪዉ በሚያተኩርባቸዉ ዘርፎች በዋናነት የክልሉን የሰብልና የእንስሳት ሀብት የሚጠቀሙ አግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን ከግብርና ዉጤቶች ጋር ማስተሳሰር፦-** የሰብል እና የእንስሳት ሀብት የሚጠቀሙ አግሮ-ፕሮሰሲንግ (ምግብና መጠጥ) መካከለኛ 19፣ ከፍተኛ 8 በድምሩ 26 ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ21፣ ከፍተኛ 5 በድምሩ 26 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም /በአዲስ ምርት/ በማስጀመር ከግብርና ዉጤቶች ጋር ማስተሳሰር ተችሏል፡፡

**ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማቶች ላይ ርብርብ ማድረግ፤**የአምራች ኢንዱሰትሪዎችን ምርታማነት በመጨመር የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ያለባቸውን የመሰረተ ልማት ችግር በሚፈልጉት መጠንና ጥራት ማሟላት የሚያስፈልግ ሲሆን መካከለኛ 116 ከፍተኛ 47 በድምሩ የ163 ኢንዱስትሪዎችን የመሰረተልማት ችግር ለመፍታት ታቅዶ ለ176 መካከለኛ ለ82 ከፍተኛ በድምሩ ለ258 ኢንዱስትሪዎች ለሚሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሰረተ ልማት ችግር መፍታት መፍታት የተቻለ ሲሆን ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሰረተ ልማት ችግር ማለትም ውሃ ችግር ያለባቸዉ የ14 ፕሮጀክቶችን ችግር ለመፍታት ታቅዶ 53 (100%) እንዲሁም የመብራት ችግር ያለባቸዉ 75 ፕሮጀክቶችን ችግር ለመፍታት ታቅዶ 96 (100%) መፍታት ተችሏል፡፡

**ሰፋፊ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ፋብሪካዎችን፣የቆዳ እና መጫሚያ ፋብሪካዎችን ማቋቋም፤** 6 የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 7 ከፍተኛ 2 በድምሩ 9 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር የተቻለ ሲሆን 1 የቆዳና መጫሚያ ፋብሪካዎችን ለማቋቋም ታቅዶ መካከለኛ 1(100%) ኢንዱስትሪ ማቋቋም/በአዲስ ምርት ማስጀመር ተችሏል፡፡

**ለመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ 17 ኢንዱስትሪዎችን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ ማስቻል፦-** የኢንዱስትሪዎች ሁለንተናዊ ድጋፍ ተደርጎላቸው ችግሮቻቸው ከተፈቱላቸው የማምረት አቅማቸው ከፍ እንደሚል ይጠበቃል በመሆኑም በዋናነት በሚያሳዩት እድገት የካፒታልና የሰው ኃይል ጭማሬ/ለውጥን/እና ሌሎች መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ደረጃቸውን ካሉበት ወደ ቀጣዩ የተሻለ ደረጃ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም 9 ኢንዱስትሪዎችን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ለማሸጋገር ታቅዶ 14 (100%) ኢንዱስትሪዎችን ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ማሸጋገር ተችሏል፡፡

**በዘርፉ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲኖር ማስቻል፤** ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ክህሎት ያለው የሰው ሀይል ማቅረብ ለምርትና ምርታማነት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡ በመሆኑም 666 በተለያዩ ዘርፎች ክህሎት ያለው የሰው ሀይል ለማቅረብ ታቅዶ 1,870 የሰለጠነ የሰው ሃይል ማቅረብ ተችሏል፡፡

**አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎችንእና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በማቋቋምና ነባሮችን በማጠናከር 62,069 ዜጎች ቋሚእና 6,069 ጊዜያዊ የስራ እድል በመፍጠር የሴቶችንና የወጣቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-** በአምራች ኢንዱስትሪውና በሌሎች የኢንንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለ35,390 ዜጎች ቋሚና ለዜጎች 3,033 ጊዜያዊ ስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ 33,875 ቋሚና ለ9,072 ዜጎች ጊዜያዊ በድምሩ 42,947 (ወንድ 23,969 ሴት 18,979) (100%) ዜጎች የስራ እድል የተፈጠረ ተፈጥሯል፡፡

## 2.2. ዘመናዊ ግብርና

**በ2017/18 የምርት ዘመን 5,398,393 ሄ/ር መሬት በማልማትና ምርቱንም በ10% በማሣደግ 187,540,749 ኩ/ል ምርት በማምረት ምርታማነቱን በ2016/17 ምርት ዘመን ከነበረበት 32.3 ኩ/ል/ በሄ/ር ወደ 34.7 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ፡-** በ2017/18 ምርት ዘመን በመኸር (በመደበኛና በኮሞዲቲ) ሠብሎች 5,398,393 ሄ/ር መሬት በማልማት 187,540,749 ኩ/ል ምርት ለማምርት ታቅዶ 5,533,592 (103%) ሄ/ር መሬት በዘር በመሸፈን እስከአሁን ባለዉ መረጃ 138,011,468 ኩ/ል (77%) ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በዚህም በምግብ ሰብል 75,275,997 ኩ/ል (66.6%) ፣ በኢንዳስትሪ ሰብል 51,347,089 ኩ/ል (80.46%) እና በኤክስፖርት ሰብል 11,388,382 ኩ/ል (108%) ምርት መሰብስብ ተችሏል፡፡ በዚህም 1,793 ትራክተሮችን በመጠቀም 1,037,598 (100%) ሄ/ር መሬት ማረስ የተቻለ ሲሆን 76 ኮምባይነር እና 119 ትሬሸር በመጠቀም ምርት ተሰብስቧል፡፡

በምርት ዘመኑ በ10 በተመረጡ የኮሞዲቲ ሰብሎች 2,791,913 ሄ/ር ጠቅላላ ከሚለማው መሬት 52% ለማልማት ታቅዶ 39,873 ክላስተር በማደራጀት 2,730,603 (98%) ሄ/ር ማሳ በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ሰብልን በመስመር መዝራት በምርት ዘመኑ ይለማል ተብሎ በእቅድ ከተያዘው መሬት ውስጥ 2,698,437 ሄ/ር በመስመር ለመዝራት ታቅዶ 2,318,995 ሄ/ር (86%) መሬት በመስመር ተዘርቷል፡፡

**የ2017/18 ምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት፡-** ለምርት ዘመኑ በአዲስ ተገዝቶ የሚቀርብ 8,800,000 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ (ዳፕ 4,400,000 እና ዩሪያ 4,400,000) ለማቅረብ ታቅዶ 8,800,000 ኩ/ል የተገዛ ሲሆን ከዚህም በአዲስ ከወደብ የቀረበዉን 7,539,696 በማቅረብ እስከዚህ ሩብ ዓመት ለመኸር እና ለመስኖ ልማት 7,100,000 ኩ/ል (94%) የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ ለ2017/18 ምርት ዘመን ተገዝቶ የቀረበዉ የአፈር ማዳበሪያ ከባለፈው ምርት ዘመን ከተገዛው 8,057,900 ኩ/ል ጋር ሲነጻጸር የዚህ ዓመቱ በ742,100 ኩ/ል ብልጫ አለዉ፡፡

**የ2018/19 ምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፡-** ለምርት ዘመኑ በአዲስ ተገዝቶ የሚቀርብ ዳፕ 3,888,000 ኩ/ል ዩሪያ 4,752,000 ኩ/ል በድምሩ 8,640,000 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ እስከዚህ ሩብ ዓመት ወደብ ላይ የደረሰ 1,435,790 ኩ/ል ሲሆን ከዚህም 625,999 ኩ/ል ወደ ዩኔን ማስገባት ተችሏል፡፡

በዘላቂነት የተቀናጀ የአፈር ለምነትን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በቁልፍ ተግባር ተይዘዉ ከሚከናወኑ ተግባራት ዉስጥ በበጀት ዓመቱ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ተግባራትን በማከናወን በዘላቂነት የመሬት ለምነትን ለማሻሻል ጥራትን መሰርት ያደረገ 76,589,920 መደበኛ ኮምፖስት ለማዘጋጅት ታቅዶ 81,277,546 ሜ/ኩብ በማዘጋጀት ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡ ፡ እንዲሁም 599,450 ቨርሚ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 447,772 (100%) ማዘጋጀት ተቸሏል፡፡ በተመሳሳይ 216,170 ሜ/ኩ ባዮስለሪ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 197,129 ሜ/ኩ (91%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

**የህየዉ ማዳበሪያ ልማት፡-** በምርት ዘመኑ 775,000 ሳቸት በመጠቀም 193,750 ሄ/ር የጥራጥሬ ሰብል በህየው ማዳበሪያ ለማልማት ታቅዶ 682,836 ሳቸት (88%) ህየወ ማዳበሪያ በመጠቀም 170,709 ሄ/ር (88%) ማሳ የጥራጥሬ ሰብል ማልማት ተችሏል፡፡

**ሌላው የኮትቻ አፈር ልማት፡-** በምርት ዘመኑ በዘመናዊ 123,199 ሄ/ር እና በባህላዊ 527,294 ሄ/ር በድምሩ 650,493 ሄ/ር ማሳ ለማጠንፈፍ ታቅዶ 428,594 ሄ/ር በመለየት በ5,271 ክላስተር በማደራጀት በቢቢኤም 83,759 ሄ/ር እና በባህላዊ ደግሞ 596,977 ሄ/ር በድምሩ 680,736 ሄ/ር (105%) በማንጣፈፍ ማልማት ተችሏል፡፡

**ሄልማቲክ ጆንያ አጠቃቀም፡-** በበጀት ዓመቱ በዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት በተያዙ ወረዳዎች እና በሌሎች ባልታቀፉ ወረዳዎች 1,500,000 ሄልማቲክ ጆንያ ለማቅረብ ታቅዶ 1,648,692 (100%) የሄርማቲክ ጆንያ ጥቅም ላይ ማዋል እንዲሁም የብረት ጎተራ አቅርቦትና ስርጭት በዓለም ምግብና

እርሻ ድርጅት በተያዙ ወረዳዎችና በሌሎች ባልታቀፉ ወረዳዎች 1,100 ዘመናዊ የብረት ጎተራ ለማቅረብ ታቅዶ 897 (81.5%) ዘመናዊ የብረት ጎተራ ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

**ከአምራች ኢንዱስትሪዎች 6,419,760 ኩንታል ኖራ በማስመረት 320,988 ሄ/ር መሬት ማከም በተመለከተ፡-** የአፈር አሲዳማነት ለመከላከል በ15,450 ሄ/ር መሬት ላይ 61,975 የአሲዳማ አፈር ናሙና ለማሰባሰብ ታቅዶ በ8,325 ሄ/ር መሬት ላይ 31,303 የአፈር ናሙና በመሰብሰብ 25,245 (81%) ናሙና በላብራቶሪ በማስመርመር የ18,498 ናሙና ዉጤት የተገለጸ ሲሆን በዚህም 7,329 ናሙና ወይም 2,082 ሄ/ር ማሳ አሲዳማ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አሲዳማ አፈርን ለማከም በምርት ዘመኑ 370,800 ኩ/ል ኖራ በመጠቀም 12,360 ሄ/ር መሬት ለማከም ታቅዶ ከቀረበው 187,048 ኩ/ል ውስጥ 162,758 ኩ/ል ለ23,645 አርሶ አደሮች ማሰራጨት ተችሏል፡፡

**በ2016/17 የምርት ዘመን ከመኸር አትክልት፣ ስራስር እና ቅመማ ቅመም ሰብሎች የተገኘውን 29.5 ሚሊየን ኩንታል ምርት 286,506 ሄ/ር መሬት በማልማት ምርቱን ወደ 32.48 ሚሊየን ኩንታል ማሳደግ፡-** በአጠቃላይ በአትክልት፣ ስራስርና ቅመማቅመም ሰብሎች 286,506 ሄ/ር መሬት በማልማት 32,478,975 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 312,044 (109%) ሄ/ር መሬት በማልማት 32,762,562 ኩ/ል ምርት (101%) ተሰብስቧል፡፡ የስራስር ሰብሎች በመኸር 148,626 ሄ/ር በማልማት 23,349,280 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 152,565 (103%) ሄ/ር መሬት ማልማት ተችሏል፡፡ እንዲሁም አትክልት ሰብሎች በመኸር 49,388 ሄ/ር በማልማት 7,905,265 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 54,107 ሄ/ር (110%) በዘር ተሸፍኗል፡፡ በተመሳሳይ ቅመማ ቅመም ሰብሎች በመኸር 88,492 ሄ/ር በማልማት 1,224,431 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 105,372 ሄ/ር (118%) መሬት በማልማት 1,469,959 ኩ/ል (120%) ምርት መሰብስብ ተችሏል፡፡

**የእርሻ መካናይዜሽን አጠቃቀምን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 21.73 በመቶ ወደ 28.68 በመቶ ማሳደግ፡-** 1,476,792 ሄ/ር ሜካናይዜሽን እርሻ ምቹ የሆነውን መሬት ለማልማት ታቅዶ 1,023,540 (69.31%) ማልማት የተቻለ ሲሆን 1,000 ትራክተሮችን ለአርሶ አደሩ ለማሰራጨት ታቅዶ 416 (41.3%) ትራክተር ማሰራጨት ተችሏል፡፡ 1,000 የውሀ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ ለማሰራጨት ታቅዶ 3876 (100%) እንዲሁም 50 አነስተኛ መዉቂያ ማሽን እና 1 ትሬሸር ማሰራጨት እንዲሁም የምርት ብክነትን ለመቀነስ የምርት መሰብሰቢያ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም በበጀት ዓመቱ 400 ኮምባይነር፣ 250 ትሬሸር እና 219 ሸለር ለማቅረብና ለማሰራጨት ታቅዶ 6 ኮምባይነር (1.5%)፣ 304 ትሬሸር (100%) እና 320 ሸለር (100%) ማሰራጨት ተችሏል፡፡

**በመስኖ የሚለማውን 383,686 ሄክታር መሬት በድግግሞሽ በማልማት ከ30.098 ሚሊየን ኩንታል ምርት በ2018 ወደ 52.346 ሚሊየን ኩንታል ማሳደግ፡-** በነባር 232,509 ሄ/ር (70%) እና በአዲስ 51,554 ሄ/ር (99%) በድምሩ 284,063 ሄ/ር (74%) በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡

**በበጋ ስንዴ የለማውን 207,081 ሄክታር መሬት በ2018 ወደ 260,000 ሄክታር መሬት በማድረስ አማካይ ምርታማነቱን 39.31 በማድረስ 10.2 ሚሊየን ኩንታል ማምረት፡-** በበጀት ዓመቱ 260,000 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 284,309 ሄ/ር (109%) በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡

**በ2017 የምርት ዘመን ከግል ባለሃብት ልማት የተገኘውን 4.62 ሚሊየን ኩ/ል ምርት ወደ 6.0 ሚሊየን ኩ/ል ማሳደግ፡-** በ2017/18 ምርት ዘመን የግብርና ውል እርሻ ስራ በ10 ዞኖች በ650,000 ሄ/ር መሬት በማልማት 6 ሚሊዮን ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 873,813 ሄ/ር ውል በመያዝ በቢሮው ምርት ትንበያ መሰረት 9,493,639 ኩ/ል ማምረት ተችሏል፡፡

**ለተለያዩ ስነ-ምህዳሮች ተስማሚ የሆኑ 88 አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችና ምክረ-ሀሳቦችን ማዉጣት እንዲሁም መነሻ ዘር ብዜት ማባዛት፤-** በበጀት ዓመቱ ቴክኖሎጂ/ምክረሃሳብ ለማመንጨት 551 ሙከራዎችን ለመስራት ታቅዶ 489 (88.75%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በመሆኑም ከተከናወኑ ሙከራዎች ዉስጥ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 88 ቴክኖሎጂ/ምክረ-ሃሳቦች ይወጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ ስራ፡-** በበጀት ዓመቱ 28 በምርምር የወጡና ምርት ላይ እንዲዉሉ የተመከሩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና የተሻሻሉ የአሰራር ዘዴዎችን ለተጠቃሚው አርሶ አደር ለማስተዋወቅና ለመምረጥ 23 (82.14%) እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 44 የቅድመ-ማስፋት ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ 43 (95.56%) ማከናወን ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሚቀርበዉን የግብርና ግብዓትና በዘር ብዜት የተሸፈነዉን የዘር ማሳ 100 በመቶ የጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ስራዎችን ማካሄድ፤-** በመኸር መስክ ሰብል የተሸፈነውን የመስክ ሠብል ዘር ብዜት 10,434 ሄ/ር፣ የአትክልት ዘር ብዜት 123.50 ሄ/ር እና የመኖ ዘር ብዜት 225 ሄ/ር በድምሩ 10,782.5 ሄ/ር መሬት 100% የጥራት ቁጥጥር ሥራ መስራት ተችሏል፡፡ በዘር ብዜት ከተሸፈነው ማሣ ውስጥ 9,836 ሄ/ር (94.3%) የጥራት ደረጃ መስፈርቱን አሟልቶ ያለፈ ሲሆን 598 ሄ/ር በግለላ ርቀት፤ 8.5 ሄ/ር የአትክልት ዘር ማሳ እና 2 ሄ/ር የመኖ ዘር ማሳ በግለላና በዝርያ መቀላቀል ምክንያት በድምሩ 608.5 ከጥራት ደረጃ መስፈርት በታች በመሆኑ ውድቅ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

**የእንስሳት በሽታ ቅድመ መከላከል ህክምናን ከ18 ሚሊየን ወደ 32.9 ሚሊየን እና የእንስሳት ክትባትን ከ43 ሚሊየን ወደ 70.4 ሚሊየን** ማድረስ፡- የእንስሳት በሽታ ለ35,228,500 ክትባት ለመስጠት ታቅዶ 40,220,869 ወይም 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለ23048422 ሚሊየን ለሚሆኑ እንሰሳት ቅድመ መከላከል ለመስጠት ታቅዶ 23,198,554 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 5,660,207 ሚሊየን የፈዉስ ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 7,252,724 ሚሊዮን ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

**የስጋ ምርትን በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 476,212 ቶን በ2018 ወደ 674,041 ቶን ማሳደግ፡-** 380,904 ቶን የስጋ ምርትን ለማምረት ተቅዶ 496,391 ቶን ስጋ ምርት በማምረት የዕቅዱን ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል ፡፡

**በ2017 በክልሉ ከአንድ የአካባቢ ላም በአማካይ በቀን የሚገኘውን 1.81 ሊትር ወተት ወደ 2.1 ሊትር እንዲሁም ከአንድ ክልስ ላም በአማካይ በቀን የሚገኘውን 10.88 ሊትር ወተት ወደ 13.5 ሊትር ከፍ በማድረግ የወተት ምርትን በ2017 የምርት ዘመን ከነበረበት 1.6 ሚሊየን ቶን በ2018 ወደ 2.4 ሚሊየን ቶን ማሳደግ፡-** ምርታማነት ከአካባቢ ላም 1.87 ሊትር (87%) እና ከተሸሻሉ ዝርያ 11.67 ሊትር (86%) ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 1,703,786.15 ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 1,635,002 ቶን የወተት ምርት የዕቅዱን 96 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**የዓሳ ምርትን በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 28,003 ቶን በ2018 ወደ 44,252 ቶን ማሳደግ፡-** 21,324 ቶን የዓሳ ምርት ለማምረት ታቅዶ 20,888 ቶን የዕቅዱን 96% መፈጸም ተችሏል፡፡

**የማር ምርትንም በ2017 ምርት ዘመን ከነበረበት 25,857 ቶን በ2018 ወደ 33,330 ቶን ማሳደግ እንዲሁም የሰም ምርትን ከ950 ቶን ወደ 1,015 ቶን ማሳደግ፡-** 23,334 ቶን የማር ምርት ለማምረት ታቅዶ 31,882 (100%) ማምረት የተቻለ ሲሆን 1321 ቶን የሰም ምርት ለማምረት ታቅዶ 1439 ከዕቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

**መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ቁጥርን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 31,417 በ2018 በጀት ዓመት ወደ 34,247 በማድረስና የአባላት ቁጥርን ከ6,434,689 ወደ 6,584,689 በማሳደግ የሰብል ምርት ግብይትን ከ933,292 ኩንታል ወደ 1,048,950 ኩ/ል ማሳደግ በተመለከተ፡** ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጥቅም ግንዛቤ ለማሳደግ እና ፍላጐት ለመፍጠር 4,027 የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች በቀበሌ ደረጃ ለማካሄድ ታቅዶ 4,277 (ከ100% በላይ) መድረኮችን በማዘጋጀት ግንዛቤ መፍጠር የተቻለ ሲሆን መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማቋቋም የሚያስችል 1,916 የአዋጭነት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 2,120 (ከ100% በላይ) የአዋጭነት ጥናት

ማካሄድ የተቻለ ሲሆን 2,120 (ከ100% በላይ) መሠረታዊ የህብረት ስራ ማኅበራትን ማቋቋም ተችሏል፡፡ ሌላው 1,420 የህብረት ስራ ማኅበራትን በመመዘን ደረጃቸውን ለመለየት ታቅዶ 1,067 (75%) ህብረት ስራ ማኅበራት የተመዘኑ ሰሆን ከደረጃ በላይ ለሆኑ 957 የህብረት ስራ ማህበራት የቅጥር ሰራተኛ ድልድል፣ 549 የህብረት ስራ ማህበራት ሰርተፊኬታቸውን እንዲያሳድሱ፣ 107 የህብረት ስራ ማህበራት እንዲዋሀዱ፣ 201 የህብረት ስራ ማህበራት በህጋዊ አሰራር መሠረት ህጋዊ ሰውነታቸውን እንዲያጡ ማድረግ ተችሏል፡፡

የህብረት ስራ ማህበራትን ካፒታል 968,324,694 ለማድረስ ታቅዶ 1,012,324,694 በማድረስ ከ100% በላይ መፈጸም የተቻለ ሲሆን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅ/ስ/ማ/ትን ቁጠባና ኢንቨስትመንት ለማሳደግ 2,969,517,819 መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 2,987,517,820 ብር በመሰብሰብ ከ100% በላይ መፈጸም እንዲሁም ለአባላቱም 3,719,444,220 ብር ብድር ለመስጠት ታቅዶ 4,319,800,112 (ከ100% በላይ) የብድር አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 1,297,796,523 ብር (ከ100% በላይ) ውዝፍ መሠብሰብ ተችሏል፡፡

የገበያ ማረጋገትን ተግባርን አጠናክሮ በማስቀጠል የሰብል ምርት አቅርቦትን እየተተገበረ ሲሆን 261,551 ኩ/ል የሰብል ምርት አቅርቦት፣ 15,532,552 ሊትር የወተት ምርት፣ 158,387 (66%) የግብርና ምርት በማቅረብ ገበያን የማረጋጋት ስራ መስራት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአግሮ ኢንዱስትሪ ውጤታማነትን ለማሳደግ 17,891 ኩ/ል (ከ100% በላይ) የፊኖ ዱቄት፣ 21,534 ኩ/ል (ከ100% በላይ) የእንስሳ መኖ፣ 1,400,000 (ከ100% በላይ) የፒፒ ቀረጢት ምርት ለማቅርብ ታቅዶ 10,573 ኩ/ል (ከ100% በላይ) 64,633 (74%) ሊትር የምግብ ዘይት ምርት ማቅረብ ተችሏል፡፡

## 2.3. የማዕድን ሀብት

የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ የስነ ምድር ጥናትና ክምችት በመለየት ማዕድን ነክ ኢንቨስትመንቶችን ለማስፋፋት፣ ከውጭ አገር የሚገቡ ማዕድናትን በአገር ውስጥ ማዕድናት ለመተካት፤ የማዕድን ምርትና ግብይት ህጋዊነት ለማስፈን፣ ፍትሃዊ የማዕድን ሀብት ልማት እና ግበይትን ለማጠናከር ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን በሩብ ዓመቱ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ወደ ውጭ የሚላኩ የከበሩ ማዕድናት ምርት መጠንን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 23,558.8 ኪ.ግ ምርት በ2018 በጀት ዓመት ወደ 25,796.9 ኪ.ግ በማሳደግ በዘርፉ የሚገኘውን የውጪ ምንዛሬ ገቢን ከ9,034,539 ወደ 10,389,720 የአሜሪካ ዶላር ማሳዳግ፦ 12,569.695 ኪ.ግ የከበሩ

የማዕድን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 5,194,860 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 12,289.57 ኪግ በመላክ 8,768,032.01 የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ አፈጻጸም ከምርት 97.77% እንዲሁም ከምንዛሬ 100% በላይ ተከናዉኗል፡፡

ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚመረተውን ተኪ የምርት መጠን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,432,642 ቶን በ2018 በጀት ዓመት ወደ 1,713,258 ቶን በማሳደግ የሚድን የውጪ ምንዛሬ መጠንን ከ113,117,736 ወደ 124,846,559 የአሜሪካ ዶላር ማሳደግ፡- 856,629 ቶን ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት 62,423,279.6 USD የውጭ ምንዛሬ ለማዳን ታቅዶ 1,755,025 ቶን ምርት በመተካት 100,092,350 USD የምንዛሬ ወጭን ማዳን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም የምርትና የምንዛሬ ›100% በላይ ተከናዉኗል፡፡

የብረትና የፌሮ ብረታ ብረቶች (Iron and ferro — alloy metals) ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ማወቅ፡- 20 ካ.ኪ.ሜ ብረትና የፌሮ ብረታ ብረቶች (Iron and ferro alloy metals) ማዕድን አይነት፣ ክምችት መጠን፣ ስርጭት እና ጥራት ስራን ለማሳወቅ 15% ለማጠናቀቅ ታቅዶ የላብራቶሪ ዉጤቶችን በመንተን እና በማደረጃት 100% ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ በዚህ ጥናት 146.72 ሜትሪክ ቶን ብረት እነዲሁም በሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሚገመት ሳነድሰቶን ማዕድናት ተገኝቷል፡፡

ፌሮዎስ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች (Nonferrous metals) ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ማወቅ፡- ፌሮዎስ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች (Nonferrous metals) ፈልጎ ማግኘትና የክምችት መጠኑንም ለማሳወቅ 15% ለማጠናቀቅ ታቅዶ የሊብራቶሪ ዉጤቶችን በመንተን እና በማዯረጃት 100% በማከናወን ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን በሚሊዮን ቶን እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡

የኢንዱስትሪ ማዕድናትን (Industrial Minerals) ፈልጎ ማግኘትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡- የኢንዱስትሪ ማዕድናትን (Industrial Minerals) ፈልጎ ማግኘትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ 30% ለማጠናቀቅ ታቅዶ የዓመቱን ጨምሮ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

የኮንስትራክሽን ማዕድናት (Construction Minerals) ፈልጎ ማግኘት፡- የኮንስትራክሽን ማዕድናት (Construction Minerals) ፈልጎ ማግኘት የክምችት መጠኑን ማወቅና ጥቅም ላይ ለማዋል 30% የጥናት ተግባራትን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ በማዕድን ሃብት ልማት ተቋም ለ40,710 ዜጎች የስራ እድል መፍጠር በተመለከተ፡- ለ22,855 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ21,912 (95.7%) ዜጎች ስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

## 2.4. ቱሪዝም

**በክልሉ የሚገኙ ቅርሶች በበቂ ሁኔታ መንከባከብና መጠገን ባለመቻሉ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እየተጋለጡ የሚገኙ በመሆኑ የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ ለቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ጥገና በማድረግ ዘላቂ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤን ማሳደግ፡-** ለ200 ቋሚ ቅርሶች የጉዳት መጠን በደረጃ ለመለየት ታቅዶ ለ152 (76%) ቋሚ ቅርሶች የጉዳት መጠን የልየታ ስራ ተከናወኗል፡፡ ሌላው በፌዴራልና በክልሉ መንግስት የካፒታል በጀት ድጋፍና በህብረተሰብ ተሳትፎ በሚሰበሰብ ገንዘብ የጉዳት መጠን በተለየባቸው ለ25 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ61 ቋሚ ቅርሶች እንዲሁም ለ300 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ መስራት ታቅዶ ለ428 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡

**የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ በቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ ምዝገባ በማድረግ ጥበቃና እንክብካቤን ማሳደግ፡-** 9,500 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችንና 150 ቋሚ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 2023 (56) ተንቀሳቃሽ ቅርሶችንና 84 (21 በመቶ) ቋሚ ቅርሶችን መመዝገብ ተችሏል፡፡ ባህላዊ ቅርሶቻችን ለማልማትና ለማስተዋወቅ ያመች ዘንድ ለ73 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 56 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን መመዝገብ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ 76.7 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

ቋሚ ቅርሶችን፣ የአርኪወሎጅ እና ፓሊዮንቶሎጂ ስፍራዎች ይዞታ በማስከበር ለማልማት ያመች ዘንድ ለ160 ቋሚ ቅርሶች፣ የአርኪወሎጅ እና ፓሊዮንቶሎጂ ስፍራዎች የይዞታ ማረጋገጫና ወሰን ክለላ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 154 (96) ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫና የወሰን ክለላ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

**ወጎችን ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በስነምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፡** የትምህርት ተቋማት፣ የዕምነት ተቋማት፣ የልሂቃን (የፖለቲካና የኢኮኖሚ) እና የሚድያ ተቋማት የተመረጡ እሴቶችን (ሙያዊ ብቃት፣ አገልጋይነት፣ ባህልን መጠበቅ፣ ሕግን ማክበር፣ ሕዝባዊ ወገንተኝነት፣ አርበኝነት፣ ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ መጠቀም፣ ለልዕለ ሐሳብ ተገዢነት፣ ግብ ተኮር፣ ብዝሐነትን መቀበል፣ ምርምርና ፈጠራ፣ ቅንጅታዊ አሠራር እና ግልፅነትና ተጠያቂነት) እንዲተገበሩት ለማስቻል 6 ታቅዶ በ22 ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ በተለያዩ መድረኮች ውይይት በመካሄዱ ከዕቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ በዚህ ስድስት ወራት 16 ሃይማኖታዊና ባህላዊና ክብረ በዓላት የተከበሩ ሲሆን የአሱራቴ፤ የዘመን መለወጫ፤ ፊፊ፣ የስላሴ ክብረ በዓል፣ የአዬ ምኒሊክ፣ የፊታውራሪ ገበየሁእና የእቴጌ ጣይቱ የልደት በዓል፣ የቡሄ በዓል፣ የህብር ቀን፣ የደመራ እና የመስቀል በዓልን፤ የሻደይ፤ አሸንድየ፤ ሶለል፤ የእንግጫ

ነቀላና የመሳሰሉት በተለያዩ ባህላዊ እሴቶች ህብረ-ብሔራዊነትን እና ብዝሃነትን ባከበረ መልኩ የማክበርና በመረጃ የተደገፉ ሥራዎችን መሥራት ተችሏል፡፡

## 2.5. ትምህርት

**የትምህርት ተደራሽነትንና ጥራትን ማሳደግ በተመለከተ፤** 5% ቅ/አንደኛ ደረጃ፣ 2% አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና 5% ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ደረጃ 3 እንዲሁም 2% ቅ/አንደኛ ደረጃ፣ 1% አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና 0.25% ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ደረጃ 4 ለማድረስ ታቅዶ ከ844 ቅድመ አንደኛ፣ ከ9,433 አንደኛና መካከለኛ እንዲሁም 687 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 405፣ 2,005 እና 185 በቅደም ተከተል ኢንስፔክት የተደረጉ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 69 (17%)፣ 238 (12%) እና 57 (31%) ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች **ደረጃ 3** የሆኑ ሲሆን 1 (0.25%) ቅድመ አንደኛ፣ 1 (0.05%) አንደኛና መካከለኛ **ደረጃ 4** ናቸው፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት ደረጃ 4 የደረሰ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የለም፡፡

የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን 844 ለማድረስ ታቅዶ 815 (97%)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች 9,433 ለማድረስ ታቅዶ 9099 (96.45%)፣ በሁለተኛ ደረጃ የመፀዳጃ ቤት ያላቸውን ት/ቤቶች 708 ለማድረስ ታቅዶ 669 (94.5%) ትምህርት ቤቶች መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች 422(50%) ለማድረስ ታቅዶ 634 (100%)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች 3,013 (33%) ለማድረስ ታቅዶ 3,751 (100%) እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 618 (90%) ለማድረስ ታቅዶ 595 (97%) ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አንፃ አፈፃፀሙ 96% ደርሷል፡፡

ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 3,854 (38%) ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ 9,433 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 3,024 (32%) ትምህርት ቤቶች የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ክፍሎች ያላቸው ሲሆን ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍል ያላቸው 1,355 (36%) ሲሆን አፈፃፀሙ 84% ብቻ ነዉ፡፡ በተመሳሳይ ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍል ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 460 (67%) ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ 687 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 480 (70%) ትምህርት ቤቶች የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ክፍሎች ያላቸው ሲሆን

ደረጃውን የጠበቀ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍል ያላቸው 317 (46%) ሲሆን አፈፃፀሙ 66% ነው፡፡

በሌላ በኩል የመጠጥ ውሀ ያላቸው የቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 844 ለማድረስ ታቅዶ 771 (93%)፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 4,812 (51%) ለማድረስ ታቅዶ 4,852 (100%)፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 708 ለማድረስ ታቅዶ 548 (80%) ትምህርት ቤቶች የመጠጥ ውሃ ያላቸዉ ሲሆን በስታንዳርዱ መሰረት ለተማሪዎች ተደራሽ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 734(87%) ለማድረስ ታቅዶ 725 (88%)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 8,207 (87%) ለማድረስ ታቅዶ 4,144 (51%)፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 550 (80%) ለማድረስ ታቅዶ 501 (91%) ትምህርት ቤቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለተማሪዎች ተደራሽ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸዉ መሆኑን ያሳያል፡፡

በተጨማሪም ሁለገብ ቤተ ሙከራ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 4,528(48%) ለማድረስ ታቅዶ 4,474 (99%) ትምህርት ቤቶች ሁለገብ ቤተ ሙከራ ያላቸው ሲሆን የሳይንስ ኪት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 4,845 (50%) ለማድረስ ታቅዶ 4,845 (100%) ትምህርት ቤቶች ሳይንስ ኪት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ በሶስቱም የትምህርት ዓይነቶች የሳይንስ ቤተ ሙከራ ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 447 (65%) ለማድረስ ታቅዶ 334(49%) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሶስቱም ትምህርት ዓይነቶች የሳይንስ ቤተ ሙከራ ያላቸው ሲሆን አፈፃፀሙ 74.7% ሆኗል፡፡

ቤተ-መጻህፍት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 6,255 (65%) ለማድረስ ታቅዶ 4,772 (76%) እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 644 (91%) ለማድረስ ታቅዶ 614 (95.3%) ትምህርት ቤቶች ቤተ-መጻህፍት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት 1:30 ለማድረስ ታቅዶ 625,299 ተማሪዎች በ7,856 ሴክሽኖች በመማር ላይ ሲሆን ጥምርታው 1:49 የሆነ ሲሆን አፈጻጸሙ 61% ነው፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን 1:40 ለማድረስ ታቅዶ 2,028,014 ተማሪዎች በ33,214 ሴክሽኖች በመማር ላይ ሲሆኑ ጥምርታው 1:44 በመሆኑ አፈጻጸሙ ወደ 91% ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታውን 1፡40 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን 329,249 ተማሪዎች በ7,567 ሴክሽኖች በመማር ላይ ሲሆን ጥምርታው 1፡44 በማድረስ አፈጻጸሙ 91% ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 1፡40 ለማድረስ ታቅዶ 314,956 ተማሪዎች በ6,378 ሴክሽኖች ለመማር በመምዝገባቸው ጥምርታው 1፡40 የደረሰ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ከላይ የተገለጸው የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ አፈፃፀም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት በክልላችን በተከሰተው የፀጥታ ችግር ምክንያት መመዝገብና መማር የሚገባቸው ሁሉም እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትና ታዳጊዎች ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ባለመቻላቸው ነው፡፡ እንዲሁም የትምህርት ተደራሽነትን ለማሳደግ በተለያዩ ምክንያቶች ምዝገባ የማይካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች እና ወረዳዎች እንዳሉ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በዘመኑ በክልላችን 1,004,196 (ወንድ 511,180፣ ሴት 493,015) የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 50% (ወንድ 50% ወንድ፣ ሴት 50%) ለማድረስ ታቅዶ 848,984 (ወንድ 431,162 ፣ ሴት 417,822) ህፃናት በመመዘገብ ጥቅል ተሳትፎውን 42.41% (ወ-42.27% ሴ-42.55%) ሲሆን የአንደኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ በሁሉም እድሜ በአንደኛ ክፍል 1,783,978 (ወንድ 874,293፣ ሴት 909,685) ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 110% (ወ- 110%፣ ሴ- 110%) ለማድረስ ታቅዶ 847,987 (ወንድ 438,172፣ ሴት 409,815) ህፃናት በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 112.03% (ወንድ 113.76%፣ ሴት 110.24%) መሆኑን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ በዘመኑ በክልላችን 756,924 (ወንድ 385,162፣ ሴት 371,762) የአንደኛ ደረጃ በ7 ዓመት እድሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ቅበላ ምጣኔውን 100% (ወንድ 100%፣ ሴት 100%) ለማድረስ ታቅዶ 560,266 (ወንድ 285,478፣ ሴት 274,788) የ7 ዓመት ህጻናት የመጀመሪያ ጊዜ ምዝገባ በማከናወን ንጥር ቅበላው 74.02% (ወንድ 74.12%፣ ሴት 73.92 %) ሆኗል፡፡

የአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በዘመኑ በክልላችን 4,493,294 (ወንድ 2,258,955፣ ሴት 2,234,339) ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 85.23% (ወንድ 85.29% ወንድ፣ ሴት 85.18%) ለማድረስ ታቅዶ 2,642,138 (ወንድ 1,315,780፣ ሴት 1,326,358) ህፃናት በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 63.7% (ወ-62.86% ሴ-64.56%) ሲሆን የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በዘመኑ በክልላችን 742,705 (ወንድ 355,440፣ ሴት 387,265) የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 65.28% (ወንድ 60.59%፣ ሴት 70.2%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 420,218 (ወንድ

190,082፣ ሴት 230,136) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 33.68% (ወንድ 29.81%፣ ሴት 37.73%) ደርሷል። የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በዘመኑ በክልላችን 1,205,351 (ወንድ 535,577፣ ሴት 669,774) የሚሆኑ ነባርና አዲስ ገቢ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 42.78% (ወንድ 37.81%፣ ሴት 47.9%) ለማድረስ ታቅዶ 426,963 (ወንድ 187,614፣ ሴት 239,349) በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 15.97% (ወንድ 13.87%፣ ሴት 18.13%) ሆኗል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህር መምሪያ፣ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች አንድ ለአንድ ባልደረሱባቸው የትምህርት ዓይነቶች የመጻህፍት ህትመት በማሳተም እና በማድረስ የመጽሀፍ ተማሪ ጥምርታውን 1:1 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በተገኘው በጀት የህትመት ስራ በመሰራቱና የመፅሐፍት ስርጭት ስራ የተከናወነ ሲሆን በመማር ላይ ካሉት ተማሪዎች አንጻር 1:1 ማድረስ ተችሏል። ይሁን እንጅ የመጽሐፍት ጥምርታውን 1ለ1 የሆነበት ምክንያት በክልላችን የተመዘገቡ እና ወደ ትምህርት ቤት የመጡ ተማሪዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ በመሆኑ ነው። ሌላው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ያለው የቅድመ አንደኛ እና አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምገባ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 2,861,848 ተማሪዎችን ለመመገብ ታቅዶ 317,500 (ወንድ 156,731 ሴት 160,769) ወይም 11.09% ተማሪዎችን መመገብ የተቻለ ሲሆን ከሩብ ዓመቱ ዕቅድ አንፃር ደግሞ አፈፃፀሙ 34.89% ማድረስ ተችሏል።

**የትምህርት አመራሩን እና መምህራንን አቅርቦት፣ ሥነ ምግባር፣ተነሳሽነትና ብቃትን ማሳደግ በተመለከተ፡** ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን 78.9% ለማድረስ ታቅዶ  99.5% (92.9% ወንድ 96.859% ሴት) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን 80% ለማድረስ ታቅዶ 81.89% (ወንድ 81.15%፣ ሴት 81.6%) ደርሷል።

በትምህርት አግባብነትና ጥራት ማስጠበቅ ውስጥ የትምህርት አመራሩን እና የመምህራን አቅርቦት፣ የስራ ተነሳሽነትና ብቃትን ማሳደግ አንድ ትልቅ ግብ ነው። በዚህም ትምህርት ቤትን መሰረት በማድረግ አዲስ በተቀረጸው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛና መካከለኛ እና የ2ኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ 64.5% ለማድረስ ታቅዶ 30.7% (29.8% ወንድ 34.2% ሴት) ደርሷል።

ትምህርት ቤትን መሰረት በማድረግ አዲስ በተቀረጸው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ እንዲሁም የ2ኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ 90% ለማድረስ ታቅዶ 89.5% (ወንድ 89.2%፣ ሴት 90.1%) ደርሷል፡፡ ከተቀመጠው እቅድ አንጻር አፈጻጸሙ 99.4% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በጀማሪ መምህርነት ለሚሰሩ 10,663 መምህራን የሙያ ትውውቅ እና ልምምድ እንዲያደርጉ ታቅዶ 72.9% (ወንድ 74.5%፣ ሴት 71.3%) ጀማሪ መምህራን በፕሮግራሙ በመሳተፍ ላይ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራንን በሚያስተምሩት ትምህርት አይነት ይዘት እና የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ብቃታቸውን ለማሳደግ በተሰጠው የ13 ቀን ስልጠና 10,000 መምህራንን ለማሳተፍ ታቅዶ 8,272 (ወንድ 5,844 ሴት 2,431) ነው፡፡ የመምህራን የስራ የመልቀቅ ምጣኔ ከ 2% እንዳይበልጥ ለማድረግ ታቅዶ ወደ 1.48% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የሥርዓተ-ትምህርቱን ተገቢነትና ጥራት በተመለከተ፡-** የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል አፍ መፍቻ 3ቱ ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አዊኛ እና አፋን ኦሮሞ) የመጻህፍት ህትመት የተማሪ መማሪያ እና የመምህር መምሪያ ማሳተም 447,678 ታቅዶ 404,599 የተማሪ መማሪያ እና 5,100 የመምህር መምሪያ መጻህፍት በድምሩ 409,699 (91.5%) መፃህፍት ማሳተም ተችሏል፡፡

የተሻሻሉ የመማሪያ መጻህፍት እና ዲጂታል የማስተማሪያ ማቴሪያሎችን ተደራሽነት ማሻሻል 25% ለመስራት ታቅዶ የታተሙ መጻህፍትን በሁሉም ዞኖች ማድረስ በመቻሉ እና በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የተላከውን የቲቶርያል ሊንክ እና የመጻህፍቶቻችንን ሶፍት ኮፒ በተለያየ መንገድ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ የርቀት ትምህርት ሞጁሎችን ከ7 እስከ 8ኛ እና ከ9 እስከ 12ኛ ክፍል ለሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በሶፍት ኮፒ እንዲደርስ ስራ ተሰርቷል፡፡

በተለያዩ የክፍል ደረጃ የተማሪ መፃህፍት ማሳተም 3,644,009 የታቀደ 3,644,009 በክልሉ መንግስት ታትሞ የተሠራጨ ሲሆን 4,526,225 የተለያዩ አይነት መጻህፍት በትምህርት ሚኒስቴር እና ዩኒሴፍ ትብብር ታትመው ወደ ደሴ እና ጎንደር ክዘና ማዕከላት በመጓጓዝ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

ከ3ኛ-6ኛ ክፍል የግዕዝ ቋንቋ መጻህፍት የተማሪ መማሪያ እና የመምህር መምሪያ መጽሐፍት 218,468 ለማሳተም ታቅዶ 144,185 የተማሪ መጽሐፍ እና 15,408 የመምህር መምሪያ በድምሩ 159,593 (73%) ማሳተም ተችሏል፡፡ በ4ቱም ማዕከላት በአማርኛ ቋንቋ በአዲስ የተዘጋጁ

የትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞችን ዝግጅት 5 ለማድረስ ታቅዶ ሁሉም ፕሮግራሞች ቀድመዉ ስለተጠናቀቁ አፈፃፀሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡

**የተማሪዎችን የማቆየትና የማሳለፍ ምጣኔ ማሻሻል በተመለከተ፡** የ6ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች 76% ማድረስ ሲሆን የ2017 ዓ.ም በሁለቱም ዙር ፈተናውን ከወሰዱ ተማሪዎች ድምር 138,700 (ወንድ 61,221 ሴት77,479) መካከል ድምር 114,328 (ወንድ 50,697 ሴት 63,631) ተማሪዎች 50% እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን አፈጻጸሙም 82.43% ነው፡፡ በተመሳሳይ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች የአመቱ እቅድ 60% ማድረስ ሲሆን የ2017 ዓ.ም በሁለቱም ዙር ፈተናውን ከወሰዱ ተማሪዎች ድምር 136,949 (ወንድ 58,650 ሴት78,299) መካከል ድምር 78,560 (ወንድ 35,106 ሴት 43454) ተማሪዎች 50% እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን አፈጻጸሙም 57.36% ነው፡፡ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶ እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች የአመቱ እቅድ 12% ማድረስ ሲሆን ፈተናውን ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል 49.5% እና በላይ አማካኝ ውጤት ያሰመዘገቡና የዩኒቨርስቲ መግቢያ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ድምር 12,228 (ወንድ 7,948 ሴት 4,280) ተማሪዎች ሲሆኑ አፈጻጸሙም 12.92% ነው፡፡

**የትምህርት ፍትሃዊነትንና አካታችነትን ማሻሻል፡-** የልዩ ትምህርት ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከል ያደራጁ ት/ቤቶች ብዛት 317 ማድረስ የታቀደ ሲሆን በዩኒሴፍ ድጋፍ 10 በኢትኦል ድጋፍ 19 በድምሩ 29 ትምህርት ቤቶች እንዲደራጁ የተመረጡ በመሆኑ ወደ 329 (103.78%) ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.00 በዘመኑ በ1.00 ለማስቀጠል ታቅዶ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 32% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 31.06% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.03 ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (ከ1ኛ-6ኛ ክፍል) ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.05 በ2018 ትምህርት ዘመን ወደ 1.0 ለማሻሻል ታቅዶ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 50.28% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 48.78% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.03 ነው፡፡

የመካከለኛ ደረጃ (ከ7-8ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.35 በዘመኑ 1.1 ለማድረግ ታቅዶ በዘመኑ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 30.18% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 23.61% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.27 ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ

(ከ9ኛ-12ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1.37 በዘመኑ ወደ 1.15 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ በ2018 ዓ.ም በሁለተኛ ደረጃ የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 13.87% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 10.37% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.34% ነው።

ቅድመ አንደኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ትምህርት በዘመኑ በክልላችን 2,859 (ወንድ 1,457፣ ሴት 1,402) የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 0.8% (ወንድ 0.8%፣ ሴት 0.8%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 2,129 (ወንድ 1,219፣ ሴት 910) ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 0.43% (ወንድ 0.49%፣ ሴት 0.36%) ነው።

የአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍል) ልዩ ፍላጎት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በዘመኑ በክልላችን 55,665 (ወንድ 29,388፣ ሴት 26,277) የአንደኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 10% (ወንድ 10%፣ ሴት 10%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 28,166 (ወንድ 15,472፣ ሴት 12,694) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 2.9% (ወንድ 3.2%፣ ሴት 2.6%) ነው። የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ልዩ ፍላጎት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በዘመኑ በክልላችን 18,555 (ወንድ 9,796፣ ሴት 8,759) የመካከለኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 6% (ወንድ 6%፣ ሴት 6%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 5,132 (ወንድ 2,789፣ ሴት 2,343) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 2.3% (ወንድ 2.4%፣ ሴት 2.16%) ነው።

የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ልዩ ፍላጎት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በዘመኑ በክልላችን 11,630 (ወንድ 6,284፣ ሴት 5,347) የሚሆኑ የሁለተኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 3.5% (ወንድ 3.5%፣ ሴት 3.5%) ለማድረስ ታቅዶ 4,727 (ወንድ 2,415፣ ሴት 2,312) በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 0.99% (ወንድ 1%፣ ሴት 0.98%) ማድረስ ተችሏል።

**የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ማጠናከር፡** የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተደራሽነትን እና የህጻናት ልማት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት 1 ለመስራት ታቅዶ ከ2018 እስከ 2022 ዓ.ም የሚያገለግል የ5 ዓመት ረቂቅ ሮድ ማፕ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል። በመሆኑም የክፍል ውስጥ መጫዎቻ ቁሳቁስ ከማሟላት አንጻር ከ688 የራሳቸው ግቢ እና አስተዳደር ካላቸው ተቋማት ብዛት 78.2 ለማድረስ ታቅዶ በ493 (71.7%) ትምህርት ቤቶች በማከናወን የራሳቸው ግቢ እና አስተዳር ያሟሉ ሲሆን የውጭ መጫዎቻ ከማሟላት አንጻር ከ688 የራሳቸው ግቢ እና

አስተዳደር ካላቸው ተቋማት ብዛት 76.5 ለማድረስ ታቅዶ ከ500 (72.7%) የራሳቸው ግቢ እና አስተዳር ያላቸዉና የክፍል ውጭ መጫዎቻ ያሟሉ በመሆኑ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህር መምሪያ፤ የመጻህፍት ህትመት ማሳተም እና ማድረስ ጥምርታ በምጥጥን 1ለ1 ለማድረስ ታቅዶ በአማርኛ ሚድያው ከዚህ በፊት ታትሞ 1ለ1 ማድረስ ተችሏል፡፡

**የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ማረጋገጥ፤** ማንበብና መጻፍን እና የሙያ ትምህርትን ጨምሮ የጎልማሶች መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራም በተገቢው መንገድ መተግበር፣ በመሰረተ ትምህርት የሚሳተፉ ጎልማሶችን ሽፋን 368,242 (ወ 32,390፣ ሴ 24,424) ለማድረስ ታቅዶ 57,031 (17.5%) (ወንድ 32,259፣ ሴት 24,772) መስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በስታንዳርዱ መሰረት የተቋቋሙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት 70 ለማድረስ ታቅዶ 61 (87.1%) የተቋቋሙ ሲሆን የተቋቋሙ መማማሪያ ጣቢያዎች 5,500 ለማድረስ የታቅዶ 5,472 ጣቢያዎችን በመክፈት የእቅዱን 99.49% ማከናዎን ተችሏል፡፡ የማታ ተማሪዎችን ሽፋን 100 ፐርሰንት ለማድረስ ታቅዶ በ7 ዞኖችና በ23 ትምህርት መሰጠት ተጀምሯል፡፡ በተጨማሪም የተፋጠነ ትምህርት ተሳታፊ ተማሪዎችን ሽፋን 63,350 ለማድረስ ታቅዶ 64,298 (100%) (ወንድ 33,561 ሴ 30,737) ተማሪዎች ተመዝግበው መማር የጀመሩ መሆኑን ያሳያል፡፡

**የትምህርት አመራርና ተጠያቂነትን ማጠናከር፡-**ለደረጃው የተፈቀደውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አመራሮችን 80% ለማድረስ ታቅዶ 81.41% (ወንድ 81.75%፣ ሴት 85.9%) የትምህርት ደረጃ አሟልተዋል፡፡

በክልሉ በሚገኙ ሁሉም የአንደኛ፣ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወላጆችን፣ መምህራንን እና ባለድርሻ አካላትን የመማር ማስተማር ተግባራትን አንድ ጊዜ እንዲገመግሙ ታቅዶ 11,074 ትምህርት ተቋማት መካከል በ4,294 (38.78% ትምህርት ቤቶች ግምገማው ተከናውኗል፡፡

በተመሳሳይ ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያሉ የትምህርት ቤት አመራሮች ትምህርት ቤትን መሰረት ባደረገ ተከታታይ ሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) 65% እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 38.9% (ወንድ 37.8% ሴት 43%) ሲሆን ለ3,500 የ1ኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አመራሮች የአመራር ብቃታቸውን ለማሳደግ የ10 ቀን ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ3,162 (90.3%) ስልጠናቸውን አጠናቀዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለ6,093 ዜጎች የስራ እድል መፍጠር፡ ለ3,000 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ- 6,404 ሴት 880 በድምሩ 7,284 (100%) የስራ እድል ተጥሯል፡፡

## 2.6. ጤና

**የጨቅላ ህፃናትን እና ህፃናትን ሞት መቀነስ በተመለከተ፡-** ሞተው የሚወለዱ ጨቅላ ህጻናትን (Still Birth) በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥናት መሰረት (Still Birth) 15/1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ህይወታቸው አልፎ ይወለዳሉ ተብሎ ከሚገመተው 308,974 ጨቅላ ህፃናት ውስጥ 2,786 ህይወታቸው አልፎ የተወለዱ ሲሆን ይህም ሲሰላ 9/1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ሞተው የተወለዱ ናቸዉ፡፡ በወሊድ ወቅት የአተነፋፈስ ችግር ያጋጠማቸው 5,497 (90.9%) ድጋፍ ተደርጎላቸው ህይወታቸውን ለማትረፍ በመስራት 5,381 (97.9%) ሕይወታቸውን ማዳን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው (ከመውለጃ ቀናቸው ቀድመው የተወለዱ ጨቅላ ህጻናት (የKMC) 4,896 (>100%) አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት በሳምባ ምች ታመው ፀረ ተዋህሲያን 410,618 (89%) ለመስጠት ታቅዶ 532,612 (>100%) (97.3%) ሽፋን ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከጽኑ ህሙማን ክፍል ውስጥ ታክመው አገግመው (ድነው) የወጡ በጨቅላ ሕጻናትን 17,282 (85%) ለማድረስ ታቅዶ 16,754 (96.9%) ሽፋን ማድረስ ቢቻልም 1,427 የጨቅላ ህጻናት ሞት ሲመዘገብ ከሚጠበቀዉ 5/1000 በህይዎት ከሚወለዱ አፈጻጸሙ 4.6/1000 መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የህጻናት ሞት ከስታንዳርዱ በታች ቢሆንም ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቃል፡፡

ሌላው ከ1 ዓመት በታች የመጀመሪያውን የጸረ አምስት (ፔንታቫለንት-1) የህጻናት ክትባት 377,086 (100%) ለመስጠት ታቅዶ 423,650 ሽፋን (>100%) የተሰጠ ሲሆን ሁሉንም የክትባት አይነቶች የሚያገኙ 373,314 (99%) ታቅዶ 402,405 (>100%) መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም የመጀመሪያ ዙር ኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን 373,314 (99%) ለመስጠት ታቅዶ 404,215 (>100%) መስጠት ሲቻል ሁለተኛውን የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት (MCV2) 373,314 ህጻናት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 381,276 (102.4%) ክትባቱን አግኝተዋል፡፡

በሌላ በኩል የአፍላ ወጣቶችና የወጣቶች ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል የልጅነት እርግዝናን ወደ 6% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ 16,386 እርግዝና የተከሰተ በመሆኑ አፈፃጸሙ (6.8%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህ ተግባር ትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡ እድሜያቸው ከ9 እስከ 14 ዓመት ለሞላቸው ሴት ልጆች የማፀን በር ካንሰር መለካከያ ክትባት 3,977,054 (97%) ለመስጠት ታቅዶ 3,977,054 በመፈፀም 100% ማሳካት ተችሏል፡፡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከል እና ህክምና

በ6 ወራት ከታቀደዉ 222,925 የማህጸን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ልየታ ዉስጥ 151,589 (68%) ሴቶች ስክሪን (ልየታ) ተደረገዉ 4,393 (2.9%) የማህፀን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ምልክት ተገኝቶባቸዉ 3,710 (84.5%) ህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

**የእናቶችን ጤና ማሻሻል በተመለከተ፡-** የእናቶች ጤና አገልግሎት (maternal health) ለ2,184,886 (89%) የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 2,683,796 (>100%) ሽፋን የደረሰ ሲሆን ከቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚዎች መካከል 932,946 (42.7%) ታቅዶ 534,647 (ሽፋን 22.1%) እናቶች የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተመሳሳይ የነፍሰ ጡር እናቶች ቅድመ ወሊድ (ANC1) ለ402,837 (100%) አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ420,562 (>100%) ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የነፍሰ ጡር እናቶች ቅድመ ወሊድ (ANC4) ለ357,024 (85%) አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ372,176 (>100%) ሲሰጥ ቅድመ ወሊድ አንድ ካገኙት ጋር ሲነጻጸር 48,386 (100%) የሚሆኑ የአቋራጭ ምጣኔ መኖሩን ያሳያል፡፡ የድህረ ወሊድ አገልግሎት በ48 ሰዓት 357,432 (87.5%) ከወለዱ እናቶች ውስጥ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ታቅዶ 327,570 (92%) አገልግሎቱን አግኝተዋል፡፡ እስከ 7ኛው ቀን የድህረ ወሊድ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከታቀዱ 85% እናቶች ውስጥ 417,179 (>100%) የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም 338,642 (82.9%) እናቶች በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ 305,584 (90%) የተሰጠ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 26,361 (8.6%) እናቶች በቀዶ ህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ በወሊድ ምክንያት 139 እናቶች የሞቱ ሲሆን ከሚጠበቀዉ ስታንዳርድ 70/100,000 አንጻር 34/100,000 መሆኑ የተሻለ መፈጸም የተቻለ ቢሆንም በቀጣይ በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡

**ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር፡-** የመጀመሪያውን 95 ኢላማ ማለትም ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለባቸው ራሳቸዉን እንዲያውቁ 173,442 ታቅዶ 163,219 (94%) ራሳቸዉን እንዲያውቁ ሲደረግ ሁለተኛዉ 95 ቫይረሱ በደማቸዉ ውስጥ ከተገኘባቸው 163,219 መካከል 161,913 (99%) የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ሲጠቀሙ ሶስተኛውን 95 ኢላማ በደም ዉስጥ የኤች አይ ቪ ቫይረስ መጠን በሚ.ሊ. ከ1000 ኮፒ በታች ማድረግ 95% ታቅዶ 97% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከእናት ወደ ጽንስ ኤች አይ ቪ እንዳይተላለፍ ለመከላከል 396,239 (97%) ታቅዶ 428,764 (>100%) ምርመራ ከተደረገላቸው ውስጥ 2,022 (86%) ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ነፍሰ ጡር እና አጥቢ እናቶች ሲኖሩ 1,788 (88%) የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ሌላው ለ16,813 የሁሉም አይነት ቲቢ ልየታ ለመስራት ታቅዶ 10,992 (65%)፣ ከታከሙት የቲቢ መዳን ምጣኔን 95% ለማድረስ ታቅዶ 93%፣ የህክምና ስኬት 98.5% ለማድረስ ታቅዶ 97%፣ ለ120 መድኃኒት የተላመደ ቲቢ ህክምና ለመስጠት ታቅዶ 72 (60%) ሽፋኑን (60%) ማድረስ ተችሏል፡፡ የማህበረሰብ አቀፍ ቲቢ ልየታ 25.5% የሚጠበቅ ሲሆን 2,293 (20%) ሲሆን ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ5% ጨምሯል፡፡ እንዲሁም የግል ጤና ተቋማት ቲቢ ልየታ 30% የሚጠበቅ ሲሆን 2,230 (20%) ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ1% መቀነስ አሳይቷል፡፡ የስጋ-ደዌ ለመከላከልና ለመቆጣጠር 388 ታቅዶ 517 (>100%) ማሳካት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 2,764,935 የወባ ተጠርጣሪዎች ለሚሆኑ የላቦራቶሪ ምርመራ ከተደረገላቸው ውስጥ 895,422 ወባ የተገኘባቸው ሲሆን 23 ሰዎች በወባ በሽታ ምክንያት የሞቱ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር በተመለከተ፡-** ለ2,672,784 የደም ግፊት ልየታ ለመስራት ታቅዶ 4,480,649 (>100%) የደም ግፊት ልኬታቸዉ ከፍ ያለባቸው ሰዎች ተገኝተዉ 52,798 (63%) ሰዎች የህክምና ክትትል ተደርጎላቸዋል፡፡ እንዲሁም የስኳር መጠን ልኬታ 1,381,847 ለመስጠት ታቅዶ 1,492,400 (>100%) ሰዎች የስኳር መጠናቸዉ ከፍ ያለ ሲሆን 11,284 (59%) የህክምና ክትትል ተደርጎላቸዋል፡፡ እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ለ15,758 ወይም 1,300/1,000,000 የአይን ሞራ ግርዶሽ ቀዶ ህክምና (Cataract surgery) ታቅዶ ለ13,689 (87%) (564/1,000,000) ሰዎች ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ ለ41,725 የአይን ቆብ ፀጉር ወደ ውስጥ መቀልበስ ተጠቂዎች ህክምና 20,863 ለመስጠት ታቅዶ 11,547 (55%) አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

**ጥራት ያለው የጤና አጠባበቅ አገልግሎትን ማሻሻል በተመለከተ**፡- መሰረታዊ ድንገተኛ ቀዶ ህክምና (OR) ብሎክ (ግንባታቸዉ ያለቀ) ያላቸዉ ጤና ጣቢያዎች 104 ሲሆኑ የተሟላ ህክምና መሳሪያ እና ግብዓት ያላቸዉ 56 ጤና ጣቢያዎች ናቸዉ፡፡ ከነዚህ ዉስጥ 37 ጤና ጣቢያዎች መሰረታዊ የድንገተኛ ቀዶ ህክምና አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን የተሰጠው አገልግሎትም ለ65,000 ህሙማን ዋና ቀዶ-ህክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 53,179 (81.8%) አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 2.5% ከታካሚ በተመላላሽ ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ 34,675,569 (3.1%) ደርሷል፡፡ የተኝቶ ህክምና ሞት <1.8% በታች ለማድረስ ታቅዶ 1.65% ሲሆን አፈጻጸሙም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር መሻሻል አሳይቷል፡፡ የተሻሻለዉ የሆስፒታል ሪፎርም አማካይ ክልላዊ 80% ለማድረስ ታቅዶ 79.3% መፈፀም የተቻለ ሲሆን 90% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙን 84% ማድረስ ተችሏል፡፡

በክልሉ ባሉ ጤና ተቋማት ከመድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት እና ከጤና ቢሮ በድምሩ 657,449,362.75 ብር የሚያወጡ የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች የተሰራጩ ሲሆን በተጨማሪም 7,069,531,688.59 ብር የሚያወጡ መድኃኒቶች፣ የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች፣ ኬሚካሎች እና ሬጀንቶች ስርጭት የተከናወነ ሲሆን የማህበረሰብን ደህንነት ለማስጠበቅ በመድሃኒት ቸርቻሮ ተቋማት፣ ኦዲቴብል የሆነ የፋርማሲ አገልግሎት (APTS) የተገበሩ ሆስፒታሎቸ እና ጤና ጣቢያዎች 222 ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ በ430 የመድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች፣ በ1,548 የተለያዩ ደረጃ ባላቸዉ የመንግስትና የግል የጤና ተቋማት፣ በ15,000 የምግብ ተቋማትና በ52,622 ጤና ነክ ተቋማት በ69,600 የተለያዩ የህብረተሰብ ጤና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ተብለዉ ቁጥጥር በሚደረግባቸዉ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 398 (92%) የመድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች፣ በ4,180 (>100%) የተለያዩ ጤና ተቋማት፣ በ12,233 (81%) የምግብ እና 28,984 (55%) ጤና ነክ ተቋማት በአጠቃላይ በ45,795 (65%) የተለያዩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት (ድርጅቶች) ላይ የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡

በሌላ በኩል 2 የተጨመቁ ምርምሮች ለማዘጋጀት ታቅዶ 11 (>100%) እና 5 የዳሰሳ ጥናት ለማጥናት ታቅዶ 6 (>100%) ተፈጽሟል፡፡ ጤናና ጤና ነክ አገልግሎት ጥራት ቁጥጥር ኦዲትን መሰረት ያደረገ የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በ69,600 (92%) የተለያዩ አገልግሎት ሰጭ ጤና ነክ ተቋማት (ድርጅቶች) ላይ የቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡

**የስነ-ምግብ እና የምግብ ዋስትናን ማሻሻል በተመለከተ፡-** የአጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታ አገልግሎት በየወሩ 2,743,763 እንዲያገኙ ታቅዶ 2,743,763 (ሽፋን 100%) የምግብ እጥረት ተገኝቶባቸው ወደ ህክምና ከገቡት ተኝተው ከታከሙት የስርዓተ-ምግብ ልየታ እና ምክር አገልግሎት 5,185 ህጻናት ውስጥ 4,205 (83.2%) ድነው የወጡ ናቸው፡፡ ለነፍሰጡር እና አጥቢ እናቶች ለ628,264 እናቶች ለመስጠት ታቅዶ 545,705 (86.9%) ልየታ ተሰርቶላቸዋል፡፡ እንዲሁም ከ90 በላይ የደም ማነስ መከላከያ የአይረን ፎሌት ኪኒን ለ421,406 ነፍሰ-ጡር እናቶች ለመስጠት ታቅዶ 460,688 (>100%) ነፍሰ ጡር እናቶች መስጠት ተችሏል፡፡

**የስነ-አዕምሮ ጤና ደህንነትን ማስፋፋት በተመለከተ፡-** ቅድሚያ በተሰጣቸዉ ዋና ዋና የሥነ-አእምሮ በሽታዎች የታከሙ ህሙማን በ294 የጤና ተቋም ለ169,798 ሰዎች ለመስጠት ታቅዶ 57,765 (34.01%) አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

**የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን (WASH) እና አካባቢ ጤና አጠባበቅን ማሻሻል በተመለከተ፡-** በጤና ኤክስቴንስሽን ፕሮግራሙ ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተሰሩ ሲሆን ከጤና ኤክስቴንሽን እና ከጤና

ጣቢያ ባለሙያዎች ተመድቦላቸው በክትትሉ ፍሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ የሚያስወግዱ አባዎራዎች/እማዎራዎች 4,059,283 ታቅዶ 3,626,716 (89.3%)፣ ጤናማ የመኖሪያ ቤት ያላቸው ቤተሰቦች 4,352,453 (77.2%) ለማድረስ ታቅዶ 3,723,602 (85.6%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 4,059,283 (80%) የተሻሻለ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት የሚጠቀሙ አባወራዎች/እማወራዎች ለማድረስ ታቅዶ 3,626,716 (89.3%) የደረሰ ሲሆን 1,435 (48.2%) ከአይነ ምድር የጸዳ ቀበሌ ለመፍጠር ታቅዶ 1,380 (96.2%) አፈጻጸሙ ከፍተኛ ቢሆንም በቀጣይ ተግባሩን በቅንጅት በመስራት አፈጻጸሙን ማሻሻል ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም 4,143,851 (73.5%) ሞዴል ቤተሰብ ለመፍጠር ታቅዶ 3,902,295 (94.2%) መፍጠር ተችሏል፡፡

የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን 4,568,184 አባላት ለማፍራት ታቅዶ 2,098,880 (66.1%) ማፍራት ሲቻል 7.1 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ በእቅድ ተይዞ ከከፋይ አባላት 2,614,071,758 ብር 2,292,834,609 (88%) ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**በማህበረሰብ ድንገተኛ የጤና አደጋዎች አስተዳደር እና የድህረ ግጭት ማገገምና መልሶ ማቋቋም ፕሮግራም** በምዕ/ጎንደር ዞን፣ ቋራ ወረዳ በርሚል በሚባል ቦታ ላይ ታህሳስ 24 ቀን 2017 ዓ.ም የጀመረው የኮሌራ ወረርሽኝ 1,568 የኮሌራ ህሙማን ሲሆኑ ሞት 15 በህሙማን መዘርዝር ሪፖርት ተደርጓል፡፡ በሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቅኝትም 118 የኩፍኝ ወረርሽኝ ከተከሰተባቸው በ5 ዞኖችና 6 ወረዳዎች በህሙማን መዘርዝር ሪፖርት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የልጅነት ልምሻን ለመቆጣጠር ፖሊዮ ያልሆነ የፖልዮ ልየታ መጠን >2% ታቅዶ 3.1% ተፈጽሟል፡፡

በኢንተርፕራይዝ ለተደራጁ እና በልዩ ልዩ ተግባራት የስራ እድል ፈጠራ 7,322 በአፍላ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶችና ወጣት ሰቶች በገቢ ማስገኛ ስራ እንዲሰማሩ የመነሻ ካፒታል ድጋፍ እንዲያገኙ በዕቅድ ተይዞ 3,683 ድጋፍ ያገኙ ሲሆን ይህም የዕቅዱን (50%) መድረስ ተችሏል፡፡ ሌላው በሚገነባቸው በ144 ፕሮጀክቶች በኢንተር ፕራይዝ ለተደራጁ ወጣቶች ለ 503 ወንድ ለ 217 ሴት በድምሩ 720 ወጣቶች የስራ ዕድል ተፈጠረ ሲሆን በወጣቶች ግንባታ ላይ ከነበሩት ፕሮጀክቶች 44 ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል፡፡ ለ40 ወጣቶች ክትባት ለጤና ተቋማት ማመላለስ ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር ስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል አሁን ሞተር ተሰጥቷቸዋል፣ ክፍያም አላቸዉ በጠቅላላዉ ለ 542 ቋሚ እና 4443 ጊዜያዊ total 4985 የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

## 2.7. ንግድና ገበያ ልማት

**ትኩረቱን ምርት በብዛት እና በመጠን በማቅረብ በኩል ተፅዕኖ ያላቸውን የንግድ ተዋንያን ላይ በማድረግ እና ለአዳዲስ የንግድ ሀሳብ፣ ፈጠራና ክህሎት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ወደ ንግድ መረቡ**

**ማስገባትና የንግድ መሰረቱን ማስፋት በተመለከተ፡-** ጅምላ አቅራቢ 4,500 ታቅዶ 10,627 (>100%)፣ ቸርቻሪ ነጋዴ 29,779 ታቅዶ 38,647 (>100%)፣ አዲስ ንግድ ምዝገባ ማካሄድ 51,650 ታቅዶ 60,470 (>100%)፣ አዲስ ንግድ ፈቃድ መስጠት 61,850 ታቅዶ 85,561 (>100%)፣ ንግድ ፈቃድ እድሳት 352,052 ታቅዶ 247,194 (70%) በአጠቃላይ የኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት 301,390 ለመስጠት ታቅዶ 445,669 (>100%) አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ ይህም ከእጅ ንክኪ ነፃ የሆነ አገልግሎት ከመሰጠቱ ባሻገር አገልግሎት ፈላጊው በሚኖርበት አካባቢ አገልግሎቱን ማግኘት በመቻሉ ይደርስበት የነበረውን የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ጫናን ማስቀረት ቢቻልም የንግድ ፈቃድ እድሳት አፈጻጸም የንግድ ስራውን ከህገወጥ እጅ ለማውጣት በልዩ ስልት አቅዶ መስራት ይጠበቃል፡፡

**የንግድ ውድድር እና ህጋዊነትን በማስፋት የሸማቹን ደህንነት በመጠበቅ ህጋዊ የንግድ ሽፋኑን 61.6% ወደ 65% ማሳደግ፡-** በ352,052 ነጋዴዎች ላይ የበር ከበር ጉብኝት እና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ352,017 (99.99%) ጉብኝት በማድረግ 63% የሚሆኑ የንግድ ድርጅቶች ህጋዊ የንግድ ስርአቱን ተከትለዉ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን መረጃው ያመላክታል፡፡ በዚህም ሂደት 71,502 ህገ-ወጥ ተግባራት ፈፅመው በተገኙ ድርጅቶች ውስጥ በ71,502 ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ 69,467 እንዲያስተካክሉ ሲደረግ የንግድ ውድድርና የምርት ጥራትን በመጠበቅ የሸማቾችን ደህንነት ለማረጋገጥ 3,397 ድርጅቶች ደረጃውን ባልጠበቀ መለኪያ መሳሪያ ሲሰሩ በተገኙ ድርጅቶች እርምጃ ተወስዷል፡፡

**የመሠረታዊ ምርት አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ፡-** ስኳር 50,264 እና ዘይት 3,454,422 የቀረበውና የተሰራጨ ሲሆን 126,751,151 ሊትር ነዳጅ (37,599,687 ሊትር የሚሆነው ቤንዚን) ቀርቦ የተሰራጨ ቢሆንም አሁንም የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭቱን በህገወጥ መንገድ በማዛባት በተጠቃሚው ማህበረሰብ የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈጠረ በመሆኑ በማደያዎች፣ ቸርቻሪ ነጋዴዎች፣ በአሽከርካሪዎችና በተቆጣጣሪ አካላት የሚስተዋሉ የህገወጥነት ዝንባሌዎችን በልዩ ትኩረት እየተከታተሉ ማስተካከል ይጠይቃል፡፡

**የአነስተኛ ባለይዞታ አርሶ አደሮችን የገበያ ተደራሽነት በማሳለጥ የዘመናዊ ግብርና ውጤቶችን 4,736,354 ኩ/ል ወደ 4,900,000 በበቂ መጠን ለሸማቾች እንዲደርስ በማድረግ አምራቹንና ሸማቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ በተመለከተ፡-** የብርዕና አገዳ አህል 375,703 ኩንታል ለማቅረብ ታቅዶ 1,244,623 (100%)፣ ጥራጥሬ 212,707 ኩንታል ታቅዶ 326,214 (100%)፣ ቅባት እህል 35,517 ኩንታል ታቅዶ 46,095 (100%)፣ ቅመማ ቅመም 37,776 ኩንታል ታቅዶ

99,767 (100%) እና አትክልትና ፍራፍሬ 552,025 ኩንታል ታቅዶ 1,557,667 (100%) በድምሩ 1,213,728 ኩንታል ታቅዶ 3,272,366 ኩ/ል (100%) በማስተሳሰር አምራቹንና ሸማቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የአገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤቶችን ተፈላጊነት በማሳለጥ የገቢ ንግድ በአገር ውስጥ ምርት እንዲተካ ማድረግ በተመለከተ፡-** (ሰሊጥ 54,444 ታቅዶ 86,703 (100%፣ አኩሪ አተር 608,221 ታቅዶ 541,092 (89%)፣ ስንዴ 113,794 ታቅዶ 272,533 (100%)፣ በቆሎ 117,531 ታቅዶ 343,456 (100%) እና የቢራ ገብስ 38,976 ታቅዶ 51,958 (100%) በድምሩ 932,966 ኩንታል ለማስተሳሰር ታቅዶ 1,295,742 (100%) ኩንታል ተኪ ምርት ለፋብሪካዎች በማስተሳሰር ይወጣ የነበረዉን የዉጭ ምንዛሬ ማስቀረት ተችሏል፡፡

**የኬላ ላይ ቀረጥን ጨምሮ የባለ ድርሻ ተዋንያን መበራከትን ማስቀረት፡-** በአቅራቢዎች ወጪ መብዛት ምክንያት ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ለማድረግ የተለዩ 145 ህገወጥ ኬላዎችና አዲስ በሚከፈቱ ምክንያት የምርት ዝውውር ቀልጣፋ እንዳይሆን እና ሸማቹ ለኑሮ ውድነት ተጋላጭ እንዲሆኑ በማድረግና የምርት ዝውውሩ በአቅርቦቱ ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳርፍ የሚያደርጉ ህገወጥ ኬላዎችን 100% በማስነሳት ያልተገቡ የምርት ዝዉዉርን የሚገድቡ 145 ኬላዎች ሙሉ በሙሉ ተነስተዋል፡፡

**የኤክስፖርት ምርት በዓይነትና በመጠን እንዲሁም በጥራት በማቅረብ ወደ ውጭ የሚላከውን የምርት መጠን ማሳደግ በተመለከተ፡-** የቅባት እህል 1,282,403 ታቅዶ 784,599 (61%) እና ጥራጥሬ 1,739,966 ታቅዶ 1,093,198 (63%) በመሸኛ በመላክ ከዚህም 280,701,120 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 181,973,025 (65%) ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የቁም እንስሳትን በቁጥር 8,030 ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 13,920 (100%) የተላከ ሲሆን ከዚህም 893,408 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 1,140,180 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ 3,022,369 ኩ/ል የቅባት እህል፣ የጥራጥሬ እህል እና ቡናን ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 1,877,797 (62.1%) ኩንታል መላክ የተቻለ ሲሆን ከሰብል ምርትና ከቁም እንስሳት በድምሩ 281,599,537 ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 183,022,610 (65%) ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡

**የገበያ ተዋንያንን አቅም በማሳደግ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት በትስስር ለማቅረብ የንግዱ ዘርፍ ለመዋቅራዊ ሽግግር የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ፡-** የተቋሙን የንግድና ግብይት ስርዓት ለማሳለጥ የገበያ ተዋንያንን እና ባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ ለመፍጠር 524,475 ታቅዶ 1,856,900

(100%) ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም 689 የንግድ ምክር ቤትና የዘርፍ ማህበራት አደረጃጀቶችን ለማጠናከር ታቅዶ 689 (100%) (428 የዘርፍ ማህበር፣ 95 የዘርፍ ማህበር ምክር ቤት፣ 94 የንግድ እና የዘርፍ ማህበር ምክር ቤት እና 69 የነጋዴ ሴቶች ማህበር) በማጠናከር የንግድና ግብይት ሂደቱን በንግድ ስርዓት የህዝብ ክንፍ አደረጃጀቱ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል፡፡

**የገበያ ማዕከላትን በማስፋፋት እና የመረጃ ስርዓትን በማዘመን ግብይቱን በምርት ዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ተደራሽ ለማድረግ** 12 ታቅዶ 56 (100%)፣ 153 ነባር የእሁድ ገበያን ማጠናከር ታቅዶ 187 (100%)፣ 35 ሁለገብ የግብይት ማዕከላትን በአዲስ ለማቋቋም ታቅዶ 56 (100%)፣ 350 ነባር የግብይት ማዕከላትን ለማጠናከር ታቅዶ 557 (100%) ተከናውኗል፡፡

**የገበያ ተዋንያንን አቅም በማሳደግ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት በትስስር በማቅረብ የንግዱ ዘርፍ ለመዋቅራዊ ሽግግር የድርሸውን እንዲወጣ ማድረግ በተመለከተ፡-** የግብይት ትስስሩን በማጠናከርና የፋይናንስ አቅርቦቱን በማሳደግ ገበያውን ማረጋጋት ለሸማች ህብረት ስራ ማህበራትና ለዩኒየኖች 566,000,000 የተዘዋዋሪ ብድር ለማቅረብ ታቅዶ 1,375,608,000 ብር (>100%) የተከናወነ ሲሆን በተገኘው የተዘዋዋሪ የብድር አቅርቦት 1,818,639 ኩንታል የሰብል ምርት በትስስር ለማቅረብ ታቅዶ 2,054,168 (100%)፣ 916,315 ኩንታል የኢንዱስትሪ ምርት ለማስተሳሰር ታቅዶ 648,462 ኩ/ል (100%)፣ 11,892,467 ሊትር የኢንዱስትሪ ፈሳሽ ምርት ለማቅረብ ታቅዶ 10,914,327 ሊትር (90%) እንዲሁም 100 በንግድ ትርኢት ባዛርና ኢግዚቢሽን በማዘጋጀት ምርት ለማቅረብ ታቅዶ 105 (100%) ማቅረብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም አሳ 835 ቶን ታቅዶ 1,529 (100%)፣ ስጋ 327 ቶን ታቅዶ 438 (100%) ቶን፣ ማር 9,732 ቶን ታቅዶ 10,743 (100%)፣ ዶሮ 1,657,530 ታቅዶ 2,795,980 (100%)፣ እንቁላል 16,275,000 ታቅዶ 24,186,659 (100%)፣ የቁም እንስሳት 922,473 ታቅዶ 783,401 (85%)፣ ቆዳና ሌጦ 1,950,012 ታቅዶ 2,413,590 (100%) እና የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ 1,632 ቶን ታቅዶ 2,501 (100%) በማከናወን የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋትና ማህበረሰቡ ላይ የሚደርሰውን የኑሮ ውድነት ጫና ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡

**በንግድና ገበያ ልማት ዘርፍ ያሉ አቅሞችን መሰረት አድርጎ በሚሰራዉ ስራ ሁሉ የስራ እድል ፈጠራን ግብ ለማሳካት** በተቋሙ እስከ ታች ድረስ በተሰራዉ ስራ ዜጎች የስራ ዕድል ሊያገኙባቸው በሚችሉ ተግባራት ላይ 1000 ለመቅጠር ታቅዶ 2,511 (100%) የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን በመሠረተ ልማት 225 ታቅዶ 826 (100%) እና በሽርክና 100 ታቅዶ 593 (100%) ዜጎች የስራ ዕድል መፈጠር ተችሏል፡፡

## 2.8. ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ

**የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፡-** ለ11,542 የአነስተኛ፣ መለስተኛ እና ከፍተኛ ተሽከርካሪዎች የህዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 10,354 (88%) ሲሆን 4,843,925 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ ስምሪት ለመስጠት ታቅዶ 108,090,743 ህዝብ በመገንዝ 313,955,570 ኪ.ሜ መሸፈን ተችሏል:: ሌላዉ 298 ለሚሆኑ አዲስ የተሽከርካሪ የኦፕ/ብ/ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 346 (100%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ለ5,470 የተሽከርካሪ የኦፕ/ብ/ማረጋገጫ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ 2,683 (49%) ታድሷል፡፡

በተጨማሪም 32 አዲስ የህዝብ ትራንስፖርት መስመር ለመክፈት ታቅዶ 25(78%) መክፈት የተቻለ ሲሆን በ6 ወሩ 22 መናኸሪያዎች የኢ-ትኬቲንግ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ ታቅዶ 40 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 5,793,831 ተሽከርካሪዎችን በመናኸሪያ ዉስጥ ቁጥጥር ለማካሄድ ታቅዶ 4,211,876 (73%) ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን የመናኸሪያዎችን ስታዳንዳርድ ማስከበር 87% ለማድረስ ታቅዶ 76% የደረሰ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም 4 አዲስ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 5(100%) የተሰጠ ሲሆን 45 ነባር ከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ 76 (100%) ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም 187,187,783 የከተማ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 488,121,608 ህዝብ ለማጓጓዝ ታቅዶ 193,513,505 ተሽከርካሪዎችን ስምሪት መስጠት 481,644,862 (99%) ህዝብ ማጓጓዝ የተቻለ ሲሆን 687,026,339 ኪሎ ሜትር ለመሸፈን ታቅዶ 686,373,827 (100%) ኪ.ሜ መሸፈን ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ 178 ጀልባዎችን መረጃ በመሰበስብና አንድ አዲስ የጀልባ ማህበር በማደስ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 159 (89%) መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን 47,074 ህዝብ በዉሃ ትራንስፖርት ለማጓጓዝ ታቅዶ 56,694(100%) ማጓጓዝ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በ247 መናኸሪያዎች አገልግሎት አሰጣጡን ኢንስፔክት በማድረግ ስታንዳርዱን ለማስከበር ታቅዶ 234 (94%) ማከናወን ተችሏል፡፡

**ነባር ደረቅ ወደቦችን ማሻሻልና አማካይ ርቀትን መሰረት ያደረጉ ስትራቴጂካዊ ደረቅ ወደቦችን በአዲስ ለመገንባት መሰረት መጣል፡-** ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የኮምቦልቻ እና የወረታ የደረቅ ወደብ ተጨማሪ የማስፋፊያ ግንባታ እንዲደረግለት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ክትትል እተደረገ ይገኛል፡፡ በሪጀፖሊታን ከተሞችደረጃዉን የጠበቀ Off road parking እና የኤሌክትሪክ ቻርጅንግ ማዕከላት እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ በበጀት አመቱ

በ8ቱ ሪጆፖሊታን ከተሞች በእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ደረጃዉን የጠበቀ Off road parking እና የኤሌክትሪክ ቻርጅንግ ማዕከላት እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በተያዘዉ እቅድ መሰረት ከኮሪድር ልማቱ ጋር በተያያዘ ባበህር ዳር ከተማ ከአባይ ምንጭ ሆቴል እስከ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባህር ዳር  ቅርንጫፍ መ/ቤት ባለዉ መንገድ 4 አነስተኛ Off road parking ለምቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

የኤሌክትሪክ ቻርጅንግ ማዕከላት ከመገንባት አኳያ የጎንደር 1፤ የደብረብረሃን 1 እና የደሴ ከተማ 2 አስተዳደሮች በድምሩ 4 ለገዟቸዉ አዉቶቢሶች የሚጠቀሙበት የኤሌትሪክ ቻርጅ ማድረጊያ ማዕከል በመገንባትና መሳሪያዉን በመግጠም ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

**ለኢንዳስትሪያላዊነት የሚመጥን ክልላዊ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ በመቅረጽ የብዙሃን ትራንስፖርትን (Mass Transport) ማስፋፋት፡-** 38,494 በብዙሀን ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠ 4,749,018 ህዝብ በድግግሞሽ ለማጓጓዝ ታቅዶ 32,819 (85%) ተሽከርካሪዎችን ስምሪት በመስጠት 4,088,464 (86%) ህዝብ የተጓጓዘ ሲሆን 322,641 ኪ/ሜትር ለመሸፈን ታቅዶ 320,145 (99%) መሸፈን ተችሏል፡፡

**የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ዘርፉ በቴክኖሎጂ የዳበረ እና በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲመራና እንዲሰራ ማድረግ፤** 3,448 አመራሮችና ባለሙያዎች አጫጭር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 2,188 (63%) አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠናዉን መስጠት ተችሏል፡፡

**ከዓለም አቀፍ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ሥርዓቶች ጋር የሚያገናኝ ስትራቴጂካዊ የትራንስፖርት እና የሎጂስትክስ ሥርዓት መዘርጋት፡-** የጭነት ትራንስፖርት ፍላጎትና አቅርቦትን በዘመናዊ መንግድ ማሻሻልና አሰራር አደረጃጀት እና አሰራር በመፍጠር አገልግሎቱን 100% በማዘመን ቀልጣፋና ተደራሽ ማድረግ፣ በተያዘው እቅድ መሰረት የጭነት ትራንስፖርት ፍላጎትና አቅርቦትን በዘመናዊ መንገድ ለማዘመን በእያንዳንዱ ዞን ያሉ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መረጃ ማሰባሰቢያ ፎርም በማዘጋጀት 2,454 የጭነት ተሽከርካሪዎች መረጃ የመሰብሰብ ስራ የተሰራ ሲሆን ለጭነት ትራንስፖርት እንቅስቃሴ እንቅፋት የሆኑ በየቦታው የተዘረጉ ህገወጥ ኬላዎችን ፎርም በማዘጋጀት መረጃዉን የማደራጀት ስራ እየተሰራ ሲሆን እስካሁን ባለው መረጃ 86 ኬላዎች ተለይተው 14ቱ እንዲነሱ ተደርጓል፡፡ ለ5 የጭነት ተሽከርካሪዎች የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 5 (100%) መሰጠት የተቻለ ሲሆን የዲሜሬጅ የክፍያ አገልግሎት በመመሪያው መሰረት እንዲፈፀም መደገፍና ማስፈፀም በተመለከተ 3 ተሽከርካሪዎች ያለአግባብ 5 ቀን የቆዩበት በቀን 2,000 ብር ታሳቢ ተደርጎ 30,000 ብር እንዲከፈላቸው ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ለጭነት ተሽከርካሪዎች ተርሚናል ቦታ ልየታ ደሴ 12,557 ካ.ሜ፣ እንጅባራ 28,000 ካ.ሜ፣ ዋግህምራ 9,783 ካ.ሜ፣ ወልቃይት ሰቲት ሁመራ 40,000 ካ.ሜ እና ሰሜን ወሎ (ጋሽና) 20,729 ካ.ሜ በድምሩ 111,069 ካ.ሜ መረከብ ተችሏል፡፡ በክልሉ ባሉ ዞንና ከተሞች 254 ህገወጥ ኬላዎች የተለዩ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ 171(67%) ኬላዎችን ማስነሳት ተችሏል፡፡

**በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሰውን የሰው ሞት በ10 ሽህ ተሽከርካሪ አሁን ካለበት 35 ወደ 23 መቀነስ፤** 77,922 ነባር አሽከርካሪዎች አደጋን ተከላክሎ ማሽከርከርን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 79,036 (100%) የተሰጠ ሲሆን 1,599,768 ተሽከርካሪዎችን መደበኛ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 2,111,709 (100%) ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን 388,768 ተሽከርካሪዎችን በድግግሞሽ በራዳር ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 205,752 (53%) ቁጥጥር ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 6,768 አሽከርካሪዎች ላይ በአልኮል መጠን ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 14,414 (100%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን 27,835 ተሽከርካሪዎች ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ በማከናወን የቴክኒክ ብቃታቸው እንዲረጋገጥ ለማድረግ ታቅዶ 31,322 (100%) እንዲሁም 196 የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት በኢንስፔክሽን በማረጋገጥ ህግን ለማስከበር ታቅዶ 163 (83%)፣ 63 የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራትን አሰጣጥ በኢንስፔክሽን በማረጋገጥ ህግን ለማስከበር ታቅዶ 52(82.5%) ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም 850 የክስ ፓዶችን ኢንስፔክት በማድረግ ህገ ወጥነትን ለመቀነስ 1,328 (100%)፣ 5,496 የኦፕሬተር ፈቃድ በመመሪያው መሰረት መሰጠቱን በኢንስፔክሽን ለማረጋገጥ ታቅዶ 5,378 (98%) ማከናወን ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ቁጥጥር ከተደረገባቸው 2,111,709 አሽከርካሪዎች መንጃ ፍቃድ በተመለከተ ፎርጅድ/ሃሰተኛ መንጃ ፈቃድ 137፣ በጥርጣሬ የተያዘ መንጃ ፈቃድ 215፣ መንጃ ፈቃድ ሳይኖረዉ ሲያሽከረክር የተገኘ 278፣ ትክክለኛ መንጃ ፈቃድ 2,111,079 እና የመናኽሪያ መውጫ ሳይዙ ሲሰሩ የተገኙ 452 ሲሆኑ ለ15 ቀን ከስምሪት በማገድ 1,377,500 ብር ቅጣት እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በ140,000 ተሽከርካሪ የደረሰ የትራፊክ አደጋ 282 ሲሆን 7,514,691 ብር የሚገመት ውድመት እንደደረሰ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በ10,000 ተሽከርካሪ የደረሰ የሞት የአደጋ ብዛት 20 ሲሆን በ2017 ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ከደረሰው 7 አደጋ በ35% አደጋ መጨመሩን ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ ለ40,086 እጩ አሽከርካሪዎች የፅሁፍ /የንድፈ ሀሳብ/ ፈተና ለመስጠት ታቅዶ ለ31,488 (79%) የተሰጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ 3.4% ነው:: ለ40,086 እጩ አሽከርካሪዎች የተግባር ፈተና ለመስጠት ታቅዶ 31,612 (79%) የተሰጠ ሲሆን ለ31,836 ብቁ

ለሆኑ አሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 26,292 (83%) ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለ40,000 አዲሱን መንጃ ፈቃድ /የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ/ ለማደስ ታቅዶ 46,540 (100%) ታድሷል፡፡ በሌላ በኩል 5000 ነባር መንጃ ፈቃድ /አሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ/ ለማደስ ታቅዶ 5,907 (100%)፣ 70 የአሽ/ማሰ/ተቋማት ፈቃድ ማደስ ታቅዶ 44 (63%)፣ 154 የትራንስፖርት ቴክኒሽያን ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለማደስ ታቅዶ 108(70%)፣ ለ276 የትራንስፖርት ቴክኒሽያን ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ 216(79%)፣ ለ500 ዓለም አቀፍ አቻ መንጃ ፈቃድ ማረጋገጫ ደብዳቤ ለመስጠት ታቅዶ 555 (100%)፣ ለ76 የልዩ ማሽነሪ ሰልጣኝ መንጃ ፈቃድ ለመስጠት ታቅ 18 (24%)፣ ለ45 ልዩ ማሽነሪ ሰልጣኝ መንጃ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ26 (58%)፣ ለ54,160 ዓመታዊ ምርመራ ላለፉ ተሽከርካሪዎች የቦሎ ተለጣፊ ለመስጠት ታቅዶ 35,614 (66%) ማከናወን ተችሏል፡፡

እንዲሁም 5,892 ወደ ክልላችን ለሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎች ምዝገባ ማድረግና ሰሌዳ ለመስጠት ታቅዶ 3,330 (68%) የተሰጠ ሲሆን ለ4 የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 1 (25%) ተከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም ለ175 ተቋማት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ 56 (32%) ለማደስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 7,966 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ስመ-ንብረት ዝዉዉር ለማድረግ ታቅዶ 3,434 (51%)፣ የ5,368 ተሽከርካሪዎች የፋይል ዝዉዉር ለማድረግ ታቅዶ 4,949 (92%) የተከናወነ ሲሆን 3,060 ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ለውጥ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 1,126 (37%) መስጠት ተችሏል፡፡

**የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነት በማሻሻል የመረጃ ስርዓትን ማዘመን እና ዘርፉን ተወዳዳሪና ውጤታማ ማድረግ፡-** የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሶፍትዌርን በቀላሉ ለመተግበር የሚያስችል የሞባይል አፕልኬሽን በማስለማት ከ100% ወደ ስራ ለማስገባት ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የደብረ ብርሃን ትራፊክ ኮምፕሌክስ ለሲሲቲቪ ለካሜራ ዝርጋታ የተገዙ 21 ካሜራዎች፣ ኤን ቪ አር ሰርቨር፣ ሰዊችና የተለያዩ ኬብሎችን በመላክ ተቀርጦ የነበረዉን የተግባር ፈተና በአዲስ በማሰራት አገልግሎቱ እንዲጀምር የማድረግ ስራ ተሰርተዋል፡፡ የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሶፍትዌርን በቀላሉ ለመተግበር የሚያስችል የሞባይል አፕልኬሽን በማስለማት ከ100% ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በ4 ዞኖች የአሽከርካሪ ብቃት የተግባርና የንድፍ ሃሳብ ፈተና አሰጣጡን በሲሲቲቪ ካሜራ ክትትል እና ቁጥጥር ዉስጥ እንዲሆን በማድረግ 100% ወደ ስራ ለማስገባት የባህር ዳር እና የጎንደር ዞኖች የትራፊክ ኮምፕሌክሶችን የተግባር ፈተና በቴክኖሎጅ የታገዘ ለማድረግ ስራው የተሰራ ሲሆን አፈፃሙ100% ነው ፡፡

**ለ30,087 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር፡-** በዚህ ሩብ ዓመት ለ7521 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 5,490 (72.9%) ሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡

## 2.9. ኮንስትራክሽን

**የክልሉን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናማ በማድረግ ለኢኮኖሚው ማበርከት የሚጠበቅበትን ሚና መጫዎት እንዲችል የሬጉላቶሪ እና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማሳደግ ፡-** በክልሉ የሚገነቡ ግንባታዎች 100 በመቶ የአገሪቱን ህንፃ ኮድና የጥራት ደረጃዎች ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ጥራታቸውን ጠብቀው በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ለ25,000 ፕሮጀክቶች የፕላን ስምምነት፣ ለ25,000 የግንባታ ፈቃድ እንዲሁም ለ20,000 ፕሮጀክቶች የግንባታ ወቅት ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 27,089 (108%) የፕላን ስምምነት፣ 22,246 (88.98%) የግንባታ ፈቃድ እና 22,913 (114.57%) የግንባታ ቁጥጥር ማካሄድ ተችሏል፡፡ ሌላው ተገንብተው ለተጠናቀቁ 30 ምድብ ሐ ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 76 ፈቃድ በመስጠት ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሚከናዎኑ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በጥራት እንዲፈፀሙ ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመሆን የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፣ መገምገም፣ ቁጥጥር ማድረግ በተመለከተ፡-** በውለታዎች ዝግጅት ወቅት ለ48 ፕሮጀክቶች ጥያቄ ሲቀርብ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ133 የመንግስት ፕሮጀክቶች በውለታዎች ዝግጅት ላይ ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ ሌላው 40 የመንግስት ፕሮጀክቶች የጨረታ ዶክመንት ለማረጋገጥ ታቅዶ 120 (ከ100% በላይ) የመንግስት ፕሮጀክቶችን የጨረታ ዶከመንት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ 48 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ተጨማሪ ስራ ሲፈጠር ለማረጋገጥ ታቅዶ 62 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ በቀረበው ጥያቄ መሰረት የተጨማሪ ስራ የተመረመረ እና የተረጋገጠ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ ሌላው 350 የሚደርሱ መንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 565 (ከ100% በላይ) የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል፡፡

በክልሉ የሚከናዎኑ ሁሉም ፕሮጀክቶች 2 ጊዜ ምዝገባ እንዲያከናውኑ ለማድረግ ታቅዶ 2 ጊዜ ምዝገባ ማድረግ ተችሏል አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

**በክልሉ የሚገኙ 4,273 ስራ ተቋራጮችን፣ 414 አማካሪ ድርጅቶችን፣ 3,000 ባለሙያዎችን ብቃት የማረጋገጥ ስራ በሶፍትዌር የታገዘ እንዲሆን ማድረግ በተመለከተ፡** 2000 የስራ ተቋራጮችን ለማፍራት ታቅዶ 823 (41.15%) የማፍራት፣ 200 አማካሪዎችን ለማፍራት ታቅዶ

136 (68%) እንዲሁም 1400 ባለሙያዎችን ለማፍራት ታቅዶ 478 (34.14%) ባለሙያዎችን ማፍራት ተችሏል፡፡

**ለ35,221 (50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች) ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር በተመለከተ**፡ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሪጉሌሽን ዘርፈ ለ60,000 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ58,752 ወጣቶች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ 98% ነው፡፡

## 2.10. ማህበራዊ ፍትህ

ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንንና አካል ጉዳተኞችን እንደየ ችግሮቻቸው ዓይነት በነጻ ፍላጎታቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ አቅማቸው እንዲሳተፉና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የሁለተኛዉ ሩብ ዓመት ሪፖርት እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

**የማህበራዊ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበራዊ ፍትህን ተደራሽ እና ፍትሃዊ ማድረግ፤ (አደጋ መከላከል)** በገጠር ለ293,024 እና በከተማ 36,672 ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ተገቢና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ ታቅዶ በገጠር 293,024 (100%) (ሴት 188,239) እና በከተማ ለ36,672 (ሴት 24,226) (100%) ተጠቃሚዎች ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ እንዲፈፀም ተደርጓል፡፡

በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለሚጋለጡ 1,500,000 (ወንድ 742,500 ሴት 757,500) የህብረተሰብ ክፍሎች 70 በመቶ በክልሉ (ከማህበረሰቡና ከተለያዩ አካላት) እንዲሁም 30 በመቶ በፌደራል በጠቅላላው 1,350,000 ኩንታል (ብር 13.452 ቢሊየን) በማሰባሰብ የእለት ምግብ ድጋፍ በማቅረብ ለተጠቃሚዎች የተደራሽነት ምጣኔን በ2017 ከነበረበት 97 በመቶ በ2018 በጀት ዓመት ወደ 100% በማድረስ የህብረተሰቡን ህይዎት መታደግ በተመለከተ በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣ በረጅ ድርጅቶች እና ከክልል ክምችት 575,079 ኩ/ል ለ1,443,519 የማህበረሰብና ተፈናቃይ ተጠቃሚዎች የምግብ እና ለ121,310 ሰው 184,103,683 ብር በድምሩ ለ1,564,829 ተጠቃሚዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**የጥምረት ስራዎችን በማጠናከርና በማስፋት በድህነት እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት፣ ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያንና ሌሎች ግለሰቦችንና ቤተሰቦችን በመደገፍና**

**በመንከባከብ ተጠቃሚ ማድረግ፡-** ከጥምረቱ ነባር እና አዲስ አባላት 109,250,350 ብር( በጥሬ ገንዘብ 57,367,404 እና በዓይነት 51,882,946) የሚገመት ሃብት በገንዘብ እና በዓይነት ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 182,132,078 (በገንዘብ 84,230,887፣ በዓይነት 97,901,191) መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ለ144,812 የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 186,675 (>100%) (ሴት 105,631) ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በጥምረቱ በተሰበሰበው ሀብት ለ197,616 ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 359,347 (>100%) (ሴት 201,019) የሚሆኑትን መደገፍ ተችሏል፡፡

**የሴቶች፣ የህፃናት፣ የወጣቶች፣ የአረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መብት፣ ተሳትፎንና ውክልና እና ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-**

**ከመብት አኳያ፡-** 341 ቀበሌዎች በሴቶች ልማት ህብረት ሞዴል እንዲሆኑ ታቅዶ 310 (72%) ቀበሌዎችን በሴቶች ልማት ህብረት ሞዴል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ 105 ቀበሌዎች ከልጅነት ጋብቻ ነፃ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 143 (>100%) ቀበሌዎችን ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ በአንድ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት (One-Stop-Center) የህክም፣ የስነ ልቦና ድጋፍ ካገኙት 40% (346 ሴቶች) በሴቶች ማረፊያ ቤት ተጠቃሚ የሆኑ (Safe House) (የህክምና፣ የስነ ልቦና፣ የሂይወት እና የሙያ ክህሎት ስልጠና) እንዲያገኙ ታቅዶ 371 (100%) ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተመሳሳይ በተሃድሶ ማዕከል (Safe House) አገልግሎት ካገኙት ውስጥ 39% (337 ሴቶች) በገቢ ማስገኛ ስራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ 196 (51.9%) ሴቶች ብር ከ15,000 እስከ 45,000 በመስጠት ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የአንድ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት (One-Stop-Center) 80% (173 ህፃናት) በሴቶችና በህፃናት ማረፊያ ቤቶች (Safe House) ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 40% (69 (39.8%) ህፃናት) ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተመሳሳይ የህፃናት ተስማሚ ችሎቶች መካከል 17 ማዕከላትን በስልጠና፤ በቁሳቁስ… በማጠናከር 540 (ሴት.290) ህጻናትን በምቹ የህፃናት ችሎቶች አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 23 በማጠናከር 276 (51.11%) (ሴት.136) የሚሆኑ ህጻናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ለ1,240,429 ሴቶች በአዲስና በነባር የሴቶች ልማት ቡድን ውስጥ ለማደራጀት ታቅዶ 1,438,817 (>100%) ሴቶችን ማደራጀት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 562,140 (ሴት 281,070) በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤ በመፍጠር 393,489 (ሴት 196,749) በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ 542,246 (96%) (ሴት 249,153) ለ227,206 (58%) (ሴት 90,604) በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

**ከተሳትፎና ውክልና** :- በሠላም ተሳትፎ ዙሪያ 931,069 ለሚሆኑ ሴቶች (የሰላም እጦት በሴቶች እና ህፃናት ላይ የሚያስከትለዉን ዘርፈ ብዙ ተጽኖ) ዙሪያ በተለያዩ መድረኮች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 1,380,409 (>100%) ግንዛቤ ተፈጥሯል። እንዲሁም ሴቶች ያላቸውን ዕውቀት፣ ጉልበት እና ገንዘብ በማስተባበር በነፃ በአከባቢያቸው እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን በዚህም በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት 2,200,000 ለማሳተፍ ታቅዶ 3,041,337 (>100%) ማሳተፍ ተችሏል። በሌላ በኩል 115,800 (ሴት 59,004) የሚሆኑ የህጻናት ፓርላማ አባላት በራሳቸዉ የህፃናት ፓርላማ ጉባኤዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 91,944 (79%) (ሴት 46,024) እንዲሳተፉ ተደርጓል። በተመሳሳይ ከሴቶች፣ ህፃናት፣አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ጋር ተያይዞ በወጡ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ የህግ ማዕቀፎች፣ ጋይድላይንና ፓኬጅ ዙሪያ በክልል ለ21፣ በዞን ለ231 እና በወረዳ ደረጃ ለ1,571 በድምሩ ለ1,823 የሴት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን አደረጃጀት አመራሮች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ2,537 (>100%) ስልጠና ተሰጥቷል። በክረምት በጎ ፍቃድ 4,732,104 ለሚሆኑ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ደንበኞች በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 3,912,133 (100%) (ሴት 3,450,152) በክረምት በጎ ፈቃድ ተሳትፈዋል። በተጨማሪም ለተለያዩ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና እንክብካቤ አገልገሎት የሚውል ሀብት 56,691,348 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 148,954,075 (100%) ብር (በጥሬ ገንዘብ 45,772,753፣ በዓይነት ደግሞ 103,181,322) መሰብሰብ ተችሏል።

ለ50 ሴት አመራሮችንና ተኪ ሴት አመራሮችን በክልል ደረጃ በሜንተርሽፕ የአቅም ስልጠና በመስጠት በ25 የዕርስ በርዕስ የሴት አመራሮች የመደጋገፍ ትስስር ፕላት ፎርም ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 80 (100%) ሴት አመራሮችንና ተኪ ሴት አመራሮችን የሜንተርሽፕ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት በ40 የዕርስ በዕርስ የመደጋገፍ ፕላት ፎርም ትስስር ሲፈጠር 273 ተኪ ሴት አመራሮችን በስቶክ እንዲያዙ ተደርጓል።

**ከተጠቃሚነት አኳያ:-** በሴቶች ልማት ህብረት እና ራስ አገዝ ቡድን 21,732,408 ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 80,102 ሴቶች ብር 34,246,712፣ በሴቶች በገ/ቁ/ብ/ህ/ስ/ማህበራት 135,563 ሴቶች 133,621,560 ብር እንዲቆጥቡ ታቅዶ 138,421 (>100%) ሴቶች ብር 127,726,252 (>100%) ብር እንዲቆጥቡ የተደረገ ሲሆን 111,772 ሴቶች በልማት ቡድን ህብረት፣ በራስ አገዝ ቡድን እና በሴቶች ገ/ቁ/ብ/የህ/ስራ አማካኝነት የብር 223,543,865 የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 77,485 (69%) ሴቶች የብር 163,208,775 (73%) የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። በተመሳሳይ 459,081 (ሴት 229,540) ወጣቶች ብር 1,652,691,600 እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 96,494 (21%) (ሴት 45,619) ወጣቶች ብር 1,176,662,768

(71%) እንዲቆጥቡ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ 4,590 (ሴት 2,295) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ ታቅዶ 392 (8.5%) (ሴት 174) አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ወጣቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ለ143,169 (ሴት 71,584) 1,639,575,000 ብር ብድር ለማሰራጨት ታቅዶ 43,507 (35%) (ሴት 21,391) ወጣቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ 1,176,662,768 (72%) ብር ብድር ማሰራጨት ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 1,432 (ሴት 716) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ 172 (12.01 %) (ሴት 71) አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን የብድር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 1,873 (ሴት 749) የሱስ ተጠቂ የሆኑ ወጣቶችን በሱስ ማገገሚያ ማእከላት፣ ሆስፒታሎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ወዘተ ከሱሳቸው እንዲያገግሙ ለማድረግ ታቅዶ 828 (44%) (ሴት 263) ወጣቶችን ከሱሳቸው እንዲያገግሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ 1,651 የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚ የሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎች በራሳቸው ገቢ መኖር እንዲችሉ ለማድረግ ታቅዶ 838 (51%) (ሴት304) በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ማሰማራት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው 114,989 ሴቶች 35,758 ሴቶች በተለያዩ የገቢ ማስገኛ መስኮች እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ 52,578 (>100%) በልዩ ልዩ በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የብር 571,414,939 የስራ ማስጀመሪያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የአረጋዊያን ገቢ ማስገኛ ማዕከ ኪራይ ብር 7,179,880 ገቢ ለማሰባሰብ ታቅዶ 18,262,238.31 (>100%) ብር ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን ከዚህም 1,750 (ሴት 1,425) አረጋዊያን በቋሚ በየወሩ ብር 5,250,000 ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ እንዲሁም 2,217 መሥራት የሚችሉ አረጋዊያንን በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ የአካባቢውን ፀጋ በመጠቀም፣ በጥምረቶች እና በሌላ 2,950 (100%) (ሴት 1,541) በቋሚ የገቢ ማስገኛ የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በተመሳሳይ 1,954 አካል ጉዳተኞችን በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 3,460 (100%) (ሴት 1,931) አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 66,273 (ሴት 33,136) ህጻናት በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ዉስጥ ለሚገኙ በአማራጭ የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 86,169 (100%) (ሴት46,045) ህፃናትን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በነባርና በአዲስ በተቋቋሙ የህፃናት ማቆያዎችና መንከባከቢያ ማዕከላት ዉስጥ 3,361 (ሴት1,852) የሚሆኑ ህጻናትን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 2,977 (89%) (ሴት.1,509) ህጻናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በበጋ ወራት የበጎ ፍቃድ አያገልግሎት 1,500,000 (ሴት 750,000) በማሳተፍ 1,800,000 (ሴት 900,000) የህ/ሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ በማድረግ 4 ቢሊዩን የመንግስትን ወጭ ለማዳን ታቅዶ 1,774,132 (>100%) (ሴት 795,477) በጎ ፈቃደኞችን በማሳተፍ፣ 1,273,688 (70%) (ሴት 634,783) የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች መካከል በበጎ አድራጊዎች ለ26,372 አረጋውያን በቋሚ (በገንዘብ እና በአይነት) ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 27,453 (>100%) (ሴት 17,371) ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለ6,609 አካል ጉዳተኞች በቋሚ የገንዘብ እና የአይነት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 7,059 (>100%) ድጋፍ ሲያገኙ ለአረጋውያን 30,690,230 ብር (በአይነትና በገንዘብ) ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ተቀርፀው ተግባራዊ በሆኑ ፕሮጀክቶችና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም ሴቶች 39.6 ሚሊየን ብር፣ በህጻናት 39.6 ሚሊየን ብር፣ አካል ጉዳተኛ 17.7 ሚሊየን ብር እና በአረጋውያን 6.2 ሚሊዮን በድምሩ 103.1 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 58.05 ሚሊዮን ብር በሴቶች፣ 65.88 ሚሊዩን ብር በህጻናት፣ 20.37 ሚሊዩን ብር በአካል ጉዳተኞች እና 22.35 ሚሊዩን ብር በአረጋውያን በድምሩ 166.65 (>100%) ሚሊዮን ብር ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

# ክፍል ሦስት፡ የከተማና የገጠር ልማት

## 3.1. የከተማ ልማት

**በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻልና በማዘመን የተገልጋዮችን የዕርካታ መጠን በ2017 ከነበረበት 61% በ2018 ወደ 65% ማሳደግ፡-** 94 ከተሞች ሁሉም የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርድ ተዘጋጅቶላቸው እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ በ89 (94.68%) ከተሞች (85 ከተማ አስተዳደሮች እና 4 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች) መተግበር ተችሏል፡፡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ በሚተገበርባቸው 94 ከተሞች የዜጎች ቻርተር እንዲዘጋጅ፣ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆንና አገልግሎቱም በስታንዳርዱ መሰረት እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ በ89 (94.68%) ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ የተገልጋይ እርካታን በተመለከተ፡-** ስታንዳርዱ በሚተገበርባቸው 94 ከተሞች የተገልጋዩ ዕርካታ 70 በመቶ መድረሱ በጥናት ለማረጋገጥ ታቅዶ በ15 በዞኖችና ከተሞች 6,831 ናሙና ተወስዶ ጥናት የተደረገ ሲሆን በአማካይ 62.4 ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይጠቁማል፡፡

**የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን፡-** በ8 ሪጅዮ-ፖሊታን ከተሞች እና በ14 ከተሞች (በየዞኑ 1 ከተማ) የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ (የመሬት፣ የኮንስትራክሽን፣ የአገልግሎት ገቢ፣ የከተማ ነዋሪ መረጃ ወዘተ) በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈና ፈጣን እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ 20 ከተሞች ኦንላይን አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡

**የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት፡-** በ94 ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የቁራ አገልግሎት፣ የእሣት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር፣ የዘላቂ ማረፊያ እንዲሁም የገበያ ቦታና የንግድ ቤቶች አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ የቁራ ግንባታ ባለባቸው 13 (13.82%) ዞኖችና ከተሞች 17,506 የቀንድ ከብት፣ የበግና ፍየል የቁራ እርድ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎትን በተመለከተ በ6 ከተሞች (ባህር ዳር 15፣ ጎንደር 3፣ ደሴ 12፣ ደ/ብርሃን 5 እና ኮምቦልቻ 8 እና ሰ/ሸዋ 4) በድምሩ 44 የእሳት አደጋዎች ተከስተው ሊደርስ ይችል የነበረውን አደጋ መቀነስ ተችሏል፡፡

**የህብረተሰብ ተሳትፎ፡-** በግማሽ ዓመቱ በ728 ከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎችና ፕሮጀክቶች (የመንገድ ጠረጋና ግንባታ፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ የተፋሰስና የዲች ግንባታ፣ የመብራትና የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የአካባቢ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ወዘተ) ላይ ህብረተሰቡ 15% በገንዘብ፣ 17% በቁሳቁስ፣ 20% በጉልበት በድምሩ 52% እንዲሳተፍ ለማድረግ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 906,217,952.66 ብር፣ በጉልበት 728,930,868.50 ብር፣ በቁሳቁስ 405,579,884.00 ብር፣ በድምሩ 2,040,728,705.16 ብር የሚገመት ገንዘብ ለልማት ስራዎች አስተዋጾ ተደርጓል፡፡ በመንግስት በኩልም 1,839,163,928.17 ብር ለአካባቢ ልማት ስራዎች ወጪ የተደረገ ሲሆን በጠቅላላው ለአካባቢ ልማት ስራዎች 3,879,892,633.33 ብር ወጪ የተደረገ ሲሆን የህዝብ ተሣትፎ አፈፃፀም 52.60% ነው፡፡

**የከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብ፡-** በበጀት ዓመቱ በ728 ከተሞች የገቢ ሀብታቸውን ውጤት በሚያመጣ መንገድ አሟጠው በመጠቀም ለመሰረተ-ልማትና አገልግሎት እቅርቦት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በራሳቸው የመሸፈን አቅም በ2017 ከነበረበት 45% በ2018 ወደ 50% ለማድረስ ግብ ተቀምጧል፡፡ ከዚህም አኳያ በ6 ወሩ በ643 መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች 3,566,272,000 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 675,515,897 ብር (18.94%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በገቢዎች ቢሮ በኩል ከ85 ከተማ አስተዳደሮች 7,749,999,999.78 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 4,151,506,734.77 ብር (53.57%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በጠቅላላው በ728 ከተሞች 11,316,271,999.77 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 4,827,022,631.84 ብር (42.66%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በነዚህ ከተማ አስተዳደሮች፣ መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች መሰብሰብ ካለባቸው 59 የገቢ አርእስቶች ውስጥ በአማካይ 45 የገቢ አርዕስቶችን ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በአማካይ በ39 (86.66%) የገቢ አርዕስቶች የአገልግሎት ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ያልተማከለ የፋይናንስ ስርዓት በመዘርጋት ማዘጋጃቤት ያላቸው ከተሞች የልማትና የአገልግሎት ወጪያቸውን በራሳቸው ገቢ የመሸፈን አቅም 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 45 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም ኦዲት፡-** በበጀት አመቱ የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል 292 ከተሞች በመንግስትና በግል ኦዲተሮች ሂሳባቸውን እንዲያስመረምሩ በማድረግ የፋይናንስ አጠቃቀማቸው 100% ከብክነት ነጻ እንዲሆን ማድረግ የሚል ግብ የተቀመጠ ሲሆን ከዚህም አኳያ በ6 ወሩ 142 የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ኦዲት

ለማስደረግ ታቅዶ 52 (36.62%) ከተሞች ኦዲት አስደርገው በነዚህ ከተሞች 2,369,241.32 ብር ጉድለት የተገኘና ከተገኘው ጉድለት 1,513,809.23 ብር (63.89%) ብር የተመለሰ ሲሆን ቀሪው 855,432.09 (36.11%) ብር ያልተመለሰ ነው፡፡ ከባለፋት ዓመታት በኦዲት የተገኘው የተንከባለለ ጉድለት 12,517,553.52 ብር ሲሆን 3,988,179.41 ብር (31.86%) ተመላሽ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው በበጀት ዘመኑ እና ከባለፉት ዓመታት በኦዲት ከተገኘው 14,886,794.84 ብር የገንዘብ ጉድለት ውስጥ 5,501,988.64 (36.95%) ብር የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 9,384,806.2 (63.05%) ደግሞ ያልተመለሰ ነው፡፡

**የመኖሪያ ቤት ልማት:-** በከተሞች እድገትና በተለያዩ ገፊ ምክያቶች እያደገ የመጣውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ችግር /የመልካም አስተዳደር ችግር/ መፍታት ልዩ ትኩረት ማግኘት ያለበት ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በ6 ወሩ ይህን ችግር ለማቃለል በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች 46,471 ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ በሪልስቴት 215 ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኅበራት 15,351 ቤቶች፣ በግለሰቦች 10,448 ቤቶች፣ ለዝቅተኛ ነዋሪዎች 1,341 ቤቶች በድምሩ 27,355 (58.86%) መኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል፡፡

በሪልስቴቱ ዘርፍ ጥራት ያላቸው የቤት አልሚዎችን በማስገባት ቤት ማልማት አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ 10 ወደ ግንባታ ያልገቡ አዳዲስ የሪልስቴት አልሚዎችን ወደ ግንባታ እንዲገቡ እና 5 በግንባታ ላይ ያሉ ነባር የሪልስቴት አልሚዎችን ግንባታቸውን እንዲያጠናቀቁ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ደ/ብርሃን ላይ 1 አዲስ ሪልስቴት ወደ ልማት የገባ ሲሆን ነባር ሪልስቴት አልሚዎች ግንባታቸውን እንዲያጠናቅቁ በማድረግ በኩል ውስንነት ያለበት ተግባር ቢሆንም በቢሮው እና በከተሞች ከአሁን በፊት በልማት ላይ ለተሰማሩ የተወሰኑ የሪልስቴት አልሚዎች ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተለያዩ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለመሆን የተመዘገቡ ቤት ፈላጊዎች 1.8 ቢሊዮን ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 5.65 (ከ100% በላይ) ቢሊዮን ብር ቆጥበዋል፡፡

**የመንግስት ቤት አስተዳደር:-** በክልሉ ከተሞች የሚገኙ 10,440 በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ ቤቶችን፤ 10,049 የኮንዶሚኒየም ቤቶችን እና 29,514 የግለሰብ ቤቶችን በድምሩ የ50,003 ቤቶችን መረጃ ወደ ዘመናዊ የመረጃ ቋት ለማስገባት ታቅዶ 10,823 (82.8%) የመንግስት ቤቶች፣ 607 (6.04%) የኮንዶሚኒየም ቤቶች እና 1,863 (6.3%) የግለሰብ ቤቶችን መረጃ ወደ ሶፍትዌር ማስገባት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ዞኖችና ከተሞች ለሶፍትዌሩ ግብዓት/አመች በሚሆን መንገድ የኮንዶሚኒየም እና የግለሰብ ቤቶችን መረጃ በማደራጀት ላይ ናቸው፡፡

በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 56,292 ቤቶችን የውል እድሳት እንዲካሄድላቸው ለማድረግ ታቅዶ 34,759 (61.8%) ቤቶች የውል እድሳት ማድረግ የተቻለ ሲሆን የ2,500 የመንግስት ቤቶችን የኪራይ ዋጋ ለማሻሻል ታቅዶ የ16,333 (ከ100% በላይ) ቤቶችን የኪራይ ዋጋ ማሻሻያ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያልወጣላቸው 1500 የመንግስት ቤቶችን በመለየት ካርታ እንዲሰራላቸው ለማድረግ ታቅዶ 3,656 ቤቶች ካርታ የተሰራላቸው ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ ያለአግባብ የተያዙ 600 የመንግስት ቤቶችን በመንጠቅ ለአዲስ ተከራዮች ለማስተላለፍ ታቅዶ 230 (38.3%) የመንግስት ቤቶችን በመንጠቅ ለሌሎች ተጠቃሚዎች የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

**የተንከባለሉ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ፡-** በከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP) በታቀፉ 10 ከተሞች በፕሮጀክት ባህሪያቸውና በአፈጻጸም አቅም ማነስ ምክንያት ከ2017 በጀት ዓመት ወደ 2018 በጀት ዓመት የተንከባለሉ 29 ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 3 (10.34%) ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ 4 (13.79%) ኘሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ከ80% በላይ የሆኑ፣ 12 (41.38%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50%-80% የሆኑ እና 10 (34.48%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50% በታች የሆኑ ናቸው፡፡ በUIIDP ፕሮግራም ባልታቀፉ ከተሞች ከ2017 ወደ 2018 በጀት ዓመት የዞሩ 93 ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 93 (100%) ፕሮጀክቶች በ6 ወሩ የተጠናቀቁ ናቸው፡፡ በ2018 በጀት ዓመት ከተለዩት 995 ፕሮጀክቶች ዉስጥ 116 (11.65%) ፕሮጀክት የተጠናቀቁ ሲሆን 50 (5.02%) ፕሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ከ50 - 80% ነው፡፡ 82 (8.2%) ፕሮጀክት አፈፃፀሙ ከ50% በታች ነው፡፡ 159 (15.97%) ፕሮጀክቶች በጨረታ ሂደት ላይ ሲሆኑ 588 (59.09%) ፕሮጀክቶች ደግሞ ወደ ስራ ያልገቡ ናቸው፡፡ ለነዚህ 995 ፕሮጀክቶች 4,322,772,501 ብር በጀት የተያዘ ሲሆን 167,384,147 ብር ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ በክልሉ የሚገኙ 85 ከተማ አስተዳደሮች የመሰረተ ልማት ሃብት ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ 54 (63.53%) ከተማ አስተዳደሮች ቆጠራ በማድረግ መረጃውን ወቅታዊ አድርገዋል፡፡

**የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፡-** ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ማሻሻያ ሥራዎች አንዱ የከተማውን ህዝብ ግንዛቤ በመፍጠር የጽዳት ቀን ወስኖ ሰፈሩንና አካባቢውን እንዲያጸዳ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በ6 ወሩ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ 8 የጥናት እና 9 የተሞክሮ ሰነዶች እና 2 የንቅናቄ ሰነዶች ተዘጋጅተው እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ 8 የንቅናቄ ሰነድ እና 3 የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በ691 ከተሞች ወርሃዊ /ሳምንታዊ/ የጽዳት ቀን በማስወሰን 800,000 የሚሆኑ መኖሪያ ቤቶች እና 43,000 ተቋማት ከ20 - 50 ሜትር ርቀት

ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ ለማድረግ ታቅዶ በ526 (74.5%) ከተሞች በ448,184 (56%) መኖሪያ ቤቶች እና 47,957 (ከ100% በላይ) ተቋማትና ድረጅቶች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በ706 ከተሞች 3,200 ኪ.ሜ መንገዶችን እና 3,200 ኪ.ሜ የውሃ ማፋሰሻ ቦዮችን በመለየት በተከታታይነት የማጽዳት ስራ ለማከናወን ታቅዶ በ508 ከተሞች 3,710.75 ኪሜ (ከ100% በላይ) መንገዶችን እና 2,840.17 ኪሜ (78.7%) ማፋሰሻ ቦዮችን የማጽዳት ስራ ተከናውኗል፡፡ በክልሉ በሚገኙ 122 ከተሞችና ክ/ከተሞች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የግንባታ ፍርስራሽ ቆሻሻ በልዩ ክትትል ለማስወገድ ታቅዶ በ145 (ከ100% በላይ) ከተሞች ለማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ማህበራት የሌላቸውን 67 ከተሞችን በመለየት 137 አዲስ ማህበራትን በማደራጀት በድምሩ 2,000 ዜጎች አዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በ45 (67.16%) ከተሞች 57 (41.61%) አዲስ ማህበራትን በማደራጀት ለ1,172 (58.6%) ዜጎች የስራ እድል በአዲስ መፍጠር ተችሏል፡፡

በከተሞች በዓመቱ ከሚመነጨው 1,500,000 ሜትር ኪዩብ ደረቅ ቆሻሻ እንዲሰበሰብ እና በ20 ከተሞች ከሚመነጨው ቆሻሻ 60 በመቶ የሚሆነው በተገቢው ቦታ እንዲወገድ ለማድረግ ታቅዶ 967,462.51 ሜትር ኪዩብ ደረቅ ቆሻሻ የተሰበሰበ ሲሆን ከተሰበሰበው ውስጥ 60 በመቶ የሚሆነው ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ተወግዷል፡፡ ቋሚ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሌላቸውን 220 ከተሞች በመለየት ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለማዘጋጀት ታቅዶ በ199 (90.45%) ከተሞች ጊዜዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የቆሻሻ ማስወገድ የፋይናንስ ስርዓት ያላቸውን 104 ነባር ከተሞች ለማጠናከር እና በ30 ከተሞች አዲስ የፋይናንስ ስርዓት ለመዘርጋት ታቅዶ በ96 (92.31%) ነባርና በ22 (73.33%) አዲስ ከተሞች ከውሃ ቢልና ከሌሎች አማራጮች ጋር በማስተሳሰር ቀጣይነት ያለው የፋይናንስ ስርዓት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**የአረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎችን በተመለከተ፡-** ከሐምሌ 1/2017 ዓ/ም ጀምሮ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ እቅድ በማዘጋጀት በ728 ከተሞች 1 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ በፓርኮች፣ በመንገድ አካፋዮችና በወንዞች ዳርቻ 27.4 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 2,000 ሄ/ር አዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን ለማልማት ታቅዶ በ402 (59.20%) ከተሞች ወንድ 869,840 ሴት 701,495 ድምሩ 1,571,335 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎችን በቀጥታ በማሳተፍ 36,490,105 (ከ100% በላይ) ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ በዚህ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብርም 2,501.35 (ከ100% በላይ) ሄ/ር አረንጓዴ ቦታ ማልማት ተችሏል፡፡ በ32 ከተማ አስተዳደሮች 32 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮች በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ እና በ131 ከተሞች

ለ244 ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ በ26 ከተሞች 32 (100%) አዳዲስ የመዝናኛ ፓርኮች የለሙ ሲሆን በ127 ከተሞች ለ233 (95.49%) ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ማድረግ ተችሏል፡፡ በ153 ከተሞችና ክ/ከተሞች ለሚገኙ 213 ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ በ165 ከተሞች ለሚገኙ 192 (90.14%) ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም 20 ከተሞች 20 አዳዲስ ችግኝ ጣቢያዎችን ለማልማት ታቅዶ በ25 ከተሞች 28 ችግኝ ጣቢያዎችን ከእቅድ በላይ ማልማት ተችሏል፡፡

በ153 ከተሞች በኘላን የተመላከቱ 754 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ በ142 ከተሞች 1,003 (ከ100% በላይ) አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት ለ471 (62.47%) አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡ እስከ አሁን በጠቅላላው ለ1,736 አረንጓዴ ቦታዎች ወይም ለ1,312 ሄ/ር አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡ በ96 ከተሞች በፕላን ከተመላከቱ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሽፋኑንም 30 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 114 ከተሞች ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

**የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች፡-** በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣ በኮምፖስት ማምረት፣ አረንጓዴ ልማት፣ በቤቶች ልማት እና በመሰረተ ልማት ስራዎች ለ84,100 (የወጣቶች ድርሻ 49,453) ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ92,190 (ከ100% በላይ) ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን የወጣቶች ድርሻ 58,351 (ከ100% በላይ) ነው፡፡

## 3.2. የአካባቢ ጥበቃ ልማት

**የደን ዘርፉን በመጠበቅ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ በተመለከተ በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደን የተከለለ፣** የተለካና የይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖረው የተደረገ ሲሆን በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን 5,000 ሄክታር የተፈጥሮና ሠው ሠራሽ ደን በአዲስ በመከለልና በመለካት ይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖረው ማድረግና በዘላቂነት በማልማት የይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 7,605 (ከ100% በላይ) ሄ/ር የተፈጥሮና ሠው ሰራሽ ደን በመ-ከለልና በመለካት ይዞታ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል፡፡ ሌላው 600 ሄ/ር የመንግስት ደኖች የደን አያያዝ እና አጠቃቀም ዕቅድ እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ ታቅዶ 750 (ከ100% በላይ) ደኖች የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ እንዲሁም 2,800 ሄ/ር የማህበረሰብ ደኖች የደን አያያዝ እና አጠቃቀም ዕቅድ እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ ታቅዶ 2,967 (ከ100% በላይ) ደኖች የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ የተዘጋጀላው ሲሆን 2,240,000 ኩ/ል የከሰል ምርት፣ ተመርቶ በህጋዊ መንገድ እንዲዘዋወር ለማድረግ ታቅዶ 2,010,000 ኩ/ል የከሰል ምርት ለገበያ

በማቅረብ 89.7% መፈጸም የተቻለ ሲሆን እንዲሁም ከደንና ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች የልማትና ሮያሊቲ ክፍያ 75 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 87.88 ሚሊዮን ብር ገቢ በመሰብሰብ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ሌላው ደኖች 128,945 ነባር እና 21,055 አዲስ ደኖች በአሣታፊ የደን አያያዝ ስርዓት እንዲጠበቁ ለማድረግ ታቅዶ 116,008 (90%) ነባር እና 20,605 (97.8%) አዲስ ደኖች በደን አያያዝ ስርዓት እንዲጠበቁ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በኃይማኖትና አምልኮ ስፍራዎች የሚገኙ 2,816 ሄ/ር ደኖች በአሳታፊ የደን አያያዝ አጠቃቀም እንዲጠበቁ ለማድረግ ታቅዶ 8,548 ሄ/ር እንዲጠበቁ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸም ከ100% በላይ ነው፡፡

**የክልሉን 7 የደን ኢንዱስትሪዎች ሙሉ አቅም በመጠቀም ከደን ምርት ውጤቶች የሚገኘውን 2.2 ሚሊየን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ወደ 2.628 ሚሊየን ዶላር ማሳደግ** እና ወደ ክልሉ የሚገባውን የደን ውጤት በሀገር ምርት በመተካት ከነበረበት 50 ሚሊየን ዶላር ወደ 49 ሚሊየን ዶላር መቀነስ በተመለከተ ከደን ምርት ውጤቶች የሚገኘውን ኢክስፖርት ገቢ ወደ 1,314,000 ለማሳደግ ታቅዶ 750,000 (55.56%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ወደ ክልሉ የሚገባውን 500,000 የደን ውጤት በሀገር ምርት በመተካት ወጪን ለመቀነስ ታቅዶ 508,106 በማድረስ ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ሌላው 24,940.6 ሄ/ር መታረስ የሌለበትን ተራራማ እና በሰፋፊ ውሃ አካላት ዙሪያ ያለ መሬትን እንዲከለልና እንዲያገግም ለማደረግ ታቅዶ 73,884.65 ሄ/ር መሬት እንዲከለልና እንዲያገግም ማደረግ ተችሏል፡፡ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማሳተፍ 17,940.6 ሄ/ር በውኃ አካላት ዙሪያ የሚገኙ የተጋጋጡ ተራራማ መሬቶችን ለመለየት፣ ለመከለልና ካርታ እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ ታቅዶ 61,962.9 ሄ/ር (ከ100% በላይ) መሬቶችን የመለየት፣ የመከለልና ካርታ እንዲዘጋጅላቸው ማድረግ ተችሏል፡፡

**የክልሉን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬታ መጠን በ2012 የነበረውን 79.8 ሚሊየን ሜትሪክ ቶን ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ኢኩቫለንት ማስጠበቅ በተመለከተ፡** በዞን እና በወረዳ ደረጃ 40 የአየር ንብረት ምላሽ ሰጪ ተግባራት ፈጻሚ የዘርፍ መ/ቤቶችን አደረጃጀቶች ለማጠናከር ታቅዶ 70 ፈጻሚ አደረጃጀቶችን በማጠናከር ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ሌላው የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ሰጭ ተግባራትን ዘርፎች አካተው መተግበራቸውን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለሁለት ዘርፍ እንዲሁም ለሁለት ኢንዱስትሪ የአመራረት ስርዓቱ የአረንጓዴ ልማት አመራረት ስርዓት የተከተለ እንዲሆን ከትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

የአካባቢ ብክነትና ብክለት መቀነስ እና የውኃ አዘል መሬት አያያዝና አጠቃቀም ማጎልበት በተመለከተ 263 የአካባቢ ብክለትና ብክነትን ለመቀነስ ታቅዶ 1061 ብክለትና ብክነት መቀነስ

የተቻለ ሲሆን 50 ብክለት ይወገድልኝ ጥቆማዎች መፍትሄ መስጠት ተችሏል፡፡ ሌላው በአካባቢና በማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ በሚፈጥር 5 የአካባቢ ብክለት መንስኤ የሆነ ችግር በጥናት በመለየት ለውሳኔ ሰጭ አካላት ለማቅረብ ታቅዶ 7 (ከ100% በላይ) ችግሮችን በጥናት በመለየት ለውሳኔ ሰጭ አካላት ማቅረብ ተችሏል፡፡

**ለነባርና አዲስ 4,181,915 የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁኔታ ፈቃድና እድሳት በመስጠት** እና ህጉን የጠበቀ የሂሳብ አያያዝ እንዲኖራቸው የክዋኔ ኦዲት በማድረግ ህግ በሚጥሱ ፕሮጀክቶች/ድርጅቶች ላይ የህግ ተከባሪነትን ለማረጋገጥ ታቅዶ 5,422,641 (ከ100% በላይ) የልማት ፕሮጀክቶች የህግ ተከባሪነትን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሌላው ለ3552 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድ እንዲሁም ለ3392 ነባር ፕሮጀክቶች አድሳት ለመስጠት ታቅዶ 3,335 (93.9%) አዲስ ፈቃድ እና 3,117 (91.9%) እድሳት መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለ36 አማካሪዎች (በድርጅትና በባለሙያ) ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ41 (ከ100% በላይ) አማካሪዎች ፍቃድ እንዲሁም ለ18 አማካሪዎች እድሳት ለመስጠት ታቅዶ ለ36 (ከ100% በላይ) አማካሪዎች እድሳት መስጠት ተችሏል፡፡

በማምረቻና አገልግሎት መስጫ የልማት ፕሮጀክቶች የሚካሄድ ክዋኔ ኦዲትን ከነበረበት 3,327 በ2018 ወደ 3,970 ማሳደግ በተመለከተ ለ1,984 የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ2,744 (ከ100% በላይ) ፕሮጀክቶች ክትትል የተደረገ ሲሆን ለ1,896 የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ኦዲት/ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ2,649 (ከ100% በላይ) ፕሮጀክቶች የኦዲት ምርመራ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ህግ በማይከተሉ 276 ፕሮጀክቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ በ355 (ከ100% በላይ) ህግ በፈጸሙ ፕሮጀክቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡

በልማት ፕሮጀክቶች፣ በከተሞችና ተቋማት ላይ በ2017 በጀት ዓመት ተደርጎ የነበረውን 1,764 የአካባቢ ቁጥጥር በ2018 በጀት ዓመት ወደ 1,993 በማሳደግ የህግ ተከባሪነትን ማረጋገጥ በተመለከተ ለ996 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ቁጥጥር ለማካሄድ ታቅዶ ለ1,666 (ከ100% በላይ) ፕሮጀክቶች ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል፡፡

በ601,166 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ላይ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ988,754 (ከ100% በላይ) ከተሞች ድጋፍና ክትትል ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለ30 ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ44 (ከ100% በላይ) ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዕቅድ የተዘጋጀላቸው ሲሆን ለ24 ከተሞች ቆሻሻን በመሰብሰብ መልሶ መጠቀም (Reuse & Recycling) ለሚሰማሩ ግለሰቦች ድጋፍ

ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የተሰማሩ 70 ማህበራት እንዲጠናከሩና እንዲደራጁ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

የእምቦጭና ሌሎች የመጤ፣ ወራሪ፣ ተስፋፊና አደገኛ አረም ዝርያዎችን መቆጣጠር እና እንዲወገድ በ2017 በጀት ዓመት ከነበረት 40 በመቶ ወደ 42 በመቶ ማድረስ በተመለከተ በማህበረሰብና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በየአካባቢው በተደረገ ዘመቻ 100,000 ሄ/ር መጤ፣ ወራሪና ተስፋፊ አደገኛ የአረም ዝርያዎች ለማስወገድ ታቅዶ 124,765 ሄ/ር (ከ100% በላይ) አረም ማስወገድ የተቻለ ሲሆን በዚህ ተግባርም 862,670 (ሴት-547,247) የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

**በክልሉ የሚገኙ የዱር እንስሳት መኖሪያ ጥብቅ ሥፍራዎችን ቁጥር በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 3.5 በመቶ በ2018 ወደ 3.8 በመቶ ማሳደግ** በተመለከተ 369384 ለማድረስ ታቅዶ 305180.45 (82.6%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ስካውት፣ በኮንትራት ስካውቶች፣ በስካውቶች፣ በባለሙያዎችና በባለድርሻ አካላት 360,000 ጊዜ አሰሳና ቅኝት ለማካሄድ ታቅዶ 274,391 (76%) ጊዜ የእንስሳት አሰሳ/ቅኝት ማካሄድ ችሏል፡፡ ሌላው በ48 ጥብቅ ስፈራዎች የዱር እንስሳት በሽታ አሳሳና ቅኝት ለማካሄድ ታቅዶ ለ87 (ከ100% በላይ) ጥብቅ ስራዎች የዱር እንስሳት በሽታ አሰሳና ቅኝት ማካሄድ ተችሏል፡፡ ሌላው በኢኮ ቱሪዝም፣ ፊልም ቀረጻ፣ ንብ ማነብ፣ ጓሳ ማላመድ፣ የደንና የፍራፍሬ ልማት እና በሌሎች ስራዎች 2,000 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 6,645 (ከ100% በላይ) እንዲሁም በእጣንና ሙጫ፣ ጓሳ እና የመኖ ሳር በመሰማራት በጥብቅ ስፍራዎች አካባቢ የሚኖሩ 4,000 የህብለተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 19,140 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በጥብቅ ስፍራዎች ውስጥ የተጎዳ 3,000 ሄ/ር የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች እንዲያገግሙ ለማድረግ ታቅዶ 4,308 ሄ/ር (ከ100% በላይ) የተጎድ ጥብቅ ስፍራዎች እንዲያገግሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከቱሪዝም እና ከሌሎች አገልግሎቶች 4,247,000 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 8,494,000 ብር ገቢ በመሰብሰብ ከ100% በላይ መፈጸም የተቻለ ሲሆን በዘርፉ ለስራ አጥ ወጣቶች ለ6,544 ቋሚና ለ2,204 ጊዜያዊ የሰራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ25,371 ቋሚ እና ለ98,396 ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

# ክፍል አራት፡ የልማት አቅሞች

## 4.1. መሬት

**ለ126,784 ለባለይዞታዎች 570,531 ማሳ የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ካርታ በመስጠት የይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትና ማረጋገጥ እንዲሁም የማሳ ካርታን የብድር ዋስትና በማድረግ 23,280 ባለይዞታዎች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፡-** የገጠር መሬት ባለይዞታዎችን የይዞታ መብት ለማረጋገጥና ዋስትና ለመስጠት ለ50,714 ባለይዞታዎች 228,212 የማሳ ካርታ በማዘጋጀት የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ73,557 (>100%) (አባወራና እማወራ 25,809፣ አባወራ 20,287፣ እማወራ 20,382፣ የጋራ ይዞታ ከባልና ሚስት ውጭ 4,121፣ የወል 2,223፣ ለመንግስት ተቋማት ለ309፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት 426) ባለይዞታዎች 266,574 የማሳ ካርታ ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል።
ለ2,536 ተጋላጭ የህ/ሰብ ክፍሎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ 2,520 (>100%) (ወንድ - 1,202፣ ሴት - 1,318) (ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህፃናት 196 (ወንድ -111፣ ሴ-85)፣ አካል ጉዳተኞች 384 (ወንድ 210፣ ሴት-174)፣ አረጋውያን 1,724(ወንድ 767፣ ሴት- 957) የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት ተችሏል።

የአርሶ አደሩን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል 11640፣ በበጀት ዓመቱ ለ23,280 ባለይዞታዎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና በማድረግ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ለ17,144 (>100%) (ወንድ 11,783፣ ሴት 5,361) ባለይዞታዎች 953,464,892 ብር የብድር ተጠቃሚ ሲሆኑ ብድር ያገኙ አርሶ አደሮችን የቁጠባ መጠን ለማሳደግ ብር 25,145,009 እቅድ ተይዞ ብር 85,224,724 (>100%) ተቆጥቧል።

**በኮምፒውተር ሳይመዘገቡ የቀሩትን የመሬት ባለይዞታዎች የመሬት መረጃ ምዝገባና ወቅታዊ በማድረግ 18,444 ባለይዞታዎች 51,935 ማሳ ወደ ISLA (Information System for Land Administration) Software በማስገባት የመሬት መረጃ ደህንነትና የአሰራር ቅልጥፍና ስርዓት ይሻሻላል፡-** 9,222 ባለይዞታዎችን የመሬት መረጃ ወደ ኮምፒውተር ለማስገባት ታቅዶ የ55,181 (>100%) ባለይዞታዎችን የመሬት መረጃ ወደ ኮምፒውተር የመመዝገብ ሥራ ተሰርቷል።

**የመሬት መረጃ ወደ NRLAIS (በብሄራዊ የገጠር መሬት መረጃ ስርዓት) በማሸጋገር የሚቀርቡትን ሁሉንም የመሬት ይዞታ ግብይቶች በማረጋገጥ በ Analogue (ባህር መዝገብ) እና በ NRLAIS ሲስተም በመመዝገብ አገልግሎትቱን በማሳለጥ የመሬት መረጃ ስርዓት ደህንነትንና ቀጣይነትን ማሻሻል፡-** በሁሉም የመሬት ይዞታ ለውጦች 2,574 (ስጦታ፣ ውርስ፣ ልውውጥና ኪራይ) መረጃ

አጣርቶ ለመመዝገብ ታቅዶ 8,129 (ወንድ 4,616፤ ሴት 3,513) የመሬት ግብይት በማከናወን ከዓመቱም ሆነ ከግማሽ ዓመቱ ከእቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

**የመሬት መረጃን ወደ NRLAIS ሲስተም ማሸጋገርና በሲስተም የመሬት ግብይት ስራ፡-** 417,051 ማሳዎችን ወደ NRLAIS ሲስተም እንዲያሸጋግሩ ለማድረግ ታቅዶ በ60 ወረዳዎች በ811 ቀበሌዎች የ315,762 ማሳዎች መረጃ ወደ ሲስተም በማሸጋገር ከማሳ ብዛት የእቅዱን 76% ማከናወን ተችሏል፡፡ በሁሉም የመሬት ይዞታ ለውጦች መረጃ አጣርቶ 119,530 ለመመዝገብ ታቅዶ 189,831 (ወንድ 112,262፤ ሴት 77,569) የመሬት ግብይት የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

**በበጀት ዓመቱ ውስጥ በከተማ 155,400 ይዞታዎችን በሰነድ በማረጋገጥ አሁን ካለበት 143,631 ይዞታ ወደ 298,931 በማድረስ በክልል ደረጃ ተናባቢ የሆነ የመሬት ይዞታ መረጃ እንዲኖርና አሰራሩ ከገጠር መሬት ይዞታ አስተዳደር ጋር ተጣጥሞ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት፡-** 51,800 የይዞታ ፋይሎች/ማህደሮች ለይዞታ ማረጋገጥ ሥራው የሚያስፈልጉ ህጋዊ ሰነዶች በመለየት ከመብት ሰጭ ተቋሙ ርክክብ ለማድረግ ታቅዶ የ40,627 (78.43%) ፋይሎች ርክክብ ማድረግ ተችሏል፡፡ በከተሞች የይዞታ ይረጋገጥልኝ ማመልከቻና ሰነድ በመቀበል 51,800 ይዞታዎችን የማጣራትና የማረጋገጥ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 31,858 (61.5%፤) ይዞታዎችን የማረጋገጥ ስራ የተሰራ ሲሆን 51,800 የይዞታ ማረጋገጥ ውጤት ለህዝብ ይፋ ለማድረግ ታቅዶ 8,250 (16%፤) የተረጋገጡ ይዞታዎች ውጤት ለህዝብ ይፋ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 51,800 ባለይዞታዎች ይዞታው የተረጋገጠላቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ለመስጠት ታቅዶ ለ10,403 ባለይዞታዎች ማስረጃ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 20% ነው፡፡

**በበጀት ዓመቱ ውስጥ 93,240 ቁራሽ መሬቶችን በመመዝገብና የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለባለይዞታዎች በማሰራጨት አሁን ካለበት 73,255 ወደ 166,495 በማድረስ የባለመብቶችን የይዞታ መብትና የንብረት ዋስትና ማረጋገጥ፡-** 42,690 ባለይዞታዎች የመብት ምዝገባ ለማድረግ ታቅዶ ለ 22,405 (52%) ባለይዞታዎች የመብት ምዝገባ የተደረገ ሲሆን 42,690 ባለይዞታዎች የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ21,505 (50%) ባለይዞታዎች የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል፡፡

**በበጀት ዓመቱ ውስጥ 18,500 ባለይዞታዎችን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በመስጠት አሁን ካለበት ሽፋን ከ15,616 ወደ 34,116 በማሳደግ አገልግሎቱን በ75% ቀልጣፋና ተደራሽ ማድረግ፡-** ለ9,100 አገልግሎት ፈላጊዎች ከይዞታ ምዝገባ በኋላ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለመስጠት ታቅዶ ለ 8,858

(97%) አገልግሎት ፈላጊዎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ከተሰጡ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች 300 ሚሊዮን ብርገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 483,631,153 (>100%) ብር ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ በህገ-ወጥ መንገድ የተያዙ 34000 ይዞታዎችን መረጃ በአግባቡ መሰብሰብ፣ በህገ-ወጥ መንገድ የተገነቡ 34000 ግንባታዎችን በማፍረስ ማድረግ፡-** 14,960 አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ በህገ-ወጥ መንገድ የተያዙ ይዞታዎችን መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ የ30,323 (>100%) ይዞታዎች መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን 14,960 ህገ-ወጥ ይዞታዎችን ለማፍረስ ታቅዶ 14,252 (95%) ህገወጥ ይዞታዎች እንዲፈርሱ ተደርጓል፡፡ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል መሰረተ ልማት የተሟላለት 5850 ሄ/ር ለጨረታ እና ለምደባ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል በግማሽ ዓመቱ 2,924 ሄ/ር፣ በበጀት ዓመቱ 5,850 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 6,375 ሄ/ር መሬት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

**በ338 ከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 5850 ሄ/ር መሬት መሰረተ- ልማት ተሟልቶለት እንዲተላለፍ ማድረግ፡-** ለምቶ ወደ መሬት ባንክ/ስቶክ/ ከገባው ለተለያየ አገልግሎት የሚውል 292 **ሄ/ር** ቦታ በጨረታ ለማስተላለፍ በዕቅድ ተይዞ 47.78 **ሄ/ር** ቦታ ለተጠቃሚዎች የተላለፈ ሲሆን አፈጻጸሙም 16.36% ነው፡፡ 1579 ሄ/ር ቦታ ከማህበራት ውጪ በምደባ ለማስተላለፍ በዕቅድ ተይዞ 556.522 (35.24) ሄ/ር ቦታ ለተጠቃሚዎች የተላለፈ ሲሆን 1053 **ሄ/ር** ቦታ ለህብረት ስራ ማህበራት ለማስተላለፍ ታቅዶ 381 (36.18%) ሄ/ር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

**በከተሞች በልማት ምክንያት ተነሽ ለሆኑ ግለሰቦች በስታንዳርዱ መሰረት 10,000 ለልማት ተነሺዎች ቦታ እንዲያገኙ ማድረግ፡-** 3,500 በልማት ምክንያት ለማስነሳት ታቅዶ 5,292 ሰዎች ለልማት የተነሱ ሲሆን አፈጻጸሙ ከበጀት ዓመቱ 53 100% ሲሆን 420 ሄ/ር ትክ ለመስጠት ታቅዶ 247 ሄ/ር የተሰጠ ሲሆን 59% ከበጀት ዓመቱ 21% ነው፡፡

**በጨረታ እና በምደባ ለተጠቃሚ ተላልፈው በውላቸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ (ወደ ልማት ያልገቡ) 545 ቦታዎች እንዲነጠቁ በማድረግ 80 ሄ/ር ቦታ ወደመሬት ባንክ እንዲገባ ማድረግ፡-** 24 ሄ/ር መሬት በጨረታ እና በምደባ ለተለያየ አገልግሎት ተወስደው በውላቸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቦታዎች ለማስመለስ ታቅዶ 88 (>100) ሄ/ር መሬት ማስመለስ ተችሏል፡፡

**በሁሉም ከተሞች 260,000 የነባር እና ሊዝ ይዞታ ማህደሮች በሃርድ ኮፒ፣ 260000 (ዋና ዋና የይዞታ አመላካች ማስረጃዎች በኤክሴል፣ 26000 ጅኦግራፊካል ኢንፎርሜሽን ሲስተም (GIS) እና 260000 ስካን በማድረግ) ለከተማ መሬት ይዞታና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ስርአት ግብዓት**

**በሚሆን መልኩ ተደራጅተው እንዲያዙ ማድረግ፡-** 160,000፣ የመሬት ይዞታ ፋይሎችን በሀርድና በሶፍት ኮፒ ለማደራጀት ታቅዶ 301,520 ፋይሎችን የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡

**በ332 ከተሞች በሊዝ፣ ከኪራይ እና ከስመ ንብረት ዝውውር የተገኘ ገቢ ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ይዞታዎች በውላቸው መሰረት ተገቢውን የሊዝና የቦታ ኪራይ ክፍያ በወቅቱ እንዲፈጽሙ በማድረግ 4,433,311,957 ብር እንዲሰበሰብ ማድረግ፡-** 1,441,295,978.5 በከተሞች ከሊዝ ይዞታ፣ ከነባር ይዞታ እና ከስመ ንብረት ዝውውር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 1,475,579,834.32 ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

**ጥራት ያለዉ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አያያዝ እቅድ ለ 84,106 ባለይዞታዎች በማቀድ አሁን ካለዉ 4,156,671 የባለይዞታዎችን ወደ 4,240,777 ማሳደግ እና ለ 141,559 ባለይዞታዎችን እቅድ በመከለስ ከዚህ በፊት ከነበረዉ 94,205 ወደ 235,764 ማሳደግ፡-** 75,222 ባለይዞታ፣ 250,736 ማሳዎችን፤ በአዲስ ለማቀድና እና የእቅድ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ለመከለስ የታቀደ ሲሆን ለ55,521 ባለይዞታ፣ 226,203 ማሳዎች የመሬት አጠቃቀም እቅድ ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ከባለይዞታ 73%፣ ከማሳ ብዛት 90%፣ ማከናወን ተችኳል፡፡ የ36,234 ባለይዞታዎችን፣ 120,264 ማሳ፣ በበጀት ዓመቱ የ298,133 ባለይዞታዎችን 992,736 ማሳ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ከተዘጋጀ በኋላ በአዲስ የታቀዱትንና ርክክብ ሳይፈፀም ተቋርጠዉ የቀሩ እቅዶችን ለተጠቃሚዎች ርክክብ ለመፈፀም ታቅዶ የ60,761 ባለይዞታዎችን 220,880 ማሳዎች ማስረከብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከባለይዞታ እና ከማሳ ብዛት 100% በላይ ነው፡፡

**እስከ አሁን የመሬት አጠቃቀም እቅድ ከተዘጋጀላቸዉ 930,887 ባለይዞታዎችን ወደ ተግባር በማስገባት ከዚህ በፊት ወደ ተግባር የገቡ 2,124,880 የባለይዞታዎችን ቁጥር ወደ 3,055,767 ማሳደግ፡**465,437 ባለይዞታ፣ 1,808,372 ማሳ በተቀመጠላቸዉ የመሬት አጠቃቀም እቅድ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ታቅዶ 661,297 ባለይዞታ፣ 1,717,380 ማሳ ወደ ተግባር የማስገባት ስራ ተሰርቷል፡፡

**የመሬት አጠቃቀም እቅድ የተዘጋጀላቸዉን የ4,271,654 ባለይዞታዎችን ከNRLAIS እና ከ ISLA/ መረጃ ጋር በማናበብ የመሬት አጠቃቀም የመረጃ አያያዝ ስርአትን ማሻሻል፡-** 2,135,827 ባለይዞታ የአጠቃቀም እቅድ የተዘጋጀላቸዉን ባለይዞታወች መረጃ ወደ ኮምፒውተር ለማስገባት ታቅዶ የ1,838,899 (86%) ባለይዞታ፣ ወደ ኮምፒውተር ማስገባት ተችሏል፡፡

**ለ37,943 የልማት ተነሽዎች 13.287 ቢሊዮን ብር ተመጣጣኝ ካሳ በመገመት የካሳ ማስከፈል ሂደቱን ማሻሻል፡-** በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለሚነሱ 11,383 ባለይዞታዎች 3.986 ቢሊዮን

ብር ካሳ ለመገመት ታቅዶ ለ17,241 የልማት ተነሽዎች 7.32 (>100) ቢሊዮን ብር ካሳ የተገመተ ሲሆን በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለሚነሱት 11,383 ባለይዞታዎች ብር 3.986 ቢሊዮን፣ ካሳ እንዲከፈል ክትትል ለማድረግ በእቅድ ተይዞ ለ9,552 (አባውራና እማወራ 6343፣ አባወራ 1,589፣ እማወራ 1,620) የልማት ተነሽዎች ብር 3.724 ቢሊዮን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ካሳ የሚከፍለው ተቋም የካሳ ክፍያ እንዲፈጽም ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ ከባለይዞታ አንፃር 83% ሲሆን ከተከፈለዉ ካሳ መጠን ደግሞ 94% ነው፡፡

**በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አርሶአደር በቀበሌ ማእከል ለማሰባሰብ በ150 ቀበሌዎች 20,000 የቤት መስሪያ ቦታ በመስጠት የተጠቃሚዎችን ሽፋን ከ 200,883 ወደ 220,883 ማሳደግ፡-** በ41 የገጠር ቀበሌ ማእከላትን በብሎክ ለማከፋፈል በእቅድ ተይዞ የ92 (>100%) ቀበሌዎች ብሎክ የመክፈል ስራ የተሰራ ሲሆን 8,040 የተሸነሸኑ የግንባታ ቦታዎችን ለተጠቃሚዎች ለማስረከብ ታቅዶ ለ5,942 (74%) ተጠቃሚዎች የማስረከብ፤ ለ8,000 ተጠቃሚዎች የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 4,752 (59%) ተጠቃሚዎች የግንባታ ፈቃድ በመስጠት 6,427 (80%) ተጠቃሚዎች ግንባታ የጀመሩ ሲሆን 8,000 ሳይት ፕላንና ግንባታ ላጠናቁ ተጠቃሚዎች ቋሚ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ 6,058 (76%) ሳይት ፕላን ለ4,809 (60%) ገንቢዎች ቋሚ ካርታ የተሰጠ ሲሆን 405 ግለሰቦችን ስመ ንብረት ለማዛወር ታቅዶ 502 ተጠቃሚዎች ስመ ንብረት ዝውውር ፈፅመዋል፡፡

**30,964 ሄ/ር የኢንቨስትመንት መሬት በመለየት በባለሀብቶች አሁን የሚለማውን መሬት ከ204,322ሄ/ር ወደ 235,286 ሄክታር በማሳደግ ምርታማነትን መጨመር፡-** ለግብርና ኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል 13,924 ሄ/ር ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ 16,687 (>100%) ሄ/ር መሬት የተለየ ሲሆን ለኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚውል 2,642 (>100%) ሄ/ር መሬት ተለይቷል፡፡ እንዲሁም ለአገልግሎት ዘርፍ የሚውል 57 ሄ/ር ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ 792 (>100%) ሄ/ር መሬት ተለይቷል፡፡ በአጠቃላይ ለሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚውል 15,482 ሄ/ር መሬት ለመለየት ታቅዶ 20,121 ሄ/ር(>100%) መሬት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ በግብርና፤ በአገልግሎት እና በኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት ዘርፎች በግማሽ ዓመቱ ለ49 ባለሀብቶች አዲስ ውል ለመስጠት ታቅዶ ለ47 ባለሀብቶች 930 (95%) ሄ/ር መሬት ላይ አዲስ ውል እንዲይዙ ተደርጓል፡፡

**በከተማ የ155,400 ይዞታዎችን እና በገጠር 160,535 ሄ/ር መሬት የቅየሳ ስራዎችን በመስራት ለማሳ ካርታ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ማቅረብ፡-** 51,800፣ ይዞታዎች የይዞታ ወሰን ማካለል ስራ ለመስራት ታቅዶ 29,698 የይዞታ ወሰን በማካለል 57.33% መፈጸም የተቻለ ሲሆን

51,800 ይዞታዎችን የይዞታ ወሰን ቅየሳ ስራ ለመስታት ታቅዶ 20,564 (40%) የይዞታ ወሰን መቀየስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 1,067 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ሞኑመንት በስታንዳርድ መሰረት በማምረት እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 443 (42%) የመትከል ስራ ተሰርቷል፡፡ ለገጠር መሬት ካዳስተር ምዝገባ ስራዎች 49,192 ሄ/ር መሬት ለመቀየስ ታቅዶ 33,069 (67%) ሄ/ር መሬት የተቀየሰ ሲሆን በግማሽ ዓመቱ 15,482 ሄ/ር፣ በበጀት ዓመቱ 30,964 ሄ/ር መሬት ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል መሬት የቅየሳ ቦታ ልየታ ስራ ለመስራት ታቅዶ 18,222 ሄ/ር መሬት የመቀየስና የመለየት ስራ በመስራት ከግማሽ ዓመቱ >100%፤ ከዓመቱ 62% መፈጸም ተችሏል፡፡ ለገጠር ቀበሌ ማዕከል 240 ሄ/ር መሬት ለመቀየስ ታቅዶ 1,383 (>100%) ሄ/ር መሬት ተቀይሷል፡፡

**የሁለተኛ ደረጃ ይዞታ ማረጋገጥ ስራ ለሚከናወንባቸው የ56 የቀበሌዎች 28,000 የመስክ ካርታ፣ የ**319,789 **የትቻታ ካርታዎችን፣303,798 የማሳ ካርታዎችን ማዘጋጀትና በግብዓትነት ማቅረብ፡-** 15,000 የመስክ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 15,994 (>100%) የመስክ ካርታ የተዘጋጀ ሲሆን 159,895 የመሬት መረጃዎችን ዲጂታይዝ ለማድረግ ታቅዶ 152,065 (95%) መረጃዎችን ዲጂታይዝ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 159,895 ለህዝብ ትቻታ የሚሆን የቀበሌ ኢንዴክስ ማፕ እና ኢስላ ፕሪንት አውት ለማዘጋጀት ታቅዶ 152,065 (95%) የተዘጋጀ ሲሆን 151,000 የባለይዞታዎች የማሳ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 219,947 (>100%) የማሳ ካርታ የተዘጋጀ ተዘጋጅቷል

**በከተሞች 156 የቀጠና፣ 780 የሰፈር ካርታ እና 93,240 መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣ 98 የኢንቨስትመንት ካርታ በስታንዳርዱ መሰረት እንዲዘጋጅ ማድረግ፡-** 20,000 የባለይዘታዎች መሬት/ቦታ/ኦርቶፎቶን በመጠቀም ዲጂታይዝድ ለማድረግ ታቅዶ 49,405 የባለይዞታዎችን መሬት ዲጂታይዝ በማድረግ ከከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 72 የቀጠና ካርታ እና 360 የሰፈር ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 86 የቀጠና ካርታና 413 የሰፈር ካርታ የተዘጋጀ ሲሆን ከግማሽ ዓመቱ ከ100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡ በግማሽ ዓመቱ 42,690፤ በበጀት ዓመቱ ለ93,240 ባለይዞታዎች የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ 22,447 ባለይዞታዎች ይዞታ መብት ማረጋገጫ ካርታ በማዘጋጀት ከግማሽ ዓመቱ 53% ከዓመቱ ደግሞ 24% ተፈጽሟል፡፡

## 4.2. የሰው ኃይል ልማት

**የክልሉን የሰው ኃይል ለልማት በቁጭት እንዲነሳሳ በማነቃቃት፣ በማበረታታት እና በመደገፍ የማምረት አቅሙን ማሳደግ፡-** በዲፕሎማ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በ2ኛ ዲግሪ እና በ3ኛ ዲግሪ ለ1,000 የመንግስት ሰራተኞች የረዥም ጊዜ የትምህርት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1,456 (100%) (ወ 566 ሴ 890) የረዥም ጊዜ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለ17,500 የመንግስት ሰራተኞች የአጭር ጊዜ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 33,289 (100%) (ወ 18,375 ሴ 14,914) አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት በፈፃሚው የሚስተዋሉ የአቅም ክፈተቶችን ለመሙላት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የገጠር ሴቶችን በአጫጭር ስልጠና (ኢንተርፐርነርሽፐና ቴክኒካል ክህሎት ስልጠና) በመስጠት ለ274,018 ሴቶች በስራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ለማድረግ** ታቅዶ፣ 215,389 ሴቶች በገጠር በስራ ፈላጊነት የተመዘገቡ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 121,118 ሴቶች የኢንተርፐርነርሽፐ እና 15,895 የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ስልጠና ከተሰጠ በኋላ 84,373 (ቋሚ 59,743) ሴቶችን በስራ ዕድ ፈጠራ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ በስራ ዕድል ከዓመቱ ዕቅድ 30.79% ከ6 ወሩ ደግሞ 76.97% ማከናወን ተችሏል፡፡

**በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ጋር የተጣጣሙ እንዲሁም ገበያ ተኮር በማድረግና ለተማረው ወጣት በተማረበት ዘርፍ በቂ የሥራ መስክ በመፍጠር ለኢኮኖሚው የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማጎልበት በተመለከተ፡-** በመንግስትና በግል ኮሌጆች ነባር እና አዲስ ሰልጣኝ ቅበላ በመደበኛው ስልጠና ነባር 51,492፣ አዲስ ቅበላ 86,009 ሰልጣኞችን በጠቅላላው 137,501 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ለማሰልጠን ታቅዶ፡- በ5 ዞኖች በመደበኛ ስልጠና ነባር ሰልጣኝ 69,791 (50.75%) (ወንድ 24,428 ሴት 45,363) ተመዝግበው በመሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡

**በልዩ ልዩ ንዑስ ዘርፎች እና ንዑሰ-ንዑሳን ዘርፎች የሙያ፣ የቴክኒክ፣ እና ቮኬሽናል ተግባራዊ ስልጠና እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የሚሰጥባቸው ማዕከላትን ማደራጀት በተመለከተ፡-** ለ436 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የስራ መደብ የተፈቀደ ቢሆንም እስካሁን 418 ማዕከላት ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆኑ 356 ደግሞ የተሟላ በሚባል ደረጃ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ 12 የአንድ ማዕከላት 8 ዴስክቶፕ ኮምፒዩተርና 4 ፕሪንተር በፌዴራል ደረጃ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ እንዲሁም በ140 ወረዳዎች ለሚገኙ 356 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች 496 ታብሌት ተሰራጭቷል፡፡

**ለዘመናዊ ግብርና፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ፣ ለኮንስትራክሽን እና ለሌሎች ልዩ ልዩ የከተማ እና የገጠር ኢንተርፕራይዞች የሚሆን የሰው ኃይል አቅም መፍጠር፡-** በግብርና ዘርፍ ለ153,450 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ182,613 (>100%) (ወንድ 113,880 ሴት 68,733) ከዚህ ውስጥ በቋሚ ለ125,425 (69%) ዜጐች የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን በኢንዱስትሪ ዘርፍ ለ131,529 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ130,342 (99.10%) (ወንድ 78,915 ሴት 51,427) ከዚህ ውስጥ በቋሚ ለ130,342 (84.9%) የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ ለ153,450 የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ312,436 (>100%) ከዚህ ውስጥ በቋሚ 257,898 (100%) ለስራ ፈላጊ ዜጐች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ በከተማና በገጠር በሁሉም የስራ አማራጮች የሚመጥን የሰው ሃይል ለመፍጠር 438,430 (100%) (ወንድ 215,694 ሴት 240,557) ታቅዶ ወ 316,959 ሴ 308,432 ድምር 625,391 (100%) የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

**በቴክኖሎጂ በተለይም በፋብሪኬሽን ምህንድስና እና ዲጂታል ቴክኖሎጂ ጥልቅ ሥልጠና አተኩሮ መሥራት በተመለከተ፡-** በ39 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና በ66 ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በአጠቃላይ በ105 ኮሌጆች የኢንኩቤሽን ማዕከላት የተቋቋመ ሲሆን 46 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች እና 64 ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ወደ ስራ ገብተዋል፡፡

በተዘጋጁ ሰነዶች መሰረት በዓይነት ችግር ፈቺ 171 ቴክኖሎጁን ለመቅዳት ታቅዶ 151 (88.3%) ቴክኖሎጂዎች የተለዩ የተሸጋገረ ቴክኖሎጂ 286 ታቅዶ 183 (64%) የተሻገረ ሲሆን በዚህም 2,605 ኢንተርፕራይዝ ና 5,210 አንቀሳቃሽ ተተቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 994 ኢንተርፕራይዞችና 880 አንቀሳቃሾችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ለማሻሻል ቢሮው ባለማው EMIS ሶፍት ዌር መሰረት የመንግስት እና የግል ኮሌጆች መረጃውን ማስገባት ችለዋል፡፡ በተጨማሪ ለመንግስት እና ለግል ኮሌጆች ሰልጣኞች በተዘጋጀው ሲስተም የስልጠና ማጠናቀቂያ ኮድ አገልግሎት ለ3,726 ሰልጣኞች ኮድ ተሰጥቷል፡፡

በስራና ስልጠና በተለያዩ ዘርፎች ለ339,786 እንዲሁም በሌሎች ለ49,507 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር በተመለከተ፡- በከተማና በገጠር ዩኒቨርስቲ 17,280፣ ቴክኒክና ሙያ 15,000 በድምሩ ለ32,280 ምሩቃን የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፡- የዩኒቨርስቲ 14,756 የቴክኒክ ኮሌጅ 15,273 በድምሩ 30,029 ከዚህም ቋሚ 23,644 (78.7%) የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**በክልሉ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በግብርና፣ በአገልግሎት፣ በአነስተኛ አምራች ዘርፎች፣ ወዘተ በስፋት በመስጠት ዜጎችን ተጠቃሚ**

**ማድረግ፡-** በመንግስትና በግል ኮሌጆች ሰልጣኞች 394,587 (በከተማ 197,294 በገጠር 197,293) የኢንተርፕሪነርሺፕ እንዲሁም 177,417 (በከተማ 112,660፣ በገጠር 64,757) የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 525,349 (>100%) (ወንድ 225,905 ሴት 299,444) የኢንተርፕርነርሽፕና እና የቴክኒካል ክህሎት 324,706 (>100%) (ወንድ 132,932 ሴት 191,774) ሥራ ፈላጊ ዜጐች ስልጠና ወስደዋል፡፡

**የመንግሰት ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ከ60.8 በመቶ ወደ 75 በመቶ ማሳደግ፡-** 3,450 የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት ስታንዳርድ አዘጋጅተውና በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ታቅዶ 6,886 (100%) ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና ለተገልጋዮች ግልፀኝነት እየፈጠሩ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በተገልጋዮች ለቀረቡ ቅሬታዎች 100% ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 862 ቅሬታዎች ቀርበው 792 (92%) ውሳኔ ወይም ምላሽ ሲያገኙ 70 (8%) በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

**የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ትግበራን ወጤታማነት 100 በመቶ ማሳደግ**፡- የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ስራዎች አካል ሲሆን ደንበኛ የሚበዛባቸውን አገልግሎቶች በቴክኖሎጅ በማስተሳሰር በአንድ ላይ በማቀናጀት በአንድ ማዕከል እንዲሰጡ በማድረግ ተገልጋዩን ከወጪና ከጊዜ ብክነት በመቀነስ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ አገልግሎት በማቅረብ በመንግስት ተቋማት የተገልጋዮች የአገልግሎት አሰጣጥ ችግርን ለመፍታት ያለመ ኢንሽቲቭ ነው፡፡

የክልል ተቋማት የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ስራን በ4 ማዕከላት ለማስጀመር ታቅዶ 3 (75%) ማስጀመር ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በክልል ደረጃ ከ10 ተቋማት ከ54 አገልግሎቶች፣ ባህር ዳር ከተማ 13 ተቋማት 91 አገልግሎቶች፣ ደሴ ከተማ 14 ተቋማት 83 አገልግሎቶች እና ጎንደር ከተማ 13 ተቋማት 54 አገልግሎቶች የተለዩ ሲሆን በፌድራል 4 ተቋማት በሁሉም ማዕከላት ከ7 እስከ 8 የሚደርሱ አገልግሎቶች ተለይተው ወደ መሶብ አንድ ማዕከል እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የመሶብ አንድ ማዕከል ስራ በጀመሩ በክልሉ መሶብ አንድ ማዕከል እና በ2 ከተማ አስተዳደሮች (ባህር ዳርና ደሴ) አገልገሎት ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ብዛት 30,942 ሲሆን በተሰጠው አገልግሎት የተገልጋዮች እርካታም 95.3% ማድረስ ተችሏል፡፡

**በሲቪል ሰርቪስ ተቋም ለ20,000፣ በስራና ስልጠና በተለያዩ ዘርፎች ለ339,786 እንዲሁም በሌሎች ለ49,507 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር (በሁሉም ተቋማት 50 በመቶ ሴቶች፣ 75 በመቶ ወጣቶች እና 0.27 በመቶ አካል ጉዳተኞች ይሆናሉ)፡-** በሲቪል ሠርቪስ ተቋማት 6,600 የሰው

ሃይል ስምሪት ለማድረግ ታቅዶ 5,096 (77.21%) (ወ 2,899 ሴ 2,197) የሰው ሃይል ስምሪት ተደረጓል። በተፈጠረው የሰው ሃይል ስምሪትም ሴቶች 43.1%፣ የወጣቶች 47% እና የአካል ጉዳተኞች 0.45% ተጠቃሚ ሆነዋል። በተጨማሪ በስራና ክህሎት 438,430 (ሴት 489,479) የስራ ፈላጊ ወጣቶችን በከተማና በገጠር በመለየት መረጃ ለማደራጀት በዕቅድ ተይዞ 1,102,025 (ሴት 532,515) የስራ ፈላጊ ወጣቶችን መረጃ ማደራጀት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም (>100%) ነው። ከዚህ ውስጥ 513,724 የገጠር ወጣቶች ሲሆኑ 588,301 የከተማ ወጣቶች ናቸው።

በከተማና በገጠር በሁሉም የስራ አማራጮች 1,096,074 (ቋሚ 876,859 ጊዜያዊ 219,215) እስከ ታህሳስ ወር 438,430 (ቋሚ 350,744 ጊዜያዊ 87,686) የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ቋሚ ወንድ 215,694 ሴት 240,557 ድምር 456,251 ጊዜያዊ ወንድ 101,265 ሴት 67,875 ድምር 169,140 በአጠቃላይ ወንድ 316,959 ሴት 308,432 በድምሩ ለ625,391 (>100%) የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። አጠቃላይ ከተፈጠረው የሥራ እድል ውስጥ 80% እና በላይ ዘላቂ (ቋሚ) የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ (456,251) (72.95%) ማከናውን ተችሏል።

**የገጠር ሴቶችን በማስተማርና አቅማቸውን በአጫጭር ስልጠናዎች በመገንባት የሴቶች የሥራ ዝግጁነት ምጣኔን ማሳደግ በተመለከተ፡-** የገጠር ሴቶችን በአጫጭር ስልጠና (ኢንተርፕርነርሽፕና ቴክኒካል ክህሎት ስልጠና) በመስጠት ለ274,018 ሴቶች በስራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 215,389 ሴቶች በገጠር በስራ ፈላጊነት የተመዘገቡ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 121,118 ሴቶች የኢንተርፕርነርሽፕ እና 15,895 የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ስልጠና ከተሰጠ በኋላ 84,373 (ቋሚ 59,743) ሴቶችን በስራ ዕድ ፈጠራ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። አፈፃፀሙ በስራ ዕድል ከዓመቱ ዕቅድ 30.79% ከ6 ወሩ ደግሞ 76.97% ማከን ተችሏል።

## 4.3. ቴክኖሎጅ

**በማሽን፣ በግብዓት፣ በኃይል እና በኦቶሜሽን ዝግጅት ማድረግ፡-** ልዕለ ማሽን ለማምረት 1 ማንዋል በማዘጋጀት ጽንሰ-ሀሳቡን በሚገባ ለመረዳት ታቅዶ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብ ማንዋል 100% ተዘጋጅቷል።

**በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ፣ በሲስተም ልማትና በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ተወዳዳሪና ብቁ የሰው ኃይል መገንባት፡-** ለ270 ለቢሮው፣ የዞንና ለክልል ተቋማት ICT ባለሙያና አመራሮች ከትምህርት ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች ጋር በመቀናጀት የገበያ ፍላጎትንና ተወዳዳሪነትን ያማከለ አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠትና ከዚህም ውስጥ የሴቶች ድርሻ 30% ለማድረግ ታቅዶ ለ397 (>100%) ሠልጣኞች ማሰልጠን ተችሏል። ለ4,000 ዜጐች በተለያዩ ስርዓቶችን ስልጠና ለመስጠት (Online

platforms, simulation software, e-learning platforms, mobile learning apps, AI powered educational tools) በማስፋፋት በዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ እና ቴክኖሎጂ ትራንስፎርሜሽን ተወዳዳሪነት አቅም ለማሳደግ ከዚህም የሴቶች ድርሻ 30% ለማድረስ ታቅዶ 3965 ሰልጣኞች ስልጠናው የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸም 99.13% ነዉ፡፡ 1000 ወጣቶች በኢንተርንሽፕ ስልጠና ለመስጠት በዕቅድ ተይዞ 257 ወጣቶች የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ 25.7% ነው፡፡

ለ100 እስታርታፖች ስልጠና መስጠትና ድጋፍ ማድረግ ታቅዶ ለ4631 እስታርታፖች ስልጠናና ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት በመቆጣጠር ዳታ ማዕከልን እና የሌሎች አገልግሎቶችን ደህንነት ማስጠበቅ የታቀደ ሲሆን ወደ ዳታ ማዕከል የሚገቡ ሲስተሞች ሳይበር ኦዲት ከተደረጉ በኃላ እንዲገቡ በማድረግ፣ አንቲቫይረስ ሶፍትዌርን በመጠቀም፣SSL key እና ባካፕ ዳታ በመያዝ የዳታ ማዕከል ደህንነትን ማስጠበቅ ተችሏል፡፡ አፈፃፀም 95% ነው፡፡

**የክልሉን ልማት ሊያፋጥኑ የሚችሉ የቴክኖሎጅ ፈጠራዎች ላይ በማተኮር በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን አሰራራቸውን ማዘመን፡-**
የአማራ ብረታ ብረት ኢንጅነሪግን ለክልሉ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ማሽኖችን እንዲያመርት እና ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋራ ትስስር እንዲፈጠር ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ ውይይት ተደርጓል፡፡ በተመረጡ የልማት ዘርፎች ላይ ትኩረት በማድረግ በተለይም መካከለኛ ኢንዱስትሪውን ሊያሳድጉ የሚችሉ የቴክኖሎጅ ፈጠራዎች ላይ የስልጠና የሙያ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

የቴክኖሎጅ ማዕከላትን በመገንባትና በማስፋፋት ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች አንድ ማዕከል ላይ በማሰባሰብ የፈጠራ፣ የምርምርና ሲስተም የማልማት አቅምን ማሳደግ እንዲሁም አዳዲስ ፈጠራ ይዘው የሚመጡ ስራ ፈጣሪዎችን መደገፍና ማበረታት፡- በዘርፉ የተለየ ተሰጥዖ ያላቸውን መለየትና ዉጤታማ ሊያደርግ የሚችሉ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ አንድ ኘሮግራም የተዘጋጀ ሲሆን በዚህም ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች መለየት አስችሏል፡፡

ለ90 ተማሪዎችን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል 1 ሳመር ቡት ካምኘ በማዘጋጀት፣ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያበለጽጉ ለማድረግ፣ ታቅዶ 87 ተማሪዎችን ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ጋር በመተባበር ለአንድ ወር ሳመር ቡት ካምፕ ፕሮግራም በማዘጋጀት innovation and design thinking, application development, cyber security and project idea generation በሚሉ የስልጠና ይዘቶች ላይ ስልጠና ተሰጧል፡፡ አፈፃፀሙ 96.66% ነው፡፡

ለ50 በሰርቶ ማሳያ ማዕከል እና በሌሎች ማዕከላት የስልጠና እድሎችን በተለያዩ ፕላትፎርሞችን (AI learning path) ተደራሽ በማድረግ የክልሉን ቀጣይ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል ታቅዶ በ25(50%) ማዕከሎች ለ4248 ሠልጣኞች E-learning, virtual በመጠቀም የዕውቀት ሽግግር እንዲኖር ተደርጓል፡፡

**የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ ሲስተሞችን ማልማትና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡-** በክልሉ ለሚሰለጥኑ የኢትዮ ኮደርስ ሰልጣኞች ሪፖርቲንግ ሲስተም ተለምቷል፡፡ አገልግሎትን የሚያዘምኑ የተለያዩ 2 ሲስተሞችን ለማሸጋገር ታቅዶ የተቀናጀ የፍትህ መረጃ አስተዳደር ሲስተም፣ የአማራ ዲጂታል ሊትሬሲ ለርኒንግ ማናጅመንት ሲስተም የምርትና አቅርቦት ማናጅመንት ሲስተም፦ ማሸጋገር ተችሏል አፈፃፀሙም 100% በላይ ነው፡፡ ለ5 ተቋማት የሶፍትዌር ልማት የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለገቢዎች ቢሮ eTas ሲስተም ትግበራ ላይ፣ ሞሰብ የአንድ ማዕከል፦ ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሀብት አስተዳደር ቢሮ ጋር በመተባበር ወደ መሶብ ለሚገቡ ተቋማት የሶፍትዌር ፍላጎት ጥናት ተደርጓል፡፡ እነዚህም (ትራንስፖርት ቢሮ ፣መሬት ቢሮ፣ የዜጎች አገልግሎትና የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት፣ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ፣ ማዕድን ቢሮ፣ ስራና ክህሎት ቢሮ፣ግብርና ቢሮ፣ ዲጅታላይዜሽን ዶክመንት ዝግጅት ተሰርቷል፣ ፍትህ ቢሮ፣ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፦ e-Ticket ሲስተም ለመስራት መረጃ ተሰብስቦ የዲዛይን ስራ እየተሰራ ነው፡፡

**እንዲሁም መንገድ ቢሮ** ተቋሙን ዲጅታላይዜሽን ከማድረግ አኳያ የመኪና መረጃ አስተዳደር ሲስተም ትግበራ እንዲሁም የሌሎች ሲስተሞች ላይ የማማከር ስራ ተሰርቷል፡፡ (ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣የአማራ ክልል ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ፣ ፕላን እና ልማት ቢሮ፣ ትምህርት ቢሮ የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል አፈፃፀሙ 100% በላይ ነው፡፡

**የቴክኖሎጂ ፈጠራ ላይ ያተኮሩ ዓመታዊ የቴክኖሎጅ ኤክስፖዎችን በማዘጋጀት ፈጣሪዎችን ማበረታትና የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ተጠቃሚ ማድረግ፡-** 1 የቴክኖሎጅ ማስተዋወቂያ ኤግዚቪሽን ለማዘጋጀት ታቅዶ የፈጠራ ስራ ላይ ያተኮረ ኤግዚቢሽን ማዘጋጀትና የነገው ቀን “ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ማድረግ“ በሚል መሪ ቃል በተከበረው በዓል ላይ በቢሮው የተለሙ ሲስተሞችን በማቅረብ ማስጐብኘት ተችሏል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጅ ቢሮ 5% መገንባት በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ከአሁን በፊት ተሰርቶ የቆየውን መሠረት የማስፈረስ ሂደት የተጠናቀቀ ሲሆን የግንባታ ስምምነት ለማውጣት በአዲሱ የመንገድ ጥናት በተቋሙ መሀል መንገድ በመኖሩ የግንባታ ስምምነት ሊገኝ ባለመቻሉ በቀረው ቦታ ጊዜያዊ ካርታ እንዲሰጥ እየተጠየቀ ሲሆን የዲዛይን ስራ ጨረታ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አምስት፡ መሠረተ ልማት

## 5.1. የመንገድ ዘርፍ

አጠቃላይ የክልሉ የመንገድ ሽፋን (Road Network Coverage) በ2017 በጀት ዓመት ከደረሰበት 34,572.4 ኪ/ሜ በ2018 በጀት ዓመት ወደ 37,654.39 ኪ/ሜ ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በገጠር ትስስርና ተደራሽነት ፕሮግራም 216.59 ኪ.ሜ (86.6%)፣ በወረዳ በጀትና በህ/ሰቡ ተሳትፎ 116 ኪ/ሜ (83.4%)፤ በከተሞች 101.36 ኪ/ሜ የጠጠር መንገድና 2.83 ኪ/ሜ ኮብል ስቶን፤ በፌደራል መንገዶች አስ/ር 50.6 ኪ/ሜ (50.4%) የአስፓልት መንገድ በአጠቃላይ በሁሉም የግንባታ ዘርፎች 698.77 ኪ.ሜ ታቅዶ 502.35 (71.8%) ኪ/ሜ መንገድ የተገነባ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 448.98 ኪ/ሜ ጠጠር መንገድ (gravel road)፣ 53.37 ኪ/ሜ አስፓልት መንገድ ተሰርቷል፡፡

ፕሮጀክቶችን ከማጠናቀቅ አኳያ በአለም ባንክና ክልሉ መንግስት መቀናጆ በጀት በገጠር ትስስር ፕሮግራም ተይዘው በበጀትና በጊዜ ምክንያት በፕሮግራሙ ውሳኔ ወደ 2018 በጀት ዓመት እንዲዞሩ (rolled-out) ከተደረጉ 40 የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች 33 ፕሮጀክቶች 100%፣ ከ32 ልዩ ስትራክቸር ግንባታ ፕሮጀክቶች 19 በቁጥር 100%፣ ከ18 ተንጠልጣይ የእግረኛ ድልድዮች 13 ፕሮጀክቶች 100% የተጠናቀቁ ሲሆን ከ33 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ 15ቱ ፕሮጀክቶች ከ75-95% እና 12 ፕሮጀክቶች ከ50-68% እና ቀሪ 7 ፕሮጀክቶች ከ20-50% አማካኝ አፈጻጸም ያላቸዉ ሲሆን በገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ነባር ፕሮጀክቶችን በዚህ ዓመት በልዩ ትኩረት የሚጠናቀቁና የሚመረቁ መደበኛ 6 ፕሮጀክቶች በተሻለ ሁኔታ ወደ ስራ የገቡ ሲሆን 27 ስትራክቸሮች 100% ተጠናቀዋል፣ 12 የተለያየ አይነትና መጠን ያላቸው ድልድዮች 85% አማካኝ አፈጻጸም ያሉ ናቸው፣ ሌሎች 20 የመንገድና ስትራክቸር ፕሮጀክቶች በተቻለ መጠን የማሽነሪና የግንባታ ግብዓት በማቅረብ ወደ ተግባር እንድገቡ የተደረገ ሲሆን ቀሪ 8 ፕሮጀክቶች በፀጥታ ችግርና የማሽነሪ ኪራይ እጥረት ገና ወደ ስራ አልገቡም፡፡

**የመንገድ ጥገና ስራዎች በ2017 ከተደረሰበት 16,449.68 ኪ/ሜ በ2018 ወደ 19,772.88 ኪ/ሜ መንገድ በመጠገን የጥገናና እንክብካቤ ስራውን በማሳደግ ክረምት ከበጋ አገልግሎት እንድሰጡ ማድረግ፡-** በክልሉ ውስጥ በሁሉም ዘርፍ ቀደም ሲል የተገነቡ መንገዶችን ክረምት ከበጋ አገልግሎት እንዲሰጡ በፌደራል መንገድ ፈንድ የሚገኝን የበጀት ድጋፍ ተጠቅሞ በገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ የመንገድና ስትራክቸር ጥገና በ289 የጥገና መስመሮች 6,038.34 ኪ/ሜ፣ በወረዳ በጀትና በህብረተሰብ ተሳትፎ በ755 የጥገና መስመሮች 9,600 ኪ/ሜ (3,000 ኪ.ሜ

በማሽን፣ 6600 ኪ.ሜ በሰው ሃይል)፣ በገጠር ትስስር ፕሮግራም - RCFSP በ75 ፕሮጀክቶች 717.78 ኪ/ሜ፣ በ5 የጥገና መስመሮች 54.5 ኪ/ሜ ድንገተኛ (Emergency) መንገድ መጠገንና 10 የፈረሱ ስትራክቸሮች መልሶ መገንባት በድምሩ በሁሉም የመንገድ ጥገና ዘርፎች በ501 የጥገና መስመሮች 16,410.62 ኪ/ሜ የመንገድ ጥገና ስራ ታቅዷል፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ቀደም ሲል በተገነቡ የአስፓልትና ጠጠር መንገዶች ጥገና በ32 ፕሮጀክቶች 3,362.26 ኪ/ሜ ታቅዷል፡፡ በጥቅሉ በሁሉም የመንገድ ጥገና ዘርፎች በ1,119 የጥገና መስመሮች በዓመቱ 19,772.88 ኪ/ሜ መንገድ ለመጠገን ታቅዶ በመንገድ ፈንድ የበጀት ድጋፍ በገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በ6ቱ የጥገና ጽ/ቤቶች 2,943.67 ኪ/ሜ (102.7%)፤ በገጠር ትስስር ፕሮግራም 411 ኪ/ሜ (93.4%)፣ በወረዳ በጀትና በህብረተሰብ ተሳትፎ 5,726.74 ኪ/ሜ (በማሽን 1,075.3 ኪ.ሜ፣ በሰው ሃይል 4651.4 ኪ.ሜ) ወይም 106.3% መንገድ መጠገን ተችሏል፡፡ ሌላው ቀደም ሲል በተገነቡ የፌደራል አስፓልትና የጠጠር መንገዶች በበጀት ዓመቱ 3,362.26 ኪ/ሜ የመንገድ ጥገና ታቅዶ 1,183.05 (86.43%) መጠገን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በሁሉም የመንገድ ጥገና ዘርፎች 8,453.78 ኪ/ሜ መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 8,550.26 ኪ/ሜ (101%) መንገድ ተጠግኖ ለአገልግሎት ክፍት የተደረገ ሲሆን በክረምቱ ምክንያት የተፈጠሩ የመንገድ መንሸራተት፣ መዘጋት፣ ድልድዮችና ስትራክቸሮች ጉዳቶች የመልሶ ግንባታ ተግባራቶችን ከሚመለከታቸው አካል ጋር በትብብር መስራት መቻሉ የጥገና ስራው ዉጤታማ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በመደበኛነት የክልሉ መንግስት ለመንገድ መሰረተ ልማት ስራዎች ከሚመድበው በተጨማሪ በ2018 በጀት ዓመት ብር 2,063,989,750 በጥሬ ገንዘብ በጀት ማስመደብና ሃብት በማሰባሰብ ለመንገድ ግንባታና ጥገና ማዋል፡፡** በሌላ በኩል ሁሉም ዞኖች ባሏቸው ወረዳዎች ተመስርተው ለመንገድ መሰረተ ልማት ዘርፉ ግቦች ተፈጻሚነት በጥሬ ገንዘብ በጀት እንዲይዙ የተደረገ ሲሆን ህብረተሰቡ በጥሬ ገንዘብ፣ በጉልበትና በአይነት ተሳታፊ እንዲሆን በትኩረት ተይዞ እየተፈጸመ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለአዲስ መንገድ ግንባታ በጥሬ ገንዘብ ብር 1,319,478,038፣ ለመንገድ ጥገና በጥሬ ገንዘብ ብር 804,000,000፣ በየአካባቢው ህብረተሰብ በጉልበትና በአይነት የሚያደርገውን ተሳትፎ በገንዘብ ሲገመት ብር 158,400,000 በድምሩ ብር 2,281,878,038 ለማሰባሰብ ታቅዶ በተግባር አፈጻጸም ሂደት ብር 949,584,058 ሃብት ለማስመደብና ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 1,886,692,505 ከዕቅድ በላይ በ134 ወረዳዎች የጥሬ ገንዘብ ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት በጀት ድጋፍ ድርሻ ብር 1,406,650,774 (74.56%) እንዲሁም የህብረተሰብ ተሳትፎ ድርሻ ብር 480,041,731 (25.44%) መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህን የወረዳና የህዝብ አቅም ወደ ስራ በማስገባት 204 ኪ/ሜ የቅየሳ፤ 153 ኪ/ሜ የምንጣሮና ጠረጋ፣ የአፈር ቆረጣና ድልዳሎ 150 ኪ/ሜ፣ የጠጠር ልባስ 96.94 ኪ/ሜ፣ 42 ቦታ የቱቦ ቀበራ የተሰራ ሲሆን በጥቅሉ በዋትድ አቬሬጅ 116 ኪ/ሜ (83%) በ34 ፕሮጀክቶች መንገድ መገንባት ማቻሉ እና በማሽን 1075.32 ኪ/ሜ፤ በሰው ኃይል 4,651.42 ኪ/ሜ በድምሩ 5,726.74 ኪ/ሜ (103%) የመንገድ ጥገና ስራ ተሰርቷል። የህብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት ስሜት በእጅጉ የሚደነቅና የሚበረታታ ሲሆን በዚህም በስራው የተሳተፈ የሰው ሃይል 546,060 (ወንድ 377,976 ሴት 168,084) ሲሆን ከጥሬ ገንዘብ ማሰባሰብ ውጭ የህዝቡ ጉልበት ወደ ገንዘብ ሲለወጥ አፈጻጸሙ ብር 178,600,411.34 ስራ ላይ ውሏል።

**በሁሉም የመንገድ ግንባታና ጥገና ዘርፍ ፕሮጀክቶች የዜጎች ተሳትፎን የሚያረጋግጡ የስራ ዕድል ፈጠራ፣ የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ**። በበጀት ዓመቱ ለ 105,898 (ወንድ 83,045 ሴት 22,853) በ6 ወሩ 34,443 ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ40,622 (ወንድ 17,809፣ ሴት 11,377) ለሚሆኑ ዜጎች ከዕቅድ በላይ የስራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2,503 (ወንድ 1,827፣ ሴት 676) ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠር መፍጠር ተችሏል።

**የተለያዩ የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችን ቁጥር ከ249 ወደ 262 ማሳደግ**፤የደብረማርቆስ አዲስ መናሕሪያ ግንባታ  እስከ 2017 መጨረሻ ድረስ 16.28% ደርሶ የነበር ሲሆን በሩብ ዓመቱ 30% ለማድረስ ታቅዶ 17.96 (59.86%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ከመናኸሪያ የዉስጥ ገቢ፣ ከመዘጋጃ ቤት፣ ከህዝብ ተሳትፎና ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ሃብት በማሰባሰብ 5 አዲስ ደረጃ ሶስት መናኸሪያዎችን ለመገንባት ታቅዶ ሰሜን ሸዋ 4 መናህሪያ አዊ ዞን 1 በድምሩ 5 መናህሪያዎች ለመገንባት በጀት ተመድቦ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የተመደበ ገንዘብ በተመለከተ ከመናህሪያ የዉስጥ ገቢ 642,059፣ ከመዘጋጃቤት /ከወረዳ ም/ቤት ብር 19,589,000 እና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብር 30,000 በድምሩ ብር 20,261,059 ሲሆን ብር 1,695,634 ስራ ላይ ማዋል ተችሏል። የእንጅባራ ከተማ አዲስ ትራፊክ ኮምፕሌክስ ግንባታን  በ2018 በጀት አመት 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 30% በማከናወን 53.33% ለማከናወን ተችሏል። በተመሳሳይ የደሴ እና የደብረብረሃን ትራፊክ ኮምፕሌክስ የአጥር፣ የጥበቃ ቤት እና መዝግብ ቤት ግንባታ 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ ግንባታዉ 100% በማጠናቀቅ ጊዚያዉ ርክክብ ተፈጽሟል። ከኮሪድር ልማቱ ጋር በተያያዘ ባበህር ዳር ከተማ ከአባይ ምንጭ ሆቴል እስከ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባህር ዳር ቅርንጫፍ መ/ቤት ባለዉ መንገድ 4(50%) አነስተኛ Off road parking ለምቶ አገልግሎት እየሠጡ ሲሆን  የጎንደር እና የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደሮች ለገዟቸዉ አዉቶቢሶች የሚጠቀሙበት የኤሌትሪክ ቻርጅ ማድረጊያ መሳሪያ ገጥመዉ ስራ ላይ አዉለዋል።  የደብረብረሃን

ከተማ አስተዳደር 2.6 ሄክታር የሚሸፍን ቦታ የሳይት ፕላን በማሰራት ከቦታዉ ለሚነሱ አርሶአደሮች የካሳ ክፍያ የጀመረ ሲሆን የካሳ ክፍያዉ ሲጠናቀቅ የተመደበዉን ብር 37 ሚሊዮን የአጥር፣ የጥበቃ ቤትና የአፈር ድልዳሎ ስራ የሚጀመር ሲሆን የደሴ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርትና ሎጅሲቲክስ ጽ/ቤት 1.2557 ሄክታር መሬት አስፈቅዶ ካርታና ፕላን ለማሰራት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ ሌላዉ የወልቃይት ጠገዴ ሴቲቱ ሁመራ ዞን በሴቲቱ ሁመራ ከተማ 4 ሄክታር መሬት ካርታና ፕላን በማሰራት በጀት በማፈላልግ ላይ ይገኛል፡፡

**የነባር አውሮፕላን ማረፊያዎች ደረጃቸው እንዲያድግ ከፌደራል መንግስት ጋር በትብብር መስራት፤**

የደብረማርቆስ ኤርፖርት ግንባታ ጥር 2014 ዓ.ም ተጀምሮ ሰኔ 2017 ዓ.ም ለማጠናቀቅ በእቅድ ቢያዝም በክልሉ በተፈጠረዉ የጸጥታ ችግር ምክንያት ግንባታዉን ከሚያከናወነዉ ድርጅት ውሉ አቋርጦ ለሌላ የተሻለ የስራ ተቋራጭ ድርጅት ተሰጥቶ በአሁኑ ወቅት ግንባታዉ 62% ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ የባህርዳር አለም አቀፍ ኤርፖርት አዲስ የመንገደኞች ማስተናገጃ ግንባታው በ2014 ዓ.ም ተጀምሮ ነሃሴ 2017 ለማጠናቀቅ በእቅድ ቢያዝም በስራ ተቋራጩ የአፈጻጸም ድክመት እና የግንባታ ቁሳቁሶች የመዘግየት ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት በአሁኑ ወቅት 65.57% የደረሰ ሲሆን የባህርዳር አለም አቀፍ ኤርፖርት የአዉሮፕላን መንደርደሪያ ሜዳ ጥገና እና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት 100% ተጠናቋል፡፡ በተመሳሳይ የኮምቦልቻ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ፡-አዲስ የመንገደኞች ማስተናገጃ ህንጻ፤ የቪአይፒ እና ተያያዥ ግንባታዎች 100% ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን የኮምቦልቻ ኤርፖርት የአዉሮፕላን መንደርደሪያ ሜዳ ጥገና እና ተያያዥ ስራዎች ፕሮጀክት በህዳር 2018 ዓ.ም ለማጠናቀቅ በእቅድ ቢያዝም በአብዛኛዉ በተቋራጩ ችግር ምክንያት ስራዉ ተጓቶ አሁን ላይ ግንባታዉ 37% ይገኛል፡፡ ሌሎች ነባር ኤርፖርቶች አገልግሎት ለማስጀመር የሁመራ፤ ደ/ታቦር፤ መካነሰላም እና ቻግኒ ነባር ኤየርፖርቶች አገልግሎት እንዲጀምሩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር፣ ክትትልና ድጋፍ በመደረግ ላይ ሲሆን ለ5 አመት ያህል አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየዉ የሁመራ ኤርፖርት በጥቅምት ወር 2018 ዓ.ም አገልግሎት እንዲጀምር ተደርጓል፡፡

**የውሃ የብልሽት ምጣኔን ከ11.55 በመቶ ወደ 11.4 በመቶ እንዲሁም የውሃ ብክነትን ከ22.63 በመቶ ወደ 21.80 በመቶ በመቀነስ አዳዲሶችን የውሃ ተቋማትን በመገንባት የክልሉን የመጠጥ ውሃ ሽፋንን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 77.25 በመቶ በ2018 በጀት ዓመት ወደ 80.44 በመቶ ማሳደግ በተመለከተ፡** 10,825 የዉኃ ተቋማት ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 10,824 የዉሃ ተቋማት ጥገና በማድረግ አፈጻጸሙን 100% ሲሆን የብልሽት ምጣኔዉን 0.5% ለመቀነስ ታቅዶ

0.6% ፐርሰት በማከናወን አፈጻጸሙ 100% መፈጸም ተችሏል። እንዲሁም 0.06% የዉኃ ብክነት ለመቀነስ ታቅዶ 0.44% በማከናወን ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል። እንደ ክልል የንጽህ መጠጥ ዉሀ ሽፋኑን 0.25% በማሳደግ የክልልሉን የመጠጥ ዉኃ ሽፋን ወደ 77.5 % ለማድረስ ታቅዶ 0.59% ሽፋን በመጨመር የክልሉን የመጠጥ ዉኃ ሽፋን **78.09 %** ማድረስ ተችሏል።

**በ2018 በጀት ዓመት 299 የተለያዩ ግንባታዎች በመገንባት የከተማን ስነ-ንጽህና ማሳደግ በተመለከተ፡-** በበጀት ዓመቱ 32 (ሰላሳ ሁለት) የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ በማከናወን በበጀት አመቱ በ2017 መጨረሻ ከተሰደረሰበት 7.33% በመነሳት አማካይ አፈጻጸማቸውን 34.22% ለማድረስ ታቅዶ 15.78% በማድረስ አማካይ አፈጻጸሙን 23.11% በማድረስ (46%) ማከናወን ተችሏል። በሌላ በኩል 2 የመለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ለማከናወን ታቅዶ የሀለቱም ቁፋሮ ስራ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። (ቅላጅ 1 እና ቅላጅ 2) እንዲሁም 366 አነስተኛ መጠጥ ዉኃ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 236 አነስተኛ የመጠጥ ዉኃ ግንባታ በማጠናቀቅ አፈጻጸሙ 64.48% ሲሆን 2018 በጀት አመት የሚጠናቀቁ 8 የገጠር የቀበሌ አገናኝ የመጠጥ ዉኃ ፕሮጀክቶችን ግንባታ በ2017 ዓ.ም ከተደረሰበት 87.02% በመነሳት በ2018 በጀት ዓመት 12.98% በማከናወን 100% ለማድረስ ታቅዶ 4.74% በማከናወን አማካይ አፈጻጸሙን 91.76% በማድረስ (36%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ጭርለባ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

**የጋራ መጸዳጃ ቤት ግንባታ፡-** በዓለም ባንክ የበጀት ድጋፍ በደሴ ከተማ 5 ነባር የጋራ መጸዳጃ ቤት ግንባታ በ2017 ከደረሱበት 80% አማካይ አአፈፃፀም በመነሳት 20% በመስራት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 100% ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ተችሏል። 7 የህዝብ መጸዳጃ ቤት ግንባታ እስከዚህ ሩብ ዓመት በአማካይ 30% ለማከናወን ታቅዶ 30% በማከናወን አማካይ አፈጻጸሙ 100 % ለማድረስ ታቅዶ l100% ማድረስ ተችሏል። 32 ነባር የተሸሻሉ የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታ 25% ለማከናወን ታቅዶ 25% ማከናወን ተቻለ ሲሆን አማካይ አፈጻጸሙ 100% ማድረስ ተችሏል። 23 አዲስ ጋራ መጸዳጃ ቤት ግንባታ በአማካይ 10% ለማከናወን ታቅዶ 10% በማከናወን አማካይ አፈጻጸሙ 100% ማድረስ ተችሏል። 8 አዲስ ህዝብ መጸዳጃ ቤት ግንባታ በአማካይ 30% ለማከናወን ታቅዶ 30% ማከናወን የተቻለ ሲሆን አማካይ አፈጻጸሙ 100% ማድረስ ተችሏል። ጎንደር፣ደሴ እና ደብረብርኃን የፍሳሽ ማጣሪያ ግንባታ 21.15% በማከናወን እስከዚህ ሩብ ዓመት 3.2 %፤ አረርቲ እና እንጅባራ የፍሳሽ ማጣሪ ግንባታ በአማካይ 30% ለማከናወን ታቅዶ 9.7 % በማከናወን አማካይ አፈጻጸም 32.5 % ማድረስ ተችሏል። በዓለም ባንክ የዉኃ ብክነት ቅነሳ 10% ለማከናወን ታቅዶ 15% በማከናወን ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል።

በክልሉ ታዳራሽ የኃይል አቅርቦትና ሽፋንን በ2017 በጀት ዓመት ከነበረበት 8.39 ሜ.ጋ ዋት ወደ 10.29 ሜ.ጋ ዋት ማሳደግ፤ በክልሉ ታዳሽ የኃይል አቅርቦትና ሽፋንን 0.299 ሜጋ ዋት የሃይል አቅርቦት ሽፋን ለማሳደግ ታቅዶ 0.49 ሜጋ ዋት በመጨመር ወደ 8.53 ሜጋ ዋት በማድረስ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 225,000 የታዳሽ ኃይል ምንጮች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 310,525 በማዳረስ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም 30,000 የኤሌክትሪክ ምጣድ እና ምድጃ ለማሰራጨት ታቅዶ 49,105 በማሰራጨት 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

27,500 ሶላር ማሾ ስርጭት ለማከናወን ታቅዶ 36,416 በማከናወን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም 17,500 የሶላር ሆም ለማሰራጨት ታቅዶ 25,089 በማከናወን 100% መፈጸም ተችሏል፡፡ ሌላው በቤተሰብ እና በተቋማት ደረጃ የባዮ-ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በሩብ ዓመቱ 375 የቤተሰብ ባዮ-ጋዝ ቴክኖሎጂዎች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 175 (46.6%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህም 880 የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሩብ አመት 375 የቤተሰብ ባዮ-ጋዝ ቴክኖሎጂዎች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 7 (1.87%) በማከናወን 35 የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በበጀት ዓመቱ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታን በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 6,148 ወደ 6,325 በማሳደግ የሚለማውን መሬት ከ260,269 ሄ/ር ወደ 297,959.7 ሄ/ር ማድረስ፡-** በመሆኑም በ2017 በጀት ዓመት ከተደረሰበት አማካኝ አፈፃፀም 66.90% ላይ 25.37% በመፈጸም ወደ 92.27% ለማድረስ ታቅዶ ከ41 ፕሮጀክቶች ውስጥ በበጀት ዓመቱ 39,730 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 27 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 900 ሄ/ር የሚያለሙ ሁለት ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ የ41 ፕሮጀክቶችን አማካይ አፈፃፀም 2.5% በመጨመር 69.4% ለማድረስ ታቅዶ 68.83% (77.2%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 77,234.93 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችልና 496,550 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ 120 የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶችን ከነበሩበት አማካይ አፈፃጸም 22.88% ወደ 97.36% ለማድረስ ታቅዶ 33.56% በማከናወን አማካይ አፈፃፀማቸዉን 56.44% ማድረስ ተችሏል፡፡፡ በበጀት ዓመቱ 44,437.93 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችልና 267,775 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 106 የመስኖ ፕሮጀክቶችን የጥናትና ዲዛይን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 1,389 ሄ/ር የሚያለሙ 15 የመስኖ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዱዚይን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 22,542.88 ሄ/ር የሚያለሙና 42,789 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ 135 (88 ነባርና 47 አዱስ) የመስኖ ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ በማስገባት በ2017 መጨረሻ ከነበሩበት አማካይ አፈፃፀም 29.11% በመነሳት በበጀት ዓመቱ አማካይ አፈፃፀሙን ወደ 79.49% ለማድረስ ታቅዶ አማካይ አፈፃፀሙን 41.5% ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 6044 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 88 የመስኖ ፕሮጀክቶችን ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 563.48 ሄ/ር የሚያለሙና 2239

አባወራወችና እማወራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 16 (13 በሴፍቲኔት፤ 2 በአፍርካ ልማት ባንክ እና 1 በዘላቂ ሌማት ባንክ) የመስኖ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል።

የግንባታ ፕሮጀክቶች የስራ እንቅስቃሴ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ወደ ግንባታ ከመግባት አንፃር በ2017 በጀት ዓመት ከ308 ፕሮጀክቶች ውስጥ 55 ፕሮጀክቶች ወደ ስራ የገቡ ሲሆን 8 የመስኖ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ ልማት መስገባት የተቻለ ሲሆን በዚህ በጀት ዓመት ደግሞ 68 ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ የገቡ ሲሆን 16 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል። በ2017 በጀት ዓመት 21 የመስኖ ፕሮጀክቶች ውላቸው ተቋርጧል።

በበጀት ዓመቱ በጀት ተይዞላቸዉ ወደ ጥገና ከገቡት 20 የጥገና ፕሮጀክቶች ዉስጥ 1315 ሄ/ር የሚያለሙ 13 የመስኖ ፕሮጀክቶች ጥገና በ2017 በጀት ዓመት ከደረሱበት አማካይ አፈፃፀም 34.1% በመነሳት 72.9% ለማድረስ ታቅዶ አማካይ አፈፃፀሙን 58.52% ማድረስ ተችሏል።

በፌደራል መንግስት በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አማካኝነት ጥናትና ዲዛይን እየተካሄደ ሲሆን 146,500 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 5 ሜጋ የመስኖ ፕሮጀክቶችን (ሽንፋ፣ አንገረብ፣ አይማ፣ መቻላ እና ተሊ) በተመለከተ አይማ በፀጥታ ችግር ምክንያት ሰራው የቆመ ቢሆንም ሌሎች ሽንፋ 100 በመቶ፣ አንገረብ 43 በመቶ፣ መቻላ 98 በመቶ እና ተሊ 90 በመቶ፣ አይማ 17.5 በመቶ ማድረስ ተችሏል:: በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ 32,090 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 5 ሜጋ ፕሮጀክቶችን (መገጭ ግደብ፣ ላይኛው ርብ፣ ታችኛወ ርብ፣ አጅማ ጫጫ እና ጣና በለስ) በተመለከተ ከዚህ በፊት ከፍተኛ መጓተት የነበረበት የመገጭ ግድብ የነበሩ ችግሮች ተቀርፈው ከዚህ በፊት በውል ያልነበረ የመስኖ አውታር ዝርጋታውን ጨምሮ አበረታች አፈፃፀም ላይ ይገኛል:: በመሆኑም ፕሮጀክቶች የደረሱበት ደረጃ ሲታይ መገጭ ግድብ 77.9 በመቶ ማከናወን ተችሏል:: አጅማ ጫጫ በተመለከተ ምንም እንኳን በፀጥታው፣ በካሳ ክፍያ እና በተቋራጩ የመፈፀም ውስንነት በእቅዱ መሰረት መፈፀም ባይቻልም የተሻለ እንቅስቃሴ ያለው ሲሆን ሎት 1 (40.5%)፣ ሎት 2 (33.27%) እና ሎት 3 (66.8%) ማድረስ ተችሏል:: ታችኛው ርብ ፕሮጀክቱን ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 98 በመቶ ማድረስ ተችሏል:: ታችኛዉ ርብ በጠቅላላዉ 1,601 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችል ስራ በማጠናቀቅ የመጀመሪያ ዙር ርክክብ በማደረግ ወደ ልማት ማስገባት ተችሏል።

**የትምህርት ቤቶች ቁጥርን ማሳደግ በተመለከተ፥** አዲስ ትምህርት ቤቶች ከመገንባት አንጻር 185 አዲስ የተገነቡ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 147 (78.3%)፣ 137

አንደኛና መካከለኛ ለመገንባት ታቅዶ 53 (43.8%) እንዲሁም 23 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 15 (65.2%) የሚሆኑ ተቋማት በአዲስ ተገንብተዋል፡፡

በተጨማሪም አዲስ በተከፈቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 3,942 መማሪያ ክፍሎችን ለመገንባት ታቅዶ 3,850 (97.7%) ክፍሎች ተገንብተዋል፡፡ የመምህራን መጠለያ ክፍል 1,036 ታቅዶ 776 (74.9%) የተገነባ ሲሆን የተጎዱ ትምህርት ቤቶችንና ክፍሎችንም የመጠገን ስራ ለመስራት በአንደኛና መካከለኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት 4,455 ተቋማት ለመጠገን ታቅዶ 4,291 (96.32%)፣ 11,363 መማሪያ ክፍሎችን ለመጠገን ታቅዶ 13,242 (100%) ክፍሎች፣ አስተዳደር ክፍል 2,526 ታቅዶ 2,446 (96.8%)፣ የመምህራን መጠለያ ክፍል 3,569 ታቅዶ 4,321 (100%) የሚሆኑትን መሰረተ ልማቶችን መጠገን ተችሏል፡፡

**በትምህርት ቤቶች የትምህርት ፋሲሊቲ ማሟላት፡-** አዲስ መጸዳጃ ቤት 1,108 ለመገንባት ታቅዶ 493 (44.49%)፣ ቤተመጽሃፍት ክፍል 424 ታቅዶ 147 (34.6%)፣ ቤተሙከራ ክፍል 486 ታቅዶ 88 (18.1%) የተገነባ ሲሆን ቤተ-መጽሃፍት ክፍል 1,039 ታቅዶ 989 (95.2%)፣ ቤተ-ሙከራ ክፍል 1,521 ታቅዶ 1,379 (90.6%)፣ 3,453 ትምህርት ቤቶች የመጠጥ ውሃ ጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ 939 (27.2%)፣ በ2,689 መጸዳጃ ቤቶች ለመጠገን ታቅዶ 2,319 (86.24%) የጥገና ስራ ማከናወን ተችሏል፡፡

**በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ምቹ የትምህርትና ስልጠና አካባቢ መፍጠር፡-** የቤተ ሙከራዎችን አጠቃቀም አስመልክቶ የተሟላ የሣይንስ ቤተሙከራ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ኮሌጆች ብዛት በመቶኛ 40% ይሆናሉ ተብሎ ግብ የተጣለ ሲሆን የሰባቱ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ቅድመ ዝግጅት ተወስዶ ሲታይ የተሟላ የሣይንስ ቤተሙከራ አገልግሎት መስጠት የተጀመረ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የተሟላ የአይሲቲ ማዕከላት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ኮሌጆች ብዛት በመቶኛ 40% ለማድረስ ታቅዶ በስድስቱ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የተሟላ የአይሲቲ ማዕከላት መኖራቸውና በአንጻራዊነት የተሻለ አገልግሎት እየተሰጠ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በእነዚህ ኮሌጆች ለሠልጣኞች በቂ የአይሲቲ ማዕከላት የሚያገኙ ሲሆን በማዕከሉ ተገቢ ቁሳቁሶች የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የመረጃ ሥርዓታቸውን ዲጅታል ያደረጉ ኮሌጆች 50.0% ለማድረስ ታቅዶ 50.0% የደረሰ ሲሆን ይህም አፈጻጸም 100% ነው፡፡ የተማሪ መረጃ ሥርዓታቸውን ዲጅታል ያደረጉ ኮሌጆች 3.0% ለማድረስ ታቅዶ 90% የደረሰ ሲሆን ይህም አፈጻጸም 100% ነው፡፡ የብሮድባንድ ኢንተርኔት

ተጠቃሚ የሆኑ ኮሌጆች 20% ለማድረስ ታቅዶ 100% የደረሰ ሲሆን ይህም አፈጻጸም 100% ነው፡፡ ዲጂታል ቤተ-መፅሐፍት ተጠቃሚ የሆኑ ኮሌጆች 10% ለማድረስ ታቅዶ 100% የደረሰ ሲሆን ይህም አፈጻጸም 100% ነው፡፡ ቤተ-መፅሐፍታቸውን ኦቶሜት ያደረጉ ኮሌጆች 5.0% ለማድረስ ታቅዶ 50% የደረሰ ሲሆን ይህም አፈጻጸም 100% ነው፡፡ የተለያዩ መተግበሪያዎችን መጠቀም የቻሉ ኮሌጆች 10% ለማድረስ ታቅዶ 10% የደረሰ ሲሆን ይህም አፈጻጸም 100% ነው፡፡

በሁሉም ኮሌጆች የተሰሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ድምር 75 እንደሚደርስ ክልላዊ እቅድ የታቀደ ሲሆን ከሁሉም ኮሌጆች ከተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ የተቻለው 268(165 መሰረታዊ፣ 103 ድርጊታዊ) የምርምር ሥራዎች የጥናት ፕሮፖዛላቸው ጸድቆ ወደሥራ የገቡ መሆኑን ነው፡፡

**በሁለተኛው ሩብ አመት የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች፦** ቢሮው በተለያዩ ጊዜ ካስጀመራቸው በርካታ ግንባታዎች አብዛኞቹ የተጠናቀቁ ሲሆን በሁለተኛ ሩብ ዓመት 17 ግንባታዎች ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የሁሉንም ፕሮጀክቶች (218) የሰድስት ወር አማካይ የግንባታ ሂደት አፈጻጸም 4.45% ሲሆን አሁንም ግንባታዎች በተያዘለቸው የጊዜ ቀጠሮ ባለመጠናቀቃቸው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡

**የትልልቅ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም፦** ባለፈው ስድስት ወር በርከታ ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ቢሆንም 22 የትልልቅ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በአማካይ 1.27% ብቻ ነው የተከናወነው፡፡ይህ የግንበታ ፍጥነት የተለየ ከትትል ካልተደረገ በተያዘው በጀት አመት ለማጠናቀቅ ፈታኝ ይሆናል፡፡ በአንጻራዊነት የአዕምሮ ማገገሚያ ማዕከላትና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ግንበታ ሂደት አፈጻጸሙ ዝቀተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በከተሞች ደረጃውን የጠበቀ 15 የገበያ ማዕከላትና 2,032 የመስሪያና የመሸጫ ሼድ በመገንባት በድምሩ በቁጥር በ2016 ከነበረበት 20,456 በ2018 ወደ 22,503 ማሳደግ፤ ዘመናዊ የገበያ መሠረተ-ልማት እና የመረጃ ስርዓትን በመዘርጋት የንግድ ስርዓቱ በቴክኖሎጅ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ በተመለከተ፡- 297 የኦንላይን አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን በማጠናከርና በማስፋፋት የንግድ ተቋሙን አሰራር በማዘመን አገልግሎቱን ለማሳለጥ ታቅዶ 297 (100%) ጣቢያዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል 384 የነዳጅ ማደያዎች የአሰራር ስርዓቱን ተከትለው በቴሌና ሲኢቢ ብር የሽያጭ አገልግሎት እንዲሰጡ አሰራራቸውን ለመደገፍና ለማጠናከር ታቅዶ 384 (100%) ዋይፋ በማስገባት ጭምር አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ እንዲሁም በ8ቱ ሪጅኦፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች አምራችና ሸማችን ለማገናኘት በተገነቡ ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት

ላይ የግብይት ስርዓቱን ለማዘመን ያስችል ዘንድ LED display/ የወቅታዊ ዋጋ መረጃ ማሳያ/ ስክሪን ለማስገባት 2 ለማስገባት ታቅዶ 8(100%) በግዥ ሂደት ላይ ናቸው፡፡

የመስሪያና የመሸጫ ሸድ አቅርቦት በተመለከተ፡- በከተማና በገጠር የቦታ አቅርቦት 7,216 ሄ/ር መሬት፣ ለ7,216 ኢንተርፕራይዞች፣ ለ46,672 አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ፡- በከተማ 1,208.0161 (25.17%)፣ በገጠር 11,992.5737 (90.58%) በድምሩ 13,200.5898 (100%) ሄክታር ቦታ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም 8,291 (100%) ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 43,147 ሴት 23,748 በድምሩ 66,895 (100%) አንቀሳቃሾች) በተዘጋጀው መሬት ተጠቃሚ ለማድረግ በተዘጋጀው ቦታ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው በከተማ 509.915 (100%) በገጠር 7,188.2523 (59.94%) ሲሆን በድምሩ 7,698.1677 (58.32%) ሄክታር ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በከተማና በገጠር 1,040 ሼዶችን በመገንባት 4,160 ኢንተርፕራይዞችን እና 16,640 አንቀሳቃሾችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ፡- 826 ሼዶች ተጠናቀው 819 ሼዶች ለ3,766 (90.53%) ኢንተርፕራይዞች፣ 9,926 (59.65%) (ወንድ 5,461 ሴት 4,465 አንቀሳቃሾች) ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡

# ክፍል ስድስት፡ ስርዓታትና ልማት

## 6.1. የዳኝነትና የፍትህ ዘርፍ

**ፍትሐዊ እና ተገማች የህግ አወጣጥ ስርዓት መዘርጋት፤** በጥናት ላይ በመመስረት እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ አዳዲስ እና ነባር ህግጋትን የማሻሻል ስራ መስራትን በተመለከተ 100% ታቅዶ የተቋማት አመራሮችን፣ የምክር ቤት አባላትን፣ ፕላንና ልማት ቢሮንና የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ለቢሮው እንዲሰሩ ከመጡ 80 (አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ) ረቂቆች ውስጥ 80 (100%) የተዘጋጁ ሲሆን የሚሻሻሉ፣ የሚረቀቁ እና የሚወጡ ህግጋት ጥራት ምጣኔን 100% ለማድረስ ታቅዶ ሁሉንም የቀረቡ ህጎችን በጥራት መስራት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ስራቸውን በህግ መሰረት ስለማከናወናቸው ክትትል የተደረገላቸው የክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላት 2 ለመከታተል ታቅዶ 19 (100%) ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የቀረቡ የህግ ረቂቆች ከህገ-መንግስቱም ሆነ ከክልልና ከፌዴራል መንግስት ህግጋት ጋር መጣጣማቸውን 100% ለማረጋገጥ ታቅዶ ሁሉም የተዘጋጁ የህግ ረቂቆች ከህገ መንግስቱ ጋር መጣጣማቸው እየተረጋገጠ ስለተሰሩ አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

በህግ ጉዳዮች ላይ የህግ ምክር ለቀረቡት ለክልሉ መንግስት ተቋማት 100% ለመስጠት ታቅዶ የቀረቡ 2(100%)ጉዳዮች ላይ የህግ ምክር መስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በአስተዳደር ተቋማት

የሚወጡ መመሪያዎችን ህጋዊነት በመመርመር ምዝገባ ማካሄድ እና ዌብሳይት ላይ 100% ለመጫን ታቅዶ 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ አዳዲስ ህጎችን ለሚመለከቸዉ አካላት 60% ለማስተዋወቅ ታቅዶ የወጡ 6 አዋጆችን የማስተዋወቅ ስራ በመሰራቱ አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

**በዘርፉ ተቋማት ሙያዊ ነፃነት፣ ገለልተኝነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ**፤የስነ-ምግባር ጉድለት የታየባቸው ፈፃሚዎችን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ 100% ተጠያቂ ለማድረግ ታቅዶ ለዐቃቤ ህግ ከቀረቡት 50 የዲሲፕሊን ጉዳዮች ዉስጥ ዐቃቤ ህግ በ50ዎቹ ላይ ዉሳኔ በመስጠት አፈጻጸሙን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በዐቃብያነ ህግ ዋና ጉባኤ 13 ጉዳዮች በክርክር ላይ የነበሩ ሲሆን በ13ቱም ላይ ዉሳኔ በመስጠት አፈጻጸሙን 100 % ደርሷል፡፡ **የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውጤታማነትን ማረጋገጥ፡-** የክልሉን የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋን 75% በማድረስ ተጨማሪ ቀበሌዎች ላይ በማስፋት ወንጀልን ለመቀነስ ታቅዶ በክልሉ ካሉ 4,136 ቀበሌዎች መካከል በኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ የተሸፈኑ ቀበሌዎች 1,051 (25.4%) ብቻ ሲሆኑ 3,085 (74.6%) የሚሆኑት ቀበሌዎች ደግሞ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ የላቸውም፡፡

**አጠቃላይና እና ዋና ዋና ወንጀልን በተመለከተ፡-** አጠቃላይ ወንጀልን ባለፈዉ ዓመት ከተከሰተው በገጠር በ23% እና በከተማ በ27% ለመቀነስ ታቅዶ በ2017 ተመሳሳይ ወቅት በገጠር 1714፣ በከተማ 3,208 በድምሩ 4,922 ወንጀል የተፈፀመ ሲሆን በ2018 2ኛ ሩብ ዓመት በገጠር 2,753 በከተማ 4,850 በድምሩ 7,603 ወንጀል ተፈፅሟል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሩብ ዓመት የተፈፀመው አጠቃላይ ወንጀል ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በገጠር 1039 (60%) እንዲሁም በከተማ 1642 (51.18%) አጠቃላይ ወንጀል ጨምሯል፡፡ በተመሳሳይ ዋና ዋና ወንጀል ከባለፈው ዓመት ከተከሰተው በገጠር በ27% እና በከተማ በ33% ለመቀነስ ታቅዶ በ2017 በ2ኛዉ ሩብ ዓመት በገጠር 881፣ በከተማ 1223 በድምሩ 2,104 ወንጀል የተፈፀመ ሲሆን በ2018 2ኛ ሩብ ዓመት ደግሞ በገጠር 1568፣ በከተማ 1923 በድምሩ 3,491 ዋና ዋና ወንጀሎች የተፈፀሙ ሲሆን የተፈፀመው ዋና ዋና ወንጀል ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በገጠር 687(77.98%) እንዲሁም በከተማ 700 (57.23%) ዋና ዋና ወንጀል ጨምሯል፡፡

**የወንጀል ምርመራ** አፈፃፀም፡- በልዩ ልዩ ወንጀሎች ምርመራ የማጣራት አቅምን 56% ለመፈፀም ታቅዶ የቀረበ የወንጀል ጥቆማ ብዛት 8,877 ሲሆን ለአቃቢ ህግ የተላከ 6,609፣ በፖሊስ እጅ ያለ 1964 እና በልዩ ልዩ ምክንያት የተቋረጠ 304 በመሆኑ አፈፃፀሙ 77% ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በልዩ ልዩ ወንጀሎች የቀረቡ የወንጀል ጥቆማዎች ምርመራ ጥራት 56% ለማድረስ ታቅዶ ለዓቃቢ

ህግ ከተላከዉ 6,609 የምርመራ መዝገቦች ውስጥ በጥራት ጉድለት የተመለሰ መዝገብ 164 ሲሆን አፈፃፀሙ 97.5% ነው፡፡

**ሌላው በሙስና ወንጀል የቀረቡ የወንጀል ጥቆማዎች የማጣራት አቅምን 56% ለማድረስ ታቅዶ** ጠቅላላ የቀረበ የሙስና ወንጀል ጥቆማ ብዛት 709 ሲሆን ለአቃቢ ህግ የተላከ 354፣ በፖሊስ እጅ ያለ 175 ሲሆን አፈፃፀሙም 75.31% ነው፡፡ በተጨማሪም በሙስና ወንጀሎች የቀረቡ የወንጀል ጥቆማዎች ምርመራ ጥራት 56% ለማድረስ ታቅዶ ለዓቃቢ ህግ ከተላከው 534 የምርመራ መዝገቦች ውስጥ በጥራት ጉድለት የተመለሰ መዝገብ 79 በመሆኑ 85.2% መፈፀም ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ የፎረንሲክ ምርመራ አቅምን 56% ለማድረስ ታቅዶ ከቀረቡ 5909 ተመርማሪ ሰነዶችና ናሙናዎች ውስጥ 3041 ምርመራ ውጤታቸው ተጠናቆ ለፍትህና ለሚመለከተው አካል የተላኩ ሲሆን 51.46% መፈፀም ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፎረንሲክ ምርመራ ጥራትን 100% ለማድረስ ታቅዶ የምርመራ ውጤታቸው ተጠናቆ ከተላኩ 3041 ተመርማሪዎች በነጥብ የተመለሰ ባለመኖሩ የፎረንሲክ የምርመራ ጥራቱ 100% ሆኗል፡፡ የወንጀል ምርመራ መዛግብት የመወሰን ቅልጥፍናን 98% ለማድረስ ታቅዶ 9,014 መዛግብት ቀርበው 8,872 መዛግብት ላይ / 98.42%/ ዐቃቤ ህግ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን 142 መዛግብት በዐ/ህግ እጅ ይገኛሉ፡፡

የክስ አይቀርብም የውሳኔ አሰጣጥ የክትትል ምጣኔን 98.5% ለማድረስ ታቅዶ 245 የቀረቡ የክስ አይቀርብም ውሳኔዎች ቀርበው በ243 ውሳኔዎች ላይ ክትትል በማድረግ አፈጻጸሙን 99.18% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የወንጀል መዛግብት የክስ አይቀርብም የውሳኔ ጥራት ምጣኔን 98.5% ለማድረስ ታቅዶ ከቀረቡት 245 መዛግብት ውስጥ 235 ውሳኔ የተሰጣቸው መዛግብትን በመመርመር 203 መዛግብት ሲጸድቁ 9 መዛግብት በመሻራቸዉ አፈፃፀሙ 95.75% ነው፡፡

በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ 10,107 መዛግብት ለፍርድ ቤት ቀርበው በፍርድ ቤት ዉሳኔ ካገኙት 3,323 መዛግብት ዉስጥ 3,133 መዛግብት /94.28%/ ማሸነፍ የተቻለ ሲሆን 190 መዛግብት ተከሳሾች በነፃ ተሰናብተዋል፡፡

የዓቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን 72% ለማድረስ ታቅዶ፤ 584 መዛግብት ለፍ/ቤት ቀርበው በፍርድ ቤት ከተወሰኑት 284 መዛግብት ዉስጥ 204 መዛግብት ማሸነፍ የተቻለ ሲሆን 80 በመሸነፍ ውሳኔ ያገኘ ሲሆን አፈፃፀሙ 71.83% ሲሆን የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን 90% ለማድረስ ታቅዶ፤ 753 መዛግብት ቀርበው በፍርድ ቤት ከተወሰኑት 753 መዛግብት ዉስጥ 699 መዛግብት ላይ በማሸነፍ

54 መዛግብት በመሸነፍ ውሳኔ ያገኘ ሲሆን አፈፃጸሙ 92.83% ነው፡፡ በሌላ በኩል በተከሳሽና ምስክር አለመቅረብ የመዛግብት መቋረጥ የማቋረጥ ምጣኔን 12% ለመቀነስ ታቅዶ ታቅዶ ለፍ/ቤት ከቀረቡ 10,107 መዛግብት ውስጥ 854 መዛግብት በማዘጋት /8%/ ተከሳሽና ምስክር ባለመቅረቡ የሚዘጉ መዛግብት ምጣኔን ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

በወንጀል ጉዳይ የተመዘበረ ሃብትን ከማስመለስ አንጻር በወንጀል ጉዳይ የተወሰደን ብር 51,934,083.57፤ መሬት ደግሞ 12,201 ካ.ሜ የከተማ ቦታ እና 17.2 ሄክታር የገጠር መሬት፤ ከውርስ 470,806,257.60 ከዋስትና 2,317,000.00 ብር ገቢ ተደርጓል፡፡ ከኤግዚቢት 109,916,954.39 ብር የሚገመት (የጦር መሳሪያ 3,292፣ ጥይት 13,596፣ የአፈር ማዳበሪያ 856.54 ኩ/ል፣ ቤንዚንና ናፍጣ 10,262 ሊትር፣ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪዎች፣ የቤት ዕቃዎች እና ሽቀጣሽቀጥ ብዛት 117፣ እህል፣ የቅባት እህል እና ቅመማቅመም 117.5 ኩ/ል፣ እንስሳት 65፣ 4 ካርቶን የሰውና እንስሳት መድሃኒት) ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡ ከወንጀል ቅጣት በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በገንዘብ መቀጮ የሚቀጡትን ገንዘብ ለመንግስት ለመሰብሰብና ለማስፈጸም የሚያስችል ወጥ የአሰራር ሥርዓት ምን መሆን እንዳለበት በፍትህ ቢሮ የተዘጋጀ ሰነድ ውይይት ተደርጎበት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በዚህ መሰረት ከወንጀል ጉዳይ ከቅጣት ብር 5,397,501.00 ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡

የክስ አይቀርብም የውሳኔ አሰጣጥ የክትትል ምጣኔን 98.5% ለማድረስ ታቅዶ 109 የቀረቡ የክስ አይቀርብም ውሳኔወች ቀርበው በ101 ውሳኔዎች ላይ ክትትል በማድረግ አፈጻጸሙን 92.6% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የወንጀል መዛግብት የክስ አይቀርብም የውሳኔ ጥራት ምጣኔን 98.5% ለማድረስ ታቅዶ ከቀረቡት 109 መዛግብት ውስጥ 101 ውሳኔ የተሰጣቸው መዛግብትን በመመርመር 98(97.02%) መዛግብት ሲጸድቁ 3 መዛግብት መሻራቸዉን ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ 7,710 መዛግብት ለፍርድ ቤት ቀርበው በፍርድ ቤት ዉሳኔ ካገኙት 2,027 መዛግብት ዉስጥ 1,879 መዛግብት / 92.70% / ማሸነፍ የተቻለ ሲሆን 148 መዛግብት ተከሳሾች ነፃ ሆነዋል፡፡

በቀረቡ የዋስትና ጥያቄዎች በወቅቱ እና በአግባቡ ያለው የዋስትና አስተያየት መስጠት ውጤታማነትን 97% ለማድረስ ታቅዶ 3,366 መዛግብት ቀርበው 3,317(98.54%) መዛግብት ላይ ዐ/ህግ በሰጠው መሰረት የተወሰነ ሲሆን የዓቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን 72% ለማድረስ ታቅዶ 325 መዛግብት ለፍ/ቤት ቀርበው በፍርድ ቤት ከተወሰኑት

107 መዛግብት ዉስጥ 72 (67.29%) መዛግብት ማሸነፍ የተቻለ ሲሆ 35 በመሸነፍ ውሳኔ አግኝቷል፡፡

በተመሳሳይ የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን 90% ለማድረስ ታቅዶ 491 መዛግብት ቀርበው በፍርድ ቤት ከተወሰኑት 367 መዛግብት ዉስጥ 341(92.9%)መዛግብት ላይ በማሸነፍ 26 መዛግብት በመሸነፍ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

የንቃተ ሕግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች ብዛትን በተመለከተ ወንድ 276,164 ሴት 285,121 ድምር 561,285 ለሚሆነው የክልሉ ህዝብ የንቃተ ህግ ለመስጠት ታቅዶ ወንድ 359,781 ሴት 361,320 ድምር 721,101 / 128%/ ለሚሆነው ህብረተሰብ ክፍል ትምህርቱ ተሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል በተከሳሽና ምስክር አለመቅረብ የመዛግብት መቋረጥ የማቋረጥ ምጣኔን 12% ለመቀነስ ታቅዶ ለፍ/ቤት ከቀረቡ 7,710 መዛግብት ውስጥ 494 መዛግብት በማዘጋት (6%) ተከሳሽና ምስክር ባለመቅረቡ የሚዘጉ መዛግብት ምጣኔን ዝቅ ያለ ሲሆን በሌሉበት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ፍርደኞች የፍርድ ውሳኔ ተፈፃሚነትን ዉጤታማ ለማድረግ በሌሉበት የተፈረደባቸዉን ፍርደኞች 100% ለፖሊስ ማሳወቅና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ሁሉንም ክትትል ማድረግ የተቻለ በመሆኑ አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

የንቃተ ሕግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች ብዛትን በተመለከተ የንቃተ ሕግ ትምህርት የተሰጣቸው ዜጎች ብዛትን ወንድ 654,373 ሴት 668,367 ድምር 1,322,740 ለሚሆነው የክልሉ ህዝብ የንቃተ ህግ ለመስጠት ታቅዶ 905,313 /68.44%/ ለሚሆነው ህብረተሰብ ክፍል ትምህርቱ ተሰጥቷል፡፡

**የፍትሐብሔር ፍትህ አስተዳደር ውጤታማነትን በተመለከተ፤** ሰነዶችን በጥራትና በፍጥነት የመመዝገብና የማረጋገጥ ስራዎችን በትኩረት በመያዝ ለምዝገባና ለማረጋገጥ የቀረቡትን ሰነዶች ጥራታቸውን በመጠበቅ ማከናወን 100% ለማድረስ ታቅዶ *145,565* /አንድ መቶ አርባ አምስት ሽህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት/ ሰነዶችን የመመዝገብና ማረጋገጥ ስራ በመስራት ብር *580,700,802.85* /አምስት መቶ ሰማንያ ሚሊየን ሰባት መቶ ሽህ አምስት መቶ ስምንት መቶ ሁለት/ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በተመሳሳይ በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስ፣ ይግባኝ መልስና ሰበር መልስ ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት የማጥራት ቅልጥፍናን** 97.5% **ለማድረስ በእቅድ ተይዞ** ብር 5,950,645,261.94 /አምስት ቢሊየን ዘጠኝ መቶ ሀምሳ ሚሊየን ስድስት መቶ አርባ አምስት ሽህ

ሁለት መቶ ስልሳ አንድ/ ብር የያዙ 4,971 መዛግብት ቀርበው ብር 5,811,823,416.28 /አምስት ቢሊየን ስምንት መቶ አስራ አንድ ሚሊየን ስምንት መቶ ሀያ ሶስት ሽህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ የያዙ 4,727 መዛግብት ውሳኔ በመስጠት የማጥራት ምጣኔዉን በመዝገብ 95.09% መፈጸም ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን 90.5% ለማድረስ ታቅዶ ብር 12,334,831,112 /አስራ ሁለት ቢሊየን ሶስት መቶ ሰላሳ አራት ሚሊየን ስምንት መቶ ሰላሳ አንድ ሽህ አንድ መቶ አስራ ሁለት/ በያዙ 4,632 መዛግብት ላይ ክርክር ተደርጎ ብር 596,579,073 /አምስት መቶ ዘጠና ስድስት ሚሊየን አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሽህ ሰባ ሶስት ብር/ የያዙ 1,085 መዛግብት /በገንዘብ 96% በመዝገብ 87%/ በአሸናፊት፤ ብር 27,916,419 /ሀያ ሰባት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ አስራ ስድስት ሽህ አራት መቶ አስራ ዘጠኝ ሽህ ብር/ 161 መዝገብ ላይ በተሸናፊ ተወስነዋል፡፡

የመንግስትን ሃብትና ንብረት ከብክነት ለመከላከል እንዲቻል ለመንግስት ተቋማት ህግ ምክር አገልግሎትን 100% ለማከናወን በእቅድ ተይዞ 1,930,942,376 ብር የያዙ 2,266 ጉዳዮች ቀርበው ሁሉም ተከናውኗል፡፡ አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

በፍትሐብሔር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ስራን ማለትም የዉል ረቂቅ የመመርመር፤ እና ረቂቅ ውልን የማዘጋጀት ስራዎችን 100% ለማከናወን በእቅድ ተይዞ 142,908,018,546 ብር የያዙ 3,792 ጉዳዮች የውል ረቂቅ መመርመር እና 240,696,134 ብር የያዙ 161 ጉዳዮች የውል ሰነድ ዝግጅት ቀርበዉ ሁሉም ተሰርተዋል፡፡ አፈጻጸሙ 100% ነዉ፡፡

የፍታብሄር ጉዳዮችን በድርድር የመፍታት ምጣኔን 14% ለማድረስ ታቅዶ ብር 17,245,808,832 /አስራ ስድስት ቢሊየን አራት መቶ ሰላሳ ሚሊየን ሁለት መቶ አርባ ሰባት ሽህ አራት መቶ ሰባ ሲስት ብር/ የያዙ 8,571 መዛግብት ውስጥ ብር 5,492,923,534 የያዙ 1,365 መዛግብት በድርድር ተቋጭቷል፡፡ አፈጻጸም በገንዘብ 46% በመዝገብ 34% ነው፡፡

የዐቃቤ ህግ ይግባኝ እና ሰበር ክርክርን ማሸነፍ ምጣኔ 65% ለማድረስ ታቅዶ ብር 487,719,512 ብር የያዙ 764 መዛግብት ላይ ክርክር በማድረግ ብር 38,310,254 ብር በያዙ 194 መዛግብት ላይ /በመዝገብ 57.6% በገንዘብ 45% በአሸናፊነት ተወስኗል፡፡ ብር 46,861,225 ብር በያዙ 143 መዛግብት ላይ በተሸናፊነት ተወስኗል፡፡ በተመሳሳይ የፍርደኛ ይግባኝ እና ሰበር ክርክር ላይ የማሸነፍ ምጣኔን 75% ለማድረስ ታቅዶ ብር 1,742,909,164 ብር የያዙ 826 መዛግብት ላይ

ክርክር በማድረግ ብር 282,715,149 ብር የያዙ 248 መዛግብት ላይ በመዝገብ 86.11 % በገንዘብ 97.89% / በአሸናፊት፤ ብር 6,086,858 ብር በያዙ 40 መዛግብት ላይ ደግሞ በተሸናፊነት ተወስኗል፡፡

መንግስት በተከሰሳባቸው ጉዳዮች ብር 9,859,425,537 ከያዙ 3,009 ውስጥ ብር 448,514,630 በያዙ 716 መዝገብ በማሸነፋችን የመንግሰትን ንብረት ከምዝበራ ማዳን ተችሏል፡፡ የአስተዳደር ፍትሕ ስርዓትን የማስተዋወቅ እና የማስረፅ ተግባራትን በተመለከተ በአድስ የወጡትን የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅ እና የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር፣ የማረሚያ ቤት ኮሚሽንን ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ለ744 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡ በበጀት አመቱ 80 የተለያዩ የህግ ረቂቅ ቀርበዉ 80ዎች ሰርተን መልሰናል፡፡ የአቤቱታ አቀባበል ውሳኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈጻሚነት ምጣኔን 98.5% ለማድረስ ታቅዶ 6,671 አቤቱታዎች ቀርበው 6,608 / 99.05%/ ዉሳኔ አግኝተዋል፡፡

**በሌላ በኩል የአስተዳደር ፍትሕ ስርዓትን የማስተዋወቅ እና የማስረፅ ተግባራትን በተመለከተ** በአዲስ የወጡትን የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት፣የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት እና የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር፣የማረሚያ ቤት ኮሚሽንን ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ለ744 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡ በበጀት አመቱ 56 የተለያዩ የህግ ረቂቅ ቀርበዉ 53ቱን ሰነዶች ሠርቶ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

**በክልሉ የሠላምና ግጭት አፈታት ባህል መገንባት፡-** የሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት ስትራቴጅ ትውውቅ ወርክሾፕ የክልል የመንግስት ተቋማት አመራሮች፣ የክልል፣ የሰሜን ጎጃምና ባህርዳር ከተማ አስተዳደር የፀጥታ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ አባላት፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች፣ ወጣቶችና ሴቶች ወንድ 120፣ ሴት 47 በድምሩ 167 ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሃይማኖት አባቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሰላምና ፀጥታ አመራሮች፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በድምሩ 888 ባለድርሻ አካላትን በ4 መድረክ ለማሳተፍ ታቅዶ ወንድ 582፣ ሴት 123 በድምሩ 705 (79.4%) የተሳተፉበት ማህበረሰብ አቀፍ የሰላም ግንባታና ግጭት አፈታት ምክክር ተካሂዷል፡፡

**የግል ሰላም ግጭት አፈታት ማዕከላት፣ የሰላም ምክር ቤቶች፣ ክበባትና ፎረሞች በየደረጃዉ እንሚመሰረቱና እንዲስፋፉ ማድረግና ማጠናከር አንጻር፡-**

**የሰላም ክበባት፡** ለ51,416 ወንድና 25,003 ሴት በድምሩ ለ80,068 የሰላም ክበባት አመራሮችና አባላት በሰላም እሴት ግንባታ ዙሪያ 623800 (98%) የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የሰላም ኮሚቴ፡-** ወንድ 31,316 ሴት 10,218 በድምሩ 41,534 የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ የሰላም ኮሚቴ አባላትና አመራሮችን በሰላም ግንባታ ዙሪያ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ታቅዶ ወንድ 30,557 ሴት 9,918 በድምሩ ለ40,475 (97.5%) የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

**ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት፡-** ቅድሚያ የሚሰጣቸው የወንጀል ጉዳዮች (priority prosecution) የጋራ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ 100% ታቅዶ የሴቶችን ጥቃት በመከላከል፣ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር 47-14.18፣ ህገ ወጥ ንግድ ፣ እገታ ወንጀል100-24.8፣ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር 47-18.78፣ አደገኛ የእፅ ዝውውር የመሳሰሉ አደገኛ ወንጀሎችን ከፌደራልና ከክልል የፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት በመሰራቱ 100% ዉጤታማ አፈፃፀም ተመዝግቧል፡፡ ሌላዉ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት ታዝዞ ተከሳሽ የማቅረብ አቅምን 66% ለማድረስ ተቅዶ 9,239 ተከሳሽ እንዲቀርብ ታዝዞ 7,144 የቀረበ ሲሆን 77.32% መፈፀም ተችሏል፡፡ እንዲሁም ምስክር የማቅረብ አቅምን 66% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን 12,151 እንዲቀርብ ታዝዞ 9,497 (78.15%) ምስክርን መቅረብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በፍትሐብሔር ጉዳይ በፍርድ ቤት ታዝዞ ተከሳሽ የማቅረብ አቅምን 66% ለመፈፀም ታቅዶ 3,250 ተከሳሽ እንዲቀርብ ታዝዞ 2,735 (84.15%) የቀረበ ሲሆን እንዲሁም ምስክር የማቅረብ አቅምን 66% ለመፈፀም ታቅዶ 2,471 እንዲቀርብ ታዝዞ 1,847 (74.74%) ማቅረብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በተጨማሪም ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ተናባቢ የሆኑ የጋራ ማሻሻያዎችን በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ 100% ታቅዶ ከክልሉ ሴቶችና ህፃናት ወጣቶች ቢሮ፣ ከፍትህ ቢሮ፣ ከፍ/ቤት ጋር በመቀናጀት በሴቶችና ህፃናት፣ በአቅመ ደካሞች ወይም በአረጋውያን ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ቀድሞ በመከላከልና ልዩ ድጋፍ በማድረግ በኩል እየተሰራ ይገኛል፡፡

ከአጎራባች ክልሎች የመንግስት ለመንግስትና ህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን በማጠናከር ችግሮችን ቀድሞ የመፍታት ባህል ለማዳበር 1 ጊዜ ውይይት ለማድረግ ታቅዶ 2 (>100) ከአፋር ክልል እና ከኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ዞኖች ጋር የህዝ ለህዝብ የጋራ ውይይት በማድረግ የፀጥታ ስጋቶችን ቀድሞ መፍታት ተችሏል፡፡

**ስነ-ምግባርን መገንባት፣ ሙስናን መከላከል እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ በተመለከተ፦** በፊት ለፊት የስልጠናና ግንዛቤ ፈጠራ በሁሉም መንገድ ለ431,117 የህብረተሰብ ክፍሎች ለመስጠት ታቅዶ ሴት-199,979 ወንድ-199,951 ድምር 399,930 (92.76%) የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ

ለመስጠት የተቻለ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ 3,826 በፊት ለፊት ስልጠና የተሰጣቸዉ ናቸዉ፡፡ ለህዝባዊና መንግስታዊ ተቋማት የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማከናወን ከፍተኛ በጀት የሚመደብባቸውን እና ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን እና ተቋማት ላይ የአሰራራር ስርዓት ጥናት ማካሄድ 5 ታቅዶ 5 (100%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን የአሰራር ስርዓት ጥናት የተከናወነላቸውን ተቋማት ወደ ተግባር ማስገባት 5 ለማስገባት ታቅዶ 4 (80%) ማድረስ ተችሏል፡፡ በአስቸኳይ መከላከል የዳነ ሀብት ፡- በገንዘብ 15,692,657.30፣መሬት 10,493.43 ካ/ሬ፣ በዓይነት 1,784,007.11 በዓይነት (ከግንባታ የተረፈ ቀለም ሲሸጥና ለግል ጥቅም ሲውል ሲል የዳነ፣ እንዲሁም 2,877,461 ግምት ያለው መድኃኒት እና ብርድ ልብስ፣ 6 ህገወጥ የሠራተኛ ስምሪት/ዝውውር እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ተግባራት በሚመለከት የመንግስት ተመራጮች፣ ተሿሚዎችም ሆኑ ሰራተኞች የዕለት ከዕለት ስራቸውን የሚያከናውኑት ለህዝብ ጥቅም እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ እነዚህ የህዝብ ወኪሎች ህዝብ የሰጣቸውን ተግባር እና ኃላፊነት የጥቅም ግጭት በሚያስከትል መንገድ እንዳይፈጽሙ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ለማረጋገጥ በህግ ሀብት የማስመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸውን ሠራተኞች ሀብት መመዝገብ አንዱ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም 2,500 ጉዳዩ የሚመለከታቸዉን ግለሰቦች ሀብት ለመመዝገብ ታቅዶ ሴት-1,326 ወንድ- 2,527 በድምር-3,853(100%) መመዝገብ የተቻለ ሲሆን በዕድሳት ምዝገባ የ10,000 አካላትን ምዝገባ ለማደስ ታቅዶ ሴት-2,961 ወንድ- 6,595 በድምር-9,556 (95.56%) የእድሳት ምዝገባ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የሕግ አገልግሎት ውጤታማነትን 100% ለማረጋገጥ** ታቅዶ 54 ጉዳዮች በጠበቆች ነፃ ህግ ድጋፍ ታይተዉ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ካገኙት 54 መዛግብት ዉሰጥ 52ቱን /96.29%/ በመርታት የተወሰኑ ሲሆን 2 ነፃ ተብለዋል፡፡ በተመሳሳይ በጠበቆች የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት የደንበኞች እርካታ ምጣኔን 85% ለማድስ ታቅዶ አፈፃፀም 96.29% ነው፡፡

በጠበቆች የስነምግባር ግድፈት ተጠያቂ የተደረጉ እና በዲሲፕሊን የቀረቡትን ውሳኔ መስጠትን 100% ለማድረስ ታቅዶ ለአቃቤ ህግ የቀረቡ የጠበቆች የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ከ2017 በጀት ዓመት የዞረ 5 መዝገብ፣ አዲስ የቀረበ 11 ጠቅላላ 16 ሲሆኑ ከእነዚህ ዉስጥ ክስ የተመሠረተባቸዉ 12፣ አያስከስስም 3፣ ለተጨማሪ ምርመራ የተላከ 1 መዝገብ ነዉ፡፡ በጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ከ2017 በጀት ዓመት የዞረ መዝገብ 32፣ አዲስ 12 በድምሩ 44 መዝገቦች የቀረቡ ሲሆን ሲሆን ጉባኤው ውሳኔ የተሰጠባቸው መዝገቦች 6 ናቸው፡፡

**በዘርፉ የህብረተሰቡን ግንዛቤና ተሳትፎ በማሳደግ ብዝሃ-ሕግ እና አማራጭ ፍትሕ መስጫ ስርዓቶችን ማጠናከር፡-** 10,000,000 ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት አሰራርና ተሳትፎ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ክንውን ወንድ 5,867,745 ሴት 6,900,710 ድምር 12,768,455 (›100%) ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡

**ሰብአዊ መብትን ማሳዎቅ፣ ማክበር፣ ማስከበር እና ማሟላት፤** ማረሚያ ቤቶችን ጉብኝት በማድረግ በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች አያያዝና አጠባበቅ ህግን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥን በተመለከተ 180 ማረሚያ ቤቶችን በድግግሞሽ ለመጎብኘት ታቅዶ 741 ጉብኘት የተደረገላቸው ሲሆን አፈፃፀሙ 100% በላይ ነው፡፡

የፖሊስ ጣቢያና ጊዜአዊ ማረፊያ ቤቶች በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች አያያዝና አጠባበቅ ህግን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ በሩብ ዓመቱ 4,608 ታራሚዎችን ለመጎብኘት ታቅዶ በ5,793 ፖሊስ ጣቢያና ጊዜአዊ ማረፊያ ቤቶች ላይ በቁጥጥር ስር ለዋሉ ሰዎች ጉብኘት ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ የብሔራዊ የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሃግብር ለተቋማት ተለይተው የተሰጡ ተግባራት በእቅድ አካትተው መተግበራቸውን ማረጋገጥ በቁጥር 23 ለመፈፀም ታቅዶ 18 የክልሉን አስፈፃሚ ተቋማት ስራቸውን በህግ መሰረትና ሰብዓዊ መብትን ያከበረ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡

የወንጀል ተጎጅዎች፣ ጠቋሚዎች እና ምስክሮች ጥበቃ የሕግ ማዕቀፍ እና አሰራር መቅረፅ እና ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ 1 ታቅዶ 1 (100%) የተከናወነ ሲሆን ለወንጀል ተጎጅዎች፣ ጠቋሚዎችና ምስክሮች ከለላ ውሳኔን ለቀረቡት 100% ለመስጠት ታቅዶ 39 የከለላ ጥያቄዎች ቀርበዉ ለ39(100%) መልስ መሰጠት ተችሏል፡፡
በሌላ በኩል የማህበራዊ አገልግሎት ያገኙ ታራሚዎች 2,500 ታቅዶ ለ5,051 (100%) ታራሚዎች የማህበራዊ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 12,202 ታራሚዎች የስነ-ልቦና ግንባታ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ7,595 (62.24%) ታራሚዎች ስነ-ልቦና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በተዘጋጀው ሜኑ መሰረት የታራሚዎች100% የምግብ አቅርቦት ለማድረግ ታቅዶ በተዘጋጀ ሜኑ መሰረት እና ለአንድ ታራሚ በቀን በሚያዝለት ሂሳብ መሰረት100% የምግብ አቅርቦት እተደረገ ቢሆንም የምግብ ሂሳብ በቂ ባለመሆኑ በተጣይ ትኩረት በመስጠት ሂሳቡን የማሻሻል ስራ ይጠይቃል፡፡

በአያያዝ እና በእንክብካቤ የተጎበኙ ታራሚዎች /የቤተሰብ ግንኙትበድግግሞሽ 65,000 ታቅዶ 200,000 ታራሚዎች በድግግሞሽ በቤተሰብ ተጎብኝተዋል፡፡ አፈፃፀሙ 307.69% ነው፡፡ የባህሪ

አመክሮና ይቅርታ ምዘና ያለፉ የህግ ታራሚዎችን 2,500 ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 585 (23.4%) ታራሚዎች በአመክሮ እንድፈቱ ሲሆን የትምህርትና ስልጠና ያገኙ የህግ ታራሚዎችን 11,322 ለማድረስ ታቅዶ 6,389 (56.42%) ታራሚዎች የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨመሪም የግብርና እና ኢንዱስትሪ የስራ እድል ተጠቃሚ ታራሚዎችን 1,124 ለማድረስ ታቅዶ 647 (57.56%) ታራሚዎች ስራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በአጠቃላይ  የወንጀል ምርመራ መዛግብት የመወሰን ቅልጥፍና 98% ለማድረስ ታቅዶ 95.04%፣ በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ 92.70% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስ፣ ይግባኝ መልስና ሰበር መልስ ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት የማጥራት ቅልጥፍናን 97.5% ለማድረስ ታቅዶ የማጥራት ምጣኔዉን በገንዘብ 24.87% በመዝገብ 96.6%፣  በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቀጥታ ክስና መልስ የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን 90.5% ለማድረስ ታቅዶ በገንዘብ 95% በመዝገብ 87% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የፍታብሄር ጉዳዮችን በድርድር የመፍታት ምጣኔን 14% ለማድረስ ታቅዶ በገንዘብ 22.9% በመዝገብ 12.95% ማድረስ መታሉ የተሻሉ ተግባራት መሆናቸዉን የሚያሳይ ሲሆን የህግ የበላይነትን ከማስፈን፣ ቅንጅታዊ አሰራርን ስርዓት ከማበጀትና ወደ ተግባር ከማስገባት አኳያ በቀጣይ በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡

## 6.2. የባህል እና እሴት ልማት

**የክልሉን የባህል፣ እሴት እና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ፤** በክልሉ የሚነገሩ7 (አማርኛ፤ ኦሮምኛ፤ ኽምጣንጋ፤ አዊኚ፤ አርጎብኛ፤ ግዝ፤ ቅማንትኛ) ቋንቋዎች ፕሮፋይል ተዘጋጅቷል፡፡ የፕሮፋይሉ አዘገጃጀት በዋናነት የያዛቸው ነጥቦች የቋንቋው መገኛ ቦታ፤የሚከተለው ሥርዓተ-ጽሕፈት፡- የትምህርት ቋንቋነት፤ የሚዲያ አገልግሎት፤ የሥራ ቋንቋነት፤ ቋንቋው፡- በሰዋስው፣ በመዝገበ ቃላትና በስነቃል፤ በፈጠራ ስራዎች ስለመሰነዱ ወዘተ ያካትታል፡፡

**በባህል ኢንዱስትሪ የገበያ ትስስር በመፍጠር ባህሉ ለክልሉ ልማት የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ** በተቋም ደረጃ 108 በባህል ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ተቋማት የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 146 ተቋማት ትስስር በመፈጠሩ ለ332 ሙያተኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ615 ተጠቃሚዎች የገበያ ትስስር በመፈጠሩ እንደቅደም ተከተላቸው 135 በመቶና 185 በመቶ አፈጻጸም ታይቷል፡፡

130 የዕደ ጥበባት አምራቾች የንግድ አውደ-ርዕይ (ባዛርና ኤግዚቢሽን) ለማካሄድ ታቅዶ 34 በመከናወኑ አንስተኛ አፈጻጸም ታይቷል፡፡ ለአፈጻጸሙ ማነስም አብዛኛዎቹ ዞንና ከተማ አስተዳደሮች (የ11 ዞኖችና ከተማአስተዳደሮች) በእቅዳቸው መሰረት ባለማከናወናቸው ነው፡፡

**የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ቁጥር በማሳደግ በቴክኖሎጂ በቁሳቁስ እና በአደረጃጀት ማጠናከር**

65 ነባር የሕዝብ ቤተመጻሕፍትን በሙያ፣ በቁሳቁስና በአደረጃጀት ለማጠናከር ታቅዶ 61 ለማጠናከር በመቻሉ 93.8 በመቶ አፈጻጸም ተችሏል፡፡ በክልሉ ለሚገኙ ቤተ መጽሀፍቶች 250,000 መጽሃፍትን በግዥና በስጦታ ለማሰባሰብና ለማሰራጨት ታቅዶ 15,675 በመሰብሰቡና በመሰራጨቱ አንስተኛ አፈጻጸም ታይቷል፡፡ የንባብ ክበባትን ማቋቋምና ማጠናከር በተመለከተ 46 የንባብ ክበባትን ለመቋቋምና ለማጠናከር ታቅዶ በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በየትቤቶች 126 ተቋቁመዋል፡፡

**መጤ ባህሎችን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እና አመለካከቶችን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስች አሰራሮችን በመዘርጋት የክልሉን ባህልና እሴት ከመሸርሸር ማዳን፡-** የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ግንባታ እና በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ቅነሳ ዙሪያ የንቅናቄ ሳምንት በመፍጠር የግንዛቤ ስራ ለመስራት 118 መድረኮችን በማዘጋጀት ለ60,000 (50 በመቶ የሴቶች፣ 30 በመቶ የወጣቶች፣ 10 በመቶ የህጻናት እና 60 በመቶ የአዋቂዎች ድርሻ) የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ግንባታ እና በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ቅነሳ ዙሪያ የንቅናቄ ሳምንት በመፍጠር የግንዛቤ ስራ ለመስራት ታቅዶ በ324 መድረኮች ለ98,977 ወንድ እና ለ98,978 ሴት በድምሩ ለ197,955 የህ/ሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

**የረጅም ዘመን የቱሪዝም ልማት አስተዳደር የመጣለትን ኅብኚ ከማስተናገድ አልፎ የዓለም የቱሪዝም ፍላጎት ትርጉም ባለው መልኩ ፍላጎትና አቅርቦትን በሳይንሳዊ ሥነ-ገበያ ተንትኖ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፡-** ባህላዊ ምግቦችና መጠጦችን በሆቴሎች፣ በሬስቶራንቶችና በተመረጡ መዳረሻ ቦታዎች እንደ አንድ የቱሪስት መስህብ ሆነው በሜኑ እንዲቀርቡና እንዲለሙ ለማድረግ በታቀደው መሰረት በደሴ ከተማ የዓለም ቱሪዝ ቀን ሲከበር የደሴና የአካባቢው የሚገኙ ከ13 በላይ ባህላዊ ምግበቦችና 5 የባህላዊ መጠጥ አይነቶች በሉሲ ሆቴል እንዲዘጋጁ በማድረግ ለተጠቃሚዎች ማለማመድ ተችሏል፡፡ ነባር መመሪያዎችን እና የአሰራር ሰነዶችን ለማሻሻል የቱሪዝም ስርዓቱን ለማዘመን እና የመስተንግዶ ደረጃውን ለማሻሻል በታቀደው መሰረት የጎንደር አለምአቀፍ አብያተ መንግስታት መዳረሻን የመግቢያ እና የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ፣ የአካባቢ አስጎብኝዎች የስምሪት መመሪያ እና የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ሰነድን በማሻሻል ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

**ውድድር ከበዛበት የዓለም አቀፍ ቱሪዝም ሥርዓት ውስጥ የአገር ውስጥ የቱሪዝም ሀብቶችን በማነጽ የገቢ ቱሪዝም እና የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ወይም በጥቅሉ የውስጥ ቱሪዝምን (Internal Tourism) ማሳደግ፡-** 233 (online and offline) ሚዲያ በመጠቀም የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን

በስፋት ለማስተዋወቅ ታቅዶ 662 ኢንተርኔትን መሰረት ያደረገ online እና 5 የህትመት ዓይነቶች (በራሪ ወረቀቶች፣ ብሮሸሮች፣ ባነር፣ ቢልቦርድ፣ ቱሪስት መሪ-መጽሐፍ) offline በድምሩ 667 ጊዜ የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በኢንተርኔት (online) እና በህትመት (offline) የተካሄደው የመስህብ ቦታዎችን እና ክብረ በዓላትን የማስተዋወቅ ተግባር ከሀገር ውስጥ ቱሪስቶች በተጨማሪ የውጭ ቱሪስቶችንም ታሳቢ አድርጎ በተለያዩ ቋንቋዎች የተካሄደ ነበር፡፡

**የክልሉን የቱሪስት መዳረሻዎች እና መስህቦች መረጃ የዘመኑን ቴክኖልጂ ሥርዓት በመጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽ ማድረግ፣ ማስተዋወቅ፦** ዘመኑ ያፈራውን ቴክኖሎጅ በመጠቀም 320 የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን በስፋት ለማስተዋወቅ በእቅድ ተይዞ 662 የመስህብ ሀብቶችን በማስተዋወቅ ከዕቅድ በላይ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

4 የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን በካርታና በጅፒኤስ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ሶስት የቱሪስት ቦታዎችን በካርታ፣ ጅፒኤስ እና ጎግል ላይ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡ የካርታና ጂፒኤስ የተሰራላቸው መዳረሻዎች የጎንደር ከተማ፣ በደቡብ ወሎ ዞን የሚገኙት የሀርቡ ፍል ውሃ እና የአርዲቦ ሐይቅ ናቸው፡

**የመስህብ ሀብቶችን መሰረተ ልማት በሟሟላት አሁን ያለትን 10 የቱሪስት መዲረሻዎች ወደ 32 ማሳደግ፦** የመንገድ ዝርጋታ ለሚያስፈልጋቸው መዳረሻዎች እና የመስህብ ሀብቶች 120 ኪ.ሜ መንገድ እንዲሰራ ለማስተባበር ዕቅድ ተይዞ 326 ኪ.ሜ መንገድ እንዲሰራ በማድረግ ከዕቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ 2 አዲስ የማህበረሰብ አቀፍ እና ኢኮ-ቱሪዝም ማህበራትን ለማደራጀት በዕቅድ ተይዞ 8 ማደራጀት ተችሏል፡፡

**የቱሪዝም ማኔጅመንት እና ሥነ ግብይት (marketing) ተግባር የቱሪዝም መስህቦችን፣ መዳረሻዎችን፣ እና ምርቶችን በማስፋፋት የቱሪስት ቁጥርን መጨመር እና የቱሪስት የቆይታ ጊዜን በማራዘም ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማሳደግ፦** በዋና ዋና ከተሞችና በቱሪስት መዳረሻዎች አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲገነቡና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ 6 ኢኮ-ሎጅና ሪዞርት፤ 50 ሆቴሎች፤ እንዲሁም 5 ባህላዊ ሬስቶራቶች እንዲገነቡና ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ለ10 ሆቴሎች የኮከብ ደረጃ ምደባ ለመስጠት ታቅዶ በደሴ፣ ኮምቦልቻ እና ደብር ብርሃን ከተሞች ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የኮከብ ደረጃ ምደባ ስራ ለ13 ሆቴሎች መስጠት ተችሏል፡፡

**የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰትን ከ12,738,575 ወደ 19,107,862 እና የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰትን ከ27,010 ወደ 59,422 በማድረስ ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘዉን ገቢ በሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት ከ5,581,206,034 ብር ወደ 15,286,289,600 ብር እና በዉጭ አገር ቱሪስት ፍሰት ከ258,329,881 ብር ወደ 356,532,000 ብር ማሳደግ፡-** 142 የአገርህን እወቅ ክበባትና የጉዞ ማህበራትን ለማቋቋም በዕቅድ ተይዞ 202 ክበባትን ማቋቋም ተችሏል፡፡ 90 የአገርህን እወቅ ክበባትን ወደ ጉዞ ማህበርነት ለማሸጋገር ዕቅድ ተይዞ 166 ክበባትን ወደ ጉዞ ማህበርነት ማሸጋገር ተችሏል፡፡ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እቅስቃሴን ለማነቃቃት በሀገር ውስጥ ሚዲያዎች 177 የሬዲዮ ፕሮግራሞችን በማሰራት መዳረሻዎችን እና የመስህብ ሀብቶችን ለማስተዋወቅ ዕቅድ ተይዞ 345 ጊዜ በሬዲዮ የማስተዋቅ ሥራ በመስራት ከዕቅድ በላይ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ 177 ጊዜ በሀገር ውስጥ ሚዲያዎች የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን በማሰራት መዳረሻዎችን እና የመስህብ ሀብቶችን ለማስተዋወቅ ዕቅድ ተይዞ 239 ፕሮግራሞችን ማሰራት ተችሏል፡፡

ክልሉን የሚጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን ቁጥር 29,000 ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ 16,797 ማድረስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ከዕቅዱ አንጻር 58% መፈጸም ተችሏል፡፡ የሀገር ዉስጥ ቱሪስት ፍሰትን 12,000,000 ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ 7,588,607 በማድረስ የዕቅዱን 63% መፈጸም ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ግማሽ ዓመት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት 12,029,000 ለማድረስ ታቅዶ 7,605,403 ማድረስ በመቻሉ የእቅዱን 63% መፈጸም ተችሏል፡፡

ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት የሚገኘውን ገቢ 81,782,760 ብር ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ 108,793,638 ብር ማድረስ በመቻሉ አፈፃፀሙን ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት ከሚገኘው ገቢ 40% ለጓደኛ እና ዘመድ ጥየቃ፣ 37% ለእረፍት እና መዝናናት፣ 20% ቢዝነስ እና ሙያ ነክ ጉዞ እና 3% ከሌሎች የጉዞ ዓላማዎች ገቢ ለማግኘት ዕቅድ በመያዝ የተሰራ ሲሆን በመጀመሪያው 6 ወር የሚከተለውን ክንውን ማሳካት ተችሏል፡፡

ከሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት የሚገኘውን ገቢ 7,643,144,000 ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ 6,990,630,617 ብር ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ አፈጻጸሙን 91% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከሀገር ቱሪስት ፍሰት ከሚገኘው ገቢ 40% ለጓደኛ እና ዘመድ ጥየቃ፣ 37% ለእረፍት እና መዝናናት፣ 20% ቢዝነስ እና ሙያ ነክ ጉዞ እና 3% ከሌሎች የጉዞ ዓላማዎች ገቢ ለማግኘት ዕቅድ በመያዝ የተሰራ ሲሆን በመጀመሪያው 6 ወር የሚከተለውን ክንውን ማሳካት ተችሏል፡ በአጠቃላይ በዚህ 6 ወራት ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘዉን ገቢን 7,724,926,760 ብር ለማድረስ

ታቅዶ 7,099,424,155 ብር በማግኘት አፈጻጸሙን ከግማሽ ዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር 91% ለመፈጸም ተችሏል፡፡

**የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ቁጥር ከ14,263 ወደ 15,362 እና የኮከብ ደረጃ ያላቸውን ሆቴሎች ከ32 ወደ 52 ማድረስ፡-** 14,263 ለሚሆኑ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሙያ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 14,324 ለሚሆኑ ቋማት የድጋፍና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡ ለ 897 የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትና ግለሰቦች የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ949 ተቋማትና ግለሰቦች የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 22 በባህርዳር ከተማ ለጀልባ የተሰጠ ብቃት ማረጋገጥ ነው፡፡

**የስፖርት ሃብትን ማሳደግ፡-** በየደረጃዉ ከህብረተሰቡ ብር150,000,000.00 ለመሰብሰብ ታቅዶ 77,932,959.00 (52%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በየደረጃዉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ብር 10,003,000.00 ሀብት ለማግኘት ታቅዶ 7,219,057.00 (72.1%) ማግኘት የተቻለ ሲሆን በየደረጃዉ ከመንግስት ድጋፍ ብር 102,000,000.00 ሀብት ለማግኘት ታቅዶ 102,605,207.00 ማግኘት ተችሏል፡፡ ስፖርቱን በባለቤትነት ይዘዉ ከሚመሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በስራቸዉ ክለቦችን ለማቋቋምና ለመደገፍ የሚያስችል 292,500,000.00 ብረት በጀት ለማስመደብ ታቅዶ 285,224,555.00 (97.5%) ብር እንዲመድቡ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በዘርፉ የሚፈጠረውን የስራ ዕድል በቋሚ ከ17,712 ወደ 27,313 እና በጊዜያዊ ከ20,591 ወደ 30,210 ማድረስ፣** በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ለ4,798 ዜጎች የቋሚና ለ9,610 ዜጎች ጊዚየዘዊ በድምሩ 14,408 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚ ለ7,255 ዜጎች የቋሚ የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን ለ89,200 ዜጎች ጊዚያዊ የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

# ክፍል ሰባት፡ የልማት ፋይናንስ

## 7.1. መዋዕለ ንዋይ

**በበጀት ዓመቱ የክልሉን የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት መጠን ወደ ብር 607.930 ቢሊየን (ከመንግስት የካፒታል ወጪ 14 በመቶ እንዲሁም ከግልና የልማት ድርጅቶ 86 በመቶ) ማሳደግ፤** በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በአግሮ /ፕሮሰሲንግ እና ፍርማስቲካል ቴክ ለ497 ባለሀብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ295 በመስጠት የተመዘገበ ካፒታል 29.05 ቢሊየን ፣ በጨ/ጨርቅና ቆዳ ለ127 ባለሀብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 50 የተሰጠ ሲሆን የተመዘገበ ካፒታል 5.36 ቢሊየን እንዲሁም እንጨትና ብረት ለ205 ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 91 በመስጠት የተመዘገበ ካፒታል 30.31 ቢሊየን በድምሩ 64.72 ቢሊየን ብር ካፒታል ተመዝግቧል፡፡

በዘመናዊ ግብርና ዘርፍ፡- አበባ ልማት እቅድ 1 ክንዉን 10 የተመዘገበ ካፒታል 1.95 ቢ.ብር፣ በእርሻ ፕሮጀክት ዘርፍ (ሰብል፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ) ለ135 ለመስጠት ታቅዶ 104 የተመዘገበ ካፒታል 7.83 ቢሊየን፣ መስኖና ዘር ብዜት ፕሮጀክት ለ13 ፕሮጀክቶች ለመስጠት ታቅዶ ለ8 በፈቃድ በመስጥ 0.34 ቢሊየን፣ በእንስሳት እርባታ ፕሮጀክቶች ለ173 ለመስጠት ታቅዶ ለ94 ፈቃድ በመስጠት 4.15 ቢሊየን እንዲሁም በደንና ንብ ማነብ ፕሮጀክቶች ለ9 ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 18 በመስጠት የተመዘገበ ካፒታል 0.5 ቢሊየን ብር በድምሩ 14.77 ቢሊየን ብር ካፒታል መመዝገብ ችሏል፡፡ በኬሚካል/ኮንስትራክሽን ግብአት ፍቃድ ያወጡ ባለሃብቶች እቅድ 277 ክንዉን 144 ሲሆኑ የተመዘገበ ካፒታል 12.32 ቢ.ብር ሲመዘገብ በአገልግሎት ዘርፍ እቅድ 773 ክንዉን 1,053 ፈቃድ በመስጠት 91.6 ቢሊየን ብር ካፒታል ተመዝግቧል፡፡

**ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል 30,964 ሄ/ር የመሬት መጠን ለአልሚዎች ማቅረብ፡-** ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሆን በሁሉም አምራች ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች 1,850ሄ/ር መሬት በሳይት ፕላንና በካርታ በማዘጋጀት እና 750 ሄ/ር ከሶስተኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 3,972.5 ሄ/ር (100%) በሳይትፕላን በማዘጋጀት 560.3ሄ/ር (75%) ከሶስተኛ ወገን ነጻ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ግምገማዉን ካለፉ 405 በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዉስጥ ለ365 ፕሮጀክቶች መሬት ለመስጠት ታቅዶ 177 (48.5%) 206.21 ሄ/ር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ለሆኑ ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚሆን 5,895ሄ/ር መሬት በሳይት ፕላንና በካርታ ማዘጋጀትና 5,091 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ለማጽዳት ታቅዶ 8,972.12 ሄ/ር (100) መሬት በሳይት ፕላንና በካርታ በማዘጋጀት 6,904.17 ሄ/ር (100%) መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለ350 ፕሮጀክቶች መስሪያ ቦታ ለማስተላለፍ ታቅዶ ለ138 ፕሮጀክቶች 3,429.96ሄ/ር መስሪያ ቦታ የተላለፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለ18 ፕሮጀክቶች 9.88 ሄክታሩ በማስፋፊያ ለነባር ፕሮጀክቶች የተላለፈ ነው፡፡ በተጨማሪም 275 የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ 183 (67%) እንዲሁም 175 ፕሮጀክቶች ግንባታቸዉን እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ታቅዶ 156 (89%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን 69 ፕሮጀክቶችን ወደ ምርት/አገልግሎት ለማስገባት ታቅዶ 85 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከአምራች ኢንዱስትሪ ውጭ ያሉ ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ አፈጻጸም ማስገባት፡ 258 ፕሮጀክቶችን ከቅድመ ግንባታ ወደ ግንባታ ለማስገባት ታቅዶ 166 (64%) ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ማስገባት የተቻለ ሲሆን 188 ፕሮጀክቶችን ከግንባታ ወደ ምርት ለማስገባት ታቅዶ 198 (100%) ፕሮጀክቶች ወደ ምርት/አገልግሎት ማስገባት ተችሏል፡፡

ለ28 ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 13 (46.42%) ሲሆን የተጠቀሙት የብር መጠን እቅድ 6 ቢሊየን ክንውን 0.86 ቢሊየን (14.3%) ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን መረጃ በተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ የተለዩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መረጃ በድምሩ 10,352 መረጃቸውን ወቅታዊ ለማድረግ ታቅዶ 1654 (16%) ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራዎችን በመስራት 3,075 ኢንቨስተሮችን በመሳብ ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ በተመለከተ ፡በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ አቅምና ፍላጎት ያላቸዉን ባለሀባቶች በመለየት መመልመል፤ በክልሉ ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚችሉ አቅም እና ፍላጎት ያላቸውን ባለሃብቶች ከመመልመል አንጻር 449 አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች በመለየት ለመመልመል ታቅዶ 967 (›100%) አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች በመለየት መመልመል የተቻለ ሲሆን የገፅ ለገፅ የፕሮሞሽን ስልቶችን በመጠቀም የኢንቨስትመንት አማራጮችንና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የክልሉን ጸጋዎች ለማስተዋዎቅ የተለያዩ የባለሃብት የኢንቨስትመንት መድረኮችን/ፎረሞችን/ ማካሄድ ዋነኛ ተግባር ሲሆን 9,785 ባለሃብቶችን ያሳተፈ 36 መድረክ ለማካሄድ ታቅዶ 7,039 ባለሃብቶችን ያሳተፈ 106 መድረክ ማካሄድ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ 18 መድረኮች የፓናል ዉይይት ሲሆኑ 1,089 ባለሃብቶችም ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም በኤሌክትሮኒክስ ሚድያ (ሬዲዮ፣ቴሌቪዥን…) ተጠቅሞ ማስተዋወቅ 77 ጊዜ በድግግሞሽ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች ለማስተዋዎቅ ታቅዶ 99 ጊዜ (100%) ጊዜ የተለያዩ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ኢንቨስትመንቱን ማስተዋዎቅ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የማህበራዊ ሚድያ /ፌስቡክ/ በመጠቀም በዚህ ሩብ ዓመት 784 ልዩ ልዩ መረጃዎችን አዘጋጅቶ በመልቀቅ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለሃብቶች የተጫነውን መረጃ በማጋራት የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች ለማስተዋወቅና ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 1,369 (100%) መረጃዎችን በመጫንና በማጋራት የኢንቨስትመንት ጸጋዎችን በማስተዋዎቅ ግንዘቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የቢሮውን የፌስቡክ ገጽ ከነበረበት 18,304 ተከታይ 20,696 አዲስ ተከታይ በማፍራት 39,000 ለማድረስ ታቅዶ በአዲስ 878 ተከታይ በማፍራት ወደ 19,637 ተከታይ ማድረስና በአጠቃላይ የክልላችን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት የተመለከቱ ዜናዎችን ከ400,000 በላይ ለሆኑ ዜጎች መረጃውን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በራሳቸው ተነሻሽነት የሚመጡትን ባለሃብቶችን ጨምሮ በተለዩ ስልቶች ፕሮሞት በማድረግ በክልሉ 243.2 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡና ወደ ስራ ሲገቡ ለ217,632 (ወ-119,698 ሴ-97,934) ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 2,210 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት

ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ 182.77 (75%) ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡና ወደ ስራ ሲገቡ ለ298,829 (ወ-162,265 ሴ-136,564) (100%) ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 1,867 (84%) ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ማደረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለ2,225 ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ1,736 (78%) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እድሳት ማካሄድ የተቻለ ሲሆን ትክ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለፈለጉ 19 (100%) አገልግሎቱን መስጠት እንዲሁም ለውጥ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለፈለጉ 11(100%) አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል፡፡

## 7.2. የመንግስት ፋይናንስ

**በጀት አስተዳደሩን ቀልጣፋና ዘመናዊ በማድረግ በጀቱ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማድረግ፡-** የ2018 በጀት ዓመት ለክልሉ ልማት ማስፈፀሚያ ከፌድራል የበጀት ድርሻ ብር 70.8 ቢሊዮን ከክልል የውስጥ ገቢ ብር 154.44 ቢሊዮን ከውጭ እርዳታና ብድር ብር 0.17 ቢሊዮን በድምሩ ብር 225 ቢሊዮን ሁኖ ፀድቋል፡፡ የ2018 በጀት ዓመት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አጠቃላይ በጀት ጣራ በ2017 ተመድቦ ከነበረው 150.6 ቢለዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 74.4 ቢሊዮን ዕድገት አሳይቷል፡፡

ከፀደቀው 225 ቢሊዮን በጀት ውስጥ ለመደበኛ 138.47 ቢሊዮን (61.5%) እና ለካፒታል 86.98 ቢሊዮን (38.5%) የተመደበ ሲሆን ለካፒታል በጀት ባለፈው በጀት ዓመት 33% ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ብልጫ እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህም የሚያሳየው የክልሉ መንግስት ለካፒታል ፕሮጀክቶች ትኩረት ሰጥቶ ከዓመት ዓመት የሚመደበውን በጀት እያሳደገ መምጣቱን ነው፡፡

**የገቢ አቅምን ከብር 60.09 ቢሊለን ወደ ብር 100.37 ቢሊየን በማሳደግ የክልሉን ልማት ማፋጠን፡** በ2018 በጀት ዓመት የክልሉ ጠቅላላ ወጪ ብር 225 ቢሊዮን እንዲሆን የጸደቀ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በክልሉ አቅም የሚሰበሰበው ገቢ 100.372 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ታቅዶ ብር 42.82 ቢሊዮን (42.7%) መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን የተሰበሰበው ገቢም 37.05 ቢሊዮን (45.18%) ከታክስ ገቢዎች፣ 0.885 ቢሊዮን (30.8%) ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እና 4.85 ቢሊዮን (31.3%) ከከተማ አገልግሎት ገቢ ነው፡፡ በአጠቃለይ የገቢ አሰባሰባችን ክልሉ ካለው አቅም፣ ከተቀመጠው ግብ እና ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ገቢ አንጻር ብዙ የሚቀረን፣ ከራሳችን እቅድም ሆነ ከሃገራችን አማካይ በታች መሆናችንን ተገንዝበን የገቢ ተቋሙን አቅም በቴክኖሎጅና በብቁ የሰው ሃይል በማጠናከር

እና ሁላችንም የበኩላችንን ርብርብ በማድረግ የዘርፉ ውጤታማነት ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

**በቴክኖሎጅ የታገዘ አሰራር በመከተልና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን 100 በመቶ በመደገፍ የሂሳብ ጥራትና ወቅታዊነትን ማሻሻል፡-** ከፌዴራል መንግስት መደበኛ የቀመር ድጋፍ ከተመደበው ብር 70.8 ቢሊዮን የበጀት ድርሻ ውስጥ ብር 34.88 ቢሊዮን ገቢ ለማድረግ ታቅዶ ብር 42.92 ቢሊዮን (100%) ለክልላችን ማስተላለፍ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከፍ ያለበት ምክንያት ለአዲሱ ደመወዝ ጭማሪ ብር 8.04 ቢሊዮን በመላኩ ነው፡፡

በሌላ በኩል አጠቃላይ የክልሉን የወጭ አፈጻጸም ስንመለከት በምክር ቤት ከፀደቀው 225 ቢሊዮን በጀት ውስጥ ብር 60.18 ቢሊዮን (26.75%) ወጭ ሆኗል፡፡ ከዚህም ውስጥ ለመደበኛ ሥራዎች ማስፈጸሚያ ከተመደበው ብር 138.47 ቢሊዮን ላይ ብር 53.81 ቢሊዮን (38.86%) ወጭ ሲደረግ እንዲሁም ለካፒታል ሥራዎች ከተመደበው ብር 86.98 ቢሊዮን ላይ ብር 6.37 ቢሊዮን (7.3%) ወጭ ተደርጓል፡፡ ለዚህ አፈጻጸም ዝቅ ማለት ዋና ምክንያት ቢሮዎች፤ ዞኖች፤ ወረዳዎችና እና ከተማ አስተዳደሮች ወቅታዊ የሂሳብ ምዝገባ ሙሉ በሙሉ በIBEX የመመዝገብ ስራን ባለማጠናቀቃቸው ነው፡፡

**የብር 11.2 ቢሊየን አቅም ካላቸው አዳዲስ ፕሮጀክቶች ጋር ስምምነት በመፈፀም የልማት ሀብት አቅርቦትን ወደ 27.1 ቢሊዮን ማሳደግ፡-** 120 አዳዲስ ኘሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም 5 ቢሊየን ብር በማግኘት 7.5 ሚሊዮን (በድግግሞሽ) የማህረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 121 (100%) አዳዲስ ኘሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም 7.2 ቢሊዮን ብር (100%) በማግኘት 7.6 ሚሊዮን (በድግግሞሽ) የማህረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

# ክፍል ስምንት፡ የማስፈጸሚያ ስልት

## 8.1. ልዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች

### 8.1.1. የክልል ፍላግሽፕ ፕሮጀክቶች

#### 8.1.1.1. ልዩ የኢኮኖሚ ዞን

በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ባለቤትነት የሚተገበር ፕሮጀክት ሲሆን የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትና የተመረጡ የሃገር ዉስጥ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ፣ የዉጭ የምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ፣ የሃገር ዉስጥ የምርት ፍላጎትን በራስ አቅም ለመሸፈን፣ ሰፊ የሥራ እድል

ለመፍጠር፣ ዘመናዊና የተቀናጀ መሰረተ ልማትን ለማሟላት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅን ጥቅም ላይ በማዋል እና ፈጠራን በማበረታታት የእዉቀትና የክህሎት ሽግግርን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችን በስምንት ከተሞች ማለትም ማክሰኝት፣ ቡሬ፣ ግንደወይን፣ ሀርቡ፣ ጋሸና፣ ቡልጋ፣ መተማ ዩሃንስ እና ባከር ከተማዎች በ5 ዓመቱ አንድ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ለመገንባት በዕቅድ ተይዝ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ለማከናወን ለበጀት ዓመቱ ብር 7,606,898,300.00 እንዲፈቀድ በቢሮ በኩል ጥያቄ ቀርቧል።

### 8.1.1.2. ሜካናይዝድ እርሻ

የግብርና ሜካናይዜሽን እና ዘመናዊነት ለተሻሻለ ምርታማነት እና ቅልጥፍና ፕሮጀክት (AMMEPEA) የሜካናይዜሽን አገልግሎቶችን ተደራሽነት በማሻሻል፣ ክህሎቶችን በማዳበር እና በግሉ ሴክተር የሚመራ እድገትን በማበረታታት የግብርና ዘመናዊነትን ለማፋጠን የተነደፈ ቁልፍ የለውጥ ኢንሼቲቭ ነው። ከ17% በታች ባለው የሜካናይዜሽን ሽፋን አብዛኞቹ ገበሬዎች አሁንም በእጅ ጉልበት እና በእንስሳት መጎተት ላይ ይተማመናሉ። ይህም ምርታማነትን እና ተወዳዳሪነትን ይገድባል። AMMEPEA 10 የክልል ሜካናይዜሽን ማዕከሎችን እና 120 የአገልግሎት ማዕከላትን ያቋቁማል የመሳሪያ ኪራይ፣ ጥገና እና የኦፕሬተር ስልጠና፣ የእርሻ ማሽነሪዎችን በአካባቢው ማምረት እና መገጣጠም መደገፍ እና ለማሽነሪ፣ ኪራይ እና ለመረጃ አስተዳደር ዲጂታል መድረኮችን ይተግብራል።

የፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ. በ 2030 ሜካናይዜድ እርሻ ከ17% ወደ 34% ማሳደግ፣ ከመኸር በኋላ ያለው ኪሳራ በ20% መቀነስ፣ አማካይ የሰብል ምርት በ10% መጨመር ሲሆን በተጨማሪም ከ10,000 በላይ ኦፕሬተሮችን እና ቴክኒሻኖችን ማሰልጠን፣ 5,000 ወጣቶችን እና ሴት ስራ ፈጣሪዎችን ማሳተፍ እንዲሁም የፋይናንስ መፍትሄዎችን በብድር እና በሌላ አማራጮችን ማቅረብ ነው።

ፕሮጀክቱ የግብርና፣ ከአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (አራሪ)፣ ኢኢአር፣ የቴክኒካል ቴክኖሎጂ ኮሌጆች፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ የግል ማሽነሪ ኩባንያዎች፣ የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማእከላት እና የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር እንደ ATI እና GIZ ካሉ የልማት አጋሮች ድጋፍ ጋር በመተባበር እየተከናወነ ይገኛል።

### 8.1.1.3. የተሻሻሉ የበግ ብዜት

ክልሉ በምርት እና ምርታማነታቸው ከፍተኛ ሆኑ የበግ ዝርያዎች እጥረት ስላለበት የአገር

በቀል የበግ ዝርያዎችን ምርታማነት በማሻሻል እና ከአካባቢ ጋር የተላመዱና የተመረጡ የበግ ዝርያዎችን በማባዛት ለአርቢው በስፋት ማቅረብ በማስፈለጉ እና የበግ ዝርያዎችን የስጋ ምርታማነት ለማሻሻል ምርታማ የሆኑ ዝርያዎችን በባለቤትነት ዝርያቸውን አሻሽሎ፣ አባዝቶና ጠብቆ ለአርቢው ማቅረብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ይህንን ተግባር በፕሮጀክት መልክ ቀርጾ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው። የተሻሻሉ በግ ዝርያዎች በክልሉ ውስጥ በተመረጡ የበግ ብዜት ማዕከለት ማለትም በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ብርሃን በግ ብዜት ማዕከል እና በአመድ ጉያ በግ ብዜት ማዕከል እና በሰሜን ወሎ ዞን በጋዝ በግ ብዜት ሲሆኑ ከዚህም በተጨማሪ የአካባቢ ማህበረሰብ የበግ መረጣ በማከናወን የማህበረሰብ አቀፍ የበግ ዝርያ ማሻሻል አገልግሎትን ይጨምራል። ይህ ፕሮጀክት በግ ሃብት ልማትን በሚመለከት በአገሪቱና በክልሉ የወጡ ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

የበግ ዝርያዎችን በማሻሻል፣ በማባዛትና በመጠበቅ ለአርቢዎች የተሻሻሉ ዝርያዎችን አቅርቦት እና ተደራሽነትን ማሳደግ፤ የበግ የሥጋ ምርታማነትን በመጠንና በጥራት በመጨመር የህብረተሰቡን የምግብና ስርዓተ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና ለስራ እድል ፈጠራ የላቀ አስተዋፅዖ ማድረግ፣ የአረባብ ስርዓቱን ወደ ዘመናዊነት በማሸገርና ገበያ ተኮር እንዲሆን በማድረግ የአርቢውን የገቢ ምንጭ እንዲያድግ በማስቻል ድህነት እንዲቀንስ አስተዋጽዖ ማድረግ የበግ የስጋ፣ የሌጦ እና የሱፍ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የክልሉን ገቢ እና የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ማሳደግ ነው። በዚህ ፕሮጀክቶች በርካታ ተግባራት በተለይም አሃር በቀል የበግ ዝርያዎችን ምርታማነት በማሻሻል፤ ከአካባቢ ጋር የተላመዱና የተመረጡ የበግ ዝርያዎችን በማባዛትና ለአርቢው በስፋት በማቅረብ እንዲሁም የበግ ዝርያዎችን የስጋ ምርታማነት ለማሻሻል ምርታማ የሆኑ ዝርያዎችን በባለቤትነት ዝርያቸውን አሻሽሎ በማቅረብ በኩል ሰፊ ስራ የተሰራ ቢሆንም ሪፖርቱ ተጠናቅሮ ባለመምጣቱ ማካተት አልተቻለም።

## 8.1.1.4. አሲዳማ አፈር ማከም

"የተቀናጀ የአሲዳማ አፈር መልሶ ማቋቋም ኢንሽቲቭ" በግብርና ቢሮ፣ በአማራ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ARARI) እና በማዕድን ቢሮ በአሲድ የተበላሸ አፈርን ወደ ነበረበት ለመመለስ እና በመላው ኢትዮጵያ አማራ ክልል የሰብል ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመረ የለውጥ ግብርና ፕሮግራም ነው። የፕሮጀክቱ ዋና አላማዎች የኖራ እና ኦርጋኒክ ማዳበሪያዎችን ተደራሽነት ማሳደግ፣ ተቋማዊ ቅንጅት እና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማሻሻል፣

አማራጭ የአፈር ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣ የገበያ ተደራሽነትን እና የፖሊሲ ድጋፍን ማሳደግ እና በአፈር ላቦራቶሪዎች፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እና የገበሬዎች ኔትወርኮች አቅምን ማጠናከር ናቸው።

ይህ ፕሮጀክት ከ36% በላይ የሚሆነውን የክልሉን መሬት የሚጎዳ እና ከ21 ሚሊዮን ቶን በላይ አመታዊ የምርት ኪሳራ ለሚያስከትል ሰፊ የአፈር አሲድነት ምላሽ ለመስጠት ፕሮጀክቱ በሊሚንግ፣ በኦርጋኒክ ማዳበሪያ እና በተቋማዊ ማሻሻያዎች በማጣመር የአፈርን ጤና ለማሻሻል ያለመ ነው። በመሆኑም ለከፍተኛ የአፈር አሲድነት የተጋለጡ ቦታዎችን እንደ ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ እና ምስራቅ ጎጃም በማነጣጠር ፕሮጀክቱ የኖራ ሃብት ካርታ ስራን፣ በአቅራቢያው ያሉ ክሬሸሮችን መትከል፣ የፔሌት ኖራ እና ሜካናይዜድ ማሰራጫዎችን ማስተዋወቅ እና በገበሬ የሚመራ ኦርጋኒክ ማዳበሪያ ምርትን በማዋሃድ የአፈርን ጤና ወደነበረበት ለመመለስ እና ምርትን ለመጨመር አሲድ- ተከላካይ የሰብል ዜርያዎችን እና የጥበቃ እርሻ ልምዶችን ማስተዋወቅ ነው።

በዚህ መሰረት እስከ ግማሽ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ 200,000 ሄክታር የኖራ ድንጋይ ክምችቶችን ካርታ ማድረግ፣ 119 ቢሊዮን ቶን የኖራ አቅምን መለየት እና የኖራ እንክብሎችን እና ሜካናይዜድ ስርጭት ቴክኖሎጂዎችን ማብራራት ስራ የተከናወነ ሲሆን ፕሮጀክቱ በኖራ እና ማዳበሪያዎች ጥምር አጠቃቀም ከ167- 290% የሚደርስ የምርት ጭማሪ አሳይቷል፣ በባቄላ እና በስንዴ ምርታማነት ላይ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል።

#### 8.1.1.5. የዘር አቅርቦት ማሻሻል

የአማራ መደበኛ የዘር ስርዓት (TAFSS) በአማራ ክልል የግብርና ምርታማነትን እና የምግብ ዋስትናን የሚያሳድግ ጠንካራ፣ ሁሉን አቀፍ እና በገበያ ላይ የተመሰረተ የዘር ስርዓት ለመፍጠር ያለመ ነው። ምንም እንኳን ጠንካራ የምርምር አቅም ቢኖረውም የዘር ዘርፉ እንደ የተሻሻሉ ዝርያዎች ዝቅተኛ (ከ 15% በታች) ደካማ ደንብ እና የግሉ ሴክተር ተሳትፎ ውስንነት የመሳሰሉ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል:: በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ TAFSS የዘር ምርትን፣ የጥራት ቁጥጥርን እና የማከፋፈያ ስርዓቶችን በፈጠራ፣ በሽርክና፣ በአቅም ግንባታ እና በምርምር ዘር መገልገያዎች እና መሠረተ ልማት ዘመናዊ ያደርጋል።

ፕሮጀክቱ ቀደምት ትውልድ እና የተመሰከረላቸው ዘሮችን በሁሉም የምርት ወቅቶች የመንግስትና የግል ሽርክና ያሳድጋል፣ የዘር ቁጥጥር እና የላብራቶሪ መሠረተ ልማትን

ያሳድጋል፣ የክልሉን የዘር መረጃ ኸ የመከታተያ መድረክን ዲጂታል ማድረግ እና በወጣቶችና በሴቶች የሚመሩ የዘር ግንዶችን ይደግፋል።

መደበኛ የዘር ስርዓቶች ብዙውን ጊዜ የተደራጁ እና በንግድ የሚመሩ ናቸው፣ ይህም የተመሰከረላቸው ዘሮችን በተለይም ለሰብሎች እና ለተዳቀሉ ዝርያዎች ተደራሽነት ይሰጣል። የተዳቀሉ በቆሎ እና የተዳቀሉ አትክልቶች ብዙውን ጊዜ የሚመረቱት እና የሚሰራጩት በእነዚህ ስርዓቶች ነው። ፕሮጀክቱ በመላው ክልሉ ይከናወናል። በአማራ መደበኛው የዘር ስርዓት በተቋማዊ ቅንጅት እና በታለሙ ጣልቃ ገብነቶች የዘር ጥራትን፣ ተደራሽነትን እና የገበሬዎችን ጉዲፈቻ ለማሳደግ ያለመ ነው። ስርዓቱ እንደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (EIAR)፣ የአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ARARI) እና እንደ አማራ ዘር ኢንተርፕራይዝ (ASE) ያሉ የዘር ኩባንያዎችን የመሳሰሉ ብሄራዊ እና ክልላዊ ድርጅቶችን ያጠቃልላል።

የተሻሻሉ ዘሮች የሚመረቱት በምርምር ማዕከላት ሲሆን በመንግስትም ሆነ በግል ዘር አምራቾች ይሰራጫሉ። ASE የተመሰከረላቸው ዘሮችን በማሰራጨት ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። የቁጥጥር አካላት የጄኔቲክ ንፅህናን፣ የመብቀል መጠንን እና የበሽታን መቋቋምን ለማረጋገጥ የዘር የምስክር ወረቀት እና የጥራት ቁጥጥርን ይቆጣጠራሉ። ዘሮች የሚሰራጩት በህብረት ስራ ማህበራት፣ በማህበራት እና በአግሮ አዘዋዋሪዎች በኩል ነው። ይሁን እንጂ የሎጂስቲክስ እና የመሠረተ ልማት ተግዳሮቶች አሁንም አሉ። በአነስተኛ ገበሬዎች መካከል የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለማበረታታት የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እና የማሳያ ቦታዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

እ.ኤ.አ. በ2030 የተረጋገጠ የዘር ምርት ከ176,000 ወደ 1 ሚሊዮን ኩንታል ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል፤ የተሻሻለ የዘር ሽፋን ከ15% ወደ 25% ያድጋል፣ በዋና ዋና ሰብሎች እና ስልታዊ ምርቶች ላይ ያተኩራል። ፕሮጀክቱ የወጣቶችን እና የሴቶች ቡድኖችን ያካትታል፣ የምርምር ማዕከላትን አቅም ያጠናክራል እና የተቀናጀ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው የዘር ስርጭትን በሁሉም ክልሎች ያረጋግጣል።

በአማራ ክልል የግብርና ቢሮ (BOA)፣ በአማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ARARI) እና በአማራ ስር ኢንተርፕራይዝ (ASE) ከEIAR፣ ESE፣ የግል እና የህብረት ስር አምራቾች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የልማት አጋሮች ጋር በመተባበር የተተገበረው TAFSS በክልሉ ምርታማነትን፣ የመቋቋም አቅምን እና የገጠር ኑሮን የሚያሻሽል፣ ሁሉን አቀፍ እና ተወዳዳሪ የዘር ስርዓት ሽግግርን ይወክላል።

#### 8.1.1.6. የማዕድን ላቦራቶሪ

በክልላችን ራሱን የቻለ የጂኦሎጂካል ላብራቶሪ አለመኖሩ ትክክለኛ የማዕድን ባህሪያትን፣ የጂኦቴክስ ግምገማዎችን እና የአካባቢ ክትትልን ለማድረግ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ይህ ክፍተት የክልሉን ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የመሠረተ ልማት ደህንነትን የማረጋገጥ እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ የመሬት አጠቃቀም እቅድን የመደገፍ አቅምን ይገድባል፡፡ የክልል ጂኦሎጂካል ላብራቶሪ ማቋቋም የላቀ የጂኦሳይንሳዊ ትንታኔዎችን ለማካሄድ፣ ኃላፊነት የሚሰማው የማዕድን ቁፋሮን ለማበረታታት እና ለአየር ንብረት መቋቋም እና ለአደጋ ስጋት ቅነሳ አስተዋፅዖ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች እና እውቀቶች ተቋማትን ያስታጥቃል፡፡

ፕሮጀክቱ እንደ XRD እና ኦፕቲካል ማይክሮስኮፖች ያሉ የተራቀቁ መሳሪያዎችን እንዲሁም የድንጋይ እና የአፈር ጂኦቴክኒካል ትንተና እና የምርምር አገልግሎቶችን በመጠቀም አጠቃላይ ትንታኔዎችን (ፔትሮሎጂካል፣ ሚኔራሎጂካል፣ ጂኦኬሚካላዊ ትንታኔዎችን) ለማቅረብ የሚያስችል ዘመናዊ የጂኦሎጂካል ላብራቶሪ በመመስረት የክልሉን ጂኦሳይንሳዊ አቅምን ማሳደግ፣ ዘላቂ የማዕድን እና የሀብት አስተዳደርን መደገፍ፣ ኢንቨስትመንትን እና የኢኮኖሚ እድገትን ማፋጠን፣ የአካባቢ ተቋማትን እና ባለሙያዎችን ማበረታታት እና የጂኦሳይንስ አገልግሎቶችን ተቋማዊ ማድረግ ነው፡፡

የጂኦሎጂካል ላብራቶሪ ማዕከሉ የአማራ ክልል ዋና ከተማ በሆነችው ባህርዳር ከተማ የሚቋቋም ይሆናል፡፡ በክልሉ የጂኦሎጂካል ላብራቶሪ ማቋቋም ለዘላቂ ልማት፣ ለፖሊሲ ፈጠራ እና ለክልል የመቋቋም አቅም ከፍተኛ የረጅም ጊዜ ጥቅም ያለው ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንት ሲሆን ከሚያበረክታቸው ጠቀሜታዎች መካከል የሀብት ሉዓላዊነትን እና የኢኮኖሚ ልዩነትን ያበረታታል፣ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ እቅድ መሰረት ይሰጣል፣ የማዕድን ኮሪደር ልማትን ይደግፋል፣ የአካባቢ ጥበቃን ያረጋግጣል እና የአየር ንብረት መላመድን ይረዳል፣ ሁሉም ስነ-ምህዳሮችን ለመጠበቅ ወሳኝ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ክልላዊ ፈጠራን እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚን ያበረታታል፣ ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃ ይፈጥራል፣ የሰው ካፒታል ልማትን ይጨምራል፣ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ከጂአይኤስ መድረኮች እና የውሂብ ማከማቻዎች ጋር መቀላቀል መልካም አስተዳደርን፣ ግልጽነትን እና ሴክተር አቋራጭ ትብብርን ይደግፋል የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም በዚህ ፕሮጀክት ሲከናወኑ ቁልፍ ተግባራት መካከል የላብራቶሪ ህንፃዎችን መገንባት፣ መሳሪያዎችን ግዥ መፈጸም፣ መገልገያዎችን እና የደህንነት ስርዓቶችን

(ኤሌክትሪክ፣ የቆሻሻ አወጋገድ፣ የጭስ ማውጫ መከለያዎች፣ የውሃ ማጣሪያ፣ የታመቀ አየር፣ የደህንነት ባህሪያት እና የአደጋ ጊዜ ስርዓቶች) ማቋቋም፣ ለጂኦሎጂካል ናሙናዎች እና የማጣቀሻ ቁሳቁሶች የማከማቻ ቦታዎችን መገንባት፣ ለሰራተኞች ስልጠና (የሰለጠኑ ፔትሮግራፈርቶችን እና ቴክኒሻኖችን መቅጠር፣ የስልጠና ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣ የምስክር ወረቀቶችን መስጠት) እና የስልጠና እና የመሰብሰቢያ ክፍሎችን መገንባት፡፡

### 8.1.1.7. የቤት ልማት

በክልሉ የሚኖሩ ህዝቦች በተመጣጣኝ ዋጋ ጥራት ያለው መኖሪያ ቤት ማግኘት በብዙ ታዳጊ የከተማ ማዕከላት ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ከሚያጋጥሟቸው ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ አንዱና ወሳኙ ነው፡፡ ፈጣን የከተሞች መስፋፋት፣ የህዝብ ቁጥር መጨመር እና የግንባታ ወጪ መጨመር የመኖሪያ ቤት እጥረት አስከትሏል፣ ይህም ብዙ ቤተሰቦች በተጨናነቀ እና ደረጃቸውን ባልጠበቁ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል፡፡ የቤቶች ልማት መርሃ ግብር በገበያ ላይ የተመሰረተ መኖሪያ ቤት መግዛት ለማይችሉ ዜጎች በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ዘላቂ እና ዘመናዊ የመኖሪያ ቤቶችን በመገንባት ይህንን ችግር ለመፍታት ታስቦ እየተሰራበት የሚገኝ ፕሮጀክት ነው፡፡ ይህም ሃሳብ አገራዊና ክልላዊ የልማት ግቦችን፣ የድህነት ቅነሳ ስልቶችን እና የከተማ እድሳት ፖሊሲዎችን በቀጥታ ስለሚደግፍ እንደ ዋና ፕሮጀክት ይቆጠራል፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፉን እና የስራ እድል መፍጠርን በማበረታታት ሁሉን አቀፍ እድገትን፣ ማህበራዊ መረጋጋትን እና ለዜጎች የተሻሻለ የኑሮ ደረጃን ለማሻሻል በተወሰነም ቢሆን ሲሰራ የነበር እና ቀጣይም በሰፊው የክልሉን ህዝብ የቤት ፍላጎት ለማሟላት በእቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው፡፡

የቤቶች ልማት አጠቃላይ ዋና ዓላማ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች በዘላቂ የከተማ ልማት ተነሳሽነት ተመጣጣኝ እና ጥራት ያለው መኖሪያ ቤት ተደራሽነትን ማሻሻል ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ተመጣጣኝ እና ጥራት ያለው የመኖሪያ ቤቶችን መገንባት፣ ያለፕላን ወይም መደበኛ ባልሆኑ ሰፈሮች ውስጥ የሚኖሩ ዜጎችን ቁጥር መቀነስ፣ በቤቶች እና በግንባታ ዘርፎች የሥራ ስምሪት እና የክህሎት ማጎልበት ዕድሎችን መፍጠር እንዲሁም እንደ ውሃ፣ መንገድ እና ኤሌክትሪክ ያሉ መሰረታዊ የከተማ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ማሳደግ ናቸው፡፡

ፕሮጀክቱ በክልሉ ውስጥ ባሉ የሪጂዮፖሊታን ከተሞች እንደ ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ወልዲያ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ እና ደብረ ታቦር የሚተገበር ሲሆን

በመጀመሪያ ከፍተኛ ፍላጎት ባላቸው አካባቢዎች ላይ ያተኮረ ነው። ዒላማውም ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት፣ የከተማ መሠረተ ልማት እና የማህበረሰብ ልማት በማምጣት ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች፣ በሴቶች የሚመሩ ቤተሰቦች፣ ወጣቶች እና የመንግስት ሰራተኞች የሚያካትት ሲሆን ፕሮጀክቱ በክልል መንግስት በጀት የሚደገፍ ነው። ድጋፉ የመሬት አቅርቦትን፣ የገንዘብ ድጋፍን፣ የቴክኒክ እውቀትን እና ዝቅተኛ ወለድ ያለው የመኖሪያ ቤት ብድርን ያካትታል።

ፕሮጀክቱ በመጀመሪያው ምዕራፍ ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ (ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ እያንዳንዳቸው 30,000 ቤቶች፤ ኮምቦልቻ፣ ወልዲያ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ እና ደብረ ታቦር እያንዳንዳቸው 10,000) በአጠቃላይ 140,000 የመኖሪያ ቤቶች የተገነቡ ከ 700,000 በላይ ዜጎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ዘመናዊ መኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በግንባታ እና በተዝማጅ ዘርፎች ወደ 280,000 የሚጠጉ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ስራዎችን መፍጠር 4 የሰፈር ህዝብ ቁጥር መቀነስ እና የተሻሻለ የከተማ የኑሮ ሁኔታ (የስራ እድሎች ተፈጥረዋል 280,000) መፍጠር ከመቻሉም በላይ የተጠናከረ የማህበረሰብ ኔትወርኮች እና የቤቶች ህብረት ስራ ማህበራት (መደበኛ ባልሆነ መኖሪያ ቤት ውስጥ መቶኛ ቅነሳ 50-60% በተሰራላቸው አካባቢዎች እና በሴቶች የሚመሩ ቤተሰቦች መቶኛ 60% ማድረስ ተችሏል)።

በዚህ ፕሮጀክት የክልል መንግስት የፋይናንስ ድልድል፣ ANRS የከተማ ልማት እና መሠረተ ልማት የፖሊሲ ቁጥጥር፣ የቁጥጥር ድጋፍ፣ ዲዛይን እና ግንባታ፣ የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ቅንጅት፣ የመሬት እና የጣቢያ ልማት፣ የቴክኒክ አተገባበር ድጋፍ፣ የንግድ ባንኮች/ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት የመኖሪያ ቤት ብድር እና የክፍያ ስርዓቶችን ያቀርባሉ። ህብረት ስራ ማህበራት/ ዜጎች በፋይናንስ እና በቤቶች አስተዳደር ውስጥ ተሳትፎ ይኖራቸዋል።

### 8.1.1.8. ስልጡን መንደር

የመሬት ቢሮ ባለፉት ዓመታት ከገጠር ቀበሌ ማእከላት አንፃር በተመረጡ የክልላችን ቀበሌዎች የቀበሌ ማዕከል ፕላን በማዘጋጀት በዘርፉ በሰለጠኑ ባለሙያዎች እንዲመራና እንዲከታተሉ በማድረግ በተበታተነ መልኩ ይኖር የነበረውን ማህበረሰብ በተሰባሰበ መልኩ ከተሜነትን ማስጀመር ተችሏል። የስልጡን መንደር ግንባታ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በተበታተነ መልኩ የሚኖረውን ማህበረሰብ በማሰባሰብ በፕላኑ መሰረት ግንባታዎችን እንዲያካሂድና ምቹ የመሰረተ ልማት አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል፣ መንገድንና ለከተማ ቅርበት ያላቸውን ቦታዎች

በመለየት እየተስፋፋ የመጣውን ህገወጥ ግንባታ በመከላከል ህግ የማስከበር ስራ ለመስራት ያስችላል፣ የቀበሌ ማዕከል ተጠቃሚዎች በፕላን መሰረት ሲገነቡ የመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል እንዲሁም የክልሉ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ስታንዳርዱን ሲያሟሉ ወደ ታዳጊ ማዘጋጃ ቤት እንዲሸጋገሩ ማስቻል ነው፡፡

ስራው በ2009 በጀት ዓመት የተጀመረ ሲሆን እስከ 2017 በጀት ዓመት ድረስ ለ200,883 ተጠቃሚዎች በገጠር ቀበሌ ማእከሉ ውስጥ ቦታ ተሸንሽኖ ተሰጥቷል፣ ከዚህ ውስጥ 114,166 ተጠቃሚዎች ግንባታቸውን አጠናቀዋል፣ 53,141 ተጠቃሚዎች ደግሞ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተ□ጋጅቶ ተሰጥቷል፡፡ ይህ ተግባር በምስራቅ አማራ በስፋት የተሰራበትና አጥጋቢ ውጤትም የታየበት ሲሆን በሌሎቹ አካባቢዎች በተመሳሳይ መልኩ ለማስኬድ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ መሰረት ከፕላን ዝግጅት በኋላ በ2 ቀበሌዎች፣ በበጀት ዓመቱ የ150 ገጠር ቀበሌ ማእከላትን በብሎክ ለማከፋፈል በእቅድ ተይዞ የ17 ቀበሌዎች ብሎክ የመክፈል ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈፃፀሙ ከግማሽ ዓመቱ ከ100% በላይ ሲሆን ከዓመቱ 9% ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በግማሽ ዓመቱ 3,002፣ በበጀት ዓመቱ 20,000 ቦታዎችን ሸንሽኖ ለተጠቃሚዎች ለማስረከብ ታቅዶ 1,153 ቦታዎችን ማስረከብ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከግማሽ ዓመቱ 38% ነው፡፡ ከዓመቱ 6% ነው፡፡ በግማሽ ዓመቱ 2,998፣ በበጀት ዓመቱ 20,000 ተጠቃሚዎች ግንባታ እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ታቅዶ 1,331 ግንባታቸውን አጠናቀዋል፣ አፈፃፀሙ ከግማሽ ዓመቱ 51%፣ ከዓመቱ 8% ነው፡፡ በግማሽ ዓመቱ 3,002፣ በበጀት ዓመቱ 20,000 ግንባታ ላጠናቁ ተጠቃሚዎች ቋሚ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ ለ 1,576 ገንቢዎች ቋሚ ካርታ ተሰቷል፣ አፈፃፀሙ ከግማሽ ዓመቱ 52% ሲሆን ከዓመቱ 7% ነው፡፡

### 8.1.1.9. የምርምር ስርዓቱን ማዘመን

"የግብርና ምርምር ስርዓትን ዘመናዊነት" በአማራ ክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የክልሉን የግብርና ምርምር መሠረተ ልማት፣ የሰው ሃይል እና ተቋማዊ አቅምን ለማሻሻል የተጀመረው ቁልፍ የአቅም ግንባታ ተነሳሽነት ነው። የዙህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በፍጥነት እያደገ ላለው የህዜብ ፍላጎት፣ የአየር ንብረት ተለዋዋጭነት እና የምግብ ዋስትናን፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን እና የኤክስፖርት ዕድገትን ለመደገፍ እንዲቻል የምርምር አገልግሎቶችን ተደራሽነት ማሻሻል፣ ጊዜ ያለፈባቸው መሠረተ ልማቶችን ማዘመን፣ የምርምር ሰራተኞችን ማጠናከር እና ተቋማዊ መዋቅሮችን ከታዳጊ የግብርና ቅድሚያ

ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር ማመጣጠን ነው።

ፕሮጀክቱ የሚመራው ከአማራ ክልላዊ መንግስት፣ ከግብርና ቢሮ፣ ከእንስሳት እና አሳ ሀብት ቢሮ፣ ከዩኒቨርሲቲዎች እና ከብሔራዊ የምርምር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ነው። የእውቀትን፣ የገንዘብ ድጋፍን እና ፈጠራን ለማሰባሰብ ከአለም አቀፍ የምርምር ተቋማት፣ ለጋሽ ኤጀንሲዎች እና ከግሉ ሴክተር ተዋናዮች ጋር ስልታዊ ሽርክና ይፈልጋል። እነዚህ ሽርክናዎች የቴክኒክ ጥራትን ለማረጋገጥ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን እና በምርምር ስርዓቱ ውስጥ ዘላቂነትን ለማሳደግ አስፈላጊ ናቸው።

በፕሮጀክቱ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የሰብል ዝርያዎችን ለማልማት የሚያስፈልገውን ጊዜ ከ2-3 እጥፍ መቀነስ፣ የድህረ ምረቃ መመዘኛዎች ያላቸው የምርምር ሰራተኞች ከ30-50% መጨመር እና የክልሉን ቴክኖሎጂዎችን የማመንጨት፣ የማላመድ እና የማስተላለፍ አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ማስፋፋትን ያካትታል። ፕሮጀክቱ የምርምር ስርዓቱ የክልሉን 33% የብሔራዊ እርሻ ድርሻ፣ 32% የሰብል ምርት እና 30% የእንስሳት ምርትን በዘመናዊ ምላሽ ሰጪ እና ያልተማከለ የምርምር ስርዓት እንዲደግፍ ያስችላል። እንዲሁም በአመጋገብ-ተኮር ግብርና እና የአየር ንብረትን የሚቋቋም ፈጠራ ላይ ወሳኝ ክፍተቶችን ለመፍታት ይሰራል።

## 8.1.1.10. የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ

የክልሉ በጦርነት የተጎዱ ቦታዎች መልሶ መገንባትና ማቋቋም ፈንድ ጽህፈት ቤት በክልሉ መንግስት ፈንድ፣ በአለም ባንክ እና በዩኤንዲፒ የሰላም ድጋፍ ፕሮግራሞች ድጋፍ ከቢሮዎች እና ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በመተግበር ላይ ይገኛል። በተለይም ከ2015 ጀምሮ የክልሉ መንግስት ከግጭቱ ተፅእኖ ለማገገም እና በሁሉም የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ግንባታ ጥረቶች ግንባር ቀደም ለመሆን በክልሉ በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች ለመልሶ ማቋቋም እና መልሶ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየዓመቱ በጀት በመመደብ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

የተመረጡት የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ግንባታ ዘርፍ ፕሮጀክቶች ጂኦግራፊያዊ ወሰን ሁሉንም ዞኖች እና የሜትሮፖሊታን ከተማን በክልሉ ወረዳዎች እና የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ይሸፍናል። የእነዚህ ፕሮጀክቶች ዘርፍ በትምህርት፣ በጤና፣ በውሃ እና ኢነርጂ፣ በጉልበት እና በክህሎት፣ በግብርና፣ በእንስሳት እና በአሳ ሀብት፣ በሴቶች፣ በወጣቶች እና በማኅበራዊ ጉዳዮች፣ በሰላምና በደህንነት፣ በፖሊስ፣ በማረሚያ ቤት፣ በፍትህ፣ በጠቅላይ

ፍርድ ቤት እና በሚሊሻ ጽ/ቤት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

2015 እስከ 2017 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 192 ፕሮጀክቶች እንደገና ተገንብተዋል፡፡ ለ2018 የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች ለመልሶ ማቋቋም እና መልሶ ግንባታ ፕሮጀክቶች ብር 1.5 ቢሊዮን መድቧል፡፡ የበጀት ዓመቱ የመልሶ ማቋቋም እና የመልሶ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ጉዳት እና አስቸኳይ የህዝብ አገልግሎት ፍላጎት ባላቸው 15 ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቢሮዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

በፕሮጀክቱ ከተገኙ ወጤቶች መካከል ለታካሚዎች የጤና አገልግሎት ለመስጠት የተበላሹ የጤና ጣቢያዎችን እና ሆስፒታሎችን እንደገና ተገንብተዋል፤ ህጻናት የትምህርት ተደራሽነት እንዲኖራቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እንደገና ተገንብተዋል/ታድሰዋል፤ የተበላሹ የTVET ኮሌጆች፣ ኤፍቲሲዎች እና የመዋዕለ ሕፃናት እንደገና ተገንብተዋል፣ ማህበረሰቡን ለማገልገል ሁለት የተበላሹ የእንስሳት ላቦራቶሪዎችን፣ የቴክኒክ ትምህርት ኮሌጆችን እና የማቆሚያ ማዕከላትን እንደገና ተገንብቷል፣ ተንቀሳቃሽ የውሃ መገልገያዎች ታድሰዋል፣ የይስማ-ንጉስ የባህል ሙዝየም ተጠግኗል፣ ማህበረሰቡን ለማገልገል የወረዳ እና የዞን የሰላም እና የደህንነት ቢሮዎችን እንደገና ተገንብተዋል፤ የፖሊስ ኮሌጅ እና የፖሊስ ጣቢያዎችን እንደገና ገንብቶ ለፖሊስ መኮንኖች የሥልጠና ማዕከላት ሆነው እንዲሰሩ እና የአካባቢ ፖሊስ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲችሉ ተደርጓል፣ የፍትህ ቢሮዎችን፣ የማረሚያ ቤት ተቋማትን፣ ሚሊሻ ቢሮዎችን እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶችን ለማህበረሰቡ ፍትህ ማድረስ እንዲችሉ ታድሰዋል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በበጀት አመቱ ፕሮጀክቶቹ የሚከናወኑት በአማራ ክልል ቢሮዎች ሲሆን ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ፣ ትምህርት ቢሮ፣ ግብርና ቢሮ፣ እንስሳት እና አሳ ሀብት ልማት ቢሮ፣ ጤና ቢሮ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ማረሚያ ቤት፣ ሰላምና ደህንነት ቢሮ፣ ሚሊሻ ጽህፈት ቤት፣ ፍትህ ቢሮ፣ ባህልና ቱሪዜም ቢሮ፣ ውሃ እና ኢነርጂ ቢሮ፣ የስራና ስልጠና ቢሮ እና የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ነው፡፡

## 8.1.2. የፌዴራል ፍላግሽፕ ፕሮጀክቶች

### 8.1.2.1. የገጠር ኢንዱስትራላይዜሽን

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር ለመሳለጥ ወሳኝ ሚና ያለው ዘርፍ ሲሆን ባለፉት አመታት የውጪ ምንዛሪ ግኝት፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት

መሳብ፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እና ዘላቂ የሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋፅኦ እያደገ ይገኛል። ይህን ለማስቀጠልና ወደተሻለ አፈፃፀም ለማሳደግ ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱ ስራዎች አንዱ በገጠሩ አካባቢ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የማቋቋምና የማስፋፋት ስራ ነው። ለዚህም በ2017 ዓ.ም የገጠር ኢንደስትሪላይዜሽን ኢኒሼየቲቭ ሰራ ለመጀመር እንቅስቃሴ ላይ ነን። መንግስት ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በሰጠው ትኩረት ምቹ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መቀረጹ፣ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም እቅድ፣ የሌማት ቱሩፋት፤ የ10 አመት የልማት እቅድ፣ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማት ፍኖተ ካርታ፣ ኢንዱስትሪያላይዜሽን ኢኒሼየቲቭ እና የተለያዩ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችና የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ተገብቷል። ይህን መነሻ በማድረግ በ2017 ዓ.ም በሀገሪቱ ገጠር አከባቢዎች የሚገኙትን እምቅ ሀብቶች ላይ እሴት በመጨመር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋምና እንዲስፋፉ የገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ኢንሽቲቭ በማዘጋጀት ወደ ስራ ተገብቷል።

የፕሮጀክቱ በክልሎች/ከተማ አስተዳደር ያሉ የዘርፉ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት በገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ዙሪያ የጋራ የሆነ ግንዛቤ በመያዝ የአከባቢዉን ዕምቅ ሀብት መሰረት በማድረግ በገጠር መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ በመደገፍ የገጠር ኢንዱስትሪላይዜሽን ኢኒሸየቲቭን ማስፈጸም ነዉ።

በመሆኑም በገጠር መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝች፣ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ህብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒየኖች፣ ሀብት ያፈሩ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች፣ የዩኒቨርሲቲ እና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን፣ በሌሎች ዘርፎች የተሰማሩ ባለሀብቶች እና የገጠሩ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች የገጠር ኢንዱስትራላይዜሽን የሚያካትታቸዉ እና ተጠቃሚ ሲሆኑ አብዛኞቹ በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ የሚከወኑ ወይም የሚተገበሩ ናቸዉ። በገጠር የተቋቋሙ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር፣ የስራ እድል ፈጠራ፣ የሀገር ውስጥ ምርትና ምርት ዕሴት ጭማሪ እና የፋይናንስ አቅርቦት መሻሻል የገጠር ኢንዱስትራላይዜሽን መዳረሻና መለኪያ ተግባራት ናቸዉ።

## 8.1.2.2. የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት

የአማራ መስኖ ስንዴ ማጠናከሪያ ፕሮጀክት (AIWIP) የክልሉን ሰፊ የመስኖ አቅም በመጠቀም በስንዴ ራስን መቻልን ለማሳካት፣ የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን ለመደገፍ የተነደፈ ትልቅ እና ለውጥ እያመጣ ያለ ፕሮጀክት ነው። አማራ ከ2 ሚሊዮን

ሄክታር በላይ ለመስኖ ተስማሚ የሆነ መሬት ቢኖርም በአሁኑ ጊዜ ለመስኖ ስንዴ የሚውለው መሬት በጣም አነስተኛ ነው። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ AIWIP የመስኖ መሠረተ ልማትን የማሻሻል፣ በፀሃይ ሃይል የሚንቀሳቀሱ እና በስበት ኃይል የሚመገቡ የመስኖ ስርዓቶችን ተግባራዊ የማድረግ እና የአየር ንብረት-መልካም የግብርና ልምዶችን የማበረታታት ስራ ያከናውናል።

ፕሮጀክቱ 50,000 አርሶ አደሮችን፣ ወጣቶችን እና በሴቶች የሚመሩ የህብረት ስራ ማህበሮችን ማሰልጠን፣ 150 የመስኖ ህብረት ስራ ማህበራት እና 30 የሜካናይዛሽን አገልግሎት ማዕከላት በማቋቋም የመስኖ ስንዴ ሽፋን ወደ 250,000 ሄክታር በማስፋፋት በሄክታር ከ32 ወደ 55 ኩንታል ምርት ማሳደግ ነው።

ፕሮጀክቱ በአራት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በሶማሌ እና በአፋር ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን እነዚህ ክልሎች የተመረጡት በሚከተሉት መመዘኛዎች ላይ በመመርኮዜ ነው ሀ) ለስንዴ ምርት ምቹ የሆነ አግሮ- ኢኮሎጂ; ለ) በክላስተር እርሻ ላይ ሰፊ ልምድ; እና ሐ) ከፕሮጀክቱ ጋር ተዚማጅነት ያላቸው ኢኮኖሚያዊ እና የገበያ እድሎች መኖራቸው ናቸው። መርሃግብሩ የሚያተኩረው ለሁለቱም አቢዮቲክ እና ባዮቲክ ጭንቀቶች የሚቋቋሙ የተሻሻሉ የስንዴ ዝርያዎችን በሳይንስ ላይ ከተመሰረቱ የግብርና ልምዶች ጋር ተዳምሮ በመጠቀም ላይ ነው። ለታዳጊ የዝገት ዘሮች ምላሽ ለመስጠት አዳዲስ ዝርያዎችን ቀጣይነት ያለው ማልማት እና አዲስ የተለቀቁ ተከላካይ ዝርያዎችን መቀበል መደገፍ አነስተኛ ባለቤቶች የዝገት ተግዳሮቶችን እንዲቆጣጠሩ እና ለዝገት ተጋላጭ በሆኑ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከፍተኛ ምርት እንዲኖራቸው ይረዳል። የተቀናጀ የተባይ አስተዳደር (አይፒኤም) ኢኮኖሚያዊ፣ የጤና እና የአካባቢ አደጋዎችን በሚቀንስ መልኩ ተባዮችን ለመቆጣጠር ባህላዊ፣ አካላዊ፣ ኬሚካላዊ እና ባዮሎጂካል ዘዴዎችን የሚያጣምር አካሄድ ነው።

### 8.1.2.3. የገጠር ኮሪደር

እንደ ሃገር የከተሞች የኮሪደር ልማት በከተሞች ብቻ ታጥሮ እንዳይቀር እና የገጠሩ ህዝብ ልክ እንደ ከተማው የኮሪደር ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የገጠር ኮሪደር ልማት በመጀመር እና የገጠሩን አርሶ አደር ህይወት ማሻሻልና የገጠር ሽግግር ማምጣት የአጠቃላይ ኢኮኖሚ እደገት ሪፎርም ግቦች በመሆናቸው የሁለም ባለድርሻ አካላትን ርብርብ ይጠየቃል። የገጠር ኮሪደር ልማት የአርሶ አደሩን ህይወት ለማሻሻል የተቀረጸ ፕሮግራም ሲሆን ዋና አላማውም የገጠሩን ህብረተሰብ በራሱ አቅም ዘላቂነት እና ቀጣይነት ያለው የኑሮ መሻሻል እንዲያመጣ የሚያስችል

እና የገጠር ሽግግርን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በገጠር መሰረተ ልማትን ማለትም መንገድ፣ ድልድይ፣ የንጹህ መጠጥ ዉሃ፣ የሀይል አቅርቦት የጤና እና ትምህርት ተቋማት የመሳሰሉትን ማስፋፋትን ይመለከታል፡፡ በጥቅሉ ተወስዶ ሲታይ ዘላቂነት ያለው የማህበረሰብ እድገት ማምጣት የአርሶ አደሩን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል እና በገጠር እና ከተማ ያለውን የልማት ክፍተት ለመሙላት ከፍ ሲልም የሀገራችንን የረጅም ጊዜ የዜጎች እድገት እና ግብን ለማሳካት ማዕከል ያደረገ የልማት አቅጣጫ ነው፡፡ በመሆኑም በአማራ ክልልም ይህን የገጠር የኮሪደር ልማት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም እና የገጠሩን ህዝባችንን የአኗኗር ዘይቤ ለመቀየርና አጠቃላይ የአኗኗር፣ የባህል ለውጥ ለማምጣት የገጠር ኮሪደር ልማት ምንነት እና የአፈፃፀም አቅጣጫ በሰነድ በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ፈጥሮ ወደ ስራ መግባት ወሳኝ ነዉ፡፡

ፕሮጀክቱ በክልሉ በሚገኙ በተመረጡ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና የገጠር ቀበሌዎች የሚሸፍን በተዘጋጀላቸው ፕላን መሰረት ብሎክ መክፈት፣ ቦታ የመሸንሸንና ለተጠቃሚ ማስተላለፍ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመስጠት፣ እንዲሁም ወደ ታዳጊ ማዘጋጃ ቤት እንዲሸጋገሩ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራዎችን ያጠቃልላ፡፡ በተዘጋጀው ፕላን መሰረት አብዛኛው የቀበሌ ማዕከል ተጠቃሚ በሚኖርባቸው የመሰረተ ልማት አቅርቦት (መንገድ፣ ውኃ፣ መብራት…) እንዲሟሉ መከታተል፣ በተመረጡ የገጠር ቀበሌዎች እና ወረዳዎች ላይ ህገ ወጥ የቤት ግንባታን በመከላከል ህግ የማስከበር ስራ መስራት ነው፡፡

የቴክኖሎጂ እና የዕውቀት ሽግግር በማምጣት የሀገራችንን እድገት ለማገዝ የሚከተለትን ውጤት ያመጣል የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ዕድገት በማሻሻል የነዋሪዎችን ህይወት ይለውጣል፤ የአካባቢ ሥነ-ምህዳር መከላት በማሻሻል እና እድገታቸውን በአግባቡ በመምራት ለአካባቢው ዘላቂ እድገት መሠረት ይጥላል፣ ለአካባቢው ነዋሪዎች የገበያና የአገልግሎት ማዕከል በመሆን ሁለንተናዊ ልማትን ያፋጥናል፣ የአስተዳደር ማዕከል በመሆን የፍትህ አሠጣጥን ተደራሽ ያደርጋል፣ ያልተማከለ አስተዳደርንም ያጠናክራል፣ መንግስት የተበታተነውን የገጠር ነዋሪ በእያለበት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ለማዳረስ የሚያወጣውን ከፍተኛ ወጭ በአንድ ማዕከል እንዲገነባ በማድረግ ያለንን ውስን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል፣ የመኪና መንገድን ተከትለው በየቦታው በመቆርቆር ለመሬት ወረራ እና መጎሳቆል የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ይረዳል፣ ፍትሀዊ የመሰረተ ልማትና የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ያስችላል፣ የገጠሩን ነዋሪ የቤት አያያዝና የአኗኗር ዘይቤ

ወደ ከተማነት ለመቀየር ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታል፣ ገጠሩና ከተማው ተደጋግፈውና ተመጋግበው እንዲያድጉ የጎላ ሚና ይጫወታል፣ የገጠር ነዋሪው ልዩ ልዩ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ የሚያደርገውን ረዥም ጉዞ በማስቀረት በአካባቢው እንዲያገኝ በማድረግ ጊዜና ገንዘቡን እንዲቆጥብ ያደርጋል እና ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሰት ምክንያት በትልልቅ ከተሞች የሚፈጠረውን ከፍተኛ የህዝብ መጨናነቅና ስራ እጥነት ቁጥር የመጨመር ጫና ይቀንሳል፣ ወዘተ…

የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ኮሪደር ልማት መተግበር አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በክልላችን በተበታተነ መልኩ የሚኖረውን አርሶ አደር ወደ አንድ ቀበሌ ማዕከል በማሰባሰብ በፕላን እንዲመሩ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የትኩረት አቅጣጫ መሆኑ፣ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት በፕላን የማይመሩ በመሆናቸዉ በአካባቢያቸዉ ያለዉን ለም የእርሻ መሬት እና በደን የተሸፈነ መሬት በመሸማት ለአካባቢ ሥነ-ምህዳር መዛነፍ ምክንያት እየሆኑ በመምጣታቸዉ ይህንን ከወዲሁ ለመግታት የአሁኑን ትውልድ በሃብት የመጠቀም ፍላጎት ጥያቄ ውስጥ ሳያስገባ ነገር ግን መሬትን በቁጠባ እና እሴት በሚፈጥር መልኩ እየተጠቀሙ የቀጠዩን ትውልድ በዘላቂነት የመጠቀም ዋስትና ማረጋገጥ፣ በተበታተነ መልኩ የሚኖረውን አርሶ አደር ወደ አንድ ማዕከል በማሰባሰብ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ተደራሽ ማድረግ፣ የገጠር ቀበሌ ማዕከላቱ ከወዲሁ በፕላን እንዲለሙ ማድረግ ወደፊት ወደ ከተማነት አድገው በዝርዝር በከተማ ፕላን እንዲመሩ ሲደረግ የሃብት ብክነትን ለመቀነስ ስለሚያስችሉ እና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሆነው እንዲያድጉ ለማስቻል ሲሆን እነዚህን አላማዎች ለማሳካት የሚመለከታቸው ባለድርሻና አጋር አካላት ተቀናጅተውና ተሳስረው በዚህ ረገድ የታቀዱትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 8.1.2.4. የከተማ የኮሪደር ልማት

በአማራ ክልል ያሉ አብዛኛዎቹ ከተሞች የመሠረተ ልማት እጥረት፣ ከፍተኛ ስራ አጥነት፣ የተጨናነቀ እና ያለ ፕላን የተሰሩ ወይም መደበኛ ያልሆኑ ሰፈሮች፣ የትራንስፖርት ችግሮች እና የአካባቢ ጉዳዮች ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ውስብስብ የከተማ ችግሮች ለመቅረፍ አቅዶ የከተማ መስፋፋት ሽግግር እና እንደ ኮሪደር ልማት ያሉ አዳዲስ ሀሳቦችና መፍትሄዎችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የኮሪደር ልማት ፈጣን የከተማ እድገትን እና የህዝብ ቁጥር መጨመርን ለመቆጣጠር እንዲሁም በክልሉ ከተሞች ውስጥ እየጨመረ የመጣውን የትራንስፖርት እና የመሠረተ ልማት ፍላጎት ለማሟላት ወሳኝ በመሆኑ እንደ ዋና ተግባር

በመያዝ ተግበራዊ ማድረግ ግድ ይላል። ይህም ከተሞችን ለማዘመን፣ ለኑሮ እና ለነዋሪዎች ምቹ አካባቢዎችን ለመፍጠር ያለመ ስልታዊ የከተማ ፕላን አካሄድ ነው።

የኮሪደር ልማት ዋና ግብ በታቀዱ እና በተቀናጁ የልማት ስራዎች የከተሞችን አጠቃላይ እድገት ማሳደግ ሲሆን ዋና ዋና አላማዎች ደግሞ የተደራጁ መንገዶችን እና አረንጓዴ ቦታዎችን በማዘጋጀት የከተማ ውበትን ማሳደግ እና ለነዋሪዎች እና ለጎብኚዎች ማራኪ አካባቢ መፍጠር፤ የመንገዶችን፣ የውሃ አቅርቦትን፣ ኤሌክትሪክን እና የፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓቶችን በማሻሻል እና በማስፋፋት የወደፊት የከተማ እድገትን የሚደግፍ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት፤ ለንግድ እና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን በማቅረብ የኢኮኖሚ ልማትን ማሳደግ፣ የስራ እድል በመፍጠር እና የዜጎችን ገቢ ማሳደግ፤ የዜጎችን የኑሮ ጥራት ለማሳደግ እና ማህበራዊ ፍትሃዊነትን ለመደገፍ ማህበራዊ አገልግሎቶችን (የጤና እንክብካቤ፣ ትምህርት፣ መዝናኛ) ማሻሻል እንዲሁም በዘላቂ የልማት አቀራረብ አካባቢን መጠበቅ፣ አረንጓዴ ቦታዎችን መፍጠር እና የአየር ብክለትን መቀነስን ያካትታል።

የኮሪደር ልማት ቁልፍ ተግባራት ከሚያካትታቸው ተግባራት መካከል የመሠረተ ልማት የእግረኛ እና የብስክሌት መንገዶችን ጨምሮ ዋና መንገዶችን መገንባት፣ ማሻሻል እና የውሃ አቅርቦት፣ ኤሌክትሪክ፣ ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓቶችን ማዳበር፤ የኢኮኖሚ ልማት የኢንቨስትመንት እና የንግድ እድሎችን መፍጠር፣ የስራ እድል መፍጠርን ማስተዋወቅ፣ የቱሪስት መስህቦችን ማሻሻል አና ማህበራዊ እና የከተማ ፕላን የማህበረሰብ ተሳትፎን ማጠናከር፣ ዘመናዊ የከተማ አቀማመጦችን ከተቀናጀ የንግድ እና የመኖሪያ አካባቢዎች መንደፍ፣ ዘላቂ የልማት ልምዶችን መተግበር እና ሌሎች ተያያዥ የአካባቢ ልማቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በፕሮጀክቱ ከተገኙ ውጤቶች መካከል የተለወጠ የከተማ ገፅታ፣ ለነዋሪዎች ዘመናዊ፣ ምቹ እና ማራኪ የኑሮ ሁኔታን በማቅረብ፣ ቱሪዝምን ያሳድጋል፤ ለመንገድ፣ ለውሃ፣ ለቴሌኮሙኒኬሽን፣ ለኤሌክትሪክ እና ለፍሳሽ ማስወገጃ የተሻሻለ እና የተስፋፋ መሠረተ ልማት፤ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፣ የንግድ ልማትን በማበረታታት እና የስራ እድሎችን በመፍጠር የተፋጠነ የኢኮኖሚ እድገት፤ የተሻለ የማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነት እና ለዜጎች የተሻሻለ የኑሮ ጥራት፤ የትራፊክ መጨናነቅ መቀነስ እና የበለጠ ቀልጣፋ የሰዎች እና የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ምቹ፣ አረንጓዴ ቦታዎችን በመፍጠር እና የአየር ብክለትን በመቀነስ የአካባቢ ጤናን ማሻሻል ተጠቃሾች ናቸው።

የዚህ ልማት ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ የተለያዩ ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን (ትራንስፖርት፣ መኖሪያ ቤት፣ ንግድ እና ማህበራዊ) በአጠቃላይ እና ባለብዙ ሞዳል ማዕቀፍ ውስጥ በማዋሃድ ዘላቂ የከተሞች መስፋፋትን ማሳደግ ነው፡፡ ይህ ሰነድ ራሱ የልማት ጥራት እና አቅጣጫ ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊ መመሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በመጨረሻም የክልሉን ከተሞች ለኑሮ፣ ለስራ እና ለመዝናኛ ተስማሚ ያደርገዋል፡፡ ስኬታማ እና ዘላቂ ትግበራ የዘላቂ ልማት መርሆዎችን ማክበር፣ ጠንካራ አመራር፣ ግልጽ የመሬት አስተዳደር ስርዓት እና ከሌሎች ብሄራዊ ፖሊሲዎች እና የህግ ማዕቀፎች ጋር የተቀናጀ እቅድ ማውጣትን ይጠይቃል፡፡

### 8.1.2.5. አረንጓዴ አሻራ

በአማራ ክልል ውስጥ ስነ-ምህዳሮችን ወደ ነበረበት መመለስ እና የአየር ንብረት መቋቋምን መገንባት (REBCRA) የተበላሹ መልክዓ ምድሮችን ለማደስ፣ የስነ-ምህዳር አገልግሎቶችን ለማጠናከር እና የአየር ንብረትን የማቋቋም መተዳደሪያዎችን ለመደገፍ የተነደፈ ባለራዕይ እና ለውጥ ፈጣሪ ፕሮጀክት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ የሚከናወነው በአማራ ግብርና ቢሮ፣ እንስሳት ቢሮ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ ደን ኢንተርፕራይዝ እና አራሪ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚ ማህበራት፣ ከወጣቶች እና የሴቶች ህብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የልማት አጋሮች እንደ MoA፣ GIZ እና UNDP ጋር በመተባበር ነው፡፡ ፕሮጀክቱ የመሬት መራቆት፣ የደን ጭፍጨፋ እና ተደጋጋሚ ድርቅ ሲገጥም ፕሮጀክቱ የተበላሹ መሬቶችን ወደነበረበት ለመመለስ፣ ከ2 ቢሊዮን በላይ ዚፎችን ለመትከል እና በየዓመቱ 2,000 ሚሊዮን ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ችግኞች የሚያመርቱ 400 ዘመናዊ ችግኞች ጣቢያዎች ይቋቋማሉ፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትሩ በ2013 የተጀመረው የኢትዮጵያ አረንጓዴ ሌጋሲ ኢኒሼቲቭ የደን ጭፍጨፋን ለመዋጋት፣ የአካባቢ ዘላቂነትን ለማሳደግ እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዘፎችን በመትከል የአየር ንብረት ለውጥን ለመቅረፍ ያለመ ነው፡፡ ምንም እንኳን ብሄራዊ መርሃ ግብር ቢሆንም እንደ አማራ ክልል በሀገሪቱ በሕዝብ ብዛት እና በሥነ-ምህዳር የተለያየ አካባቢ ያለው አንዱ ነው፡፡ የአረንጓዴ ሌጋሲ ኢኒሼቲቭ የደን ጭፍጨፋን እና የመሬት መራቆትን ለመቅረፍ በኢትዮጵያ መንግስት የተጀመረ መጠነ ሰፊ የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም ሲሆን የአካባቢ ዘላቂነትን ያሳድጋል፡፡ በሰሜናዊ ኢትዮጵያ የሚገኘው የአማራ ክልል በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራ ቢሆንም በተለይ በግብርና ጠቀሜታ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት እና ስነ-ምህዳሮችን ወደነበረበት የመመለስ አስፈላጊነት የተነሳ ጉልህ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ደኖችን ወደነበረበት በመመለስ፣ የአፈርን ጤና በማሻሻል እና የአየር ንብረት ለውጥን ተፅእኖ በመቀነስ

ላይ አተኩሮ ይሰራል።

በመሆኑም ፕሮጀክቱ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ GL-REBCRA የአግሮ ደን ልማት ስርዓቶችን የማስፋት፣ የውሃ ተፋሰስ አስተዳደርን የማሳደግ፣ የአፈር እና የውሃ ጥበቃ እርምጃዎችን የማዋሃድና እና ከ300,000 በላይ አረንጓዴ ስራዎችን የሚያመነጩ አረንጓዴ ንግዶችን እና ኢኮ-ኢንዱስትሪዎችን የማስዋወቅ ተግባራትን ለማከናወን ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ የገባ ፕሮጀክት ነው። ጂአይኤስ እና የርቀት ዳሰሳን ጨምሮ የላቁ ዲጂታል ክትትል መሳሪያዎች በአካባቢ እድሳት እና በካርቦን ቀረጻ ላይ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ስራም ያከናውናል።

### 8.1.2.6. የትምህርት ቤት ምገባ

የትምህርት ቤት ምገባ በማሻሻል የመቅረትን ምጣኔ በመቀነስ እና የትምህርት ፍትሃዊነትን በመደገፍ በኩል ከፍተኛ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በተለይ በገጠር፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ፣ በአርብቶ አደር እና በድርቅ በተጠቁ ክልሎች ብዙ ህጻናት በረሃብ ይማራሉ ወይም በቤተሰብ የምግብ እጦት ምክንያት ያቋርጣሉ። የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና ማይክሮ ኢለመንቶች እጥረት የእውቀት (ኮግኒቲብ) እድገትን፣ ትኩረትን እና የረጅም ጊዜ የጤና ችግር ያመጣል። የሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ ኢንሸቲብ ልጆች በትምህርት ቤት መደበኛ እና የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ በማድረግ የትምህርት እና የአመጋገብ ስርዓቶችን ማሳደግ ነው። ይህ ፕሮግራም በቀጥታ መመገብን፣ ማቆየትን፣ የጾታ እኩልነትን ይደግፋል፣ እና የልጆችን የመማር ችሎታ ያሻሽላል። እንዲሁም ለአካባቢው ማህብረተሰብ የምግብ አቅርቦት እድሎችን ይፈጥራል፣ ትምህርት ቤቶችን ከገበሬዎች እና ከአካባቢው ገበያዎች ጋር በማስተሳሰር የአካባቢን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት እና ጠንካራ የምግብ ስርዓትን ለመገንባት ያስችላል።

በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ እና ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ወጥ የሆነ እና የማይቋረጥ የትምህርት ቤት ምገባን በማረጋገጥ የተማሪዎችን ጤና፣ አመጋገብ እና የትምህርት ውጤቶችን ለማሻሻል በሀገር ደረጃ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የሚከተሉት ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች አሉት። የተማሪዎችን ምገባ እና የትምህርት ክትትልን ለማሳደግ፤ ልጆች በትምህርት ቤት እንዲቆዩ ለማድረግ፣ የመማር ማስተማር ውጤታማነትን ማለሻሻል፤ የህፃናት የአመጋገብ ጤናን ለመጠበቅ፤ የአካባቢ የምግብ ስርዓቶችን እና የኑሮ ሁኔታዎችን ለማጠናከር፤ ዘላቂ እና ሊሰፋ የሚችል ስርዓቶችን ለመገንባትና ቅንጅታዊ አሰራርን፣ የገንዘብ ድጋፍ ዘዴዎችን እና የመንግስት ባለቤትነትን ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው እና በግጭት በተጎዱ ዞኖች ውስጥ ያሉ ቅድመ-መጀመሪያ ደረጃ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መሰረት ያደረገ ሲሆን ደረጃ በደረጃ የክልል የልቀት ሞዴልን በመጠቀም ሽፋንን ቀስ በቀስ ማስፋፋት፤ ለሴቶች ልጆች፣ ለአካል ጉዳተኞች ልጆች እና የምግብ ዋስትና ለሌላቸው ቤተሰቦች ቅድሚያ መስጠት ሲሆኑ የምግብ አቅርቦትን በተመለከተ ከአካባቢው ገበሬዎች፣ ከህብረት ሥራ ማህበራት እና ከሴቶች ማህበራት የሚቀርቡትን ግብአቶች በመጠቀም ነው፡፡

በፕሮጀክቱ ከተገኙ ውጤቶች መካከል ተማሪዎች በተሻለ ትምህርት ላይ የመገኘት እና የመቆየት ሁኔታን ለማሳደግ አስችሏል (በተለይም በሴቶች መካከል የትምህርት ማቋረጥ መቀነስ)፤ የመማርና ማስተማርን ሂደቱን ለማሻሻል፤ የተሻለ የክፍል ተሳትፎ እና አፈፃፀም፤ ረሃብ እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ለመቀነስ እና ጤናማና የበለጠ ንቁ ተማሪዎች ለማግኘት ያግዛል፡፡ በፕሮጀክቱ ዘሪያ የተከናወኑ ተግባራት አህዛዊ መረጃ ስላልተላከ ማካተት አልተቻለም፡ ፡

በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም በሰው ልጅ ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ነው፡፡ ልጆች በየቀኑ ገንቢ ምግቦችን እንዲያገኙ በማድረግ ኢትዮጵያ በትምህርት ዘርፉ ያቀደችውን አቅድ ማሳካት ያስችላታል፣ የተማሪዎችን ጤናና ደህንነትን ያሻሽላል፣ እንዲሁም የአካባቢውን የግብርና ልማት ለማነቃቃት ያስችላል፡፡ ይህ ስትራቴጂካዊ አላማ ሊሰፋ የሚችል እና የቀጣዩን ትውልድ የወደፊት ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚረዳ ስትራቴጂካዊ ግብ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡

### 8.1.2.7. ትምህርት ለትውልድ

የህዝብ ንቅናቄን ማጠናከር፣ ማህበረሰቡ የትምህርት ቤት ደረጃዎችን እንዲከታተል እና አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ፣ ትምህርት ቤቶችን ይበልጥ ተስማሚ በማድረግ የትምህርት ጥራትን ማሻሻል እና ሁሉም እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት እና ያቋረጡ ህጻናት ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በክልላችን ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች የሏቸውም፡፡ ለምሳሌ በአካባቢው ከሚገኙት 9,604 አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (EMIS, 2015 E.C.) 58.3% የውሃ እጥረት፣ 22.9% የመጸዳጃ ቤት ችግር፣ 78.6% የመብራት ችግር፣ 57.2% የቤተ-መጻህፍት ችግር፣ እና 95.38% የአይሲቲ ቤተ-ሙከራ የሌላቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከ685 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 28.5% ውሃ የሌላቸው፣ 8.9% የመጸዳጃ ቤት፣ 36.5%

የመብራት ችግር፣ 34.5% የቤተ-መጻህፍት ችግር፣ እና 54% የአይሲቲ ቤተ-ሙከራ የሌላቸው ናቸው፡፡የትምህርት ለትውልድ ኢንሼቲቭ ፕሮግራም በትምህርት ጥራት፣ ፍትሃዊነት እና አስፈላጊነትን በማጠናከር ላይ ያተኮረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በክልሉ ለሚገኙ ህጻናትና ወጣቶች የትምህርት ጥራትን በማጠናከር ላይ ነው፡፡ መርሃግብሩ ከቅድመ ልጅነት እና ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ሽግግር ድረስ ያለውን ይሸፍናል፡፡ በተለይም በመሰረታዊ ትምህርት (ከ1ኛ- 4ኛ ክፍል) ማንበብና መጻፍ፣ የቁጥር እና ዋና የመማር ችሎታዎች መለየት፤ የመምህራን አቅም እና ሙያዊ እድገት - ስልጠና መስጠት፤ ሁሉን አቀፍ እና ፍትሃዊ ተደራሽነት ማሳደግ (የገጠር ትምህርት ቤቶችን፣ ልጃገረዶችን እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ቅድሚያ መስጠት) ለህይወት፣ ለስራ እና ለዜግነት ስልጠና ምስጠት ናቸው፡፡

በቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል የተሻሻለ የመሠረታዊ ማንበብና መፃፍ ማስቻል፤ በት/ቤት ላይ በተመሠረተ ሲፒዲ፣ በአማካሪነት እና በማሰልጠን የመምህራን የማስተማር ውጤታማነትን ማሳደግ፡፡ በከተማ እና በገጠር ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን የመማር ማስተማር ልዩነት መቀነስ፣ እና ልጃገረዶች እና አካል ጉዳተኛ ልጆችን ማካተት፤ የተሻሻሉ የመማሪያ አካባቢዎች፤ በቂ ቁሳቁሶች፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ ቦታዎች እና የቴክኖሎጂ ትምህርት ድጋፍ እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡ የትምህርት ለትውልድ ኢንሼቲቭ መርሃ ግብር ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የመንግስት ተቋማትን፣ የልማት አጋሮችን፣ የማህበረሰብ መዋቅሮችን እና የግሉ ሴክተርን የተቀናጀ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ለትምህርት ውጤታማነት እና የሥርዓት አቅምን ለማሻሻል ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

#### 8.1.2.8. ማዕድ ማጋራት

ማዕድ ማጋራት መደጋገፍን፣ አንድነትንና መተሳሰብን የሚያጎላ መልካም እሴት ሲሆን በዚህም የህብረተሰቡን፣ የባለሀብቱን እና የአጋር አካላት አቅም በማስተባበር በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ዜጎች በዘላቂነት ራሳቸውን የሚችሉበት አማራጮችን በማስፋት ሀገራቸውን በእውቀታቸውና በጉልበታቸው ያገለገሉ አረጋውያን፣ እናቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ማገዝና መደገፍ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በ6 ወሩ የክረምት በጎ ፍቃድ አማካኝነት 500,000 ለሚሆኑ ድጋፍ/ ማዕድ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ለማጋራት እቅድ ተይዞ ለ470,464 የህብረተሰብ ክፍሎች በማዕድ ማጋራት ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻፀሙ ከዕቅዱ ጋር ሲነጻፀር 94.09% ነው፡፡

በተጨማሪም በበጋ በጎ ፍቃድ 24 ኩንታል ምግብ ነክ ቁሳቁሶች በማሰባሰብ 1,607 (ሴት 1,114) የቁሳቁስ እንዲሁም በተመሳሳይ ለ1,517 (ሴት 759) የህብረተሰብ ክፍሎች የማዕድ ማጋራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ቀን ምክንያት በማድረግ ጧሪና ደጋፊ ለሌላቸው አቅመ ደካማ አረጋዊያን በዓሉን ምክንያት በማድረግ ለ1,339 (ሴት 763) አረጋዊያን ቋሚ ድጋፍ፣ ለ17,568 (ሴት 9,671) አረጋዊያን ጊዜያዊ የገንዘብና የአይነት ድጋፍ እና ለ10,467 (ሴት 5,170) አረጋዊያን ማዕድ ማጋራት ተችሏል።

## 8.1.2.9. የሌማት ትሩፋት

የሌማት ቱሩፋት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጀመረ የኢትዮጵያ ኢንሽቲቭ ሲሆን ራስን በመቻል የምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ ዋስትናን ለማሻሻል ያለመ ነው። መርሃግብሩ በቤተሰብ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተመጣጠነ ምግብን ለማረጋገጥ፣ የስራ እድል ለመፍጠር፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ለመጨመር እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመቀነስ የግብርናውን ዘርፍ በተለይም የእንስሳት እርባታን በማዳበር ላይ ያተኮረ ነው። ግቡ የተመጣጠነ ምግቦችን በተለይም እንደ ወተት፣ እንቁላል እና ማር ያሉ በእንስሳት ላይ የተመሰረቱ ምርቶችን በማምረት እና ፍጆታን በማሳደግ በምግብ ራስን መቻል እና 'የተመጣጠነ ምግብን ተትረፍርፎ' ማግኘት ነው።

መርሃግብሩ የእንስሳት እና የአሳ ሀብት ዘርፎችን በመለወጥ በምግብ ራስን መቻልን ለማሳካት፣ የአመጋገብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና በቤተሰብ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት ያለመ አጠቃላይ የአራት አመት የልማት ዘመቻ ሲሆን በተለይ በምግብ ራስን መቻል እና የተመጣጠነ ምግብ ተትረፍርፎ ለማግኘት የወተት ተዋጽኦ፣ እንቁላል፣ የዶሮ እርባታ እና ማር የግብርና ምርታማነትን በማሻሻል ላይ ያተኮረ ነው። ፕሮግራሙ አላማውን ለማሳካት በጥንቃቄ እቅድ እና አተገባበር ላይ የተመሰረቱ ተጨባጭ ግቦችን በማውጣት ወደ ስራ ገብቷል።

የሌማት ቱርፋት ኢንሽቲቭ ስልታዊ ጠቀሜታ በበርካታ ቁልፍ ቦታዎች ላይ ይገኛል። ከብሔራዊ የልማት ዕቅድ ጋር መጣጣም - የሌማት ቱርፋት የኢትዮጵያ "10 በ10 ፕሮግራሞች" እና የአስር አመት አመላካች ዕቅድ (2020-2030) የማዕዘን ድንጋይ ሲሆን

ይህም ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ሀገራዊ ግቦች ወደ ተጨባጭና ተግባራዊ ኢላማዎች መቀየር ነው። "መላው መንግስት" እና "መላው ህብረተሰብ" አቋም ኢንሸቲቭ በተለያዩ የመንግስት ኤጀንሲዎች፣ በግሉ ሴክተር፣ በአካዳሚክ፣ በምርምር ተቋማት እና በሲቪል ማህበረሰብ መካከል ያለውን ትብብር አስፈላጊነት አጉልቶ በማሳየት የምግብ ስርዓቱን መለወጥ የብዘ ዘርፍ ተሳትፎ እና ብሄራዊ አጣዳፊነት ስሜትን ይጠይቃል። ኢንቨስትመንትን መሳብ - የበለጠ ምቹ እና ደጋፊ አስተዳደራዊ እና ፋይናንሺያል አካባቢን በማጎልበት መርሃግብሩ የግል ኩባንያዎችን በከብት እርባታ ንዑስ ዘርፍ ላይ በጋራ ኢንቨስት እንዲያደርጉ በማድረግ እንደ ጄኔቲክ ማሻሻያ፣ የምግብ ቴክኖሎጂ እና ማቀነባበሪያ ያሉ ዘርፎችን ጨምሮ ማበረታታት ያስፈልጋል።

## 8.1.2.10. ቀዳማዊ ልጅነት

የቀዳማዊ ልጅነት ልማት መርሐግብር ከጽንሰት ጀምሮ እስከ 6 ዓመት ያሉ ህጻናት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ሲሆን በሴቶች፣ ወጣቶች እና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ በክልላችን በሁሉም አከባቢዎች የሚተገበር ፕሮጀክት ነው። በፕሮጀክቱ ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዩች የህጻናት ማዋያዎችን ቁጥር ማሳደግ፣ ህጻናት የተሻለ አስተዳደግ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ቤተሰቦች በተሻለ የህፃናት አያያዝና አስተዳደግ ፕሮግራም ላይ ስልጠና መስጠት፣ ሕፃናት ሁለንታዊ ድጋፍና ክብካቤን የሚያገኙበት የስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን ጊዜያቸውን እንዲያሳለፉ ማድረግ ወ.ዘ.ተ ናቸው።

የህጻናት ማዋያዎችን ቁጥር በማሳደግ የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በመንግስት ሴክተር መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በተያዘዉ ዕቅድ መሰረት በግማሽ ዓመቱ መንግስታዊና ልማት ድርጅቶች በክልል 2፣ በዞን እና በወረዳ 8 በድምሩ 10 የህፃናት ማቆያዎችንና መንከባከቢያ ማዕከላትን ለማቋቋም በእቅድ ተይዞ በክልል 1፣ በዞን እና በወረዳ 6 ማቋቋም ተችሏል። በነባርና በአዲስ በተቋቋሙ የህፃናት ማቆያዎችና መንከባከቢያ ማዕከላት ዉስጥ 1,222 (ወንድ 549 ሴት 673) የሚሆኑ ህጻናትን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በዕቅድ ተይዞ 1,684 (ወንድ 854 ሴት 830) ህጻናት በተቋቋሙ ማዕከላት ዉስጥ ገብተዉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ።

ህጻናት የተሻለ አስተዳደግ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመተባበር 1,150 (ወንድ 503 ሴት 647) ለሚሆኑ የቅድመ መደበኛ መምህራን በተሻለ

የህፃናት አያያዝና አስተዳደግ ፕሮግራም ላይ ስልጠና ለመስጠት በተያዘዉ እቅድ መሰረት 1,426 (ወንድ 560 ሴት 866) ለሚሆኑት ስልጠናዉ ተሰጥቷል፡፡ በቀዳማይ ልጅነት ልማት ዘመን ላይ 50,577 (ወንድ 25,289 ሴት 25,288) ለሚሆኑ ቤተሰቦች ግንዛቤ ለመፍጠር በእቅድ ተይዞ 53,738 (ወንድ 28,583 ሴት 25,155 ለሚሆኑ ቤተሰቦች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነዉ፡፡

በ2017 ዓ.ም ወደ ትምህርት ቤት ያልገቡ ህፃናትን ለ2018 የትምህርት ዘመን ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ለማድረግ ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ በተያዘዉ ዕቅድ መሰረት ለ902,926 (ወንድ 422,072 ሴት 480,854) ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡

## 8.1.2.11. ኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት

"ኢትዮጵያ ታምርት" የተሰኘ ሀገር አቀፍ የኢንቨስትመንት ንቅናቄ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ሀሳብ አመንጭነት በ2014 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን የንቅናቄውን ሙሉ ተግባርና ኃላፊነት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በመውሰድ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ይህን ንቅናቄ ለማሳካት ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የድርሻቸውን መወጣት ይችሉ ዘንድ ዋነኛ ተግባራቸው አድርገው እየሰሩበት ይገኛሉ፡፡ የክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮም የክልሉን የኢንቨስትመንት ተወዳዳሪነት የሀገር ህልውና ጉዳይ አድርጎ በመውሰድ ትርጉም ያለውና ዘላቂ ልማትን ለማሳካት ንቅናቄው በየዓመቱ በተለያዩ ክንዋኔዎች ማለትም በውይይት፣ በባዛር፣ በኢግዚቢሽን እና ኤክስፖ ይከበራል፡፡

የፕሮጀክቱ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል በአገሩ ምርት ላይ እምነት፣ የአስተሳሰብ ለዉጥ እንዲኖረዉ እና የአገሩን ምርት ከመጠቀምም አልፎ ሌሎች እንዲጠቀሙት የግንዛቤ ለዉጥ ማምጣት፣ የአገር ዉስጥ ምርቶችን መጠቀም እንደ ባህል እና እምነት እንዲደረግ ነዉ፡፡ የዘርፉን ውስብስብና ሁለንተናዊ ችግሮች ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በመፍታት የማምረት አቅም ማሳደግ፣ ማምረት ያቆሙ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ምርት በመመለስ፣ አዳዲሶችን በመሳብና በማጠናከር ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉ ማድረግ፣ ለሀገር በቀሉ የኢኮኖሚ ሪፎርም ስኬትና መዋቅራዊ ሽግግር በማምጣት ተወዳዳሪና ቀጣይነት ባለው መልኩ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

በፕሮጀክቱ ከተገኙ ውጤቶች መካከል የኢንዱስትሪ ልማቱን ለማፋጠን የተለያዩ የድጋፍ

ፓኬጆችና ማበረታቻዎች ተቀርፀው ወደ ስራ እንዲገባ መደረጉ፤ የኢንዱስትሪ መንደሮችን ማልማትና ለባለሃብት የማስተላለፍ ስራው እየተሻሻለ መምጣቱ የኢንቨስትመንት መሬት፣ መሰረተ- ልማት በተለይም የኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ብድር በተሻለ መንገድ ማቅረብ መጀመሩ፣ የኢንዱስትሪ መንደሮችን የመሰረተ-ልማት ችግሮችን ለመፍታት ከፍተኛ በጀት ተመድቦ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑ፤ ፕሮጀክቶች ለረዥም ጊዜ አጥረው የያዙትን መሬት ከንቅናቄው በኂላ በተሰራው መነሳሳትና ጥብቅ ክትትል እርምጃ በመውሰድ ወደ የመሬት ባንክ ማስመለስ መቻሉ፤ ማምረት አቁመው የነበሩ ፕሮጀክቶች ችግራቸው ተፈቶ ወደ ማምረት እንዲመለሱ ማደረግ መቻሉ፤ ንቅናቄውን ለማስቀጠልና ችግሮቹን እየተከታተሉ ለመፍታት የሚያችስሉ ከአጋርና ባለድርሻ አካላትጋር መድረኮች መካሄዳቸው፣ የጋራ ስምምነቶች መፈረም መቻላቸው ወዘተ ትልልቅና በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ፕሮጀክቶች እየተፈጠሩ መሆኑ ዋና ዋናቹ ናቸው፡፡

## 8.1.2.12. የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ

ፕሮጀክቱ ለችግር ተጋለጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች) የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ለማስቻል የህብረተሰቡን፣ የባለሀብቱን፣ የአጋር አካላት እና በጎ ፍቃደኖች አቅም በማስተባበር ቤት ሌላቸው ቤት እንዲኖራቸው እንዲሁም ቤት እያላቸው የፈረሰ ወይም ያረጀ ካለ በማደስ ደስተኛ ህይወት እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡

በ6 ወሩ የስራ አፈጻጸም የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ የክረምት በጎ ፍቃድ ማስጀመሪያ ምክንያት በማድረግ ከክልሉ ከአረጋዊያን ማህበር ጋር በመተባበር ከክልሉ የአረጋዊያን ገቢ ማስገኛ ማዕከል ከተገኘው ገቢ ላይ ብር 500,0000 ወጪ በማድረግ በባህር ዳር ከተማ ነዋሪ ለሆኑ 4 ወንድ እና 2 ሴት በድምሩ 6 አቅመ ደካሞች የቤት ጥገና የተካሄደ ሲሆን ለ18,917 (ሴት 12008) የተለያዩ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ነባር ቤቶችን መጠገን እንዲሁም ለ7,194 (ሴት 4863) አዲስ ቤቶችን ለመገንባት ተችሏል፡፡ በተመሳሰይ በወጣቶች በጎ ፍቃድ አማካኝነት ለአቅመ ደካማ 9,296 ቤቶችን በአዲስ መልኩ ለመገናባት ታቀዶ 6,196 አዲስ ቤቶች የተገነቡ ሲሆን 18,592 ነባር ቤቶችን ለመጠገን/ ለማደስ ታቅዶ 12,535 ነባርና የተጎዱ ቤቶች ታድሰዋል/ ተጠግነዋል፡፡ እንዲሁም በበጋ በጎ ፍቃድ አማካኝነት 23 አዲስ ቤት እና 29 ቤት ጥገና ለአቅመ ደካሞች እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

## 8.1.2.13. ዲጅታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት (መሶብ)

የዲጂታል አንድ ማእከል አገልግሎት (መሶብ) የህዝብ አገልግሎት እና የአስተዳደር ማሻሻያ ስርዓት አካል ነው። ይህ ፕሮጀክት በአንድ ማእከል ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ተደራሽ አገልግሎቶችን በማቅረብ የደንበኞችን አገልግሎት ለማሻሻል ያለመ ነው። በርካታ በቴክኖሎጂ የሚደገፉ አገልግሎቶችን በአንድ ቦታ ያዋህደ፣ ይህም ለተጠቃሚው ወጪዎች እና ጊዜ ይቀንሳል። በባህር ዳርና በደሴ የተጀመረ ሲሆን ቀጣይም በሰፊው የክልሉን ህዝብ የሚፈልገውን አገልግሎት ለማሟላት በእቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው።

ፕሮጀክቱ በርካታ በቴክኖሎጂ የሚደገፉ አገልግሎቶችን ወደ አንድ ማእከል በማዋሃድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ተደራሽ አገልግሎቶችን በማቅረብ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ላሉ ደንበኞች የአገልግሎት አቅርቦትን ለማሳደግ ወጪን በመቀነስ ለደንበኛው ጊዜ ለመቆጠብ ነው።

በ6 ወሩ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣ የ4 የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎትን (1 የክልል ተቋማትና በ3 ከተማ አስተዳደሮች) ስራ ለማስጀመር በእቅድ ተይዞ ክንውን 3 (75%) (የክልል ተቋማት፣ የባ/ዳር ከተማ አስተዳደርና የደሴ ከተማ አስተዳደሮች) የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎትን አጠናቆ በማስመረቅ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል። የጎንደር ከተማ አስተዳደር መሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት በግንባታ ሂደት ላይ ሲሆን በአማራ ክልል መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችን ይዘው የገቡ የክልል ተቋማት ስራና ስልጠና ቢሮ፣ ፍትህ ቢሮ፣ መሬት ቢሮ፣ ገቢዎች ቢሮ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ፣ ኢንቨስት መንት ቢሮ፣ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ፣ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ፣ የሲቪል እና የቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት፣ ትራንስፖርታና ሎጅስቲክ ባለስልጣን እንደዚሁም ከፌደራል ተጠሪ ተቋማት ኢትዮ ቴሌኮም፤ ኢትዮ ፖስታ፤ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በክልል መሶብ /ANRS-MESOB/ የአንድ ማዕከል አገልግሎት 14 ተቋማት (10 የክልል ና 4 የፌደራል ተጠሪ ተቋማት) አገልግሎት የእየሰጡ ሲሆኑ በእነዚህ በክልል ተቋማት (54- አገልግሎቶች)፣ በባህርዳር ከተማ አስተዳድር በ13 ተቋማት (91 አገልግሎቶች)፣ በደሴ ከተማ አስተዳደር በ14 ተቋማት (83-አገልግሎቶች)፣ ጎንደር ከተማ አስተዳደር በ13 ተቋማት (54 አገልግሎቶች) ተለይተው ወደ መሶብ አንድ ማዕከል እንዲገቡ ተደርጓል።

## 8.2. ክትትልና ግምገማ

**የአጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማቀድ ክልሉን በትክክለኛ አስተቃቀድ ስልት እንዲመራ ማስቻል፡-** የክልሉን ልማት በዕቅድ መመንጠቅ የሚያስችል የ25 ዓመት ፍኖተ ካርታ እና የ5 ዓመት የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም የክልሉ ህዝብ ሁለተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ክልላዊ ማስፈፀሚያ ሰትራቴጅዎች በማዘጋጀት ለ188,075 (ወ 136,760 ሴ 51,315) በክልሉ የሚመለከታቸውን የመንግስት የስራ ኃላፊዎችን፣ ዳይሬክተሮችን እና የዞንና የሪጅኦፖሊታን ከተማ አመራሮችን በሙሉ ለማሳተፍ ታቅዶ 100% በማሳተፍ ስልጠናዎችን በመስጠት ግንዛቤ በመፍጠር በተዋረድ ወደ ስራ መግባት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተቋማት የሚልኳቸው ዕቅዶች የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን እና የአረጋውያንን የማህበራዊ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች፣ የሰነ-ሕዝብ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባትን ወዘተ ጉዳይ እንዲያካትቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 100% የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

ሌላው አዋጭ ፕሮጀክቶች ፍትሃዊ የበጀት ድልድል መረጃ በማደራጀት 764 አዲስ እና 852 ነባር በድምሩ ለ1,616 የካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድ በመስራት አዋጭ ፕሮጀክቶች ፍትሃዊ የበጀት ድልድል መረጃ በመደልደያ ቀመር እና በመመዘኛ መስፈርቱ መሰረት ቅደም ተከተል በማስያዝ ለሚመለከተው አካል መላክ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ፕሮጀክቶችን ለማመንጨት፣ ለማጥናት፣ ለመተግበርና ለመገምገም የሚረዱ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሃሳቦች እንዲጠኑ 1 ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 1 (100%) ብዙ ፕሮጀክት ላላቸው (መንገድ፣ ውሃ፣ መስኖ፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ትምህርት እና ጤና) ተቋማት ጥናት ማድረግ እንዲችሉ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል።

**የክልሉን የመረጃ አሰራር ስርዓትን በቴክኖሎጂ በማዘመን ስታትስቲክሳዊና ስፓሻል መረጃ ማደራጀትና አገልግሎቱን ማሻሻል፡-** የክልሉን ገጽታ በሚያሳይ መልኩ የጂኦ-ስፓሻል እና የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ፕሮፋይል 1 ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 (100%) የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተመረጡ 2 ወረዳዎች የመሰረተ-ልማት ተቋማት ስርጭት ከስታንዳርዱ አንጻር ፍትሀዊነታቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 3 (100%) (እንሳሮ፣ ቋሪት እና ጋዞ) የመሰረተ ልማት ስርጭትን የሚያሳይ ሰነድ በጥራት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡

ሌላው ለክልሉ የሰብአዊ ልማት አመልካቾች (RHDI) የሚጠቀሙ የትምህርት እና ጤና አመልካቾች ተጨማሪ መረጃዎችን በማሰባሰብ የዳሰሳ ትንታኔ ስራ ለመስራት ታቅዶ 100% መፈጸም ተችሏል፡፡

የንዑስ ዘርፎችን እሴት ጭማሪ ወደ 3ቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች እሴት ጭማሪ የማጠቃለል እና ከበፊት ዓመታት ጋር ያላቸውን የእድገት ምጣኔ እና የኢኮኖሚ ድርሻ አዝማሚያ /trend/ መገምገም 21 ታቅዶ 21 በማከናወን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት ጥቅል ምርት (RGDP) በወቅቱ የገበያ ዋጋ እና በቋሚ ዓመት ዋጋው መሠረት ምርቱ በመነጨበት የአገማመት ዘዴ በመገመት የእድገት አዝማሚያውን (Growth trend) በመገምገም 1 ሰነድ ለማዘገጀት ታቅዶ 1 ሰነድ በማዘጋጀት 100% መፈፀም ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ተቋሙ የመረጃ ቋት በማልማት በቴክኖሎጅ በማዘመን ሶፍትዌሮችን የማበልፀግና ወደ ዳታ ቤዝ የመመዝገብ ስራ የተሰራ ሲሆን በአጠቃላይ 7 ፕሮግራሞችን በማልማት (የፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ የተቋማት መመዘኛ፣ የስታቲስቲክስ ማቀነባበሪያ፣ የዲጂታል ቤተ-መጽሀፍት፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደር፣ የንብረት አስተዳደር እና የነዳጅ መቆጣጠሪያ) ሲስተሞችን/ሶፍትዌሮችን በማልማት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ተደጓል፡፡

**በጥናት ላይ በመመስረት ክልላዊ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በተቋም ምዘና የማስፈጸም አቅም መገንባት፡-** በ2017 በተያዘው የምዘና ዕቅድ መሠረት የሁለተኛው አጋማሽ /ዓመታዊ የተቋማት/ ምዘና 50 ተቋማትን ለመመዘን ታቅዶ 50 የክልል ተቋማትን መመዘን የተቻለ ሲሆን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ በምዘና ውጤቱም 23 (46%) ተቋማት ከፍተኛ፣ 27 (54%) ተቋማት መካከለኛ ሲያገኙ ዝቅተኛ እና በጣም ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ የክልል ተቋም የለም፡፡ ክልል ተቋማት በተጨማሪ የዞን ተቋማትም በምዘናው እንዲልፉ የተደረገ ሲሆን በአፈፃፀማቸው ብልጫ ላመጡ ተቋማት የክልሉ መንግስት የዕውቅናና የማበረታቻ ሽልማት ሰጥቷል፡፡

የ2018 በጀት ዓመት የምዘና ዕቅድ (KPI) የምዘና ተግባሩን ከሰው ንክኪ ነፃ እንዲሆንና በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የታገዘ እንዲሆን ለማድረግ የ48 የክልል ተቋማትን የምዘና እቅድ እየተለማ ባለው (KPI Management System Software) ለማስገባት ታቅዶ የ46 ተቋም (95.8%) ማስገባት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ዓመታዊ የክልሉ የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት የጸደቀ ዕቅድ፣ የ2018 የተቋማት እቅድና

ሪፖርት እንዲሁም የ1ኛው እና 2ኛው ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ውጤት ሲስተሙ ላይ መጫን ተችሏል፡፡

የ2018 የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅዱን መሠረት ያደረገ በመስክና በዴስክ ለክልል ተቋማት፣ ለዞን እና ለከተማ አስተዳደሮች ተቋማት በተደረጃ ቼክሊስት ክትትልና ድጋፍ 2 ጊዜ ለማድረግ ታቅዶ 2 ጊዜ ማካሄድ የተቻለ ሲሆን በክትትሉም 19 የክልል ተቋማት፣ 10 የከተማ አስተዳደር ተቋማት፣ 12 የዞን ተቋማት በድምር ለ41 ተቋማት በማየት 100% መፈጸም ተችሏል፡ ፡ በተጨማሪም በተደረገው ድጋፍና ክትትል የተገኙ ግኝቶችን መሠረት የዋናው ሪፖርት አካል ሆነው በማዘጋጀት ለውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲቀርቡ በማድረግ ከክልል ተቋማት ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን ለሁሉም የክልል፣ ዞንና እና ከተማ አስተዳደረ ተቋማት የተደረገውን ድጋፍና ክትትል መሰረት አድርጎ ድጋፍ ላልተደገረባቸው ተቋማት ጭምር ልምድ እንዲወስዱበት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ግብረ-መልስ መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡

በክልሉ ያሉ ልማትን በመደገፍ ኢኮኖሚያዊ እድገትን የሚያፋጥኑ ፕሮጅክቶችን በወቅቱ በመምራት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ (Project Management SoftWare) በማልማት አዲስ 475፣ ነባር 3,014 በድምሩ 3,489 ፕሮጀክቶችን እና 4,697 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወደ ሲስተሙ በማስገባት በሚመለከታቸው አካላት ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፡፡

**የክልሉን የስነ-ህዝብ መረጃና የፖሊሲ ጥናትና ምርምር አሰራር ስርዓትን በማዘመን መረጃን ማደራጀትና ለልማት እንዲውል ማስቻል፡-** ክልላዊ ዕቅድን ለማስፈፀም የሚያስችሉ 42 የተጠሪ ተቋማት ረቂቅ ደንብ ለማዘጋጀት ታቅዶ 42 (100%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 1 የማስፈፀሚያ ደንብ፣ 1 ጋይድላይን እና 3 መመሪያዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 ደንብ /የፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ደንብ/ እና 3 መመሪያዎችን (መረጃ ጥራት መቆጣጠሪያ፣ የአስተዳደራዊ ወሰን ለውጥ እና የቀበሌ ማህበረሰብ አሳታፊ እቅድ አዘገጃጀት መመሪያዎች) እና 1 ጋይድላይን 100% አዘጋጅቶ በማጠናቀቅ ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል የክልሉን የማክሮ ኢኮኖሚ እድገት አዝማሚያ የሚያሳይ 1 ሪፖርት ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 በማዘጋጀት 100 መፈፀም ተችሏል፡፡

## 9. ማጠቃለያ

በ2018 በጀት ዓመት ክልሉ ያለበትን ወቅታዊ የጸጥታ ችግር ተቋቁሞ የታቀደውን የአሻጋሪና የዘላቂ ልማት ዕቅድ ከግብ ለማድረስ ሠላምን ከማስፈን ጎን ለጎን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ

ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በአፈጻጸም በኩል የተገኘውን ውጤት በዝርዝር ከላይ በየዘርፉ ለማስቀመጥ ጥረት የተደረገ ሲሆን የክልል ተቋማትን ሪፖርት መሠረት በማድረግ አጠቃላይ የታዩ ዋና ዋና ጥንካሬዎችን እና ያልተፈጸሙ ተግባራት በመለየት በማደማደሚያ ለማመላከት ጥረት ተደርጓል፡፡

ሌላው ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ወደ ተለያዩ አፈጻጸሞች ማስገባት የተቻለ ሲሆን በዚህም በሁሉም 275 ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ ለማስገባት ታቅዶ 183 (67%) ወደ ግንባታ፤ 69 ፕሮጀክቶችን ወደ ምርትና አገልግሎት ለማስገባት ታቅዶ 85 (100%) ፕሮጀክቶችን ወደ ምርት ማስገባት ተችሏል፡፡ እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታቸዉን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ከማሳደግ አንጻር 36,819 ቶን ምርት በመላክ 83.8 ሚሊ/ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 42,182.07 (100%) ቶን ምርት በመላክ 119.6 (100%) ሚሊየን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ የፋብሪካ ምርቶችን በሃገር ውስጥ ለመተካት እየተሰራ ባለው ስራ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 219,150 ቶን በማምረት 280 ሚሊ/ዶላር ለማዳን ታቅዶ 296,966.57 (100%) ቶን የሚሆን ተኪ ምርቶችን በማምረት 335.77 (100%) ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማዳን ተችሏል፡፡

የዘመናዊ ግብርና ዘርፍ የኢኮኖሚ አፈጻፀም ሲታይ ደግሞ የተሻለ አፈጻፀም የተመዘገበው በሰብል ምርት ነው፡፡ በ2017/18 ምርት ዘመን በመኸር (በመደበኛና በኮሞዲቲ) ሠብሎች 5,398,393 ሄ/ር መሬት በማልማት 187,540,749 ኩ/ል ምርት ለማምርት ታቅዶ 5,533,592 (103%) ሄ/ር መሬት በዘር በመሸፈን እስከአሁን 138,011,468 ኩ/ል ምርት ማምርት ተችሏል፡፡ በዚህም በምግብ ሰብል 75,275,997 ኩ/ል፣ በኢንዲስትሪ ሰብል 51,347,089 ኩ/ል እና በኤክስፐርት ሰብል 11,388,382 ኩ/ል ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የወተት ምርታማነትን በተመለከተ ከአንድ ላም በቀን በአማካኝ የሚታለብ የወተት ምርት ከአካባቢ ላም 2.1 ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች ወደ 13.5 ሊትር ለማድረስ ታቅዶ ከአካባቢ ላም 1.87 (87%) ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች 11.67 (86%) ሊትር ማድረስ የተቻለ ሲሆን 1,703,786.15 ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 1,635,002 ቶን (96%) ማምረት ተችሏል፡፡

የማዕድን ዘርፉን ዉጤታማ ለማድረግ የማዕድናትን ፍለጋ ክምችት ግመታ ጥናትን በ1:30,000 መስፈርት በክልሉ በተመረጡ ልዩ ልዩ ቦታዎች በ10 ካ.ኪ.ሜ የኢንዱስትሪ ማዕድን፣ በ30 ካ.ኪ.ሜ የዳይሜንሽን ስቶን ማዕድን፤ 30 ካ.ኪ.ሜ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድን እንዲሁም 30 ካ.ኪ.ሜ የኮንስትራክሽን ማዕድን ክምችት፣ መጠን፣ ጥራትና ስርጭት ጥናት መረጃ ሽፍንን

ለማሳደግ በግማሽ ዓመቱ 15% በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ የሚከናወኑ የጥናት ተግባራትን ለማጠናቀቅ ዕቅድ ተይዞ 100% ማከናወን የተቻለ ሲሆን 5,194,860 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 12,289.57 ኪግ በመላክ 8,768,032.01 (100%) የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል። ሌላው 856,629 ቶን ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ምርት በመተካት 62,423,279.6 USD የውጭ ምንዛሬ ለማዳን ታቅዶ 1,755,025 ቶን (100%) ምርት በመተካት 100,092,350 USD የምንዛሬ ወጭን ማዳን ተችሏል።

ቱሪዝም ልማት የክልሉን ገጽታ ለመገንባት በክረምት ወራት የሚከበሩ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ህዝባዊ ክብረ በዓላት በማስተባበር በርካታ ቁጥር ያላቸው ጎብኝዎችን ወደ ክልሉ መሳብ ተችሏል። በዚህም መሰረት 10,199,290 የአገር ውስጥ እና 24,913 የውጭ አገር ቱሪስቶች ክልሉን ጎብኝተዋል። ከአገር ውስጥ ቱሪስቶች 7,757,069,283 እና ከውጭ ቱሪስቶች 121,404,198 በድምሩ 7,878,473,481 ብር ገቢ ተገኝቷል።

በክልላችን ከሚገኙ 11,088 ትምህርት ቤቶች (አጸደ ህጻናት 757፣ አንደኛ እና መካከለኛ 9,623 እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ 708) መካከል አስቻይ ሁኔታ ባላቸው 9,703 ትምህርት ቤቶች ምዝገባ ተጀምሮ በትምህርት ዘመኑ በሁሉም እርከኖች ለመመዝገብ ከታቀደው 7,445,545 ተማሪዎች መካከል እስከ ግማሽ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ መመዝገብ የተቻለው 4,344,269 (ወንድ 2,127,472፣ ሴት 2,216,797) አፈፃፀሙ (59.06%) ብቻ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት ስራችን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች በእጅጉ እየተፈተነ ቢሆንም የክልሉ ትምህርት ቢሮ ችግሩን ለመቅረፍ የሚበጁ ስልቶችን በመቀየስ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ እየተሰራ ይገኛል። ይሁን እንጂ ከችግሩ ጥልቀትና አሳሳቢነት የተነሳ ክልላችን ብሎም ሀገራችን ከገጠመን ወቅታዊ ችግር ፈጥኖ ለመውጣት የሁሉንም አካላት ልዩ ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል።

የንግድ ፈቃድ እድሳት፣ የገበያ ማዕከላትን በማስፋፋት እና በማጠናከር የግብይት ስርዓቱን ተደራሽ በማድረግ በወቅት ከሚሰበሰቡት የሰብል አይነቶች በሃገር ውስጥ ትስስር ላይ በቀጣይ ወራት አሰራርን ለማሻሻል የአምራች እና የሸማቹን የገበያ ትስስር በማጠናከር የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት የክልሉ ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተሰሩ ተግባራት ዝቅተኛ በመሆኑ፣ በሃገር ውስጥ ተኪ ምርት ማስተሳሰር የቅንጅት ስራ በተለየ ማደያዎች ላይ ቁጥጥር ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የታቀዱ ተግባራትን በማከናወን ላይ ሲሆን ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል 4,843,925 የህዝብ ትራንስፖርት ተሸከርካሪዎች

በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 108,090,743 ህዝብ በማጓጓዝ 313,955,570 ኪሎ ሜትር የመሸፈን ስራ ተሰርቷል፡፡

ከተማ ልማት ዘርፍ ከአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደር ማሻሻያ ስራዎች አኳያ በተቋሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ 534 የመልካም አስተዳደር ችግሮች ተለይተው 408 (76.40%) ተፈተዋል፡፡ በ728 ከተሞች 11,316,271,999.77 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 4,827,022,631.84 ብር (42.66%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ሌላው የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬትን የብድር ዋስትና በማድረግ 11,640 ባለይዞታዎች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 17,144 (>100%) ባለይዞታዎች ብር 953,464,892 (>100%) ብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል ዘመናዊ የመሬት መረጃ ስርዓትን ለመገንባት እንዲቻል መረጃን ወደ NRLAIS ሲስተም ለማሸጋገር የ 417,051 ማሳ እቅድ ተይዞ የ 315,762 (76%) ማሳዎችን የመሬት መረጃ ወደ ብሄራዊ የገጠር መሬት መረጃ ስርዓት (NRLAIS) ማሸጋገር ተችሏል፡፡

የፍትህና የዳኝነት ዘርፉን ዉጤታማ ለማድረግ የወንጀል ምርመራ መዛግብት የመወሰን ቅልጥፍና 98% ለማድረስ ታቅዶ 98.4%፣ በቀጥታ ክስ የወንጀል መዛግብት የዐቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ 94.28% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስ፣ ይግባኝ መልስና ሰበር መልስ ክርክሮች የዐቃቤ ህግ መዛግብት የማጥራት ቅልጥፍናን 97.5% ለማድረስ ታቅዶ የማጥራት ምጣኔዉን በመዝገብ 95.09%፣ የዐቃቤ ህግ ይግባኝ እና ሰበር ክርክርን ማሸነፍ ምጣኔ 65% ለማድረስ ታቅዶ ብር 487,719,512 ብር የያዙ 764 መዛግብት ላይ ክርክር በማድረግ ብር 38,310,254 ብር በያዙ 194 መዛግብት ላይ /በመዝገብ 57.6% በገንዘብ 45% በአሸናፊነት ተወስኗል፡፡

ፕላንና ልማት ቢሮ ለክልል 19 ተቋማት እና ለዞን 24 ተቋማት የድጋፍና ክትትል ስራ ያካሄድ ሲሆን በክልል ተቋማት ድጋፍና ክትትል ወቅት የታዩ ጥንካሬዎች የክልል አመራሮች ስራውን በባለቤትነት ይዘው ስራን ቆጥረው ሰጠው መረከባቸው፣ ለድጋፍና ክትትሉ ትኩረት ሰጥተው መምራታቸው፣ አብዛኛው የቅድመ ዝግጅት ተግባራት በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ መሆናቸው፣ ከአምስት ዓመቱ የተቀዳ የ2018 በጀት ዓመት አሻጋሪ እድገትና ዘላቂ ልማት መደበኛና የፕሮጀክት ዕቅድ በአግባቡ ማቀዳቸው፣ የተቋሙን ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቶች (KPI) ዕቅድ በወቅቱ ማዘጋጀታቸው፣ በማህበራዊ ክላስተር አስተባባሪ መመሪያ መሰረት የማህበራዊ ዘርፍ ተቋማት በKPI ሶፍትዌር ዙሪያ ለማኔጅመንት አካላት ስልጠና እንዲሰጥ መደረጉ፣ ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣

ደንቦች መመሪያዎች እና ማኑዋሎች መዘጋጀታቸው እንዲሁም ወደ ታች ለሚገኙ ተቋማት KPI ማውረዳቸው እና የድጋፍና ክትትል ስራ መደረጉ በጥንካሬ የታዩ እይታዎች ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ጥንካሬዎች ቢኖሩም በድጋፍና ክትትሉ ወቅት የታዩ ውስንነቶች አብዛኛው ተቋማት በKPI ሶፍትዌር ዙሪያ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩ፣ የተወሰኑ ተቋማት ሁሉን ፕሮጀክቶች ወደ ፕሮጀክት አስተዳደር ስርዓት ሶፍት ዌር መመዝግብ አለመቻላቸው፣ የሚዘጋጁ ሪፖርቶች ከKPI ዕቅድና በምክር ቤት ከጸደቀው ዕቅድ ጋር የተናባቢነት ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣ በፌደራል የሚሰሩ እና የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ወደስራ አለመግባታቸው እንዲሁም በአዲሱ በጀት ዓመት የተዋሀዱ ተቋማት በተዋሀዱት መሰረት ተግባራትን ተረክቦ የመፈጸም ክፍተት መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ጥንካሬዎች እና ክፍተቶች በመለየት በድጋፍና ክትትሉ ወቅት በቃለጉባኤ ተደግፎ ግብረ መልስ እና አስተያየት የተሰጠ ሲሆኑ የጽሁፍ ግብረ-መልስ ተዘጋጅቶ ለመማር ይረዳ ዘንድ ለሁሉም የክል ተቋማት የሚደርስ ይሆናል፡፡

ሌላው በዞን ደረጃ ለሚገኙ 24 ተቋማት ድጋፍና ክትትል የተደረገ ሲሆን በድጋፍና ክትትሉም የ2018 በጀት ዓመትን የአሻጋሪና ዘላቂ ልማት እቅድ አመራሩ በውጤታማነት ለመምራት በተከታታይ ግምገማ በማድረግ እየመራ መሆኑ፣ ከአመራሩ እስከ ባለሙያው ያለው መናበብና ቅንጅታዊ አሰራር የተሻለ መሆኑ፣ ስትራቴጅክ ግቦችና ለህብረተሰቡ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት እይተሰራ መሆኑ፣ ቡልጋ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ መንደር የከተማ አስተዳደሩና የዞኑ ኢንቨስትመንት ቦርድ ውሳኔን በማስቀም ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ብቻ በክልል ኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲመራ መደረጉ፣ የመንግስትና የባለሀብቶችን ቅንጅት በማጠናከር በባለሃብቶች 44.8 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ 121 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎ ማሰራቱ እንዲሁም 6 ኪ.ሜ የመብራት መስመር 162 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎ ማሰራት መቻሉ፣ በጋ መስኖ ስንዴ ልዩ ትኩረት በመስጠት አካባቢው ከዚህ በፊት ምንም አገልግሎት የማይሰጥ መሬትንና ለቀን ስራ ተሰዳጅ የነበረውን አርሶአደር በበጋ መስኖ ስንዴ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፣ አመራሩ ወረዳና ቀበሌውን በመከፋፈል ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ መሆኑ፣በፌደ ልና በክልል የሚከናወኑ ኢንሸቲቮችን ትኩረት በመስጠት ውጤታማ ማድረግ መቻላቸው (51,277,760 ብር በጀት መንግስት ከመደበው በተጨማሪ ት/ቤቶች ደሮ በማርባት፣ በግ በማድለብና ሰፊ የጓሮ አትክልት እርሻ በማልማት የትምህርት ቤት ምገባ በቅድመ አንደኛና በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ለ7,913 ተማሪዎች ምገባ እየደገፉ መሆኑ፣ የአልትራሳውንድና ሌሎች

ኬሚስትሪ ማሽኖች ምርመራ በጤና ጣቢያና ሆስፒታሎች ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣ የመድሃኒት እጥረት ለመቅረፍ ሰባት የማህበረሰብ ፋርማሲ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣ በክልሉ በዞኑ ያለውን የምርጥ ዘር አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ባለፈው ዓመት በተሰጠው አስተያየት መሰረት በአካባቢው ካሉ ዮኒኖች ጋር በቅንጅት በመስራት ችግሩን መቅረፍ መቻሉ እንዲሁም በክልል ቢሮዎች የሚሰጡ ድጋፎችን በመውሰድ ወደ ውጤት መቀየር መቻላቸው በጥንካሬ የታዩ ስራዎች ናቸው፡፡

እንደ ዞን ተቋማት በክፍተት የታዩ ተግባራት የ5 ዓመት ሥትራቴጅክ እቅድ ለማቀድ ገና በሂደት ላይ መሆኑ፣ በአካባቢዉ የሚመረተዉን ሰብል ለፋብሪካዎች በግብዓትነት ለመጠቀም የሚያስችል ትስስር አለመፍጠር፣ በዞን ደረጃ ሁሉም ትምህርት ቤቶች መከፈት አለመቻል፣ ሁሉም ዘርፍ የአካባቢውን ጸጋ በመለየት ተግባራትን መፈጸም አለመቻል፣ በዞኑ ውስጥ ያለውን ተፈናቃይ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ዘለቄታዊ መፍትሄ ማፈላለግ አለመቻሉ በእጥረት የታዩ ተግባራት ሲሆን እነዚህ ችግሮች ቀርፎ ወደ ስራ ለመግባት ከዞኑ እና ከተማ አስተዳደር አመራሮች ጋር ውይይት በማድረግ የመግባባት ስራ የተሰራ ሲሆን ድጋፍ ለተደረገላቸው ዞኖች በቃለጉባኤ የተደገፈ ግብረ-መልስ ተሰጧል፡፡

በጥቅሉ ክልላችን በዚህ በጀት ዓመት ሰላም ከማስከበር ጎን ለጎን ከወትሮውም በተሻለ ሁኔታ በጠንካራ የአመራር ድጋፍና ክትትል ታግዞ የህብረተሰቡን የልማት ተጠቃሚ በማረጋገጥ በኩል የመጣው ለውጥ እጅግ የሚያበረታታ በመሆኑ እና ለቀጣይ ሩብ ዓመት ለስራ ስንቅ በመሆኑ ሁሉም የመንግስት አካላት የበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይኖርብናል፡፡